# ሀገሬን

2ኛ ዕትም



በሄኖክ ስዩም /ተጓዡ ጋዜጠኛ/

# አበርክቶት

የእየማማዩሁ ንኢጋይ

የቋየቆዩኩን ጸጋዬ

# ምስጋና፤

ይህ የሁለተኛው ዕትም ምስጋና ነው።

መቶ አይደላችሁም፤ ብዙም። እልፍ ናችሁ።

"ሀገሬን" የሚል ሰው፤ "የሀገሩ ሰው አለው" ብላችሁ፤ የሀገር ሰውነታችሁን አሳይታችሁኛል። የመጀመሪያው ዕትም በአጭር ጊዜ አልቆ ለሁለተኛው ዕትም በቅቷል። በተለያየ መንገድ "ሀገሬን" ሀገር እጅ ትገባ ዘንድ ስራውን ከሰሪው ጋር አብራችሁ ላነሳችሁ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ምስጋናዬ ወደር የለውም፤ በማኅበራዊ ሚዲያ ስለ "ሀገሬን" ለሀገሬ ሰው ያበሰራችሁ በስም እንኳን ለመዘርዘር ከመጽሐፉ ጥራዝ ለምትበልጡ ብዙ ሺህዎች በእናት ሀገር ኢትዮጵያ ስም ደጋግሜ ምስጋና አቀርባለሁ። አንብባችሁ ስሜታችሁን የገለጻችሁ። ሞላህን ላላችሁም፤ ብትሞላው ብላችሁ ተጨማሪ መረጃ ለሰጣችሁኝም ውለታ መላሽ ያድርገኝ ብያለሁ። እጁን ዘርግቶ የትም ቤቴ እንዲሆን ባደረገኝ የሀገሬ ሰው ስም እጃችሁን ዘርግታችሁ መጽሐፌን ለተቀበላችሁ፤ ደስታችሁን ለገለጻችሁልኝ ስሜታችሁ ዳግም ጉልበት ሆኖ አበርትቶኛል። የዚህ የሁለተኛ ዕትም ምስጋና ለእናንተ ለሁላችሁም ሆኗል። በድጋሚ በኢትዮጵያዊ ፍቅር እጅ ነስቼ አመሰግናለሁ ብያለሁ።

# ማውጫ

ቀዳሚ ቃል............
ከአባይ ሸለቆ እስከ ዳንጉር እናት
የጠረፍ ሀገር ጀግኖች................................ 8
በአባይ ሸለቆ ውስጥ................................ 21
ወደ ዳንጉር እናት................................ 28
ደቅ................................................... 41
በእሳት ባህር አፋፍ........................................ 58
ኮማንዶ-የደናከሉ ፈጥኖ ደራሽ................................ 68
በምድር ከርስ ውስጥ........................................ 73
የዱር ሕይወት ዓለም..................
ጮፈሮ በጨርጨራ ሰማይ........................ 108
ትልቁ ፍጡር ስር................................ 115
የቀጮኔዎች ዳና........................................ 131
የእሳት ዳር ጂኒዎች................................ 136
ከግዙፉ እንስሳ ጋር................................ 146
ከጎፋዎች ጋራ........................................
ጥበበኛን የሚያከብረው ንጉሥ................................ 159
ማስቃላ ዮ........................................................ 169
ወደ ሩቁ ገዳም ........................................................ 178
ጉንዳ ጉንዶ ማርያም................................................192
ነገረ እንበሳ........................................................212
ዝከረ አበው
መልከዓ ምኒልክ........................................228
ተአምረ ምኒልክ........................................233
ገድለ አበው ዘ አድዋ................................239
ገድለ አበው ዘ ኢትዮጵያ........................246
ዋቢ ሰነዶች........................................................252

## መግቢያ

ሀገሬን..... የመከራ ኡኡታ አይደለም፤ የደስታ እልልታ እንጂ፡፡ "እንዲኽ አለን" ብሎ የመደሰት፡፡ ሁሉም ታሪኮች ለዚህ የመብቃታቸው ምስጢር ጉዞ ነው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ጥናት፡፡ ሁለቱ የወለዷቸው ታሪኮች በዚህ መልኩ የጉዞ ማስታወሻ ለመኾን በቁ፡፡

እነኚኽ የጉዞ ማስታወሻዎች ለታሪክ ጸሐፊዎች፣ ለተጨማሪ ተመራማሪዎችና ከዚህ የረዘመ ርቀት መሄድ ለሚፈልጉ ወገኖች ሁሉ ጎዳና ላይ እንደ ቆሙ ምልክት ጠቋሚዎች ሆነው ካገለገሉ እንኳን ትርፉ ብዙ ነው፡፡

ቀደም ያሉት አሳሾችና የጉዞ ጸሐፍት በዘመናቸው የነበረውን አሰቀምጠውልን በማለፋቸው ዛሬ ታሪክ ብለን የታሪክ አንድ መረጃ በማድረግ ልንጠቀምባቸው በቅተናል፡፡

ያዩትንና የሰሙትን የጻፉ የጉዞ ጸሐፍት ለኋለኛው ዘመን መረጃ ፈላጊዎች የጨለማ መብራት ነበሩ፤ ለምሳሌ የጀምስ ብሩስ የአባይን መነሻ ፍለጋ ለብዙ የእኛ ዘመን ታሪክ ጸሐፊዎችና ተመራማሪዎች የእውቀት መነሻ የሚኾኑ አያሌ የመረጃ ፍንጮችን ሰጥቷል፡፡ እኔ እንኳን በዚህ መጽሐፍ የተጠቀምኩባቸው በርከት ያሉ ምንጮች ትናንት የጉዞ ምልከታና የከራሞት ማስታወሻ ሰነዶች ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያ የጉዞ ጋዜጠኝነት እንብዛም አልተለመደም፤ ምክንያቱ ሀገሬው ለብዙ ጉዳይ ከዳር ዳር ሲንቀሳቀስ ያየውን የሚያኖርበትና የሰማውን የሚናገርበት የራሱ ባህላዊ አሴቶች እያሉ ስለኾኑ ይኾናል፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ የውሎ ዘገባን ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታና ከመልከዓ ምድር፣ ሰውና ኩነት ጋር አስተሳስሮ ከሰነድ ጋር የማኖሩ ልምድ በዜና መዋዕል ጸሐፍቱ ዘንድ ሲተገበር ኖሯል፡፡ በሌላ በኩል የገድላት ጸሐፊዎች የቅዱሳኑን ፋና ተከትለው በሚጽፉት ገድል ላይ መሰል የውሎ ማስታወሻዎችና የጉዞ ዘገባዎች አሻራ ጎልቶ ይታያል፡፡

ዛሬ ተራ የሚመስሉት ውሎ ማስታወሻዎችና ውሎን የዋለው ሰው ገጠመኞች ነገ መረጃና ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ያጠፋነውንና ያለማነውን የምናይበት፤ በዚህ መጽሐፍ እንደምናየው ሩቅ ሰንሄድ አከሱም ዙሪያ ስለ ነበሩ ብዙ ሺህ ዝኆን የተጓዥ ማስታወሻ እናገኛለን፡፡ ደግሞ የዛሬ 175 ዓመት ገደማ በጎጃም ሜጫ ስለነበረ ዝኆን እንዲሁ እንሰማለን፤ ዛሬ ይኼ የቁጭት ታሪክ ነው፡፡ የዛሬ መቶ ሰላሳ ዓመት ገደማ ስለነበረ የአሞ ቀጮኔ መንጋ እንብበን የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ቀጮኔ እንደምን ብርቅ እንደሆነበት ከዱር አሰሳው አበሳ እንረዳለን፡፡ የምናነጽረው ተፈጥሮን ነው፡፡ በዚህ ልክ ባህል፣ ማኅበራዊ መስተጋብር፣ ኢኮኖሚና ታሪክ የየራሳቸውን ሰፍራ ይዘው እንዲህ ባለው ማስታወሻ ዘመናቸውን ወደ ቀጣዩ ዘመን ያሻግራሉ፡፡

ብዙዎችን መሳሉ ለማድረግ የተሞከሩት ሙከራዎች ዘገባዎችን ከትናንት እውነታዎችና ከቀደሙት ተጓዥ ትረካዎች ለማዛመድ የተደረገ ጥረት ነው፡፡ መጽሐፉ አንዳች ነገር ብታገኙበት የተጻፈ እንደኾነ እብሰሮ መልካም ንባብ በማለት በሩን ከመክፈት ውጪ ደጃፍ ላይ ማቆየቱ ረብ የለውምና እነሆ.....

# ከአባይ ሽለቆ እስከ ዳንጉር አናት፤ የጠረፉ ሀገር ጀግኖች፤

ቡክ-ዓለም የቴሌግራም ቻናል አዘጋጅቶ ያቀረበው መፅሐፍ

መስከረም 1 2014 የተለቀቀ.

"እኚህ ብኩን እጆች፣
እኚህ ጠባብ ሕልሞች፣
በፍርድ ግድግዳ እየተከለሉ፤
ሕያው ታሪኬ ላይ ቆሻሻ ይጥላሉ፤
ትቢያ ይከምራሉ፤
አሻራ ያጠፋሉ::
ይልቅ ንገሯቸው!
'ቀን ሰርቶ' ለሞተ - ለተስፈኛ ጅምር፤
ለሰላሳ ወለሉ ነው-የፍርስራሽ ክምር::"

በረከት በላይነህ:: የመንፈስ ከፍታ

ያለሁበት ለምልክት አይመችም:: ሁሉም ቤቶች ተመሳሳይ ናቸው:: 'ዳጃፉ ላይ እንዲኽ ያለ ምልክት ያለበት ቤት' ለማለት አንዳቸው ከሌላቸው ልዩነት የላቸውም:: ሙቀት ከበድ ይላል:: ጣሪያዋ በሳጠራ በተሰራ ቤት በረንዳ ቁጭ ብለናል:: ቀኑን ሙሉ ስለምንውል 'ራበኝ' ላለማለት ሆድ የሚይዘውን ፉል እየበላን ነው::
ፉሉ የድንበር ላይ ባህል ተጽእኖ አርፎበታል:: ለውዝ ስለገባበት ጣዕሙ ከባቄላው በላይ ኦቾሎኒ ኦቾሎኒ አለኝ:: አጣጥሜ በላሁ:: የበላንበትን ከፍለን ወጣን::

ደጃፉ ላይ ቆሜ ስመለከት ሁሉም እንስራ የመሰለ የባቄላ መቀቀያቸውን በግዙፍ ከሰል ምድጃ ላይ ጥደው መደዳውን ተሰልፈዋል፡፡ ዓይኔ እነሱን ጨርሶ ዘንባባዎቹ ላይ አረፈ፡፡

ዘንባባዎቹ ከዋና መንገዱ ጀርባ ናቸው፡፡ ከሰው ዓይን ተሸሽገዋል፤ አባይ ሸለቆ ውስጥ ነኝ፡፡ የጉምዝ ምድር ቆይታዬን ለመጀመር ዛሬ የመጀመሪያውን ጉዞ አጓዛለሁ፡፡ አሁን ያለሁባት ከተማ ማንኩሽ ትባላለች፡፡ ማንኩሽ የጥንት ናት፡፡ ታሪክ በአባይ ዳርቻ ቅድመ አክሱም ከነበሩ የኩሽ ከተሞች አንዷ እንደኾነች ይነግረናል፡፡[1]

ጉምዝ ምድር ነኝ፡፡ ኩሻውያንና የሳባ ዘሮች ኢትዮጵያን አቅንተዋል፡፡ ሰባት ናቸው ከሚባሉ ቀድሞት ኢትዮጵያን አቅኚዎች መካከል ጉምዞች ቀናዎቹ ናቸው፡፡ የዳር ሀገር የጥቁር አባይ ልጆች ዛሬ ታላቋ ኢትዮጵያ የምትባለው ምድር ስትፈጠር የነበሩ ቀዳሚ የሚባሉት ህዝቦች መኾናቸው ተጽፏል፡፡[2]

የጉምዝ ሕዝብ በካማሽና መተከል ዞኖች ውስጥ በሚገኙ አሰራ አንድ ወረዳዎች ውስጥ በስፋት ይኖራል፡፡ እኔ መተከል ጉባ ነኝ፡፡ ጉባ በወርቅ ትታወቃለች፡፡ ጹሩ የሙሜ ምድር ነው፡፡ ምድሩ ያልተነካ ድንግል፤ ሰው ደግሞ ፍቅር፤

---

*1. ፍስሐ ያዜ ካሳ፡፡ የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ፡፡ መጽሐፍ ፩፡፡ ገጽ 31*

*2. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ እንደጻፉት፡፡ የጎጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ፡፡ ገጽ 8*

ጉሳ የወረዳው ስም ነው:: የስሙ ሐሳብ የሆነውን ትልቁን ተራራ "ጉሳ" ብለው ይጠሩታል:: ትርጉሙ ብርሃን ማለት ነው:: "አንድ ወቅት ተራራው ጫፍ እብረቅራቂ ብርሃን ይታይ ነበር" ይላል ታሪኩ፤ ያንን ተከትሎ የብርሃን ተራራ አሉት:: የብርሃን ተራራ የሚለው ስም ደግሞ ብርሃን የሚለውን ወረዳ ፈጠረ:: የብርሃኑ ወረዳ ዋና ከተማ ደግሞ ማንኩሽ ሆነች::

ጉሳን ስሚመለከት ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንከረስት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ታሪክን በጻፉበት መጽሐፍ ከቋራ በታች ያለው የጉሳ ምድር ወርቅ የተትረፈረፈበት መሆኑን ገልጸዋል::[3] ጀምስ ብሩስም ዳሞት የሚባለው ምድር ቡሬ ሲደርስ ከጉምዝ ምድር የመጣ ማዕድን ገበያ ላይ ሲውል ተመልክቷል::

የማንኩሽ አየር ቢሞቅም ይስማማል:: በተደጋጋሚ ብጎበኛትም አልጠግባትም:: ከዓመታት በፊት ከነበረችበት አሁን ይበልጥ ደምቃለች:: ጎዳናዋ አጀብ ይወዳል:: የከባድ መኪና ጥሩምባ ቢረብሻትም አሽከርካሪዎች የድምቀቷ ምክንያት ሆነዋል::

እዚኸ ብዙ ቋንቋ ይደመጣል:: እዚኸ ብዙ ወዝ ከተማ ፈጥሯል:: ማንኩሽ እንኳን የሀገር ልጅን ይቅርና የጎረቤት ሀገር ሰው በፍቅር ጥላለች:: ጎዳናዋ ላይ ዓይኖቼን ሰድጄ ኢትዮጵያን አየኋት::

3. RICHARD PANKHURST, An Interoduction to The Economic History of ETHIOPIA) page 117

የሆቴሎቿን ስሞች አነበብኳቸው:: አሜድላ፣ ብሉ ናይል፣ ኢትዮጵያ፣ አቢሲኒያ፣ ዳህላክ ግዮን..... አቤት እንዴት ደስ እንደሚል!
አዲስ አበባ ካሳንቺስ እንዲኽ ያሉ ስሞች ነበሩባት፤ ዛሬ ባህር በተሻገረ ስም ቀይራቸዋለች:: እዚኽ የአራቱም መዓዘን ክብር ከየሆቴሉ ስያሜ ላይ ጎልቶ ተጽፏል::

ማንኩሽ ኩሽና የኩሽ ምድር ከሚለው ቃል ፍቺ ጋር ተዛምዶ ያላት ይመስለኛል:: ብዙ ኩሻውያን ያረበቡበት ወግ ሰምቼባታለሁ:: ምናልባትም ሌላ ፍቺ ይኖራት ይኾናል::

ጉባ የሰማኹት የጉምዝ ታሪክ እንዲህ ይላል:: አንድ ዘመን ረሃብ ኾነ:: ያ ረሃብ ከባድ ነበር፤ ከችግሩ የተነሳ ሲበሉ ለመድረስ ያሰበች አንዲት ሴት ድንገት አንድ ሰው ቤት ዘው ብላ ገባች:: ሴትየዋ የሚበስል ነገር መኖሩን ከጎጆ ጢስ አይታ ጪስ ተከትላ የመጣች ነበረች:: ስትገባ አላንኳኳችም፤ ድምጽዋም አልተሰማም:: እናም ጉምዝ በዚህ ምክንያት "ማንኩይጽ" አለ:: ቃሉ የጉምዝ ቋንቋ ነው:: ትርጉሙ ኮሽታ ሳያሰሙ ዘው ብሎ መግባት የሚል ፍቺ አለው ይላል ሌላው ተረክ:: ዘው ብዬ ነው የገባሁት:: ያው እንደሰሟ::

ሰላሳ ሺ የሚጠጋው የጉባ ህዝብ ስብስብ ብሎ ከሚታይባቸው አካባቢዎች አንዷ ማንኩሽ ከተማ ናት:: ማንኩሽ የደጃዝማች ባንጃው ማስታወሻ ናት:: ከብዙ ዘመን ዝምታዋ በኋላ የአባይን ሸለቆ ተከትሎ ከነበሩ ጥንታዊ የኩሽ ምድር ከተሞች አንዷ የነበረችበትን ዘመን ያደሱት ደጃዝማች ባንጃው ናቸው::

ደጃዝማች ባንጃው አብሽኮ ከዛሬ መቶ ስምንት አመት በፊት ከተማ ባደረጓት መዲና አቅራቢያ ከውብ አረንጓዴ ደን መሀል የልጃቸው የደጃዝማች መሐመድ ባንጃው ቤተ መንግሥት ይገኛል፡ወደ ቤተ መንግሥቱ ጉዞ ጀመርን፡፡

ሼኽ ረጂብ አልገመር የታላቁ ቤተሰብ አባል ናቸው፡፡ የታሪክ አሻራውን ለመተረክ አብረውን መጡ፡፡ የጉባ ወረዳ ባህል ቱሪዝም ባልደረባ የኾነው ጉታም አለ፡፡ መንገዱ ጥቂት በመኪና ይወስድና ከዚያ ደግሞ በእግር ይኬድበታል፡፡ በውብ መስክ በተንዠረገጉ ዛፎች ውስጥ፤
አበበ እና ባዩ ከአሶሳ ጉዞውን ቀና ለማድረግ አብረውን ደፋ ቀና ማለት ከጀመሩ ቀናት ተቆጥረዋል፡፡ ዛሬም አሉ፤ የካሜራ ባለሙያዬ ዮናታን አንዴ ቀና ብሎ ረዣዥሞቹን ዛፎች ሌላ ግዜ ደግሞ መሬት ተደፍቶ የምድሩን ሳር በምስል ያስቀራል፡፡ ሼኽ ረጂብ አልገመር የቤተሰቡን ታሪክ እያወጉኝ ነው፡፡

"የቤተሰቡ ታሪክ የጥንቱ ዘሩ አመጣጡ ከመጀመሪያ ብንገባ ከሣውዲአረቢያ የመጣ ነው፡፡ በዘመነ ነጋሺ፤ ብለው በ696 ዓ.ም. እንደሆነ ነግረውናል፤ ያኔ መጡና እዚህ ቀሩ፡፡ ግን በተዋረድ ከዚህ ዘር በኤርትሪያ በግብጽ ከግብጽ እስከ ሱዳን ኑባ የሚባል ጎሣ ገባ፡፡ እናታቸው ፈንጃ ትባላለች፡፡ የፈንጃ ልጅ ነው ተብሎ እስከዛሬ ድረስ የፉኝ ጎሣ እንባላለን፡፡"
በእርግጥ የፉኝ ጎሣ ብቻ ሳይኾን ጉሙዞች የከነዓን ዘር እንደኾኑ አለቃ ተክለኢየሱስ ዋቅጅራ የጎጃምን ታሪክ በጻፉበት የዘር ሀረግ አስፍረዋል፡፡[4]

4. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ እንደጻፉት፡፡ የጎጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ፡፡ ገጽ 14

ጉባ ዳግም በማዕከላዊው መንግሥት ስር የተጠቃለለችው በአብሾከ ዘመን በ1880 እ.ኤ.አ መኾኑን ኢንሳይክሎፒዲያ ኢትዮፒካ ላይ ሰፍሯል፡፡[6] በሌላ በኩል ሹቬየር የተባለው አሳሽ ጉባ በመጣ ሰዓት ያገኛቸው ሼህ አብሾከ የሃያ አምት ወጣት ነበሩ፤ አሳሹ ሲደርስ አስራ አራተኛውን ሚስት አግብተው የጫጉላ ዓለማቸውን እየቀጩ ነበር፡፡ ከዚያ ቀድሞ ሦስት ውብ የአረብ ሴቶች አስር ደግሞ ጥቁር ሚስቶች ነበሯቸው፡፡ ዘጠና ስድስት የሚደርሱ ልጆች የወለዱ ሱልጣን እንደነበሩ በተወልን ማስታወሻ ይነግረናል፡፡[7]

በጉምዝ ታሪክ የአብሾከና የጉባ ሱልጣኔት ዘመን ሰላማዊና መልካም ጊዜ መኾኑ ተጽፏል፡፡[8]

"አብሾከ ዝናኛ ነበሩ፤ ደጃዝማች ናቸው በማዕረግ?" አልኳቸው፡፡ የተቋረጠውን ገለጻ ለማስቀጠል፤ ተጓዡ ሹቬዮር አጃብን ሲመለከት ስለፊታቸው የገለጸውን ፈገግታ የተሞላ ትንሽ ፊት አሁን ከሚተርኩልኝ ሰው ላይ እያየሁ ነው፡፡

"አይ.... በቃ የጉባ ገዢ ናቸው፡፡ ሼህ ናቸው፡፡ ከዚያ ሼህ አብሾከ ሲሞቱ በኢያሱና በዘውዲቱ ጊዜ እንደ ምህል ሀገሩ በማዕረግ ደጃዝማች ተብለው ባንጃ ተሸሙ፡፡ ባንጃ የሙሐሙድ አባት ናቸው፡፡ ደጃዝማች ባንጃ በኢጣሊያ ወረራ ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር አብረው ብሪታኒያ ሄደዋል፡፡

6. Encyclopaedia Aethiopia 3 page 860

7.Juan Maria Schuver's Travels in North East Africa page 197

8. Juan Gonzalez Nunez, NORTH OF THE BLUE NILE. the Gumuz People. page 41

እዚያ ሄደው ነው ታመው የሞቱት፡፡ በእሳቸው ቦታ ነው ልጃቸው መሐመድ የተተኩት፡፡"

ደጃዝማች ባንጃው በጉባ ሱልጣናት የመጀመሪያው ደጃዝማች የተባሉ ናቸው፡፡[9] ባንጃው በአዲስ አበባው ቤተ መንግሥትም የተከበሩ ሰው ነበሩ፡፡ ክብራቸው እንደ አባጅፋር ነው፡፡ ደጃች ገብረ እግዚአብሔርና ደጃች ጆቴ የተሰጣቸውን ክብር አግኝተዋል፡፡ ሻለቃ ያልገባበትን ወታደር የልተደለደለበትን ሀገር ከሚመሩ ጥቂት ባላባቶች አንዱ መኾናቸውን ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ታሪክ ባኖሩበት ዝክረ ነገር ነግረውን አልፈዋል፡፡[10]

ወደ ቤተ መንግሥቱ ተጠጋን፡፡ ወዲያው ቆም እሉና ዙሪያቸውን ተመለከቱ፡፡ የሚያዩትን ለማየት አብሬ መሬቱ ላይ አንዳች ነገር ፈለግሁ፡፡ የፈረሰ የቤት መዓዘን ታየኝ፡፡ እተኩረው ዙሪያውን በዓይናቸው ዳሰሱ፤ የሚፈልጉትን አላገኙም፡፡ ወዲያው ፋሪስ መሐመድ ከመሬት እንጪት አነሱና አሰመሩ፡፡
"ይኼ እንግዳ ቤቱ ነው፡፡ ፈርሶ ነው፡፡"

ፋሪስ መሐመድ የደጃዝማች መሐመድ ባንጃው ልጅ ናቸው፡፡ ከረጂብ አልገመር በእድሜ ልጅ እግር ናቸው፡፡ ሁለቱም ነጭ ጀለቢያ ለብሰዋል፡፡ ሁለቱም ጥቁር ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡

9. Juan Gonzalez Nunez, NORTH OF THE BLUE NILE, the Gumuz People. page 41

10. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ ዝክረ ነገር፡፡ ገጽ 184

አልገመር ራመድ ብለው ወደ ፊት ቀደሙ ተከተልኳቸው፡፡ የቤተ መንግሥቱ አጥር ከፊት ሙሉ ለሙሉ ፈርሷል፡፡ ከኋላ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ እንደቆመ ነው፡፡
በፊት ገጽታው አምስት በሮች አንድ መስኮት ይታያል፡፡ ምናልባት ከበሮቹ የተወሰኑት በተመሳሳይ መልኩ መስኮት የነበሩ ከታች ያለው አካላቸው የፈረሰ ሊኾን ይችላል፡፡ በቀይ ሸክላ ነው የተሰራው፡፡ የበሮቹ አናት ባለ ከርቭ ነው፡፡

ሮቅና ምድር ነበር፡፡ መካከል ላይ የሮቁን ክፍል የሚያሳየው ፍራሽ ቆሞ ይታያል፡፡ አሰራሩ በሸክላ ይኹን እንጂ ከጎንደር አብያተ መንግሥታት ኪነ ሕንፃ ጋር የሚመሳሰል ነገር አለው፡፡
"ጎንደርን ይመስላል" አልኳቸው፡፡
"አዎ" አሉኝና ቆሙ፡፡ ሊያስቀድሙኝ ነው፡፡ በጠባቧ በር ቀድሜ እንድገባ የሰጡኝን ክብር መልሼ ለእርሳቸው ሰጠሁ፡፡ አልገመር ቀድመው ገቡ፡፡ ፋሪስ ውጪ መቆየቱን መርጠዋል፡፡ እኔ ተከተልኩ፤

"የጎንደርን ነው የሚመስለው፤ የሰራው ሱዳናዊ መሐንዲስ ነው፡፡ እሱ እዚሁ ሸክላውን አቃጥሎ ነው የሰራው፤ ደጃዝማች መሐሙድ የጎንደርን ቤተ መንግሥት ወደውት ስለነበር እሳቸው ናቸው 'እንዲኽ አድርግ' እያሉ ያን እንዲመስል አድርገው ያሰሩት፤"
አንዳንድ ሰነዶች ጉምዞች በጎንደርና በዙሪያዋ ይኖሩ እንደነበር ጽፈዋል፡፡"

[11] አለቃ አጽሜ፡፡ ፡፡ ገጽ

የአለቃ አጽሜ ሀሳብን የሚጋሩ የጉምዝ የታሪክ ሰነዶችም አሉ::[12] እኔን ደግሞ ጎንደርን የሚናፍቅ ኪነ ሕንፃ ጉምዝ ምድር ጠበቀኝ:: ውስጡ ገብተን አንዱ ክፍል ቆመናል:: ቀና ብለው አዩ፤ የሚያዩትን ተከተልኩ:: ጣሪያው ፈርሶ በአናቱ የገባችው ጸሐይ ዓይኔን ወጋኝ::

"ይኼ መኝታ ቤታቸው ነው::" ከዘራቸውን አነሱና ቀጥሎ ወደ አለው ክፍል እየጠቆሙ፤
"ያም መኝታ ቤታቸው ነው:: ሦስት ክፍል ነው መኝታ ቤታቸው፤" በጥያቄ አየኋቸው:: ስለገባቸው ቀጠሉ፤
"ብዙ ክፍሎች አሉት፤ ስጋ ቤት፣ እቃ ቤት፤ መኝታ ቤቱ ግን ሦስት ነው:: እንዴት መሰለህ? ደጃዝማች ይባሉ እንጂ በቤተሰቡ ሀረግ ቀድሞም ንጉሥ ነበሩ፤ ንጉሥ እኮ ናቸው:: አንዱ ጋ ናቸው ሲባል ሌላኛው ክፍል ያድራሉ:: እንደ ንጉሥ ነው የኖሩት፤"

ወደሚቀጥለው ክፍል ገቡ:: ከአንዱ ክፍል ወደሌላው የሚያገናኝ በር አለው:: ጣሪያው ብቻ ሳይኾን የሁሉም በርና መስኮቶች ወላልቀዋል:: ብዙ ጉዳት የደረሰበት ቅርስ ነው:: የወለቀውን በር ግድግዳ በእጃቸው መታ መታ እያደረጉ፤

"በ1978 ነው የፈረሰው:: ኢህአፓና ደርግ ብዙ ጦርነት አደረጉ:: ስድስት አመት የተዋጉበት አካባቢ ነው:: ያኔ እንዲህ ሆነ:: ኢህአዴግ ሲገባ ደግሞ ቅርሱ ተዘረፈ:: ጸሐይና ዝናብ ችሎ የኖረ ነው::"

12. በሰብስቤ ንጋዴ:: ቤዋ-የጉምዝ ህዝብ ጥንተ ታሪክ ምንጩና ባህሉ:: ገጽ 12

የዳር ሀገሩ ቅርስ ከነሞገሱ ቢኖር ክብሩ ለሀገር ነበር፡፡ የአባታቸው የደጃች ባንጃው ቤተ መንግሥት በእንግሊዝና በጣሊያን ጦርነት ወደመ፤ የልጃቸው ቤተ መንግሥት ደግሞ የደርግና ኢህአፓ የእርስ በእርስ ጦርነት አፈረሰው፡፡ እዚህ ፍራሽ ድንቅ ቤተ መንግሥት ውስጥ ቆሜ ለምን? ብዩ ጥፋታችንን ሞገትሁ፡፡

በስጋ ቤቱ በኩል አድርገን፤ ዋናውን ሳሎን አይተን በስተቀኝ ታጠፍን፡፡ አልገመር ቆሙ፤
"ይሄ እንበሳ ቤት ነው፡፡ ጅብም ነበራቸው"
"እንበሳው ከዋናው ሕንፃ ጋር አንድ ላይ አልኾነም?" ቤቱ እርስ በእርስ የተያያዘ ነው፡፡ አንበሳ ሲያጋሳ ያለውን አስፈሪ ድምጽ አሰብኩና ደጃዝማቹ ከመኝታ ቤታቸው አጠገብ አንበሳ ያሰሩበትን ምስጢር ማወቅ ፈለግሁ፡፡
"ደጃዝማች መሐመድ አባታቸው ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር ተዋደው የኖሩ ናቸው፡፡ ሲሞቱ ልጃቸን አደራ ብለዋቸዋል፡፡ ያኔ አዲስ አበባ ቤተ መንግሥት አንበሳ ሲመለከቱ ወደውት ነበር፤ ይኼንን ቤተ መንግሥት ሲያሰሩ የአንበሳ ቤት አንድ ክፍል አዘጋጁ፤"
"ይሄ ከጉባ መዐከል አይደለም"
"እንዴት?"
"ማለቴ አይርቅም? ጠረፍ ላይ ቤተ መንግሥታቸውን መሥራት ለምን ፈለጉ?" ጥያቄን አብራራሁ፤
"እሳቸው እኮ ጠረፍ ጠባቂ ነበሩ፡፡ ይኼ ሲሰራ ሱዳን ራሱን የቻለበት ጊዜ አልነበረም፤ በእንግሊዝ ቁጥጥር ስር ነበር፡፡ እዚህ ሆነው እንግሊዝ ጉባን ወደ ራሱ ግዛት እንዳይጠቀልለው ነው ቤተ መንግሥቱን ድንበር ላይ የሰሩት፤"

በጉምዝ ላይ በተጻፈ ታሪክ ያነበብሁትን አስታወስኩ፤ የጉምዝ ሕዝብ ከአማራ ሕዝብ ጋር የሚያመሳስለው ለብዙ ዘመን ከመጎራበታቸው ባለፈ ስለ ኢትዮጵያዊነት ጽኑና ተመሳሳይ እምነት መያዛቸው ነው ይላል፡፡[13]

የቤተ መንግሥቱ ጓሮ ጸጥ ያለ ነው፡፡ የዛፎቹ ዓይነተ ብዙነት፣ የቅጥሩ ማማር፣ የግንቡ ግጥም ያለ መኾን ከፊት ለፊት ገጽታው ጋር የተለያየ አድርጎታል፡፡ በኋላ በር ውጥተን ወደ ፊት ለፊቱ መጣን፡፡

ፋሪስ መሐመድ አንዲት ጥላ ስር አረፍ ብለው እየጠበቁን ነው፡፡ ወደ ተቀመጡበት ሄደን ተቀላቀልን፡፡ ብዙ ቤተ መንግስቱ ውስጥ ቆመን ስለነበር ጉብኝቱ አድክሞናል፡፡ ረዥም ሰዓት ዝም ብለን ተቀመጥን፡፡ ዓይኖቻችን ከሕንፃው ላይ አልተነቀሉም፡፡ የተቀመጥንበት ስፍራ የሕንፃ ፍርስራሽ ነው፡፡

"ይኼ ነበር የእንግዳ ቤቱ?" ስንገባ ስለቦታው ሲነግሩኝ የእንግዳ ቤት ነው ብለውኝ ነበር፡፡
"አዎ አሁን ይኼ የተቀመጥንበት፣ እዛ ድረስ የእንግዳ ቤት ነበር፤" ፋሪስ መሐመድ የእንግዳ ቤቱን ስፋት ለማሳየት እጃቸውን ዘርግተው የቤቱን ወሰን እየጠቆሙ አመላከቱ፡፡
"ምን መሰለህ? ጉምዝ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በገዛ ቤቱ የእንግዳ ቤት አለው፡፡ እንግዳ አይጠላም፤ ባህሉ ነው፡፡ እንኳን ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ቀርቶ፤" አሉ አልገመር፤

13. ከጉምዝ አባቶች ጋር በተደረገ ቆይታ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የሚደመጠው በኢትዮጵያዊነት ጉዳይ ጠንካራ አቋም አለን የሚለው ነው፡፡

ተገርሜአለሁ:: ፋሪስ መሐመድ በትዝታ ነጉደዋል:: ትናንትናን እየተመለከቱ ነው:: ይኼ የገባኝ ከዝምታቸው በኋላ ከሄዱበት ሲመለሱ ነበር፤

"እኔ ማንኩሽ ነው የተወለድኩት፤ ያኔ የነበረውን ለመግለጽ.....ወላሂ ከባድ ነው:: ከባድ ነው:: መግለጽ ያቅተኛል:: አባቴ ደጃዝማች መሐሙድ ሲሞቱ ስድስት አመቴ ነበር:: እስከአሁን የማይረሱኝ ብዙ ነገሮች አሉ:: ትዝታው የግቢው ውበት የሰው ሁኔታ፤ ምን ዋጋ አለው፤ ቤተሰቡ አቅም አጣ:: እንደበፊቱ አቅም ኖሮን ብንጠግነው ጥሩ ነበር፤ ግን....."

ዝምታ ዋጠን፤ ቤተሰቡ አቅም የለውም:: ፊውዳል በሚል ቅስሙ እንዲሰበር ብዙ ተሞክሯል:: መገለል የደረሰበት ቤተሰብ ነው:: በብዙ መከራ ውስጥ ያለፈው ቤተሰብ ከመቆጨት ውጪ ምንም አቅም የለውም:: እኔም ከመቆጨት ውጪ ምንም አቅም የለኝም:: ከአምስት ዓመታት በፊት ስመጣ ስለ ጉባ ቅርሶች እና ስለ ደጃዝማቹ የታሪክ አሻራዎች ተነግሮኝ ነበር:: ዛሬ ወሬው የለም፤

ከተቀመጥንበት ተነሳን:: ደጃዝማች መሐመድ ባንጃው ትልቅ ሰው ናቸው:: የኢትዮጵያ የዳር ሀገር ከንድ ናቸው:: ስለ እነኛ ቅርሶች አሰብሁ:: ባለ አንበሳ ምልክቱን መጠጫ ኩባያቸውን አይቼዋለሁ:: በ1936 የተጠቀሙባቸውን ጠረጴዛዎች እና ድንቅ የኾነውን የእንጨት አልጋ በእጄ ዳስሼዋለሁ:: በ1944 ይዘውት የነበረውን ጠመንጃ ፎቶ አንስቼው ነበር::

በ1935 ጉባ ወንጀለኛ ይታሰርበት የነበረውን የደጃዝማች ሰንሰለት የተመለከትሁ እማኝ ነኝ:: ከቀንድ በተሰራ የድቁስ በርበሬ መያዣቸው ተገርሜ አገላብጬዋለሁ:: ከነሐስ የተሰራው የእጅ መታጠቢያቸው የት ይኾን? ከሰባት መቶ ሃያ ዓመት በላይ ኖረ የተባለው ጎራዴስ?

ስለ ቅርሶቹ እያሰብሁ ከሀሳቤ ሳልወጣ መንገዱን ጨረስሁት:: የድንበር ላይ ጀግናውና ሀገሩን ባለውለታ ታሪክ ይዘከራቸው ዘንድ ስለ እሳቸው መጻፍ እንዳለብኝ አሰብሁ፤ ግን መቼ?

በመኪናችን ተሳፍረን ወደ ማንኩሸ የመልስ ጉዞ ላይ ነን:: ሹፌራችን ሸመልስ የመኪናውን ቴፕ ከፈተው::

"ተውኝ ይውጣልኝ ልጥራት ደጋግሜ
ኢትዮጵያ ማለት ለእኔ አይደል ወይ ስሜ?" ስለ ዳር ሀገሩ ጀግኖች ማውራት ስለኢትዮጵያ ማውራት አይደል? ሹፌራችንን "ድምጽ ስጠው" አልኩት፤ መኪናዋ በመንፈስ ወደ አርአያም ሄደች:: የወሰዳት የብላቴናው ሙዚቃ ነበር፤

# በአባይ ሸለቆ ውስጥ

"ያልተሄደው መንገድ
ከቶም ሄደን ሄደንማ፣ ከሰው ዐይን ካልተሰወርን
ምኑም ያለምነው ቦታ፣ እግባችን ጋ ደረስን
ከመንገድ ሁሉ ቆንጆ
አግር ያልረገጠው መንገድ ነው
እንደምንም ብለን ዘልቀን፣ ባልተሄደ መንገድ ከሄድን
ቢያንስ በማናውቀው አገር፣ አዲስ ዱካ እናኖራለን፡፡"

ነብይ መኮንን፡፡ ሰውር ስፌት

አንዳች ነገር ጮኸ፡፡ ድንገት ነቃሁ፡፡ ቀና ስል ሁሉም ሰው መሬት ተዘርሯል፡፡ በረንዳ ላይ ነው ያደርነው፡፡ አጠገባችን የቆመው ትራክተር ሞተር ሲያሞቅ ያጓራው ድምጽ እኔን ብቻ ሳይሆን ጓዶቼንም በአንድ ጊዜ አነቃቸው፡፡

ድካም ጥሎት የነበረው ሁሉ በትራክተር ድምጽ ተነሳ፡፡ የየራሳችንን መኝታ ሰበሰብን፡፡ ገና አስራ ሁለት ሰዓት መኾኑ ነው፡፡ ለትራክተሩ በተከፈተው በር የጎዳናውን መንገድ ስመለከት ሰው መንቀሳቀስ ጀምሯል፡፡ ያደርንባት ከተማ ጉብላክ ትባላለች፡፡

ብዙው ሰው ኑሮን እርሻ ላይ አድርጎ ጎኑን የሚያሳርፍባት ትንሽ ከተማ ናት፡፡ ወደ ማሳው ለመሄድ የሚጣደፈው ሰው ማጭድና ቆንጨራውን እየያዘ በየአቅጣጫው መበተን ጀምሯል፡፡

ሹፌራችን ሽመልስ መኪናችንን ሲያሞቅ እኛ ጓዛችንን ከጀርባዋ ጫንን፡፡ ለጉብላክ ቀድሞ ነው የሚነጋው፡፡ በላቡ የሚያድር ህዝብ ከተማ ስለኾነች ጨለማው ሲለቅ ሁሉም ምድርን ለመታገል ብድግ ይላል፡፡

የሆቴሏን በረንዳ አንጥፈን እንድናድርበት የፈቀደችልንን የሆቴሏን ባለቤት አመስግነን ጉዞአችንን ጀመርን፡፡ መኪናችን የሆቴሉን በር እንደወጣች አንገቴን መለስ አድርጌ የሆቴሉን ታፔላ አነበብኩት፤ "መገናኛ ሆቴል" ይላል፡፡

የቤጃሚዝን መንገድ ጀምረነዋል፡፡ የቤጃሚዝ ብሔራዊ ፓርክ ቆላማ ሥነ-ምህዳርን የጉብኝታችን መጀመሪያ አድርጌው ነው፡፡ መንገዱ ሲለው ምቹ ሲከፋ ደግሞ አበሳ ይኾናል፡፡ በሣር ደን መሃል የተቀደደውን ጎዳና ተከትለን መድረሻችንን ፍለጋ ቀጠልን፤

ሁለት ፖሊሶች ይዘናል፡፡ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የመጣ ባለሙያም አብሮን አለ፡፡ ምኒልክ ግርማ ደግሞ የዞኑ የመሬት አስተዳደር ባለሙያና ብሔራዊ ፓርኩን የከለለ ወጣት ነው፡፡ መንገዱን ደህና አድርጎ እንደሚወጣው ከተከለ ቁመናው ተረዳሁ፡፡ ስፖርተኛ እንደኾነ ጡንቻው ያሳብቃል፡፡ በዚያ ላይ ጓዝ አላበዛም፡፡

በቀላሉ የተቦረቦሩና አላስኬድ የሚሉትን ጠግነን አለፍናቸው:: ሽመልስ በእውነት የሚመሰገን ሹፌር ኾኖ አግኝቼዋለሁ:: መንገድ እየሰራ የነዳው ጣሊያን ብቻ ይመስለኝ ነበር:: ከባድ የሚመስሉ ሳንካዎችን ድል አድርገን ስንሻገራቸው በኔ ዘመኑ ሽመልስ ኮራሁ::

መኪናችን ቆመች:: ትልቅ ወንዝ ነበር ከፊታችን የሚገማሸረው:: ድምጽ አያሰማም:: ድፍርስ አይደለም፤ ይልቁንም ንጣቱ ጥም ያብሳል:: ከመኪናችን ወረድን፤ "ይኼ ዱርባ ወንዝ ይባላል፤ ፓርኩ እዚህ ጋር ነው የፓርኩ ድንበር" አለና ግርማ አንዲት ጽሑፍ የተጻፈባት ወንዙ ዳር የተተከለች ድንጋይ ጋ ቆመ:: ጥም ቆርጦ የሚቀበለው ፓርክ ለጋስ እንደኾነ ዱርባ ወንዝ አበሰረኝ::

181,627 ሄክታር ስፋት ያለውን ብሔራዊ ፓርክ ገባንበት:: ዳግም ወደ መኪናችን ገባን:: ከኋላ የተጫኑትም ተሰቀሉ:: በቅርቀሃ ደን ውስጥ እየተጓዝን ነው፤ ወደ ብሔራዊ ፓርኩ ከመምጣቴ በፊት ብሔራዊ ፓርኩን ለመከለል ጥናት ያጠኑ ሰዎችን የጥናት ውጤት አንብቤአለሁ:: በጥናቱ መሠረት ቤጃሚዝ የበርካታ ዱር እንስሳት መኖሪያ ነው:: ሃያ አራት የሚደርሱ አጥቢ እንስሳት ዝርያዎች ይኖሩበታል::[14]
በዐፄ ምኒልክ ዘመን የወጣው የአውሬ አደን ሕግ ይኽንን አካባቢ በሚመለከት ያወጣው ሕግ ትናንትናውን ለመረዳት ያስችለናል::

*14. Ethiopian wildlife conservation authority, reports of the wildlife resource assessment of Bejimiz bereha of Dangur and Guba werdas of Metekel Zone of Beneshangule Gumuz Region, prepared by Temesgen Yadeta and Abiot Hailu. may 2013*

ዝክረ ነገር በኢትዮጵያ አደን የማይፈቀድባቸውን አካባቢዎች ሲዘረዝር በቤኒሻንጉል አውራጃ ሙሉ ለሙሉ አደን ከልክል መሆኑን ይገልጻል::[15]

ከዲንደር ደቡባዊ ከፍል ያለው የጉምዝ ምድር የወርቅ፣ የዝሆን እና የጥጥ ምድር መኾኑንም አንብቤአለሁ::[16] ከቋራው አልጣሽ ብሔራዊ ፓርክ ጋር የሚዋሰነው ይኽ ሥነ-ምህዳር ብዙ ሀብት አከማችቷል::

ደከመን:: በማይመች መንገድ ረዥም ርቀት በመኪና መጓዝ በእግር ከመጓዝ በከፋ ሰውነት ይጎዳል:: ጥላ ፈልገን መኪናችንን አቆምን:: ምሳ መብላት ይኖርብናል:: ወንዝ ተጠግተን ማረፊያችንን አዘጋጀን:: አሁን ያለንበት ቦታ ከብሔራዊ ፓርኩ መግቢያ አስራ ሦስት ኪሎ ሜትር ገደማ ይርቃል::

እኛም እንደ እንስሳቱ ወንዝ ተጠግተን ነው የምናርፈውም፤ የምንበላውም:: ለምሳ የመረጥነው ውስካ ወንዝ ዳርቻን ኾነ:: የቋጠርነው ስሃን ተከፈተ:: ሁለት ቦታ ቡድን ሰራን:: እኔ ያለሁበት ቡድን አምስት ነን:: ሁለተኛው ቡድን ስድስት ናቸው:: ምሳችንን በላን፤ የበላንበትን በውስካ ወንዝ አጣጠብን:: ጥቂት እረፍት ካደረግን በኋላ ጥላው ስር መኪናችንን አቁመን ቀሪውን መንገድ በእግራችን ተያያዝነው:: የፓርኩ ጥናት ቡድን ሪፖርትን ሳነብ ያልገባኝ የፓርኩ አንድ ስጋት ሰደድ እሳት ነው የሚለው ነበር::

15. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል:: ዝክረ ነገር:: ገጽ 350

16. Encyclopaedia Aethiopia 4 page 343

ሰደድ እሳት ባቃጠለው ምድር፤ ረመጥ አፈር ላይ እየረገጥን ስንጓዝ የቃጠሎ ስጋቱን አሁን በዓይኔ አየሁት፡፡
የስድስቱ ወንዞች ምድር ሁሉን አቀፍ ነው፤ አንዳንዱ ጋ ረግኝዥም ሳር ተኝቶበታል፤ ሌላው ጋ ደግሞ ግዙፍ ሀገር በቀል እጽዋት ተንዠርገዋል፡፡ አይማ እስከ ቋራ ስሙ የገነነ ወንዝ ነው ቤጃሚዝን ያካልለዋል፡፡ የስሙ መጠሪያ የኾነው የቤጃሚዝ ወንዝም ትልቅ አፍላግ ነው፡፡ አንጃ፣ ዱርባ፣ ሂደታንና አዋዚካ ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ናቸው፡፡

በርከት ያለ እንስሳ እናገኛለን ብለን ብዙ ተጉዘን መጥተናል፤ እስከአሁን የተመለከትኩት እንስሳ የለም፡፡ ዳና እና ትኩስ በጠጥ እዚህም እዚያም ስንመለከት ፍለጋችንን በወኔ ቀጠልን፡፡ ዓይን ለዓይን እንገናኛለን ብለን ያሰብናቸው እንስሳት ብዙ ነበሩ፡፡ አንዳቸውንም ለእኛ ዓይን አላላቸውም፡፡ አንዳንዴ እንዲኽ ያለ ፓርክ ሰፊ ግዜ መውሰድ ጥቅሙ ብዙ ነው፡፡ በደርሶ መልስ እንስሳትን ለማየት ማሰብ ውጤቱ የእድል ጉዳይ የሚወሰነው ይኾናል፡፡

የመጨረሻ እድላችን አንዷት ስፍራ ጋ ሄዶ ትንሽ መጠበቅ ነው፡፡ ተፈጥሮ ሀብቱን እስኪበቃን አይተንዋል፤ በደኑ ውስጥ ሾልከናል፤ በሚያስፈሩ መንገዶች ደፍረን ተጉዘናል፡፡ ከመኪና ወርደን በእግር ብዙ ሄደናል፡፡ አጃቢዎቻችን የቀረን አንድ ቦታ መኾኑን ሲነግሩን ያለ ድካም ውሰዱን አልን፤ ብንደከምም ጉዞው ቀጠለ፤ ስለመመለስ አለማሰባችን ሳያበረታን አልቀረም፡፡ ሙቀቱ ሃይለኛ ነው፡፡ የአባይ ሸለቆ ውስጥ በቀኑ እኩሌታ መገኘት ከብደቱን ኖረው ካዩት አንዱ ኾንኩ፡፡

"እዚ ነው ቦታው...." አጃቢያችን ቆም አለና ያነገተውን መሣሪያ ከትከሻው አወረደ፤ ዙሪያውን ሳይ ምንም የለም፤ አረንጓዴና ለም የሳር ምንጣፍ ዙሪያውን በደን በተከበበ ገላጣ መሬት ላይ ተዘርግቷል፡፡ ሳሩ ያረፈበት ገላጣ መሬት ውሃማ ነው፡፡ "ምንድን ነው?" በሚል ጠየቅን፤
"ሙቅ ውሃ" አለ አሁንም አጃቢያችን፡፡
"ፍል ውሃ ነው፡፡ ጨዋማ ነው፡፡ እዚህ ነው እንስሳቱ የሚጠጡት ሳሩ ራሱ ጨዋማ ነው፡፡" ግርማ ስፍራውን በደንብ ስለሚያውቀው የተሻለ ገለጸልን፡፡ ትኩስ ዳና መሬቱ ላይ ታትሟል፡፡ ዱር እንስሳቱን ማየት አልቻልንም፤ በዳናው መከራከር ጀመርን 'የከርከሮ ነው' 'የድኩላ ነው' የሚለው ክርክር የፈለግነውን እንዳጣን አስረሳን፡፡

ለመመለስ የተነሳነው በቂ እረፍት ሳንወስድ ነበር፡፡ መንገዱ እንደሚርቅ ስላወቅን በግዜ ከዚህ መውጣት አለብን፡፡ አላየናቸውም ብለን ስለተነገረላቸው አንበሶች ከማሰብ አልተቆጠብንም፤ ሊያውም ከፍርሐት ጋር፤

የአእዋፍ ድምጽ በጣም ይሰማኝ ጀምሯል፡፡ አንዳች ምልኪ ያለው እስኪመስለኝ ዜማቸውን ከማድመጥ ምን ሊፈጠር ይኾን ብዬ ሰግቻለሁ፡፡ ፓርኩ ከ121 በላይ የሚኾኑ የአእዋፍ ዝርያዎች መገኛ ነው፡፡ የብሔራዊ ፓርኩ የጥናት ሪፖርት ላይ ስሟ የሰይጣን ዶሮ የምትባል ወደ ብርቅዬ የተጠጋች ወፍ መኖሯን ማንበቤ የአእዋፉን ዜማ ከማጣጣም ይልቅ ምን ሊመጣ ይኾን ብዬ በንቃት መጠበቅ ውስጥ ገብቻለሁ፡፡[17] የሰይጣን ዶሮ የምትባለው እንደ ስሟ ትኾን?

17. Ewca, reports prepared by Temesgen Yadeta and Abiot Hailu, may 2013

ድካም ተሰምቶናል። የእግር መንገዱ እያለቀ ነው። ከዚያ ጉዞው እንዳመጣጣችን በመኪና ነው። መመለስ መኖሩን ረስተን ብዙ ተጉዘን ነበር። መኪናችን ባቆምናት ጥላ ስር ኾና ታየች፤ ስንደርስ ብዙው ሰው ይበልጥ አቅም አጣ። እንደ ደረስን ከመሳፈር ይልቅ መኪናው ስር ከተነጠፈው ጅባ ላይ ተዘረርን። የቤጃሚዝን ሰማይ እንደ አንሶላ ለበስኩት።

# ወደ ዳንጉር እናት፤

*"አባቴማ ድሮ፣ ስንዴ እያበጠረ፣*
*አንዳንዱን እንክርዳድ፣ ይለቅም ነበረ፡፡*
*እኔ ግን ዘንድሮ፣ ግርድ አነፍሳለሁ፤*
*ከእንክርዳዱ መሀል፣ ስንዴ 'ፈልጋለሁ፡፡"*

ይስማዕከ ወርቁ፡፡ የቀንድ አውጣ ኑሮ

ማናችንም ማታ በፎከርነው ሰዓት ጠዋት አልነቃንም፡፡ ድካሙ ገድሎናል፤ 'ወፍ ሳይጮኽ' ተባብለን የወፍ ላንቃ ተቀዶም አልተነሳንም፡፡ ሀሳብ የኾነበት ሹፌራችን ቀድሞ ተነስቶ በር በራችንን ደብድቦ አስነሳን፡፡ በአባይ ሸለቆ ውስጥ ያደረግነው የእግር ጉዞ አቅም አሳጥቶን ነግቶም ደብቶናል፡፡

ተነስተን በአጭር ጊዜ ዝግጅታችንን ጨረስን:: ያደርንባት ከተማ ማንቡክ ትባላለች:: ከተማዋ ስያሜዋን ያገኘችው ከማንቡክ ወንዝ ነው:: በእርግጥ ቃሉ ቀጥታ አይደለም:: 'ማንቦጓ' ከሚለው የጉምዝ ቃል የመጣ ነው:: ማንቦጓ መዋቢያ ማለት ነው ትርጉሙ:: የጉምዝ ሴቶች ወደ ወንዙ እየወረዱ የሚዋቡበት፤ እናም ወንዙን ማንቦጓ ሲሉ መዋቢያ አሉት:: ማንቦጓ የሚለው ቃል ደግሞ ማንቡክን ወለደ አሉኝ:: ከአሶሳ ከተነሳሁ ሦስተኛ ቀኔ ነው:: ከአሶሳ ማንቡክ ያለው ርቀት 379 ኪሎ ሜትር ይደርሳል::

በጨለማ ያየነውን ስንጋ ለመብላት ቋምጠናል:: ጓዛችንን መኪናችን ላይ ጭነን ወደ ሆቴሉ ስጋ ቤት ገባን፤

ስጋ ቤቱ ትናንት የቆመውን በሬ አላረደውም መሰል፤ የስጋ ማንጠልጠያው ላይ የጠበቀን ስጋ ትንሽና ቅንጥብጣቢ መሳይ ነው:: በምናየው ነገር ግራ ተጋብተናል:: ትናንት ስናስጠነቅቅ ያመሸነው ቁርስ እንዲመጣልን ተናገርን::

"እዚህ እኮ ስጋ በጠዋት ነው" አለ ስጋ ቤቱ፤ ከአንድ ሰዓት የሚቀድም ጠዋት ስንት ይኾን? በሚል ተያየን:: ልክ ነበር፤ ማንቡክ ሲያቅላላ የታረደው በሬ ጸሐይ ስትወጣ ትዝታውም አይተርፍ::

እንዲህ ናቸው ስጋ ቤቶቿ፤ የሰጡንን ከመብላት ውጪ ምርጫ የለንም:: ለቀናት የሚኖረን ቆይታ እንዲኾ ካለው ቅንጡ ምግብ እንደሚያለያየን በየልባችን ገብቶናል:: ያለ መነጋገር ስምምነት ላይ ደርሰን የቀረበልንን በላን::

የምናበስለውን ምግብ ለመሸመት የወሰድነው ጊዜ ከገመትነው በታች በኾነ ፍጥነት አለቀ፡፡ የሚጠብቀን ተራራ አትል ሰዓት እንዳይጋፈጠን ሁሉን ነገር በጥድፊያ ነበር ያከናወንነው፡፡ በርበሬ፣ ጨው፣ ዘይት፣ ክብሪት፣ ለእጅ ባትሪ የሚኾኑ ድንጋዮች፣ ሽንኩርትና ማካሮኒ ሌላም ሌላም፤

አስቤዛችንን ለመግዛት ብዙ ሱቅ ጎራ ብለናል፤ ጊዜ ለመቆጠብ የምንገዛውን ተከፋፍለን ነበር፡፡ የማንቡክን ብዙ ሱቅ ስመለከት ከግብርና የተቆራኘ ኾኖ አገኘሁት፡፡ ሰውም ቢኾን ወጉ ስለ ምድሩ እርሻ ነው፡፡ ምድር ምን ያህል ፍሬ እንደሰጠችው የሚያወራው እና እንዲኽ ያለውን ወግ ደስ ብሎት የሚያደምጠው ይበዛል፡፡ ብዙ ቋንቋ የሚሰማባት ከተማ ናት፡፡ የሰው ልጆች ከተማ፤

838,700 ሄክታር ቆዳ ስፋት ካለው ዳንጉር ወረዳ ብዙው ምድር ቆላማ ነው፡፡ ሦስት እጁ ቆላማ በሆነበት ምድር ደግሞ ሃያ በመቶ የሚሆን አስደናቂ ደጋ አለ፡፡ ማንቡክ ግን ሞቃታማ ናት፡፡ በ1962 ዓ.ም. ነበር ከተማ ሆና የተቆረቆረችው፡፡ ከከተማዋ ታሪክ ጋር ባለውለታ ሆነው ፊታውራሪ ኢያሱ ዘለቀ እና አቶ ተፈራ ሆሬ ስማቸው ጎልቶ ይነሳል፡፡

ጣጣችንን ጨርሰን ማንቡክን ለቀን ተንቀሳቀስን፤

በመኪና ብዙ መንገድ መጥተናል፡፡ ቀጣዩን የእግር ጉዞ እያሰብን ስለነበር ርቀቱ ሳይታወቀን ከመኪና የምንወርድባትና የእግር መንገድ የምንጀምርባት ስፍራ ደረስን፡፡

ድባጉያ የምትባለው የጉምዝ መንደር ይኸች ናት። ወደ ትልቁ ተራራ ለመውጣት የእግር ጉዞው የሚጀምርባት ስፍራ። ከዚህ በኋላ መንገዱ የሚወስደው ጊዜ እንደ ጎበዝ እግር ፍጥነት የሚለካ ይኾናል። ወረዳው ዳንጉር ይባላል። ዳንጉር የሚለው ስም የተገኘው ከተራራው ነው። ተራራው እናት ደግሞ ደጋማዋ ምድር ዳንጉር ቀበሌ አለች።

'አህያ የሚያከራይ ፈልጉልን' ስንል ወዲያው አንድ 'ወጣት እኔ አለሁ' ብሎ አህያ እየጎተተ መጣ። ጓዛችንን በአህያ ለመሸከፍ ግን ብዙ ደከምን፤ ስናስረው ሲፈታ በየራሳችን ከሆነልን ብለን ስንሞክር አህያዋ እየተልመጠመጠች አደከመችን።

የድባጉያ ሰው ተረባረበ ማለት ይቻላል። አንድ የመንደሯ ታዋቂ ሰው ደህና አድርጎ ሸከፈው። ከዚያም ደረቱን ገልብጦ ከርቀት ወደሚታየን ተራራ ጉዞው ተጀመረ። እኛ አህያችንን ጭነን ሸቅብ ስንወጣ ደገኛው አህያውን ጭኖ ቁልቁል መውረድ ጀምሯል። በአኩሪ አተር ማሳ፤ በሰሊጥ እርሻ ትይዩ ቀጥ ያለውን ተራራ ተጠጋነው። ይኸ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ሁለተኛው ረዥሙ ተራራ ነው። ዓይን እግርን ቢሰማው ማንም መንገድ አይጀምርም ነበር። የምናየውን ለመድፈር እግር ጉዞ ላይ ነን።

ሳሩ እንደ አጥር ቆሞ በግራም በቀኝም ያለውን ማሳ ከዓይን ከልሎታል። 'እዚያ ተራራ ላይ እደርሳለሁ' ብሎ መንገድ ከመጀመር በላይ ተስፈኝነት የለም። ከአህያ የተረፈውን ጓዝ ተከፋፍለን በየእጃችን ይዘናል።

አጃቢው ፖሊስ የራሱን መሳሪያ ብቻ አንግቷል፤ የካሜራ ባለሙያዬም እንዲኹ የራሱ ካሜራ ይበቃዋል ተብሎ ነጻ ኾኗል፡፡ እኔ የካሜራ ትራይፖድ ከአንጠለጠልኩት የፎቶ ካሜራ ጋር ይዣለሁ፡፡

ዛሬም ያልተለየን የወረዳው ባህል ቱሪዝም ባለሙያ ይርጋለም ኃይሉ በቅጡ ያልተጠቀለለ ስሊፒንግ ባግ አንግቧል፡፡ ብዙ ነገራችንን በማገዝ እንደ ምኒልክ ውለታ የዋለልን የለም፡፡ አበበ እና ባዩም እንዲሁ ጓዝ አዝለዋል፡፡ ረዥም ርቀት ሳንጓዝ አብሮ የተነሳው ቡድን ሦስት ጎራ ተከፈለ፤

ከአንድ ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ስንነሳ የነበረው የእርምጃ ፍጥነታችን በከፍተኛ ሁኔታ ቀነሰ፤ በአልተሰበሰበ ማሳ ውስጥ አዝመራውን ሰንጥቀን እየተጓዝን ነው፡፡ ያ ርቆ የሚታየው ተራራ አሁንም በስፍራው ነው፡፡ እኛ ወደ እሱ እንሄዳለን እንጂ እሱ ወደ እኛ አይመጣም፤ በተጠጋን ቁጥር አልደረስንበትም፤

እኔ ከቀደመው ቡድን ጋር ነኝ፡፡ መካከል ላይ ከፊት እኛን ከጀርባው ደግሞ ወደ ኋላ የቀሩትን እየተመለከተ የሚጓዝ አለ፡፡ የተወሰነ ቦታ እስከንደርስ ቀድሞ መንገድ የገፋው አረፍ ብሎ የዘገየውን ይጠብቃል፡፡ የጉዞ ደንብ ያደረግነው ይኸ ሥርዓት እስከ ምሳ ሰዓት ድረስ ብቻ ነው የቆየው፤ መቼም ዳንጉርን ፍለጋ የሚጓዝ የሚያየው ተአምር ነው፡፡ የቤጃሚዝ ሌላው ስፍራ ይሄንን አልፎ ይገኛል፡፡ አቤት እጽዋት፣ አቤት የተፈጥሮ መንገድ፤ በደን ውስጥ ሽቅብ የሚያስወጣውን ኮረብታማ መንገድ ተያያዝነው፡፡

ሁሉ ነገር እንደነበር አልቀጠለም፤ መተራረቡ፣ ጨዋታው፣ ሳቁ ሁሉ ለመንገድ በሚከፈል መስዋዕትነት በዝምታ ተዋጠ፡፡
አንዲት ምንጭ ዳር ደረሰን፡፡ እውነት ለመናገር ለመጠጣት እንኳን አቅም አጣሁ፡፡ ዳሯ ላይ ዝርር ብዬ ተዘረጋሁ፡፡ ዮናታን የምንጯን ውሃ ግንባሬ ላይ አስነካኝ፤ ጫማዬን ፈታሁ፡፡ ድንጋዩ ላይ ተለጥፋ ቁልቁል ውሃውን ከምታወርደው የብሳና ቅጠል ላይ እንደ እንስሳ አፌን ለግቼ ቀዝቃዛዋን ምንጭ ጠጣኋት፡፡

አብረን ተነስተን አብረን ያልደረስነው መንገደኞች ለመጨረሻ ጊዜ የተጠባበቅነው እዚኽ ነው፡፡ የዘገየው ቡድን ከአርባ ደቂቃ በኋላ ደረሰ፡፡ የቋጠርናትን ፈታንና ምሳችንን በኅብረት በላን፡፡ ምንጯን እንደ እረፍት ውሃ ቆጠርናት፡፡ ሙሴ በበርሃ እንዳፈለቃት እረፍት ውሃ፡፡

የሚከብደው መንገድ ከዚህ በኋላ ያለው ነው፡፡ አንዳችን ሌላችንን አበረታታን፤ ቀጥ ያለውን ዳገት ጀመርነው፡፡ ቤጃሚዝ በርሃ ነው፡፡ ቤጃሚዝ ደጋም ነው፡፡ ደጋውን ምድሩን ፍለጋ ወደ ዳንጉር አናት እየወጣን ነው፡፡ እጄን ጉልበቴ ላይ እያደረግሁ ራሴን ለማኅበዝ እሞክራለሁ፡፡ የሳር ደኑን በእጆቼ እየጣስኩ ለሀሳቤ ወደ ራቀው ምድር እግሬን እልካለሁ፡፡ ሽቅብ ተራራው ቢያፈጥብኝም ያለፍኩትን ዞሬ ስመለከት እበረታለሁ፡፡ የቻልኩትን ማመን ያቅተኛል፡፡
በጤፍ ማሳ የተከበበች አንዲት የደጋ መንደር ደረስን፡፡ መንደሯ ልዩ ውበት አላት፡፡ 'ደርሳችኋል' የሚለውን ሳልሰማ መንደሯን ለማድነቅ አልፈቀድሁም፡፡ የማየውን እንዳላየ አየሁት፡፡ ሳር ቤቶች በግዙፍ ሀገር በቀል ዛፎች ተከበዋል፡፡

መንደሯ መሀል የጉድጓድ ውሃ በእጃቸው እየወዘወዙ ከጥልቁ ጉድጓድ ውሃ የሚያስተፉ ሕንፃናት አገኘን:: ከእኛ መሃል የቀደመኝ አልነበረም::

"ልጆች ይሄ ደንጉር ነው?"

"አይደለም...." ሰው እንዴት እኩል ይመልሳል? እኩል በመለሱልኝ ልጆች ተገረምሁ:: ወደ ውሃው ቧንቧ ተጠጋሁና ራሴ ላይ እንዲያፈሱልኝ ጎንበስ አልሁ:: ተሽቀዳድሞ አንዱ ልጅ ወደ ላይ የሰቀለውን ብረት ወደ ታች ጎተተው:: ራሴ እስከ አንገቴ በውሃ ራሰ::

እንደመጠባበቅ ብለን ቧንቧዋ አጠገብ ካለች ዛፍ ስር አረፍ አልን:: ልጆቹ ለዳንጉር ምን ያኸል እንደቀረን ለተጠየቁት ጥያቄ አንድ ዓይነት መልስ አልመለሱም::

"አንድ ሰዓት..."

"ኸረ ቅርብ ናት...ሳይመሽ ትደርሳላችሁ፤"

የአንዱን አልሰማነውም:: በጉምዝኛ ነበር ያወራው፤ በእርግጠኝነት እሱም እንደእነሱ 'ይኼን ያኸል ቀርቷችኋል' ነው ሊለን የሚችለው::

ተነሳን::

ጉዞው ዳግም ቀጠለ::

አሁን የምናየው ተስፋ ሰጥቶናል:: ተናፋቂዋን ደጋ ምድር ያገኘናት እስኪመስለን መንገዱ በውብ እጽዋት አጅቦናል:: ዳንጉር ተራራን በላያ ተራራ በቁመቱ ይበልጠዋል:: በላያ 2737 ሜትር ከፍታ አለው:: ዳንጉር ደግሞ ከባህር ጠለል በላይ 2488 ሜትር ይደርሳል::[18]

18. Juan Gonzalez Nunez, *NORTH OF THE BLUE NILE. the Gumuz People*, page 18

ውለው የሚገቡ ከብቶች መንደር አካባቢ ስለመድረሳችን ምልከት ሰጡኝ፡፡ አሁን 'ደርሳችኋል' የሚለውን ቃል ከመስማት በላይ የምሥራች የለም፡፡ የቅድሚ መንደር ለዚህ መንደር መንገድ ምልከት ናት፡፡ እዚኽ ያለው የጤፍ ማሳ ደግሞ እንዲኽ የሚነገር አይደለም፡፡ የታጠሩ ቅጥሮች እርግጥም ዳንጉር ይኹን አይኹን እንጃ እንጂ መንደር መድረሳችንን ነግረውኛል፡፡
"ይኼ መንደር ማን ይባላል?"
"ዳንጉር" ሞፈር ተሸክሞ የሚጓዘው ገበሬ የት መድረሳችንን አበሰረን፡፡ ደስታዬ ወሰን አልነበረውም፡፡ መንገዱ ላብ በላብ ቢያደርገኝም ከሙቀቱ ይልቅ የዳንጉር ብርድ ያዘለ ነፋስ ውስጤን ዘልቆ ተሰማኝ፡፡

እንዴት ያለ ቸር ምድር ነው፡፡ ምድሩ ላይ የተኛው የጤፍ ዛላ አይቼው የማላውቀው ዓይነት ነው፡፡ ብዛቱም ውበቱም ተለየብኝ፡፡ ከጤፍ የተረፈውን መሬት ረዣዥም ሾላና ዋርካ ተንዠርጎበታል፡፡ ከዚያ የተረፈው ደግሞ ጥድና ወይራ ነው፡፡ በቀረው ወፍ ዘራሽ ዘንባባ ይወዛወዛል፡፡

ቀበሌዋ ስብስብ ያሉ የሳር ቤቶች የፈጠሯት ከተማ አላት፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እዛና እዛ ተራርቀው ይታያሉ፡፡ ቆርቆሮ ቤት አንድ ነው፡፡ እሱም የቀበሌው ጽሕፈት ቤት መኾኑን ነግረውኛል፡፡
በጣም ደክሞናል፡፡ መንገድ ያገኘን የዳንጉር ገበሬ ወደ ቤቱ ወሰደን፡፡ አየሩ በሚስማማበት ቀዬ ገበሬ ኾኖ መኖርን የመሰለ እድል የለም፡፡ ጥጆቹ ደጁ ላይ ይቦርቃሉ፡፡ ሳር ጎጆ ናት ቤቷ፤ የበጎች ማደሪያ የኾነች ሌላ ጎጆ እልፍ ብላ አለች፡፡

በራፉ ላይ አንዲት ድመት ከሙጨሊቶቿ ጋር ተኝታለች፡፡ ወደ ቤቷ ገባን፡፡
ዙሪያውን ያለው መደብ ለመቀመጥ አልጠበበንም፡፡ ቀድመን የደረስነው አራት ሰዎች ነን፡፡ ሦስት ሰዎች ገና መንገድ ላይ ናቸው፡፡ የሰውዬው ምሽት ተንጎዳጎደች፡፡ የሚበላው ቀረበ፤ እንዴት ደስ የሚል ግብዣ ነበር፡፡ ጠላም ተፈልጎ መጣ፡፡ ቤት ያፈራው ተብሎ ምድር ያፈራችው ቀረበ፡፡ የዳንጉር አርሶ አደር ጎተራው ሙሉ መኾኑን አመንሁ፡፡

ረሃባችንን አስታገስን፣ ከድካማችን አረፍ አልን፡፡ ሆዳችን ሲሞላ ጥያቄ ጀመርኩ፤
"ገዳሙ የቱ ጋ ነው?"
"የት ነው የመጣችሁት ዳንጉር ሚካኤል ነው ደቅ ማርያም?"
ሊያስተናግደን እየተነሳ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰው፤
"ደቅ ነው የመጣነው፤" ባዩ መለሰለት፤
"ደቅ ማርያምማ ገና ነው፡፡ ግማሽ ሰዓት ያስኬዳል፡፡ ግን ቅርብ ነው፡፡ ቁልቁለት ነው፡፡ ከዚያ አግድም ነው፡፡" አቀለላት፡፡
"ዛሬ እዚህ እንደርና ነገ በጠዋት እንጓዝ፤" እኔ ነበርኩ፤ ከዚህ በኋላም ሌላ መንገድ መጓዝ ፈርቻለሁ፡፡
"አይ ለማረፉም ለማደሩም እዚያው የሚሻል መሰለኝ፡፡ ብዙ አይከብድም ዋናውን መጣችሁ" አለ ያ ደግ ገበሬ፡፡

ምክሩን ሰምተን ተነሳን፡፡
ዳንጉር የሽናሻ፣ የጉምዝ፣ የአገውና የአማራ ህዝብ አንድ ላይ የሚኖርባት ደጋማ ምድር ናት፡፡ ይርጋለም ከዚህ በኋላ ደጋው እንግዳ ተቀባይ በመኾኑ እንዲኽ ያለ አቀባበል እንደማይለየን ነገረኝ፡፡

ይርጋለም የሚኖረው ቆላው የጉምዝ ምድር ማንቡክ ነው:: ስለ ምድሩ ቸርነት ያደገበት ሆኖ ሰምቷል፡፡ ያልገባንን በአዊኛ ያስተረጉማል:: ሽናሻ ቢገጥመንም ይናገራል::

ሁለት ሁለት ሎሚ ተሰጥቶናል፡፡ ሁላችንም እጃችን ወደ አፍንጫችን ተሰዶ የተሰጠንን ሎሚ መዓዛ እንምጋለን:: ያስተናገደን ሰው ስንለመለስ እንደሚጠብቀን ደጋግሞ እየነገረን ነው:: ቀድሞ እየመራ መንደር አሳብሮ የምንጓዝበትን መንገድ አሳየን::

"አመሰግናለሁ:: እኔ ሄኖክ ስዩም እባላለሁ::" በልቶ ጠጥቶ መተዋወቅ የሚቻለው ኢትዮጵያ ምድር ደጉ ገበሬ ሰፈር ነው::

"ደግ እኔ ደግሞ አበበ ቆንጋይ እባላለሁ::" እጁን ዘረጋ:: ጨበጥሁት:: ሁሉንም ጨበጠ:: ቆሞ ቁልቁለቱን እስክንወርድ በዓይኑ ሸኘን::

መሽቷል:: አስራ ሁለት ሰዓት ሞልቶ ነው የተነሳነው:: በእርግጥ በደረሱ ሰዓት ደርሰው ኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ማደርን የመሰለ የእረፍት ስፍራ የለም::

ሰላሳ ደቂቃ የተባለው መንገድ አንድ ሰዓት ወስዶም መድረስ አልቻልንም:: ፍርሃት ተሰምቶኛል:: ጨለማ ኾኗል:: በባትሪ ነው የምንጓዘው፤ አንድና ቀጭን መንገድ ብትኾንም ሌላ ቦታ ብትወስደን ነው እንጂ እንዴት እስካሁን አይደረስም በሚል ጥርጣሬ ገብቶኛል:: በጤፍ ማሳ መሃል ባለች ቀጭን የእግር መንገድ እኔ እየመራሁ ሌሎች እየተከተሉ ነው::

የምመራው እኔ መኾኔና መድረሻዬን አለማወቄ አሳሰበኝ:: ከአምስታችን ሦስታችን ነን የእጅ ባትሪ የያዝነው:: አንዱን ኋላ አድርገናል:: አንዱ መካከል ነው:: እኔ ከፊት እያበራሁ እመራለሁ::

ሌላ ሦስት ሰው ደግሞ ብንጠብቃቸውም በማይደርሱበት ርቀት ተለያይተናል::
ቁልቁለት ነው የተባለው መንገድ መልሶ ዳገት ኾኖብናል:: የሚሰማም የሚታይም ነገር የለም:: ምናልባት እነሱም እንደኔ ካሰቡ ጭንቀታቸው ይገባኛል:: አካባቢው የነብር ቦታ ነው ተብሎ ስለተነገረኝ ነገር እያሰብሁ ዛፍና ቋጥኝ በማይለይበት ጨለማ ከተገተረ ነገር ጋር ሁሉ በዓይነ ቁራኛ እተያያለሁ:: ድንገት ጨለማ ውስጥ ባትሪ አየን:: መልሶ ግን ጠፋ:: ብዙ ኮቴ ተሰማን:: ፈርቻለሁ::

"ሰዎች....ሰዎች ይሰማል...." ተጣራሁ::
"ባትሪ አጥፉ ባትሪ አጥፉ" ምኒልክ ነው:: ራሳችንን ስለመጠበቅ ያስባል ማለት ነው:: እዚኽ ምኑን ከምን አድርገን ራሳችንን እናድናለን:: የቆምነው እንደ አመጣጣችን በረድፍ ነው::

"ሰው አለ፤ ማነው?" ምኒልክ አሁንም ጮክ ብሎ ተጣራ:: የሚንኮሻኮሸው ድምጽ እንደቀጠለ ነው:: በዚኽ ቁጥር የጎሽ መንጋ ካልኾነ በስተቀር በዚህ ጨለማ እዚህ ውስጥ ምን ሊኖር ይችላል? በድጋሚ ባትሪ ብልጭ ብሎ ጠፋ::
"ወደ ገዳም ልንሄድ ነው የገዳሙ መንገድ በየት ነው? እንግዶች ነን?" ባዬ እድሉን ለመሞከር ጮኽ ተናገረ::

"መጣሁ...መጣሁ፤" አለ አንድ ድምጽ፡፡ ከዚያም ባትሪ አብርቶ ወደ እኛ የሚመጣ ሰው ታየን፡፡ እንደደረሰ ከባዬ ላይ ጓዙን ተቀበለው፡፡

"ኑ በዚህ ኑ...." እያበራ መንገድ መራን፤ ተከተልኩት፡፡ እንደ ቅደም ተከተላችን መስመራችንን ጠብቀን ተጓዝን፡፡
ወዴት ይኾን የሚወስደን? ማን ይኾን? ስለ ገዳሙ ብዙ ሰምቻለሁ፡፡ ዳሩ እሳት መካከሉ ገነት ሲባል አድምጬዋ የመጣሁ ነኝ፡፡ የኢትዮጵያ ጥበበኞች ዙሪያውን የከበቡት ገዳም ነው ተብያለሁ፡፡ የሚደርሰው የታደለ ነው ብለው ነግረውኛል፡፡ ይኼን ሁሉ ሰምቶ የመጣ ሰው ሰማይና ምድሩ በማይታይበት ድቅድቅ ጨለማ አንድ ሰው ተከትሎ ሲሄድ የሚያስበውን እያሰብሁ ነው፡፡

የዳንጉር እናት ጥበበኞች በአጽዋት ያሻቸውን እንደሚያደርጉ ሰምቻለሁ፡፡ የሰማሁትን ሁሉ እያሰብሁ የሚጠብቀን አንዳች ተአምር ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ምን ያደርገን ይኾን? ላም ያደርገን ይኾን? በአስማት በጎች እንኾን ይኾን? ስምና ሀገራችንን ከእውቀታችን ቢወስድብንስ?

አንዲት በእንጨት በራፍ ወደ ተከበበች ጎጆ በራፏን ቀስ ብሎ ከፈተና አስገባን፡፡ ጓዛችንን እየተቀበለ ከላያችን አወረደ፡፡ ጎጆዋን ከፈታት፡፡
"ግቡ አለ"
ዝም ብለን ገባን፡፡
ቤቷ የአባወራ ቤት አትመስልም፡፡ የቤት ዕቃ የላትም፡፡ መደብ አላት፡፡ ሰውዬው እሳት አያያዘ፡፡

ብዙም ሳይቆይ አንድ ሕፃን ልጅ መጣ፡፡ በሸናሽኛ አናገረው፡፡ ልጁ ተንጎዳጎደ፤ ሽር ጉድ አለ፡፡ የሚለበስ ሊሰጠን ሞከረ፡፡ ቀጥሎ የሚኾነውን አላወቅንም፡፡ ቢበርድም ስጋት የተሰማን የት እንደኾንን ባለማወቃችን ነው፡፡ የመኘታ ልብሳችንን ፈታነው፡፡

ጥለውን ወጡ፡፡ የየራሳችንን መላምት ማስቀመጥ ጀመርን፡፡
"የገዳሙ ጠባቂ ይኾናል" አለ ምኒልክ፡፡
'ሽፍታ መስሎኛል' ልል ፈለግሁና መልሼ ተውኩት፡፡
ቆይቶ ኮቴ ሰማን፡፡ ሦስት ሰዎች ተከታትለው ገቡ፡፡ አንዱ መነኮሴ ነበሩ፡፡ ደቅ መድረሳችንን አመንኩ፡፡

ወደ ጎጆዋ ያስገባን ሰው ውሃ በገበቴ ይዞ እግራችንን ሊያጥብ ተጎነበሰ፡፡ ለመከልከል ሞከረን ነበር ግን ሥርዓት ነው አሉን፡፡ ዝምታው ሽፍታ ይኾን ብዬ እንድጠራጠር ያደረገኝ ሰው ለካንስ ከትህትናው የተነሳ ነበር የማይቅለበለበው፡፡

ሰላምታ አቅርበውልን የሄዱት መነኩሴ እግራችንን ታጥበን እንደ ጨረስን ተመልሰው መጡ፡፡ እጃቸው ሞሰብ ይዞ ነበር፡፡ የተከተላቸው ደግሞ የወጥ ሳህን ይዟል፡፡ ዳሩ እሳት መካከሉ ገነት፤ እውነትም፡፡

እራታችንን በላን፡፡ ስለቀሩት ሦስት ሰዎች ማሰብ ጀምረናል፡፡ ለመነኩሴው ነግረናቸው ስለነበር ሰው ልከዋል፡፡ ከእኛ እራት ሰዓት ዘግይተው ቀሪዎቹም የገባንባት ጎጆ ገቡ፡፡ ደክሞን ስለነበር ወዲያው እነጣጥፈን ተኛን፡፡

# ደቅ

"በሄዱበት መንገድ
መራመድ ጀምሬ
　　መቀጠል አቃተኝ፤
ተመልሼ መጣሁ
　　ልፋቴ እየቆጨኝ፤
　　እያንቀጫቀጨኝ::
ግና በመንገዱ.........
የሄዱበት ሁሉ፣ ስላልተመለሱ
አዲስ ነው ተባለ፣ መመለሴ ራሱ::"

መዘከር ግርማ ወደ መንገድ ሰዎች ሥነ-ግጥም

የወደቅንበትን አላወቅንም:: ሁላችንም እኩል ተኛን፤ እኩል ተነሳን:: የጎጆዋ በራፍ ተከፈተ:: በጣም ነግቶ ነበር:: የአእዋፍ ድምጽ ይሰማል:: ጎጆዋ ደጃፍ ላይ ቆሜ በጨለማ የገባሁበትን ስፍራ በብርሃን አየሁት:: የሚያዩትን አለማመን ፈተና ነው:: ፈተና ላይ ወድቄአለሁ:: አየሩ ይለያል:: ቢማግ፣ ቢማግ አይጠገብም::

ዓይኔን የቱ ጋ ላሳርፈው? በተራሮች በተከበበ ገላጣ ስፍራ ላይ ራሴን አገኘሁት:: ያደርኩባትን ጎጆ ዙሪያዋን አየኋት:: መስኩ ልዩ ነው:: ዛፎቹ ይማርካሉ:: ዘንባባዎች፣ የጥድ ደኖች፣ የጤፍ ማሳ......

በአጽዋት በተከበበ ዙሪያ ብቻዋን የጎነች ዐለት ታየችኝ:: ከዐለቷ ውጪ ያለው ምድር አረንጓዴ ለብሷል:: ከየት ጀምሬ እንደምጎበኝ ግራ ገብቶኛል:: ይኸ ምስጢራዊው ደቅ ገዳም ነው::

የፏፏቴውን ድምጽ ተከትለን ቁልቁል ወረድን:: ንጹህና ኩልል ያለ ወራጅ ውሃ ይገማሸራል:: ፊታችንን ታጠብን:: ከደቅ አናት ረግረጋማ ስፍራ የሚወርድ ወንዝ ነው:: ጠበል ኾኖ ካገለገለ በኋላ ወንዝ ኾኖ ቁልቁል ወደ ቆላው ይጋልባል::

እግራችንን ካፍታታን በኋላ ጥሩ ቁርስ ቀረበልን:: በጠዋትም ያገለገለን ያ ምሽት ከጫካ ውስጥ እየመራ ያመጣን ሰው ነበር:: የገዳሙ እረኛ መኾኑን ስሰማ ደግሞ ደቅ እንኳን መነኩሴው እረኛውም ዓለምን ንቋታል አልኩ::
በምሽት ያየናቸው መነኩሴ 'እንዴት አደራችሁ?' ሊሉን መጡ:: በአክብሮት ተነሳን::
"ኸረ ከምግብ ላይ በእግዚሃር በእግዚሃር" አሉ::
ፊታቸው በሪዝ የተሸፈነ ነው:: ቢጫ ቆብ አድርገዋል:: ትሁትና ረጋ ያሉ ናቸው:: ሲናገሩም ሲያደምጡም ሳቅ ብለው ነው:: በለበሱት ቀሚስ ላይ ፎጣ አገልድመዋል:: ባደንብ አስተናገዱን፤ ጥሩ ቁርስ በላን::

ቀረጻ ለመጀመር አካባቢውን ቃኘን፡፡
ደቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አትታይም፡፡ ረዣዥም የጥድ ዛፎች ጋርደዋታል፡፡ የመነኮሳቱ ቤቶች ጎጆዎች ናቸው፡፡ ከመንደራቸው የተመለከትነው ፊት ለፊት ያሉትን ብቻ ነው፡፡ ልጅ እግር መነኩሴ እንዲያግዙን ተመደቡልን፡፡

"አቤ ምን ተሰማኽ?" አልኩት፡፡ አበበ ጥላሁን በዚህ ወቅት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ነው፡፡ ፓዌ ስለተወለደ የመተከልን ምድር በጣም ይወደዋል፡፡

"አስገራሚ ነው፤ እዚህ ያለ እጽዋት ቀላል እንዳይመስልህ፡፡" ቤጃሚዝ ዋንዛ አለ ሲባል አድራሻው ደቅ ነው፡፡ ዳንጉር ምድር የቤጃሚዝ ብሔራዊ ፓርክ ደጋማ ሥነ-ምህዳር ተዘርግቷል፡፡ አበበ ከዚህ ቀደም መጥቶ ያውቃል፡፡ የእጽዋቱን ምስጢር አብልጦ የሚያውቅ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ወደዚህ ስፍራ ሲመጡ የማትነካ እጽ ነክቶ ለቀናት ስለጠፋው ተጓዥ ተረከልኝ፡፡
"አስራ አንድ ኾነን ነበር የመጣነው፤"
እዚህ አልኩት፤
"አዎ፤ አንዱ ጓደኛችን እዚህ አካባቢ ሲደርስ ጠፋ፡፡ አንድ ቀን መሰለህ ሦስት ቀን አልተገኘም፡፡ በሦስተኛው ቀን ሲገኝ ምንም አልኾነም፡፡ ደነገጥን፡፡ ያኔ ነው እጸ መሰውሯን ነክቶ እንደነበር የነገሩን፡፡"

የሰማሁትን በማየው ውበት እስከረሳ ጥቂት ደቂቃዎችን እጄን ወደ ሰማይ ሰቅዬ ምህላ እንደሚያቀርብ ሰው ለመንቀሳቀስ ሞከርኩ፡፡

ደቅ ሁሉን ያስረሳል፡፡ በእጽ መሰወር የፈራው ልቤ በዙሪያ ገባው ውበት መሰወሩ ገባው፡፡ ዙሪያ ገባውን በካሜራችን እያደንን ሳለ ተጠራን፡፡ ወደ እደርንባት ጎጆ ሄድን፡፡ አበበ የሚያውቃቸው እድሜ ጠገብ አባቶች ቁጭ ብለዋል፡፡ አንዱ በደንብ ለይተውታል፡፡

"አበበ እንዴት ነኽ?"

"ሰላም ነኝ፤ አባ ጎሩይ እርስዎስ ይበረታሉ?" በፎጣ የሸፈኑትን አፋቸውን ሳይገልጹ ጭል ጭል በምትለው ዓይናቸው ቀና ብለው ዐዩት፡፡ ብርሃኑን ፈርተውታል፡፡ ምናልባት ከዘጉበት የማይወጡ ባዐት ወዳጅ መነኩሴ ይኾናሉ፡፡

"ደህና ነኝ፤ መቼም ምን እኾን ብለህ ሳለ እሱ" ወደ ሰማይ አንጋጠጡ፡፡ ሰላሳ ሦስት ዓመታትን እዚህ ገዳም ኖረዋል፡፡ ሳይወጡ የኖሩ ናቸው፡፡ ዛሬ ደክመዋል፡፡ ከጸሐይ ጨረር ብርሃኗን ወደ መሸሸ እድሜ አሸጋግሯቸዋል፡፡

በታሕታይ ግብጽ የተወለደው አባ ጳውሊ የብትሕውና መሥራች ነው፡፡[19] እንደ አባ ጳውሊ ሁሉ በሀገረ ግብጽ የተወለደው አባ እንጦንዮስ ደግሞ የምንኩስና መሥራች ኾነ፡፡[20] አባ መቃርዮስ ትልቁን ገዳም ለመጀመሪያ ጊዜ መሠረቱ፡፡ እንደ ቀደሙት አባቶቻቸው ሁሉ በሀገረ ግብጽ የተወለዱት አባ ጳኩሚስ ደግሞ ለገዳማዊ ሕይወት ሕግና ሥርዓት አበጁ፡፡[21]

---

19. መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት፡፡ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም እና የክርስቲያናዊ የምናኔ ሕይወት ሥነ-ምግባር፡፡ ገጽ 27

20. ሊቀ ብርሃናት መርቆሪዎስ አረጋ፡፡ የቅዱሳን ታሪክ፡፡ ገጽ 43

21. መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት፡፡ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም እና የክርስቲያናዊ የምናኔ ሕይወት ሥነ-ምግባር፡፡ ገጽ 43

እንዲህ እያለ የቀጠለው የምናኔ ሕይወት ወደ ኢትዮጵያ ለመግባትና ለመስፋፋት ጊዜ እንዳልወሰደበት አጥኚዎች ይገልጻሉ፡፡[22]

አባ ኅሩይ ስለቦታው የጀመርነውን ጨዋታ ቀጥለዋል፡፡
"እኔ በሰባ ሰባት ነው እዚኽ የደረስሁ፡፡ ያኔ ብዙ መነኮሳት ነበሩ፡፡ ይኼን ያቀኑት አባ ተክለ ማርያም ናቸው፡፡ ከቡልጋ ነው የመጡት፡፡ ከዚያ ቀደም ግን ስፍራው ታሪክ አለው፡፡ በተለይ ዋሻው፤ ዋሻው ጋ ደርሳችኋል?"
"ኧረ አልሄድንም፤ ትናንት ነው የገባነው" አበበ መለሰላቸው፡፡
"የቅዱሳን ቦታ እኮ ነው፡፡ የቅዱሳን እዚያ እየገቡ የቀሩ አሉ፡፡ በማኅበረ ሥላሴ በኩል እየመጡ እየዘጉ የሚሄዱ አሉ፡፡"

አባ ኅሩይ ደከሞቻቸዋል፡፡ አፋቸውን አፍነው የሚያወሩትን በመከራ ስራቸው ተለጥፈን አደመጥን፡፡ ረዥም ሰዓት ዝም አሉ፡፡ ፊታችንን ወደ ሌላኛው አባት አዞርን፡፡ ጆሮአቸው በደንብ አይሰማም፡፡ ስለገባን ድምጻችንን ከፍ አደረግን፤

"አባ ተክለ ማርያም እንዴት ወደዚህ እንደመጡና እንደመሰረቱት ይታወቃል?" ድምጼ በጣም ከፍ ብሎ ነበር፡፡ አባ ገብረ ኢየሱስ ግን ጆሮአቸው ስለማይሰማ ለሰስ ብሎ ተሰማቸው፡፡
"አዎ ይታወቃል እንጂ፡፡ እሳቸው እኮ ስለዋሻው ሰምተው ነው የመጡት፡፡" ጭራቸውን አወናጨፉ፤
"መቼ ተመሰረተ ታዲያ?" አበበ ጠየቀ፤

22. ካህሳይ ገብረእግዚአብሔር፡፡ ምንኩስና በኢትዮጵያ፡፡ ገጽ 7

"የገዳሙን ነው የቦታውን ታሪክ የፈለጋችሁት?" በጥያቄ መለሱልን::

"የቦታው ታሪክ" የምፈልገውን ነገርኳቸው::

"ቦታውማ የጥንት ነው:: አሁን ልቤን እየሰወረኝ ነው:: ቀደም ቢኾን ብዙ የምነግራችሁ ነበር:: እኔ ብዙ ጊዜዬ ነው እዚህ፤ ምንድን ነው? ቦታው በአባ ተክለ ማርያም ይኼ ያለንበት ተገደመ:: እሳቸው ስለ ዋሻው ሰምተው ዋሻውን ፍለጋ መጡ:: ዋሻውን አይተው አስመለከታቸውና እዚህ ስፍራ ይኼን ገደሙ:: ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ ናቸው:: ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፍቃዳቸው ኾነ:: እቴጌ መነን ወፍጮ ሰጡ:: እንዲህ እያለ፤" ዝም አሉ::

"ደቅ ለምን ተባለ?" አላቸው አበበ
"ደቅ እስጢፋ ነዋ:: ይኼ ቦታ ከክርስቶስ መወለድ ቀድሞ በአንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አምስት ኩሻውያን የተባሉ አባቶች መጥተው ያረፉበት ነበር:: ብዙዎቹ ሴቶች ናቸው:: አምጥቶ እዚህ ሰወራቸው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተሰውረው ሲኖሩ የስውራን ቦታ እየተባለ ደማም ጥበበኞች ናቸው:: ብዙ ዘመናትን ኖረዋል:: ደቀ እስጢፋ ይኼን ሰምቶ ነው የመጣ፤"
"ደቀ እስጢፋ የደብረ ገሪዛኑ ናቸው?" ለማጣራት ጠየቅሁ፤
"የለም እሱ የኋላ የአሁን ታሪክ ነው::" አፉቸውን በፎጣቸው ጠረጉት::
"ከጣናው ደጋ እስጢፋኖስ ጋርስ ይገናኛል?" አላቸው አበበ፤

"ያ በእስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማዕት ስም ነው፡፡ ይሄ በጻድቁ እስጢፋ፤ ደቀ እስጢፋ የዐፄ ገብረ መስቀል ልጅ ነው፡፡ እስጢፋና እስራኤል የሚባሉት የዐፄ ገብረ መስቀል ልጆች ብዙ አይታወቁም፡፡ ሁለቱም ከመናኒያን ጋር አብረው ማሳለፍ ይወዳሉ፡፡ እስራኤል እዚያው በትግሬ ገዳም መነነ፡፡ እስጢፋ ደግሞ ከመናኒያን ስለዚህ ቦታ ሰምቶ ነበርና በማኅበረ ሥላሴ አድርጎ እየፈለገ መጣ፡፡ በዋሻው ሲደርስ የቅዱሳኑን ስፍራ አገኘው፡፡ በዚህ ተሰወረ፡፡ ዛሬ በስሙ ይጠራል፡፡ ቀበሌውም ደቅ የሚባል በዚህ ነው፡፡"

የቅኔን ፈጣሪዎች በሚመለከት መሠረቱን ቅዱስ ያሬድ ጣለው ካሉ በኋላ ቅኔ ፈጣሪዋ እከሌ ነው የሚባለው የተለያዩ ጎራዎች እንዳሉት አንብቤአለሁ፡፡ ዋድሎች ዮሐንስ ገብላዊ ነው ይላሉ፡፡[23]
ዮሐንስ ገብላዊ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን የኖረ ሊቅ ሲኾን በዋናነት በወሎ አማራ ሳይንት ይኖር የነበረና ቅኔን ያስተማረ ሊቅ ነው፡፡ ዮሐንስ ፍልሱፍም ይሉታል፡፡[24]
አለማየሁ ሞገስ ግን ቅኔን ዮሐንስ ገብላዊ ጀመራት የሚለውን አይቀበሉትም፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ የዮሐንስ ገብላዊ ቅኔ በጽሑፍም ኾነ በቃል አልተገኘም ይልቁንም የሰበሰበውና ያቀነባበረው ሰዋሰው ነው ይላሉ፡፡[25]

ቀሲስ ከፍያለው መራሔ ደግሞ የዮሐንስ ገብላዊ የቅኔ ቀደምት መምህርነትን የተጠራጠሩት አይመስሉም፡፡

23. አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል ቀሲስ ከፍያለው መራሒ፡፡ ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ሕይወት፡፡ ገጽ 17
24. ዶ/ር መርሻ አለኸኝ፡፡ በአንተ ስማ ለማርያም፡፡ ገጽ 113
25. አለማየሁ ሞገስ፡፡ የቅኔ ቤት ሥርዐተ ትምህርት፡፡ ገጽ 8-9፡፡ ያልታተመ፡፡

ቀሲስ ከፍያው ዮሐንስ ገብላዊ በአማራ ሳይንት በታቦር ተራራ ብዙዎችን አስተምሯል ይሉና አንዱ አባ ወልደ ገብርኤል የተባለው መነኩሴ ነው ሲሉ አባ ወልደ ገብርኤል ሠምረ አብን ሠምረ አብ ዐፄ ብዕደ ማርያምን ቅኔ እንዳስተማሯቸው የሚነገር መኾኑን ጽፈዋል::[26]

ተዋነይ ስምን ያተረፈው በኅበዝ ባለ ቅኔነት ብቻ አይደለም የቅኔም ጀማሪ ተዋነይ ነው የሚሉ አሉ::[27] እዚህ ከሰማሁት ደቀ እስጢፋ ከሚለው ስም ጋር የተገናኘብኝ ደግሞ ሦስተኛው የቅኔ ፈልሳፊ የሚባለው ሰው ነው::[28]

የቅኔው ደቀ እስጢፋ ግን የዐፄ ገብረ መስቀል ልጅ አይደለም:: የኖረውም በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው:: ዐፄ እስክንድርን ቅኔ አስተምሯል የሚባለው ደቀ እስጢፋ ነው:: እሱ ደግሞ በኋለኛው ዘመን የመጣ ነው::

ታሪክ ከዐፄ ገብረ መስቀል ልጆች ስለ ቆስጠንጢኖስና አባ ሙሴ ነው የሚነግረን:: ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በዋዜማ መጽሐፋቸው ገብረ መስቀልን ተከትሎ የነገሠው ቆስጠንጢኖስ እንደኾነ ይነግሩናል::[29] በሌላ በኩል ዐፄ ገብረ መስቀል አባ ሙሴ የተባለ በልጅነቱ የመነኮሰ ልጁን ወደ ኢየሩሳሌም ልኮ እንደነበር አንብቤአለሁ::[30]

26. ቀሲስ ከፍያለው መራሒ:: ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ሕይወት:: ገጽ 17
27. ዶ/ር መርሻ አለኸኝ:: በአንተ ሰማ ለማርያም:: ገጽ 113
28. ቀሲስ ከፍያለው መራሒ:: ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ሕይወት:: ገጽ 17
29. ኅሩይ ወልደ ሥላሴ:: ዋዜማ:: ገጽ 41
30. ፍስሐ ያዜ ካሳ:: የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ:: መጽሐፍ ፩:: ገጽ 186

ስመ መንግሥቱ ዐፄ እለገበዝ የሚባለውና የዐፄ ገብረ መስቀል ዓለም በቃኝ ማለትን ተከትሎ ስልጣኑን የያዘው ልጃቸው እንደ አያቱ ዐፄ ካሌብና እንደ አባቱ ዐፄ ገብረ መስቀል ይኸንን ዓለም በቃኝ ብሎ መንኗል::[31]

አሁን ደግሞ ስለ እስጢፋ እየሰማሁ ነው:: የሚነግሩኝ አባት ድካም ተሰማቸው:: ዓይኖቻቸው ባያዩም አሻግረው ተከለዋቸዋል:: ጭራቸውን ያወዛውዙታል::
ልባችን ተንጠልጥሎ የሚናገሩትን እየሰማን ነው:: ለማስቀጠል "ዋሻው ሩቅ ነው?" አልኋቸው፤

"ዋሻው የቅዱሳን ቦታ ነው:: እዚሁ ገዳሙ ክልል ነው:: አንድ ቀን ቢወስድ ነው:: እግዚሃር የፈቀደላቸው እየገቡ እየተሰወሩ ቀርተውበታል:: እኛ እንኳን ስንቱን አይተናል:: ወደ ዓለም ውጡ የተባሉት ሱባዔያቸውን ጨርሰው ይወጣሉ:: ለዚህ እኮ ነው ብጹእ አቡነ ማርቆስ እንደ ማኅበረ ሥላሴ እንደ ደብረ ቢዘን ትሁን ብለው የባረኳት:: ሲገደም የማኅበረ ሥላሴን ሥርዓትና ደንብ ተከትሎ ነው::"

እድሜን ተችረዋል:: የዘውዲቱ የንግሥና በዓል ሲከበር እሳቸው ወደ ምናኔ ገቡ:: አንድ ሁለት ብለው አይቆጥሩትም:: ተአምር በሚቆጠርበት ገዳም እየኖሩ "እድሜ መቁጠር ምን ይረባል?" ብለው ይኾናል:: ደቅ ማርያም ገዳም እንደኾነ ከገቡት ቀደምት አባቶች አንዱ ናቸው:: ዛሬ አርጅተዋል:: ስለዋሻው የጀመሩት ሀሳብ ይዞአቸው ከተጓዘበት ተመለሱ::

31. መሪራስ አማን በላይ:: የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ:: ገጽ 101

"አሁንም እኮ ሱባዔ የሚገባው ሰው ይመጣል። እንዲህ እንደናንተ እዚህ አርፎ ወደ ዋሻው ይኼዳል። እዚህ የኛ ልጆች የገዳሙ ሱባዔ እንግባ ብለው ኼዱ፤ አንዱ ተመለሰ አንዱ ተሰወረ እንዲህ ነው። ድንቅ ስፍራ ነው። ቅዱስ ስፍራ ነው። ሁለት ዓለም ይሉታል።"
"ሁለት ዓለም ምንድን ነው?" አልገባኝም ነበር። ጥቂት ዝም ብለው መመለስ ጀመሩ፤
"ጥበብ መንፈሳዊና ጥበብ ስጋዊ ይሉታል። ጥበብ መንፈሳዊ የተባለው በእስጢፋ ነው። በጻድቁ፤ ጥበብ ስጋዊ የሚሉት ደግሞ እነኚህን በጥበብ የሚኖሩትን ኩሻውያን ነው።"
"ያ ጥበብ አሁንም አለ?" ፍርሐት ተሰማኝ።
"ታዲያስ፤ መቼም አሉ እንጂ። ይኼ ገዳም ደሴት ነው። ሁለቱም አሉ። እኛ እስከአሁንም ተአምር እያየን ነው። ዱሩ ጌሾ ነው። የበላያ ሰው ጌሾ ለቀማ እዚህ ከዱሩ ይገባል። የዚያን ጊዜ የተገናኙ አሉ። እንደውም አባ አስጨንቅ ማጥንቴ የሚባል አጭር ሽማግሌ ነበር። ሁላችንም ደርሰንበታል፤ አምስት ኾነው ጌሾ ለቀማ ይመጣሉ።
አባ አስጨነቅ ምን ያያል? ውሃ ገብ ለም መሬት አታክልቱ አዝመራው ያማረ መስከ ያያል። 'ኸረ ኑ ጉድ እዩ' ብሎ ጌሾ ለቃሚዎችን ጠርቶ ቢመለስ ቅድም ያየው ጠፍቶ ዱር ፍጥጥ አለ፤ ስቀው 'ዋሾ' ብለውት ኼዱ። ቆይቶ አባ አስጨነቅ እዛው ቢሄድ ያ መጀመሪያ ያዩት ውብ መስከ አለ። ጉድ እኮ ነው።"

አፉቸውን በፎጣቸው ጠረጉት። ብዙ ስላደከምናቸው ከንፈራቸው ደረቀ። ግን የሚነገሩን ተአምር ለእሳቸውም የሚመስጣቸው ጉዳይ ሳይኾን አይቀርም።

ቀጠሉ፤

"ሌላ ደግሞ ምን ኾነ መሰላችሁ፤ አባ ለማ የሚባሉ ታላቅ የሺናሻ አባት እዚህ ጀርባ ያለች ጎጥ የሚኖሩ ነበሩ:: ሲሄዱ ራሱ ላይ ሰሌን የበቀለበት ሲግበሰበስ ተገግጣጠሙ፤ የሚሞቱበትን ቀን ነገሯቸው:: ሀገር ሱብስበው በዚህ ቀን ነው የምሞት አሉ:: ሁበታም ናቸው፤ በሬ አርደው አብልተው በተናገሩበት ቀን ሞቱ ተአምረኛማ ስፍራ ነው ብቻ፤"

የደቅ ታሪክ በምርምር የሚፈታ አይደለም:: ማስረጃም ልፈልግ ካሉ እንደ ጌሾ ለቃሚዎች ውብ መስኩ ዱር ይኾናል:: የሚነገረውን ልብ ሰጥቶ መስማት፤ የሰሙትን ማመን አለማመን የራስ ድርሻ ነው:: ደቅ እስጢፋ ትልቅ ስፍራ እንደኾነ በደንብ እንዲገባን የፈለጉት አባ ገብረ ኢየሱስ "ተዋነይን ታውቁታላችሁ አሉ?"

"የቅኔው ሊቅ" አልኳቸው:: ተዋነይ ላይ የሚደርስ ጠቢብ የለም ይላሉ ብዙዎች:: ሞትን ጭምር ሰባት ዓመት ስለመገዘቱ እንብቤአለሁ::[32] ከጠቢቡ ሰለሞን በኋላ የተነሳ ጥበበኛ አድርገውም የሚመለከቱት ብዙ ናቸው:: ጥበቡን ከተራ የጥንቆላ እውቀት ጋር ብቻ አያይዘው የሚናገሩም አሉ::33 በሌላ በኩል ተዋነይ የዐፄ በካፋ ወዳጅ እንደኾነና እሳቸውን ጭምር ጥበብ ያስተምር እንደነበር የሚገልጹ ሰነዶች አሉ::[34] ተዋነይ ተረከ ሆኗል::

32. መሪራስ አማን በላይ:: የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ:: ገጽ 10132. መልአከ ምክር ከፍያለው መራሒ:: ዝክረ ሊቃውንት:: ገጽ 39

33. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ:: የኢትዮጵያ ታሪክ:: ዝግጅት፤ ሐተታና አርትዖት በሥርግው ገላው ዶክተር:: ገጽ 176

34. አሰግድ ተሰፋዬ:: የጎንደር ታሪክ:: ገጽ 95

"አዎ፤ ተዋነይ ሊቁ:: እሱ ተማሪ እያለ መምህር ዘንድ ገብቶ ቢታገል ቢታገል ቀለም አልገባህ አለው:: እንደ ቅዱስ ያሬድ፤ ቃለ እግዚአብሔር እምቢኝ አለው:: መምህሩ 'አይ እኔ እንግዲህ ድንጋይ ተወቅሮ እንኳ ሥራ ይይዛል፡፡ የማይገባህ ኾንህ እኔ አስተምሬም አልችል ወደ እናት አባትህ ሂድ፤' ብሎ መምህሩ ያሰናብተዋል:: ሲያሰናብተው በሃዘን እየተከዘ እየተረበሸ ሲሄድ አንድ ከዚህ የቆየ መናኝ ቅዱስ ነው ከምንገድ ያገኘዋል:: 'ምን ሁነሃል? አንተ ፊትህ ጠቁሯል' ሲለው 'አይ እኔማ መምህሬ ቃለ እግዚሃር እንቢኝ ሲለኝ አባሮኝ ነው፤' ይለዋል::"
አሳላቸው:: ረዥም ሰዓት ሳሉ አስጨነቃቸው:: አፋቸውን በፎጣ ሸፍነው ሳሉ::

ትንፋሽ ለመሰብሰብ ዝም አሉ:: ጭራቸውን ብቻ እያወናጨፉ ዝም አሉ:: ልብ ሰቃይ ቦታ ስላቆሙ አፍ አፋቸውን እያየን በትግስት ጠበቅን::

"ኋላ ያ መናኝ 'እንደዚህ ያለ ቦታ ብትሄድ ጥበብ ታገኛለህ፤' ቢለው እዚያስ ቢሆን 'ማን ይወስደኛል?' ብሎ ጠየቀው:: እንግዲህ ከዚህ ቀደም እዚህ አንጉታ ዛሬ ዳንግላ የሚባለው ትልቅ ገበያ ነበር፤ ከዚያ ገበያ ሄደህ ደቅ የሚወስደኝ ደቅ የሚወስደኝ ስትል እኔ አለሁ ትልሃለች ውሰጂኝ ስትላት ትወስድሃለች:: እሷ በደመና እየመጣች ገበያ የምትውል ናት ይለዋል:: ያኔ የደቅም የዳንጉርም ገበያ እዚያ ነበር::"
ስለ ዳንጉር ገበያ ,ድምቀት አንብቤያለሁ:: እንግሊዛዊ የዓለም ጂኦግራፊ ማኅበሩ አሳሽ ቻርለስ ቤክ በቻግኒ ገበያ የጥቁር ሕዝቦችን የገበያ ውሎ በስፋት ነግሮናል::

ተዋነይ እንዲኽ ባለው ጥበብ ስሙ ደጋግሞ የሚነሳ ሊቅ ነው:: በአየር ይሄዳል:: በደመና ይንሳፈፋል:: በዐጸ መሰውር እያለ የማይታይ ይኾናል:: በዐፄ በካፋ ቤተ መንግሥት እንዲኽ ኾነ:: ንጉሡ እህል አልጠጋቸው በገበታቸው ትይዩ በዕጸ መሰውር ተሰውሮ ከንጉሡ ጋር ገበታ ይቀርባል:: ሳይጠግቡ በልተው በሚነሱበት ገበታ ያለ እህል መኖር ጀምረው መነመኑ ይኼኔ መሳፍንቱ መኳንንቱ ችግሩን ጠየቁ፤ ንጉሡም ተናገሩ:: ይኼኔ ሊቃውንቱ ተመካከሩ:: አፈ ነገሥት ውሂብ የተባሉ ጠቢብ ዕፀ መከሥት ይዘው በማዕዱ ሲጠባበቁ ተዋነይ እንደለመደው እጁን ወደ ማዕዱ ሲዘረጋ እጅ ከፍንጅ አሲያዙት::[36] ስለዚህ ሊቅ እየሰማሁ ነው:: እንዴት ትኋን ኾኖ ከደቅ እስጢፋ እንደወጣ፤ አባ ቀጥለዋል::

"እዚያ በደመና ተጭኖ ስትደርስ ውርድ ቢል እሱ:: 'እንዴት ኾነህ መጣህ? ማን አመጣህ?' ብትለው 'እኔማ ትኋን ሆኜ አይደለ ጀርባሽ ላይ ሆኜ የመጣሁ' አላት:: አየህ ተዋነይ የሚለው የመጣ ከዚህ ነው:: ተኋናይ ነው:: ትኋን የሚለው:: ከዚያ በፊት የስውር ቅዱሳን በታነቱ የሚታወቀው ከዚያ በኋላ ደግሞ የጥበብ ስፍራ መኾኑ ተገለጠ:: ይኼ ታላቅ ሊቅ ከዚህ ነው ጥበብ ይዞ የወጣ፤ ከዚያ ወደ ጎጃም ሄዶ ጉንጅ የሚባል ሀገር ገባ ለትምህርት፤"

ጎንጅ የቅኔ አንድ አእማድ ናት:: የጎንጁን ቅኔ የጠነቀቁ ሊቃውንት የቅኔን መንገድ ተምረናል የሚሉ በጎንጅ ቅኔ ልቀት የሚኮሩ ተዋነይ የጎንጅ ቅኔ መንገድ አባት ነው ብለው የሚያምኑ ናቸው::[37]

36. መልአከ ምክር ከፍያለው መራሒ:: ዝክረ ሊቃውንት:: ገጽ 39
37. ዶ/ር መርሻ አለኸኝ:: በአንተ ስማ ለማርያም:: ገጽ 114

ይኸ ታላቅ የቅኔ ሊቅ በጎጃም ይልማና ወረዳ ቆለላ ምክትል መወለዱን አንብቤአለሁ፡፡ የተወለደበት ደብር ወንደል ተክለሃይማኖት ሲባል ለጎንጅና ለጽላሎ አቅራቢያ ነው፡፡ የኖረበት ዘመን ደግሞ የዐፄ በካፋ ዘመን መኾኑ ተጠቅሷል፡፡[38]

ከደቅ ማርያም ስንመለስ ወደ ጎንጅ ስለመሄድ ማሰብ ጀመርኩ፡፡

38. መልአከ ምክር ከፍያለው መራሒ፡፡ ዝክረ ሊቃውንት፡፡ ገጽ 38

# ከእሳት መትረፍ ማግስት፤

*አባትና ልጅ*
*"ጎዳናው ድንግል ነው፣ አሻራም የለበት*
*ከቀደሙት ወገን ማንም አልሄደበት"*
*ይላል አመንትቶ፣*
*አባቱ ባለክንፍ መኾኑን ዘንግቶ::"*
*በዕውቀቱ ስዩም:: ስብስብ ግጥሞች*

ከትናንቱ ድባብ ያወጣኝ ትርኢት የሚመስለው ጉዞ ነው:: የውጪ ጎብኚዎችን የጫኑ የአስጎብኚ መኪኖች በጨው ሜዳ ላይ ይጋልቡበታል:: ከአህመድ ኢላ ወይም በተለምዶ አመዴላ ከሚሏት የጎብኚዎች ማረፊያ መንደር ሃያ አምስት ኪሎ ሜትሮችን ያኽል በውብ የጨው ሜዳ ላይ እየጋለብን እዚህ ደረስን::

ይኽ የምድር ዝቅተኛው ስፍራ ነው::

ይኽ በአፋር አይደለም፤ ይኽ በኢትዮጵያም አይደለም:: አፍሪካንም አታስቡ፤ ይኽ በዓለም የሌለ፣ ሌላ ዓለም የሚመስል፤ ዓይን በቀለማት ውበት የሚሰክርበት፣ ነፍስ በምታየው ነገር ወደ ሌላ ፕላኔት የምትመጥቅበት ድንቅ ስፍራ ነው::

መኪኖቻችን ተከታትለው ቆሙ:: ወርደን ሽቅበ ወጣን፤ ብቅ ከማለቴ ዓይኔን ተጠራጠርኩት::
ዳሎል የምድራችን ዝቅተኛ ቦታ፤ የምድራችንም ውቡ ተፈጥሮ፤ ከባድ ሽታ መጣ:: የማዕድናቱ ነው:: በአፍ ማፈኛዬ አፌን ከለልኩት፤ ፈረንጁ እንደ እኔ ዓይኑን ተጠራጥሮ ካሜራውን ያምናል:: የምድር ውብ ቀለም እዚህ አለ::
ዳሎል ስሙ ቤተሰብ፣ ለጉብኝት ባህላችን ሩቅ የነበረ፣ በህብረተሰብ ትምህርት ከልጅነታችን ጀምሮ በተተረከልን አስደናቂ መልከዓ ምድር ላይ ነኝ:: ዳሎል አይጻፍም:: ዳሎል አይገለጽም:: እንኳን እኔ እንግዳው የለመደው አፋር "ግሩም ነው፤ ይደንቃል:: አይታመንም" ከሚል ቃል ውጪ ሌላ ትንታኔ አይሰጥም::
ዳሎልን ለመግለጽ ዳሎል መኾን ይፈልጋል:: እንኳን ነጋሪን ዓይንን አያምኑትም:: አቤት ውበት:: ይሄ የገባው የውጪ ጎብኚ በየቀለሙ ላይ እየተለጠፈ ፎቶውን ይነሳል::
የተፈጥሮ ማዕድኑ ይንተከተካል፤ ድምጹን ያሰማል፤ ውበቱን ያሳያል:: የሚታየው ሁሉ ምናብ ይመስላል፤ 100 ሜትር ያኽል ከምድር ወለል ወደ ጥልቅ ወርደናል:: ከባህር ወለል በላይ ሳንኾን ከባህር ወለል በታች ነን:: አኹን ሌላው ቀርቶ የቀይ ባህር ወለል እኛ ቁርጪምጪሚት ጋር ቢደርስ ነው:: ለሰስ ብሎ የሚነፍሰው አየር ከቀይ ባህር በዝቅተኛው ምድር ላይ እየተንደባለለ ዳሎል ይደርሳል::
ይሄ የዓለምን ሊቃውንት ያፈዘዘ ተፈጥሮ ስንት ዓመታትን ተጠንቶም ገና ምስጢሩ ጅማሬ ላይ ነው:: አየሩ ይሞቃል:: የጎብኚው ቁጥር እረፍት የለውም፤ ያየው ሲመለስ አዲሱ ይመጣል:: ዳሉል እኩለ ቀኑን አያሳልፉበትም፤ ጠዋትና ማታ የሚታይ ቦታ ነው::

ዳሎል ደርሶ ጠዋት እንዲህ ያለ ውበት ያየ ምሽት ሌላ ትርኢት ለመመልከት መምጣቱ አይቀርም::
ጠራራውን ፀሐይ አህመድ ኤላ እያሳለፍን ነው::
ምሽት ሲኾን ወደ ዳሎል ሜዳ ደግመን እንሄዳለን፤ እነኛን ግመሎች ለመመልከት፣ በአንድ ቀጭን መስመር፣ አሞሌ ጨው ጭነው እንደጥንቱ የሚጓዙ ብዙ ግመሎች:: ይኼ የቅፍለት ጉዞ ነው:: ሲራራን ያስታውሳል፣ በረኸኞቹ ተጓዦች ከአዱሊስ እናሪያ እንዴት ይሄዱ እንደነበር በትዝታ መልሶ ያሳያል፤ ከአልዩ አምባ አሰብ የነበረውን ግዙፍ የአጋሰሶች ጉዞ ወደ ኋላ ወስዶ ያስተዋውቃል::
የዓለም ዝቅተኛው ስፍራ የሰው ልጅ ኑሮን ለማሸነፍ ሲተናነቅ የሚታይበት የጥረት አውድ ነው::
ግመሎቹን የጫኑ ተጓዦች በጨው ሜዳ ላይ ተከታትለው ሲጓዙ ታሪክና ባህል፣ ህይወትና ዘመን፣ ጥበብና ተረክ አንድ ላይ አንድ ስፍራ መመልከት ነው:: ለዚህ ነው ዳሎል ደርሶ ብቻ መመለስ ሞኝነት የሚኾነው::
ሞኝ አይደለንም፤ ምንም እንኳን ትናንት ያን ዓይነት የእሳት ዳር የዘጸዓት ጉዞን ያሳለፍን ብንኾንም ዛሬ አዲስ ቀን ነው ብለን አዲስ ነገር ልናይ እስኪመሽ፣ ጸሐይዋ ጉልበቷ እስኪቀንስ፣ ጥላ እስኪኾን ጠፍር አልጋ ላይ ቁጭም ጋደምም ብለን፤
እኛ የእሳት ባህር ከፍለን የተሻገርን ጋዜጠኞች:: የእሳትን ባህር ያለ ሙሴ በትር ያቋረጥን፣ የቃዴስ በርኔን ሀሩር ያለ ሌት ብርሃን በጨለማ የወጣን፤ እኛ::
ለምንድን ነው ስለትናንት ዛሬ የማስበው? እውነት ነው ትናንት ተአምረኛ ሌሊት ነበር፤

# በእሳት ባህር አፋፍ፤

አስኮሚ ባህሪ፤
ወደ እሳቱ ባህር ለመጓዝ ዝግጅትንን ጨርሰናል፤ ጓዛችን ግመሎቹ ላይ እየተጫነ ነው:: ቀና ብዬ ሰማዩን አየሁት፤ ልቤ ለምን ተስፋ እንዳልተሞላ አልገባኝም:: ጋዜጠኞቹ በሙሉ ጓጉተዋል:: ስለ እሳቱ ባህር እኛን ቀድመው የዓለም መገናኛ ብዙኃን ብዙ ሲያወሩ ሰንብተዋል::
ያለሁባት መንደር አስኮሚ ባህሪ ትባላለች:: ዓለም ወደ ታላቁ ሥፍራ ሲሄድ ማረፊያው ስለኾነች ዝነኛ ናት:: አፋር ምድር ነኝ:: ደናክል ውስጥ እገኛለሁ::
አፋር በአዋሽና በደናክል ተፋሰሶች ዙሪያ የተዘረጋ ምድር ነው:: ሚሌ፣ ደማል፣ ማሹጋላ፣ ከሰም፣ ጉሊናና ቦርከና አዋሽ የሚገቡ ወንዞች ናቸው:: አውራ ተላላኪና ጉሊና ደግሞ ደናክል ይገባሉ::
አፋር ደረቅ ምድር ለሚመስለው አንድ በመቶው ምድሩ በወንዝና በሐይቅ የተሸፈነ እንደኾነ ቢነገረው እንዴት ያምናል? አፋር የአስራ ሁለት ሐይቆች ምድር ነው የሚለው ብዙም አይደመጥም::
በአፋር ከሚገኙ ሐይቆች አንዱ አፍዴራ ይባላል:: የጨው ባህር ነው:: የጨውን የስልጣኔ ታሪክና የአፋርን ቀደምት የንግድ እንቅስቃሴ ስንመለከት ላይነጣጠሉ የሚገናኙበት ብዙ ነው::
ቀደምት ሮማውያን ለወታደሮቻቸው የሚከፍሉት ወርሃዊ ደመወዝ እዚህ ባህር የኾነውን ጨው ነበር፤ ሳለሪ የሚለው የእንግሊዘኛ ወርሃዊ ደመወዝን የሚገልጽ ቃል ሳልት ከሚለው የጨው መጠሪያ መምጣቱን ለሚያጤን አፍዴራ ብዙ ትርጉም ይሰጠው ይኾናል::

ሰላሳ የአሳ ዝርያዎች ምድር እንዲኾን ያበቃው ይህ የውሃ ሃብት ነው:: ከጠቅላላው የአፋር ምድር 82140 ሄክታሩ ውሃ ነው:: እኔ ግን ወደ እሳቱ ባህር እየሄድሁ ነው::[1]

እንደ እኛ ያለው የእሳት ባህር ብዙ ዓለም አለ:: የእኛው ግን በዓለም እጅግ ዝቅተኛው ስፍራ የሚገኝ ልዩ ተፈጥሮ ነው:: ልብስ ደርቤያለሁ:: አለባበሴ በዚህ የዓለም ልዩ ስፍራ ሌሊቱን ቆይቶ አንግቶ ለመመለስ የተዘጋጀ ነው::

ያለሁት ለኤርትሪያ ድንበር አቅራቢያ ነው:: በወዲያም አፋር ነው:: አፋር በኤርትሪያ፣ በጅቡቲና በኢትዮጵያ የሚኖር ሰፊ ቁጥር ያለው ሕዝብ ነው::

የአፋር ህዝብ የታላቅ ሀገር ባለቤት ስንኾን ድንበር ታፍሮ ይኖር ዘንድ በደሙ ታሪክ የጻፈ ኩሩ አፍሪቃዊ ነው:: ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት የሂብሩውን ዩኒቨርሲቲ ዶክተር ጠቅሰው አፍሪቃ የሚለው ቃል መነሻ አፋር የሚለው ቃል እንደኾነ ጽፈውልናል::[2]

በሌላ በኩል ሐቢብ ሙሐመድ አፋር አል-መአፈራ ከሚለው ቃል የመጣ መኾኑን ነግሮናል:: የቃሉ መነሻም ከየመን በመጡ የሀመዳን ጎሳዎች የተወረሰ ሳይኾን አይቀርም ሲል ዶክተር ሃሺም ጀማሉዲንን ጠቅሶ ጽፏል::[3]

ተንቀሳቀሱ ተባልን:: የምድርን አድማስ ሰንጥቆ ለማለፍ ቆረጠ የስደተኛ ቡድን እንመስል ነበር::

---

1 የአፋር ታሪክ:: በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጀ:: ገጽ 27

2 An Interoduction to The Economic History of ETHIOPIA from early times to 1800, RICHARD PANKHURST page 9

3. ሐቢብ ሙሐመድ:: የአፋር /ኢዳል/ ህዝብ ታሪክ:: ገጽ 19

የሚደርስበትን ቦታ እየፈራው የሚናፍቅ ተጓዥ ወደ አሳቱ ባህር ለመድረስ ከአስኮማ ባህሪ እግሩን አነሳ::
የቀድሞው ኤርታኤሌ አሁን እንደሌብ አይታይም:: ጢስ በጢስ ሆኗል:: አዲስ ፈነዳ የተባለውን ለማየት ነው ጉዞው፤ ከአስኮማ ባህሪ ኤርታ አሌ የመሄድን ያኽል ከዋናው መንገድ አስኮማ ባህሪ መድረስም ድል ነው:: እስከ ዓለም ጥግ የተዘረጋ በሚመስል አሸዋ ላይ ዝም ብሎ ለመጋለብ አቅጣጫውን ማወቅ ይፈልጋል::
ይኽ አሸዋ በሰሃራ በርሃ ውስጥ የገባሁ እስኪመስለኝ ያስፈራኝ ደግሞ እንደ ትርኢትም ቀጠርኩት:: አንዱ መኪና አሸዋ ውስጥ ሰጠመ:: እኔ የነበርሁበት መኪና ሹፌር ጥንቁቅና የት እንደመጣ የሚያውቅ ስለነበር አስፈላጊውን ቁሳቁስ ይዟል:: አሸዋ መዛቂያ አካፋም የተገኘው እሱ መኪና ላይ ነበር::
አሸዋውን ዝቆ የተሰነቀረን የመኪና ጎማ ማውጣት ሞኝነት ኾነ:: ሹፌሩ ለእኛ ሹፌር መሪውን ለቀቀ፤ ልምድ ያለው ወጣት መኪናውን ከአሸዋ ከርስ ነጠቃት:: ቀና ብዬ የምንሄድበትን የአሸዋ ሜዳ ስመለከት መጨረሻ ያለው አልመስልህ አለኝ:: ይኽ የአፋር ምድር ነው::
የአፋር ህዝብ የታላቅ ስልጣኔ ባለቤት መኾኑን ታሪክ መስክሮለታል:: አዱሊስ፣ ታጁራ፣ ዘይላና ፑንት ስልጣኔዎች መገለጫዎቹ እንደኾኑ ተጽፏል::[4] እስከ ሃያው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ የአፋር ወሰን ዘይላ ድረስ ይደርስ ነበር::[5]

4. የአፋር ታሪክ:: በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጀ::
5. ሼህ ጀማሉዲን ኢብራሂም:: አፋር/ ደናኪል ታሪክና አርኪ ምንጮ/ አልመንሀል

የአፋር ህዝብ ኩሽ ነው፡፡ ኩሽቲክ ቋንቋው አፋር አፍ ይባላል፡፡ ከአፋሮች እሴት ዳጉ ማዕከሉን የሚይዝ ምሰሶ ነው፡፡ መረጃ በሚለው ጥሬ ትርጉም ይፈቱታል፡፡ ዳጉ ግን መረጃ ከሚለው ቃል በላይ ነው፡፡ ዳጉ ሳይንስ ነው፡፡ ዳጉ ጥናትና ምርምር ነው፡፡ ዳጉ ቴክኖሎጂ ነው፤ ዳጉ ህይወት ነው፡፡ አሁን እየሄድን ያለነው በዳጉ ጥበብ ነው፡፡ አፋሮቹ ስለ ኤርታ ኤሌና አካባቢ በቂ መረጃ ይዘዋል፡፡ የሚለወጥ ነገር ካለ በአጭር ጊዜ እንሰማለን፡፡

ዳጉ ትምህርት ቤትም ነው፡፡ አካባቢን፣ አዲስ ጥበብን፣ ነባር እውቀትን፣ ወቅታዊ ዜናዎችን አንድ ሰው ባለበት ሲደርሰው ከሚሰማው ይማራል፤ ከሚያውቀው ተናግሮ ሌላ ሰው ያስተምራል፡፡

አስኮሚ ባህሪን ወደ ኋላ ጥለን ወደ ፊት ገሰገስን፤ አስኮሚ ትልቅ መንደር እንዳትመስላችሁ፤ ትንሽ ናት፡፡ አንድ የአፋር ቤተሰብ የሚኖርባት፤ ጥቂት የድንጋይ ካብ ቤቶች እስኪመሽ ጠብቀው ወደ እሳት ባህሩ ለሚያቀኑ እንዲኾኑ መደዳውን ተከበዋል፡፡ እናታቸው ሳር የለበሰ እንዲህ ባለው የሀሩር ምድር የለመለመ መስከ የእረፍት ውሃ ያኽል የሚታዩ ናቸው፡፡

ምድሩ ጥቁር ነው፡፡ የዐለቱ ፍርክስካሽ ማዳበሪያ ያልገባ የከሰል ክምር ይመስል ነበር፡፡ በዚህ ጥቁር ድንጋይ ዳርቻ ቡኒ መሳይ ሳር በቅሎ አየሁ፡፡ ተፈጥሮ እንዴት አትባልም? እንዴት ብሎ ለመጠየቅ ገና የምድር ተአምር ወደ ኾነ ስፍራ እየሄድሁ ስለኾነ ከዳርቻው አልደከምም፡፡

ኤርታ ኤሌ የሚጤስ ተራራ ማለት ነው፡፡ አፋሮች ግን የሲኦል አፍም ይሉታል፡፡ በሕይወት ዘመን አንዴ እንዲህ ያለውን ተፈጥሮ ማየት ደግሞ ገነትን በምድር የመመልከት ያኽል መታደል ነው፡፡

ታድያለሁ ለማለት ወደ ሲአል አፍ መሄድ፣ ወደ እሳት ባህሩ መግቢያ በራፍ መገስገስ::

ምሽት ኾኗል:: ብቻዬን አይደለሁም:: ከሃያ በላይ ጋዜጠኞች አሉ:: የመጀመሪያው ጥድፊያ አሁን የለም:: ድካም ፈጣኑንም ቀርፋፋውንም ያቀራርበው ጀመረ:: መንገድ መሪዎቹ የአፋር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባልደረቦች ናቸው:: የክልሉ ልዩ ኃይል ዙሪያችንን ከቦ አጅቦናል:: እኔ ውሃ ከጠማኝ በሚል ማቀዝቀዣ ኮዳዬን አንጠልጥያለሁ:: ከቀይ ባህር ገስግሶ በደናክል አድርጎ የሚመጣው ነፋስ ተሰማኝ::

ከፊት ለፊቴ አንድ ተራራ ይታየኛል:: ኮረብታ ነው:: ቅርጹና አቀማመጡ ከጠለቀችው ጸሐይ ጋር ተዳምሮ ልብ ይሰርቃል:: ልቤን በየቦታው አሰርቄ ልቤ እስኪጠፋ የወድድኳትን ሀገር ስዞር ወደ ህይወቴ ጭኜ የምመለሰው ስንቅ ይኸ ነው:: ተራራው ብዙም ከፍታ ያለው አይመስለኝም:: ምናልባት የባህር ወለል በላይ በሚሉት የርዝመት መለኪያ ጫፉ የአዲስ አበባው ሳሪስ እግር ሰፈር ሁሉ ላይደርስ ይችላል:: ይህ ከምድር ዝቅተኛው ስፍራ ነው:: እዚህ ትንሽ ከፍ ማለት ሞገስ ያላብሳል::

2063 ሜትር ከፍታ ያለው ሙሳ ዓሊ ትልቁ የአፋር ተራራ ነው:: አናቱን የረገጠ ኢትዮጵያን ጅቡቲንና ኤርትራን ይመለከታል ይላሉ:: ቡሬ ግንባር ከሾለው ድንጋይ ላይ ቆሜ አሻግሮ በእጁ እየጠቆመ"ሙሳ አሊን ተመልከው፤ እዛ ላይ ብትቆም ጅቡቲ እስከ ባህሩ፣ አሰብ እስከ ወደቡ ይታየሃል" ያለኝን ወታደር አስታወስኩት::

እንዲያ ከኾነ ሙሳ አሊ የጋራ ማማችን ነው:: ከፍ ብለን ካየን አንዳችን ሌላችንን የምንመለከት መኾኑን የሚነግረን የተፈጥሮ ምስጢር ነው:: እንዲያ ከኾነ ሙሳ አሊ ሌላ ትርጉም አለው::

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በኢትዮጵያ ጂኦግራፊ መጽሐፍ እንዳሰፈሩት ሙሳ ዓሊን የሥነ መልከዓ ምድር ጠበብት ሲገልጹት እጅግ በጣም ማራኪና ግርማ ሞገስ ያለው የእሳተ ገሞራ ተራራ ይሉታል::[6] ይኼኛው ከሙሳ ዓሊ ተራራ የተለየብኝ እንዲኽ ባለው የእሳት ባህር ምድር ተኮፍሶ ስላገኘሁት ይኾናል::

የአፋር ታሪክ ገና አልተጠናም:: ያልተነገረው ብዙ ነው:: የቀይ ባህር ዳርቻ የአንድ ዘመን ድንቅ ስልጣኔያቸውና የታሪክ ድርሻቸው ተዘንግቷል:: ቀይ ባህር ወደቦቻቸው ላይ ስለሚሰሩት ጀልባና መርከቦች የተጻፉት ጥቂት ናቸው::[7] ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ አፋሮች ድንቅ መርከብ ገንቢዎችና የተርሴስ ነጋዴዎች ተብለው በታሪክ የተመዘገቡ ስመ ጥር ባህረኞች እንደነበሩ ጽፈዋል::[8]

የአፋር ጎረምሶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ስመለከት የጸጉር አሰራራቸው የጥንት ግብጻውያን ፈርዖኖች በፒራሚድ ቅርሶች ላይ ካኖሯቸው ገጽታዎች ጋር ተመሳሳይነታቸው ገርሞኝ ነበር:: በርካታ ጥንታውያን የዋሻ ላይ ሥዕሎችና የዘመነ ፈርዖናውያን ምልክቶች ከዚህ ዘመን እውነታና እውድ ላይ ስንፈትሻቸው በጸጉር አሰራርና አቆራረጥ ከዛሬዎቹ የአፋር ወጣቶች ጋር ልክክ የሚል ተመሳሳይነት ይታይበታል::

---

6 AN INTROSUCTORY GEOGRAPHY OF ETHIOPIA, Mesfin Wolde-Mariam page 52

7. የአፋር ታሪክ:: በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጀ:: ገጽ 162

8. ስውሩና ያልተነገረው የአይሁዳውያንና የኢትዮጵያውያን ታሪክ:: ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ:: ገጽ 201

ዛሬ ማን ያውቃል? ዱሩሲላ እንደገለጸችው ኩሻውያን ሰሩት በተባለው የቀደምት ፒራሚድ ገንቢዎች ታሪካችን ኢትዮጵያውያን አፋሮች የግብጽ ስልጣኔ ዋነኛ ተዋናዮች ሆነው ቢሆንስ? እላለሁ፡፡[9]

አሁን አሁን ደግሞ ያልተነገሩ ታሪኮች ጊዜ አግኝተው መሰማት ጀምረዋል፡፡ የአፋር ህዝብ ቅድመ እስልምና እምነቱ ከጥንታዊው የግብጽ ፈረዖናውያን እምነት ጋር በእጅጉ የሚቀራረብ እንደኾነ ፍንጭ የሚሰጡ ጥናቶች እየታዩ ነው፡፡ [10]

በዓለም ዝነኛ የነበረው የኦፊር ወርቅ የአፋሮች ወይስ የሌላ የሚለውን የሚያነሱ ሊቃውንት ብዙ ምርምር ቢቀራቸውም በርከት ያሉት ግን ያ የወርቅ ምድር አፋር ነው ይላሉ፡፡

ጋሻው አዳልና ነዋይ ደበበ በሙዚቃ ስራዎቻቸው አፋርን በልጅነቴ እንዳውቀው ያደረጉ ናቸው፡፡ ነዋይ አዳል ግመሊቱን ይላታል ባራኪ እያለ ሲዘፍን አዳል ስለሚባለው ህዝብ የመጀመሪያ ነጋሪዬ ነበር፡፡ ዛሬ አዳል አይባልም ተብሎ አፋር ግመሊቱን በሚለው ተቀይሮ ሲዘፈን እሰማለሁ፡፡

አዳል የሚለው ቃል ከፉ ነገር አለው የሚለውን አላነበብኩም፡፡ የጎጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት አዳል ተክለሃይማኖት በሚለው ሌላ ስም ይታወቃሉ፡፡ ታሪክ የአዳል ሱልጣኔት የሚለውን ደጋግሞ ሲጠራው አንብቤያለሁ፡፡

9. ድሩሲላ ዱንጅን ኢ.ኤ.አ ከ1876 እስከ 1941 የኖረች አሜሪካዊት ናት፡፡ በርከት ያሉ የጥቁር ህዝቦችን ታሪክ አጥንታለች፡፡ ኢ.ኤ.አ በ 1926 የታተመው መጽሐፏ የግብጽና የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ለዓለም ያበረከተውን ምስጢር ይፋ አደረገች፡፡ ኢትዮጵያውያኑ ኩሾች በግብጽ የሚገኙ ፒራሚዶችን ስለመገንባታቸው ጽፋ የዓለምን የታሪክ ትርክት ሌላ መልክ ያስያዘች ሰው ናት፡፡

10. የአፋር ታሪክ፡፡ ገጽ 42

ሪቻርድ በርተን ምንጭ ጠቅሶ ሲጽፍ አዳል የሚለው ስም መነሻ አድ ዓሊ ከተባለው የአፋር ጎሳ የተገኘ ነው ይላል:: ጆሕንስተን የተባለው ጎብኚና ፀሐፊ አዳል የሚለው ስም ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ247 እስከ 222 በነበረው ፕቶሎሚ ኢዩርገተስ የትክል ድንጋይ ሐውልት ስሟ ተጽፎ ከተገኘው አዱሌ አዱሌ ከምትባል ጥንታዊ ከተማ ስም የተገኘ ነው ሲል አስፍሯል::"

ኤርታኤሌን ማየት የሚሻ ጎብኚ ወደ እሳት ባህሩ መጓዝ የሚችለው በዚህ ሰዓት ነው:: ቀን ሙቀቱ አይሞከርም:: ምሽት እስከ አርባ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የዋለበት መሬት ከቀይ ባህር በሚነፍስ ነፋስ የብርድ አምባ ይኾናል:: ቅዝቃዜው ጀመረ:: የዘነጠው መንሰፍሰፍ ያዘ፤ ተመክሮ ያልሰማው ጥርሱን ሲያፋጭ እንደ ሙዚቃ ሰማነው::

ያም ኾኖ መሬቱና ነፋሱ አንድ አይደሉም፤ የጋለው ምድር እሳት ሲተፋ አየሩ ቅዝቃዜ ቀዝፎ ይጋረፋል:: ጨልሟል:: ጸሐይ ጨረቃዋን ይዛት የገባች መሰለኝ:: የእጅ ባትሪዎቻችን በርተዋል:: የምንጓዘው በሰልፍ ነው:: ስንነሳ የነበረው ሳቅና ጨዋታ ራስን ብቻ በማዳመጥ ለራስ ብቻ በማውራት ተቀይሯል:: አልፎ አልፎ መሐመድ ያዮ ወይም አህመድ አይዞአችሁ ይላሉ:: እሺ ብሎ መልስ መስጠት ግን የለም:: እራሴን ከእስራኤላውያን እንደ አንዱ ቆጠርኩት፤ ከፈርዖን መዳፍ አምልጠው ቀይ ባህርን ከተሻገርኩ በኋላ ለሊቱን በደመና የሚመራው መልአክ ታሪክ ትዝ አለኝ:: መንገዳችንን ስተናል፤ መንገድ መሪዎች መካከል ገብተው የህዝቡ ጋር የምንደርስበትን ፍሊጋ አብረው ለማየት ያሰቡ ይመስላሉ:: ሙሴያችን የለም::

11. የአፋር ታሪክ:: ገጽ 49

የአፋር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጥንቅቅ ብሎ ነበር፤ በቂ ስንቅ ጭኗል:: የመንገድ ቁሳቁሶችን አሟልቷል:: ከቀናት በፊት ጉዳናውን ለመስለል የመጡት ሰዎች ምልከት ያኖሩት የድንጋይ ከምር ጠፉ፤ አሁን ተስፋችን ሰማዩ ነው:: ሰማዩ እሳተ ገሞራውን ብርሃን ከምድር ተቀብሎ ለእኛ ያሳየናል:: ብርሃንን ሰማይ ላይ እያየን ያየንበት ለመድረስ እንጓዛለን:: እያንዳንዱ ርምጃ ጥንቃቄን ይፈልጋል:: ያም ኾኖ ድው የሚለው ድምጽ የአንዱን መንገደኛ መውደቅ ይነግረናል:: መተጋገዝ ፈተና ኾኖ ከንፈር ለመምጠጥ አቅም ያጣው በዛ:: ማንም ሰው ኤርታኤሌን የሚጎበኘው በቀላሉ ነው፤ በታሪክ አጋጣሚ በእኛ እንዲኸ ያለው ከስተት ተፈጸመ::
ከርቀት ባትሪዎችን ተመለከትን፤ ወደ ባትሪ ብርሃኖቹ ፊታችንን አዙረን በሰልፍ እንደኾነን ገሰገስን:: ከቀዳሚዎቹ አንዱ ነበርኩ:: የካሜራ ባለሙያዬ ዮናታን ከእኔው እኩል ጉዞውን የሚመራውን ፊት ተጓዥ ተቀላቅሏል:: ስንደርስ ሁለት ፈረንጆች አንድ አበሻ ኾነው አገኘናቸው::
"whare is the pass?" ማናችንም አልመለስንም፤ ይልቁንስ ፊታችንን መለስን:: መድረስ ፈልገን ብዙ መንገድ ስንመጣ መንገዱ በየት ነው የሚል መንገድ ፈላጊ ገጠመን::
3 ሰዓት ይወስዳል የተባለውን መንገድ አምስት ሰዓት ተጉዘንበትም የሚታየው እሳት እየታየን እየጠፋ እኩለ ለሊቱ ሊመጣ ነው:: ፍርሃት የእሳቱን ያክል በአካባቢያችን አርብቧል፤ የምንረግጠው ይከዳናል:: የከዳነው ያፈርጠናል::ድንገት እንደ ውሃ መሬት የሚንሳፈፍ የእሳት ባህር ዳርቻ ደረሰን:: ደስታችንን ድካም ዋጠው:: ለመገረም ጉልበት ይፈልጋል:: እኛ በጭንቅ የደረሰን እንዴት እንመለስ ይኾን የምንል የእሳት ዳር መጻተኞች ኾነን:: ኤርታኤሌ የማያድር እንግዳ መጣበት::

በጣም ዝቅተኛ የሚለው ቃል ከባህር ወለል በላይ 615 ሜትር ከሚለው የተሻለ ነው:: ይኸ እሳተ ገሞራ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1873 መከሰቱ ከተመዘገበ በኋላ ከዚያ ወዲኸ ያሉት ተከታታይ የምድሩ ውስጥ ቁጣዎች በ1903፣ በ1906፣ በ1940፣ በ 1960፣ በ1967 እና በ1998 ተከስቷል:: በቅርቡ ኤርታኤሌ ዳግም ፈነዳ የሚለው የዓለምን መገናኛ ብዙኃን አጨናነቀ:: ያንን ተከትሎ የአፋር ክልል ይኼንን ተአምር የሀገሬ ጋዜጠኞች ይዩት ብሎ ይኼን ጉዞ አዘጋጀ::

እሳቱ እንደ ልድልድ ፈሳሽ ይወዛወዛል:: የፍም ወጥ በምድር ድስት ውስጥ ተዘርግፎ አየሁ:: የሚጤሰው ተራራ እንደጠበቅሁት አልጠበቀኝም፤ የሲኦል ደጃፍ የሚባለው አስፈሪ ስፍራ ልብ ያርዳል:: እሳቱ ሰማይ ላይ ብርሃኑን ለቆ ምድር የነደደች እስኪመስል ደስ የሚልም የሚያስፈራም ስሜት ፈጥሮብኛል:: ዓለም ወደ እዚህ ስፍራ እየሮጠ ነው:: የእሳተ ገሞራው ጢስ ዓይን የሚቆረቁር፣ ጉሮሮ የሚቧጥጥ መሰለኝ:: ሁላችንም አፋችን ላይ የአየር ማጣሪያ ማስክ አድርገናል:: ያስፈራል::

ትከሻውን ከሚሰብቀው የኤርታኤሌ ምድር የሚወጣው እሳት ምድሩን አየር አድርጎት ዐለቱ እየካደ የምንቆምበትን ስፍራ እስከናጣ ጭንቅ ውስጥ ገባን:: ራቅ ብሎ ገና ፈንድቶ ያልበቃለት የእሳት ተራራ እያየን ነው:: መመለስ ከሞት የማምለጥን ያክል ድል ሆኖ ጭንቀት የእሳቱን ውበት አደበዘዘብን:: ያለንበት ስፍራ የስጋት ቀጠና መኾኑን የተረዳነው መንገድ መሪዎቹ ከስፍራው ለመውጣት የሚያደርጉትን ፋታ የለሽ ጥረት ስመለከት ነበር::

መመለሱ እጅግ ከባድ ነው:: በግመል ተጭነው ካምፕሳይት ስለአረፈው ድንኳናችን፣ እራታችን እና ቁሳቁሶቻችን ግድ አልሰጠንም:: የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር መንገድ መሳታችንን ሰምተዋል:: ከዚህ መዓት እንዲያወጣን ኮማንዶን ላኩ::

# ኮማንዶ-የደናክሉ ፈጥኖ ደራሽ

"....እኛ መሀል ለሌለኸው
ታሪክህ ለተሸፈነው
ሁሉን ከሩቅ አብሰልስለህ አጠንክረህ ለምታየው፣
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፣ ለምታየኝ ላማላይህ
ለምታውቀኝ ለማላውቅህ
ማነህ ባክህ
ማነህ"

ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን
እሳት ወይ አበባ

ኮማንዶ መደበኛ ወታደር አይደለም፡፡ የዳሎል ምድርና የኤርታኤሌ የእሳት ባህርን ፍለጋ የሚመጡ ጎብኚዎች ውበቱ ብቻ ሳይኾን ሽፍታው እዚህ ምድር እንዳያስቀራቸው ይሰጋሉ፡፡ አንዳንዴ የውጪ ጎብኚዎች እንዲህ ባለው አካባቢ ጠፉ ሲባል የኤርትራ ታጣቂዎች ናቸው የሚለው ተደጋግሞ የሚሰማ ሰበብ ነበር፡፡ ሃርዱፍ የሚባሉ የመንግስት ተቃዋሚ ታጣቂ የአፋር ነጻ አውጪዎችም ይኾናሉ በሚል የሚናገሩ አሉ፡፡ ማንም ይኹን ማን አንዳንዴ በዳሎልንና በኤርታኤሌ ገብቶ መቅረት አለ፡፡

ሊያወጣን የመጣው ኮማንዶ እንደ ደረሰ
"ፍጠኑ ፍጠኑ" አለ፡፡ እግሩ ፈጥኖ መከተል የቻለው ትዕግስቱ በለጠ ነበር፡፡ እኔም ቀጥያለሁ፤ ካሳሁን የሚባል የባህልና ቱሪዝም ህዝብ ግንኙነት አብሮን አለ፡፡ ዮናታን ታደሰ የኔ ካሜራ ማን ይከተላል፡፡ ሌላውም እንዲኹ ጥድፊያ ላይ ነው፡፡
እሳተ ገሞራው እንደምራቅ በተፋቸው ሹል እና አስፈሪ ዐለቶች ላይ እየተንጠላጠልን ወደ የት እንደኾነ ግድ ሳይሰጠን ከእሳቱ ባህሩ ለማምለጥ የምንረግጠውን አናውቅም፡፡ እንዲያም ኾኖ ማንም እወጣለሁ የሚልን ተስፋ የሰነቀ አይመስልም፡፡ ካረበበው መንፈስ የተረዳሁት ጭንቀት ተስፋ አስቆርጦት ጥረት ነፍሱን እንዲያተርፍለት አስራ አንደኛዋን ሰዓት ሳትቆጥር ለማምለጥ የሚጥር ተጓዥ ነው፡፡
የብዙዎቻችን ባትሪዎች አልቀው መንጨልጨል ጀምረዋል፡፡ የሞባይል ባትሪዎቻቸውን ያበሩም ነበሩ፡፡ ስንሄድ የነበረው የባትሪ ብርሃን ሰልፍ አሁን በሰማይ ርቀው እንደሚታዩ ከዋከብት ተንጨላጭለው ተበትነዋል፡፡ ኮማንዶ ባትሪ እንዲበራ አይፈልግም፡፡ በጨለማ ይታየዋል፡፡ እኛ በጨለማ አይታየንም፡፡ የሞት መንገድ ኾነ ጉዞው፤
እሳት እንደ መስታወት ቀላል ያደረጋቸው ዐለቶች ሲረግጡዋቸው ከደው ቁልቁል ይሰዳሉ፡፡ ጣርና ማቃሰት፣ ቀስ በሉ የሚል ድምጽ ተደጋገመ፡፡ ኮማንዶ በጣም ፈጣን ነው፡፡ እሳቱ ባልጠጠረ ዐለት ላይ እንደ ጦጣ እየዘለለ ይሸመጥጣል፡፡ አንድ ቦታ ስንደርስ መውጫው ጠፋው፡፡ ድንገት ጢስ ነገር ከበበን፡፡
"ተበላን...ተበላን" ዘለለ፤ ትግስቱ ተከተለው፤ ቀጠልኩ፡፡ እሳት በሽንቁር የዐለት ቀዳዳ ጢስ እየተፋ ነበር፡፡

ፈጠንን ብለውም በእኛ ፍጥነት ማየል ኋላ ያስቀረናቸው ይኼንን አላዩም:: እኛ ውሃ ኾነናል:: ድንገት ያ ስስ ዐለት ድርምስ አለ::
"ዮናታን አንተ ነህ?" ካሜራ ማኔን ጠየቅሁት፤ ዞሮ ማየት ጊዜ ይገድላል:: በቅጽበት ከዓይን የሚሰወረውን ኮማንዶ ተከትለን እየበረርን ነው:: ድንገት ጉድጓድ የገባ ሰው እንዳለ ከወደቀው አካል ድምጽ አውቄያለሁ::
"እኔ አይደለሁም እኔ አለሁ::" አለ ዮናታን::
ቆይቶ የሚያቃስት ድምጽ ሰማሁ:: ወድቆ በመነሳት ፊት ይመራ የነበረውን ቡድን ጥርሱን ነክሶ የተቀላቀለውን ሰው ዞር ብዬ አየሁት:: ጆሲ ነበር:: ዮሴፍ የኢቢኤሱ ካሜራ ማን::
መውደቅ አኹን ብርቅ አይደለም:: በህብረት የነበረው ጉዞ በተበጣጠቁ ትንንሽ ቡድኖች ተከፋፈለ:: ምድር ደርሰናል ለማለት የግድ አፈር መርገጥ የተነሳንበት መድረስ አለብን:: ሊሊቱን በእግር ተጓዝነው፤ የፈራነው የእሳት ባህር በወላፈኑ ብርሃንና ውበት እየሸኘን ነው::
ዮናታን ከኮማንዶ እኩል መሮጡ አበሳ ኾኖበታል:: ዞር ብሎ ሲመለከት ብዙው ሰው ከኋላ ቀርቷል:: ተቆጣ:: "የራስህ ጉዳይ እኔ ራሴን ላወጣ ነው::" ኮማንዶ ፈጠነ::
ከሌላው የተቆረጠ ቡድን ኾነን ኮማንዶን ተከትለን እየሄድን ነበር:: ኮማንዶና ትግስቱ በለጠ እኛን ቆረጡን::
እኛ መንገድ የማያውቁ፣ መሪው ያመለጣቸው፤ ጓዶቻቸው ኋላ የቀሩ ኾንን:: እኔ፣ ዮናታን፣ ጆሲ፣ ሳሚ ሀሌታ፣ ካሳሁን..... ከዚኽ በኋላ ያለፍንበትን መንገድ ዛሬም ሳስበው ይጨንቀኛል:: ኮማንዶ አቋራጭ መንገድ ፍለጋ የመጣንበትን ትተን በሌላ ጎዳና ጉዞ አስጀምሮናል::

ቀጥ ብሎ በሾለ የዓለት ጦር ላይ ዘለን እያረፍን፣ ጣርና ህማም በዝቶ አንዲት ስፍራ አረፍን፡፡
ኮማንዶ ተቆጣ፡፡ ዮናታንም ተቆጣ፡፡ ዳሩ ኮማንዶ ዮናታንን በአንድ ጥይት ዝም ማስባል ይችላል፡፡ ዳሩ ኮማንዶ ሊያወጣን የመጣ እንጂ የቀጠርነው አልነበረም፡፡ ሳናውቀው የቀረን እንዲመስል ብዬ
"ኮማንዶ እኮ ቢኖር ያወጣን ነበር ያለ እሱ አንወጣም" አልኩ፡፡ ኮማንዶ ካላወቁት ሰዎች ጋር እየተጣለ መሰለው፡፡ ራሳችሁን አውጡ ብሎ ብድግ ብሎ ሄደ፡፡ ቅጠልና ቁጥቋጦ በከበባት አንዲት ደልዳላ ቦታ አርፈናል፡፡ ብቻችንን ነን፤ መውጫውን አናውቀውም፤ ቀጥሎ ያለው ፈጣን ቡድን ከአንድ ሰዓት በኋላ ተቀላቀለን፡፡
ከዚያ ቀጥሎ ያለው ሰላሳ ደቂቃ ዘግይቶ መጣ፡፡
ለሌሊት ነው፡፡ የኢቢኤስ ጋዜጠኛዋ ዮዲት ሽፈራሁ ድካም እንጂ ደህና ናት፡፡ የሪፖርተር ጋዜጣዋ ምህረት በልዩ ሃይል ፖሊስ ተደግፋለች፡፡ የፋናዋ ጺጋ ታሪኩ ሰማይ ምድሩ ተደፍቶባታል፡፡ ያደረገው ጫማ ሶሉ ተገንጥሎ መውለቁን ያላወቀ፤ ደሙን እየዘራ የደረሰ፣ የሚያቃስት፣ በእኛ ቀድሞ መሄድ የሚቆጣ፣ ሁሉም ተሰበሰበ፡፡ ዳሩ ገና ግማሽ የሚሆን መንገድ ቀርቶን ነበር፡፡
ርቦናል፡፡ ለሌሊት ስምንት ሰዓት ተኩል ሆኗል፡፡ የጫነው ስንቅ ከነግመሎቹ የት እንደገባ አላወቅንም፡፡ ሀሳባችን ስንቅ ከጫነው ግመል ጋር አንዱ ስፍራ ተገናኝተን እኩለ ለሌት እህል ልንቀምስ ነበር፡፡
ጋደም እንላለን ብለን ብዙ ሙሽማ /ጅባ/ ይዘናል፡፡ የቀጠሮው ቦታ ጠፍቷል፡፡ ሞትን ድል አድርገን አንድም ሰው ሳይጎድል ተመልሰናል፡፡

የፈላ ሽሮ ወጥ ድስት እተጣደበት እሳት ላይ ኾኖ ከዳኑን እንደከፈተ ሰው እሳት፣ ድምጽና ሽታን አምልጠን የመጣን ነን፡፡
ከባድ ጢስ አሽትተናል፤ እሳት እንደ ውሃ ሲገማሸር አይተናል፡፡ የተቆጣ ምድር እሳት እየተፋ ሲሸልል ድምጹን ሰምተናል፡፡ ከዚያ ወጥተን ነው እዚህ የተሰበሰብነው፡፡ ከዚህ በኋላ ያለው መንገድ ቀላል ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ያለው ጎዳና አይከብድም፤ ተነሱ ተነሱ ተባባልን፣ የሚያነከሰው እያነከሰ፣ የሚያቃስተው እያቃሰተ፣ ወደ ተነሳንባት ተመለስን፤
አስኮሚ ባህሪ ሲያቅላላ ደረስን፤ ፈልገው ያጡን ግመል ጭነው የሄዱ ሰዎች ተስፋ ቆርጠው ተመልሰው ቀድመውን ደርሰዋል፡፡ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ካቢኔያቸው በጭንቀት ተወጥረው ጠብቀውናል፡፡
አስኮሚ ባህሪ ስደርስ በሆዴ ይኼ ሁሉ አልፎ እኮ አንድ ቀን እጽፈው ይኾናል አልኩ፡፡

# ወደ ሆር ሆር ገዳም በምድር ከርስ ውስጥ

*"ንደፊው ከንፈሬን ንብ ሆነሽ ነይና*
*አንቺ ካልተመቸሽ እኔ ልምጣ ቡግና"*
ካሳሁን ታዬ-ዓለምዬ ሶራ

ተመችቶኝ ቡግና መጣሁ:: ይኽ የቅዱሳኑ ነገሥታት ምድር ነው:: ላስታ፤

ቡግና እንደ ስሟ አይደለችም:: ኢትዮጵያ ውስጥ የነገሥታት ሀገር ወይ ይለማሉ፤ ወይ ይከስማሉ:: ቡግና መከሰም ተፈርዶባታል:: የቅዱሳኑ ምድር ነበረች:: የንጉሥ ሀርቤ ሀገር፤

ያደርኩባት ከተማ ስም ዓይና ነው:: ዓይን ቦታ ሲሉ ንጉሥ ገብረ ማርያም ናቸው ስሟን ያወጡት:: ከሺህ አመት በፊት::

ገብረ ማርያም ስመ መንግሥት ነው። የሀርቤ፤ ሀርቤ ገብረ ማርያም አባቱ የጃን ሥዩም የበኩር ልጅ ነው።[1] የቅዱስ ላሊበላ ታላቅ ወንድም።[2] ጃን ስዮም ከላስታ ቡግና መሣፍንት አንዱና በወርቅና በብር፣ በልብስና በጌጥ፣ ባሽከርና በከብት፣ በሀብትና በንብረት የከበረ ነው።[3]

ዛሬ ዘመን ዓይኗን ሊያጠፋት ታግሎ ታግሎ ተርፋ ደርሻለሁ። የቡግና ወንጀል የሀገር ክብር መሆን ነው። የዓይና ጥፋት ዓይን ሆና እንደ ዓይናችን ልንጠብቀው የሚገባንን የሀገር ስምና ክብር ጠብቃ ማኖር ነው።

ትናንት ወደ ቅዱስ ሀርቤ ወጥቼ ነበር። የዐፄ ይምረሐነ ክርስቶስ ወንድም ልጅ። ሀርቤ 2ኛ፤ የሀገሬ ሰው ቅዱሱ የሚለው። የዓረብ ጸሐፊዎች ቀኑዳ ያሉት፣ ምዕራባውያኑ ደግሞ ሲኖዳና ሸኑዳ በሚለው ስም የሚጠሩት ታላቅ ንጉሥ።[4]

ወደ ቅዱስ ሀርቤ የሄድኩት ሶራን አልፌ ነው። ሶራ ምንጣፍ መሳዩ ምድር፤

*"ሶራ ሶራ አልኳትኝ ምንጣፉን ነው ብዬ*
*ሶራ ሶራ አልኳትኝ ላሚቷን ነው ብዬ*
*የሀገርም ሶራ አለው፤ ኸረ እናንተ ሆዬ፤"*

ዘፈኑን ስለ ምን እያወራ እንደሆነ ጎልቶ የተሰማኝ ሶራ ከተባለው ምንጣፍ መሳይ ሰፊ መስከ ላይ ስቆም ነው።

---

1. ዶክተር አያሌው ሲሳይ። የአገው ህዝቦች ታሪክ። ገጽ 130
2. ፍሰሐ ያዜ። የኢትዮጵያ የ5ሺህ ዓመት ታሪክ። ገጽ 207
3. ገድለ ላሊበላ። ገጽ 10
4. ፍሰሐ ያዜ። የኢትዮጵያ የ5ሺህ ዓመት ታሪክ። ገጽ 207

ሶራ ቡራቡሬ ወይም የተዥጎረጎረ ማለት ነው:: መነሻው ምንጣፍ እንደሆነ ሰምቻለሁ:: በንጉሥ ገብረ ማርያም ዘመን ለነገሥታቱ የሚነጠፍ ከኩበት ቆዳ የሚዘጋጅ ቡራቡሬ መልክ ያለው የክብር ምንጣፍ፤ ደግሞ ሌላ ታሪክ አለ::

አንድ ሴት ነበረች:: ምንጣፉን አምጥታ የምታነጥፍ፤ ስሟ ሶሪት ነበር ሶራ ይሉት ቃል ከእሷ መጣ ሲሉ ይናገራሉ:: የቡግና ሰው ስለ ሶራ ብዙ ብሷል::
"ለምን ትቀሪያለሽ ሶራ ከውሃው፣
ዓይና አልነበረም ወይ የናፍቆት መውጫው፤"

ናፍቆቴን ልወጣ ዓይና መጥቻለሁ:: ሀርቤ ገብረ ማርያም እየሄድሁ ነው:: የሰውም የቦታም ስም፤ ሀርቤ ለመድረስ ከዓይና የተነሳ በሶራ በኩል ያልፋል:: ከሶራ ሀርቤ በግምት ሁለት ኪሎ ሜትር ቢሆን ነው:: ያገርም ሶራ አለው የሚለው ዘፈን ኳየር የሆንኩት ከዚህ ቀን በኋላ ነው::

ሀርቤ ገናና ንጉሥ ነው:: በቅድስናውም ይወደሳል:: ዶክተር ስርግው ሀብለሥላሴ ባልታተመው የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ሀርቤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ራሷን የቻለች ትሆን ዘንድ ጳጳስ ከኢትዮጵያ እንዲሾምላት ለግብጽ ጥያቄ ያነሳ እንደነበር ጽፈዋል::[5]

ደረስን:: ኮረብታማ ስፍራ ነው:: ከመኪና ወርደን በእግር ሽቅብ መውጣት እንዳለብን ተነገረኝ:: አብረውኝ ደጋጎቹ የቅዱስና የንጉሥ ልጆች አሉ::

5. ዶክተር ሥርግው ሀብለ ሥላሴ:: የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት:: ክፍል 1 ገጽ 2::

ጥሻ ነው። ከባድ ጥሻ። ዛሬ ድረስ ሳስበው ያን በአራሙቻ የተሞላ ወርቅ ታሪክ የኖረበት ኮረብታ አጽድተውት ይኾን እላለሁ። የሳማ እሾህ እየለበለበኝ ወጣሁት። መንገድ የለውም፤ በዚያ ላይ አረሙ በሙሉ ይዋጋል። ከብሳናው ዛፍ ውጪ ያልወጋኝ የለም፤ በአጠቃላይ እሾህ ብቻ ያለው ቅጠል የበቀለበት ኮረብታ መሰለኝ።

ወደ አናቱ በተጠጋን ቁጥር የተኮለኮለው ጥቁር ድንጋይ ለመረገጥ አስቸጋሪ ኾነ። ድንጋዩ የጥንቱ ቤተ መንግሥት ፍርስራሽ መኾኑን ነገሩኝ። እንዲህ አልጠበኩም፤ የፈረሰውን መጠገን የታሪካችን ገድል አይደለም፤ ነበር ብቻ፤ ሁሉ ነበር። አናቱ ላይ ወጣን። ቡግና ቁልቁል ታየ። ሀርቤ የምትባለው ትንሽ መንደር ከኮረብታው ስራ እንደ ምንጣፍ የተነጠፈች መሰለኝ።

አብረውኝ ከወጡት አንዱ ቄስ ተፈራ ስጦታው ናቸው። ስለ ስፍራው ቁጭት እንደ አንገበገባቸው ከትረካቸው ተረዳሁ። ቄስ ተፈራ ከስሙ ትርጉም ገለጻቸውን ጀመሩ፤
"ይኼ ሮሐ ጉርጉር ይባላል። ሮሐ ወለል ያለ፣ ሰፋ ያለ ማለት ነው። ጉርጉርም ሮሐም ጥንታዊ ስሙ ነው።"

እውነታቸውን ነው። ወለል ያለ ስፍራ ነው። እስከ ተከዜ የተዘረጋ፣ እስከ እብናት የሚታይበት። ላስታን ከጎንደር የሚያነጋግር።

ሀገሬው መራ ተክለ ሃይማኖት ከሞሰበ ወርቅ ጋር ጎጆ የወጣበት አምባ ነው ብሎ ያምናል። እዚህ አምባ ላይ ነኝ።

እውነት ለመናገር ቀደምቱ የቤተ መንግሥት ፍርስራሽ አፈር እየገባ ባለ የድንጋይ ቅሪት ተቀብሮ ሊቀር ነው፡፡ ብዙ ታሪክ ያለበት ስፍራ ሲመጣ ምንም የሌለበት እስኪመስል ባድማ ኾኗል፡፡ ሀርቤ ገብረ ማርያም ቅዱሱ ቦታ ከመባል ያለፈ የሚታይን ነገር ማግኘት ከባድ ነው፡፡ በዚህ ስሜት ኾኜ ነበር የሀርቤን አሻራዎች ለመመልከት በቄስ ተፈራ መሪነት ወደ ታች የወረድሁት፡፡

ከኮረብታማው የጉርጉር አካባቢ ብዙ በማይርቅ ስፍራ የቅዱስ ሀርቤ ደብር ይገኛል፡፡

በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም የተንቆጠቆጠችው ቤተ ክርስቲያን ቅጥር በጥድና ወይራ ዛፎች የተዋበች ናት፡፡ የንጉሡን ቅርሶች እንድመለከታቸው አደረጉ፡፡ ሀርቤ ቅዱስም ጥበበኛም እንደነበሩ ዛሬ የደረሱ አልባሳቱና የተጠቀመባቸው ቅርሶች አረጋግጠውልኛል፡፡ ሙዚየም እያደራጁ ነበር፤

እንንቀሳቀስ ተባለና በመኪናችን ገባን፡፡ ዛሬ የምንውለው ሆር ሆር ነው፡፡ ምድር ሆድ ውስጥ ገብቼ ተአምር አያለሁ፡፡ ቡግና ምድሩ አይጠገብም፡፡ መልከአ ምድሩ ያፈዛል፡፡ ሸለቆውን የተሻገረ ዓይን በኮረብታው ውበት ይፈዛል፡፡ የተራሮች ውበት ኮረዳ እንዳየ ጎረምሳ የእያንዳንዱን ተመልካች ስሜት ይቆጣጠራል፡፡ ገና ዓለም ያላየው፤ ቢያየው ጉድ የሚልበት የመልከአ ምድር ጸጋ በድፍን ኢትዮጵያ ተድብቆ እንደሚኖር አምናለሁ፡፡ እንዲህ ኾኜ እዚህ ደረስኩ፡፡ ቡግና ወረዳ ብርኮ ቀበሌ፤

ከመኪና ስንወርድ የገዳሙ አበ ምኔት ጎዳናው ዳር ጠብቀውን ነበር፡፡ እንግዳን ከቤቱ ማምጣት የአብረሃም ልብ ምኞት እንደነበር ነው ያነበብኩት፤ ያው እዚህ ድረስ መጥቶ እንኳን ደህና መጣህ ማለት ከቤት የማምጣትን ያህል ለጋስ ልብ ይፈልጋል፡፡

መንገዱ እንደ ወዳጅ እያጫወተ ይሸኘኛል፡፡ የእግር ጉዞው የሚፈጀውን ሰዓት ለመቁጠር ፋታ የማይሰጥ መስክ ነው፡፡ ኮረብታው ታርሶ፣ የታረሰው ሰብል ለብሷል፡፡

በቡግና ገበሬ ማሳ ላይ ሆር ሆርን ፍሊጋ ቁልቁል ገሰገስን፤ ስመለስ መንገዱ እንደሚከብደኝ ስሄድ ማስታወስ አልቻልኩም፤ ወጉም ምድሩም ፋታ ነስቶ እግር ያበረታል፡፡ የቡግና ማር ከምን እንደሚገኝ አየሁ፡፡ ሞቃታማና ገላጣ የሚመስለው ደን አልባ ምድር ብዙ ዓይነት እጽዋት እዚህም እዚያም በቅሎበታል፡፡ አንዳንዴ እንደ ጠጠር አፈር ላይ የፈሰሰ ኮረታማ ድንጋይ ይገጥመናል፡፡ ሁላችንም እንወላገዳለን፤

የቡግና የገበሬ መንደር ሽታና የተተረከልኝ የምድር ሆድ ውስጥ ያለ ገዳም ናፍቆት ድካም የማይሰማው ተጓዥ አድርገውኛል፡፡ ምናልባት መንገድ ከጀመርሁ ከአንድ ሰዓት በላይ ይኾነኛል፡፡ ግን አሁንም ብርታት እንጂ ድካም አይሰማኝም፡፡
ከአበምኔቱ ጋር ሰባት ነን፤ አንዷ በወቅቱ የወረዳው ባህል ቱሪዝም ጽ/ቤትን በኃላፊነት የምትመራ ናት፡፡ ፈንታ ወርቅዬ ትባላለች፡፡

ቢራራ ፀሐይ ነው ደጋግሞ የመጣ የዓይና ሰው ነው:: "እንሂድ ባሉኝ ቁጥር ሆር ሆር ለመምጣት እግሬን ሰብስቤው አላውቅም" ይላል:: ዛሬም መምጣቴን ወዶት አብሮኝ ለብዙኛ ጊዜ የመጣ::

የአበ ምኔቱ አባ ገብረ ኢየሱስ መንፈስ የሚገዛ ቀልብ ያላቸው መናኝ ናቸው:: በሁሉም ነገር ቁጥብ፤ ደግሞ ፈገግ ሲሉ ሰርግ የታደምኩ እስኪሰማኝ ልቤን በደስታ የሚሞሉ፤ አይዞህ ያሉኝ እንደው አሁን መንገድ እንደጀመረ ሰው ጉልበቴን የሚያድሱልኝ፤ ድምጻቸው አጠገቤ ሆነው ከሩቅ እንደሚመጣ ሁሉ ነገሬን ውስድ የሚያደርገኝ::

አንድ ገደል አፋፍ ቆመን፤ ሜዳው ጋልበ መጥቶ ደርሶ ግዙፍ ሸለቆ የፈጠረበት ቦታ ነው:: አባ ገብረ ኢየሱስ ቆም አሉ:: "እንግዲህ አባቶች እንዳስረዱን የመጀመሪያው ታሪክ የእመቤታችን ጽላት ነበረች መጀመሪያ የመጣችው፤ እሷ በአምደ ብርሃን ነበር የመጣችው:: ስውራን አባቶች ከነበሩበት ሀገረ ግብጽ ወደዚህ እንደመጣና እንዲህ ያለ ስፍራ ታገኛላችሁ ወስዳችሁ እዚያ መስርቱ በሚል ምሪት አቡነ ሆርና አቡነ ገብረማርያም የሚባሉ ናቸው ይላል የቦታው ታሪክ::"

ዙሪያ ገባውን አየሁት:: ገደል ነው:: በእንፉቅቅ መውረድ ተጀመረ:: ቢጫ ቆብና ቢጫ ፎጣ አድርገው በእጃቸው በቻርጅ የሚሰራ ባትሪ የያዙት መነኩሴ ገደል እንደ ሜዳ በሚቆጥረው ስቃይ የለመደ እግራቸው ይሮጣሉ:: መራቃቸውን ሲመለከቱ ቀና ብለው ሸቅብ ያዩናል::

ድንጋይ ጨብጦ ድንጋይ እየረገጡ ቁልቁል መንደርደር፡፡ የሚያንሸራትት ነገር የለውም፡፡ የሚረገጠው ድንጋይ እግር ቆንጥጦ ይይዛል፡፡ ግን ደግሞ ያስፈራል፡፡ እንደ አባ ገብረ ኢየሱስ ገለጻ ብዙ የስፍራው ታሪክ ተከዜ አፋፍ ሳይኮ ኪዳነ ምህረት ይገኛል፡፡

እንዲህ ወርደን ጥላ ያለውና ዛፍ ያጀበው ቀና ቁልቁለት ተቀበለን፡፡ መንገዱ ቀለለ፤ አንዲት ወንዝ ዳር አረፍን፡፡ ስንነሳ የወንዟም ስም ነገሩኝ፡፡

ባውሽ....... ወዲያው ግጥሙ ከነ ዜማው አፌ ላይ መጣ፡፡

*"ባውሽ...ባውሽ...*

*ላስታ ላግኝሽ...."*

ላስታ ተገኝቻለሁ፡፡

ወንዟን ተሻገርን፤ አሁን ሙሉ ለሙሉ የገዳሙ ቅጥር ውስጥ ነን፡፡

ድንገት ግዙፉ ቋጥኝ የምድርን አፍ ከፍቶ የተቀበለኝ መሰለኝ፡፡ ሆር ሆር አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም፡፡ ግዙፍ ቋጥኝ፤ ቀና ብዬ አየሁት፡፡ ሰማይን የተሸከመ መስሏል፡፡ ውስጡ ሰፊ ነው፡፡ የዋሻው በራፍ ላይ ስንደርስ አብረውን ያሉት ጫማቸውን አወለቁ፡፡ አባ ቀድሞውኑም ባዶ እግራቸውን ነበሩ፡፡ ጫማዬን ለመፍታት ከተቀመጥሁበት ኾኜ ቀና አልኩ፡፡ ዋሻው በጣም ሰፊ ነው፡፡

ወደ ዋሻው የገባነው ባዶ እግራችንን ነው፡፡ በአባ እግሮች ቀናሁ፡፡ ስል ኮረት እንደቄጤማ በተጎዘጎዘበት ጎዳና እግሮቼ እሺ ብለው መሄድ አቃታቸው፡፡ ተንሰፈሰፍኩ፡፡

ድንገት ስንቆም ደስ አለኝ፡፡ በእግሬ የቆምኩበትን ጠረኩት፡፡ የሚወጋኝ እሾሃማ ድንጋይ የተሰካው እግሬ መዳፎች ላይ ነበር፡፡ የጸዳ መሬት ላይ ቆሜ ከህመም አልዳንኩም፡፡ እየጠዘጠዘኝ አባን ሰማሁ፡፡

"ታሪኩ ከዐፄ ካሌብ ይጀምራል፡፡ በዐፄ ካሌብ ዘመን የታነጸው መቅደስ ይኸ ነው፡፡"

ቀና አልኩ፤ ኮርኒሱ ሹል ድንጋይ ነው፡፡ ጌጥ ይመስላል፡፡ ደግሞም የሚረግፍ መስሎ ቁልቁል ተንጠልጥሏል፡፡ ግን ሺህ አመት እንዲህ ነው፡፡ እንደነገሩኝም፣ እንደመሰለኝም፡፡

ጥንታዊውን ቤተ መቅደስ አየሁት፡፡ ዋሻው ላይ ቢቆምም እንደ ይምርሃነ ከአናቱ አልተጋጠመም፡፡ ደግሞ ከምድሩ ተያይዞ በግንብ የታነጸ በጭቃ የተለሰነ ነው፡፡ ከተሰራበት ዘመን አንጻር ጥንታዊ ነው፡፡ ዛሬ እድሜውን ቆጠርኩት፡፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመት፡፡

ታሪክ እንደሚነግረን ዐፄ ካሌብ ከ485 እስከ 515 የነገሡ ንጉሥ ናቸው፡፡[6] ስማቸው ከፍ ብሎ በታሪክ የሚነሳው የዓረቢያን ምድር በማስገበር ነው፡፡ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ዜና ሀገረ ናግራንን ጠቅሶ በጻፈው የናግራን ሰማዕታት ዐፄ ካሌብ ወደ ናግራን ለመዝመት ከ120ሺህ በላይ ወታደር ማዝመቱን ይነግረናል፡፡[7] የናግራን ጠብ መነሻ ፊንሐስ የተባለው ንጉሥ በፋርስ ታግዞ በየመን የሚኖሩ ክርስቲያኖችን በማሳደዱ ነው፡፡

6. ፍሰሐ ያዜ፡፡ የኢትዮጵያ የ5ሺህ ዓመት ታሪክ፡፡ ገጽ 175

7. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፡፡ የናግራን ሰማዕታት፡፡ ገጽ 8

በኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ሰላም ማስከበርም ሆነ ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊ ዘመቻ ይህ ታሪክ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ኽኖም ኖሯል::[8]

ናግራን ዘማቹ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በሀገሩ ብዙ አሻራዎች ያሉት ባለ ታሪክ ጀግና ነው:: አንዱ ጋ መጥቻለሁ:: ምድር ሆድ በራፍ ላይ የሰራውን እያየሁ ነው:: ለነፍሱ ብዙ የደከመው ንጉሥ ከሰራቸው ቤተ መቅደሶች አንዱ ይኸ ሆርሆር የሚገኘው የዋሻ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ተነገረኝ:: አባ ጋስፓሪኒ ንጉሠ ነገሥት ካሌብ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የትልቅ ክብር ታሪካዊ ስም አለው:: ሲሉ ታላቁን ንጉሥ ገልጸውታል::[9]

ከንጉሥ ካሌብ ገድሎች ከፍ ብሎ የሚሰማው የናግራን ዘመቻው ድልና የሰማዕታቱ ጭቆና ነጻነት ነው:: ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌም በባሕረ ሐሳብ ባህርን የሰነጠቀውና የዐረብን አገር የገዛው ይሉታል::[10]

በሰሜን ከሶርያ በረሓ፣ በደቡብ ከሕንድ ውቅያኖስ፣ በምስራቅ ከፋርስ ባህረ ሰላጤና ባቢሎን በምዕራብ ደግሞ ከቀይ ባህር የምትዋሰነው ናግራን ከኢትዮጵያ መንግሥት የደቡብ ዐረቢያ ግዛቶች አንዷ ተብላ በታሪክ የተገለጸች ስፍራ ናት::[11]

8. ኮ/ል ጌታቸው ዳኛው:: የኢትዮጵያ ሠራዊት እና የጦርነቶች ታሪክ:: ገጽ 25
9. አባ ጋስፓሪኒ:: የኢትዮጵያ ታሪክ:: ገጽ 133
10. ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ:: ባሕረ ሐሳብ:: ገጽ 231
11. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት:: የናግራን ሰማዕታት:: ገጽ 5

ብዙ ሰነዶች የዐፄ ካሌብን የናግራን ዘመቻ በተመለከተ ሲገልጹ አስቀድሞ ስለ ድሉ ሥዕለት መሳሉንና ድል ቢደረግ ላይሸሽ እንደውም እንደ ናግራን ሰማዕታት ሊሰዋ ቃል መግባቱን ይገልጻሉ:: ድል አድርጎም ከተመለሰ በኋላም በአባ ጴንጤሌዮን አማካይነት አስኬማ ደፍቶ መመንኮሱንና ልጁ ገብረ መስቀል ሥልጣኑን እንዲይዝ ማድረጉን ይገልጻሉ::[12]

ከናግራን ዘመቻ መልስ በላስታና አካባቢው በርካታ ውቅር ቤተ ክርስቲያናትን እንዳሳነጸ ከየስፍራው ያገኘሁት ታሪክ ይናገራል:: ለምሳሌ ብልባላ ቅዱስ ቂርቆስ፣ ብልባላ ጊዮርጊስ፣ ማይ ማርያም፣ አርባእቱ እንስሳ፣ ሳርዛና ሚካኤልና ትኩርዛ ኪዳነ ምህረት የዐፄ ካሌብ አሻራዎች ናቸው:: ይኸ የዋሻ ውስጥ ቤተ መቅደስ ደግሞ ያልተወራለት ሌላው የዐፄ ካሌብ ቅርስ እንደሆነ እያደመጥሁ ነው::

የዋሻዋ መቅደስ ቅድስቷ ለብቻው በቅርቀሃ የታጠረ ቅጥር አለው:: ከፊት ያለው ገጽ በር ቢኖረውም መጋረጃ ለብሷል:: አባ መጋረጃውን ገለጹት:: የበሩ ቅርጽ የብልባላ ውቅር ቤተ ክርስቲያናት በሮችን ይመስላል::

"አቡነ ሆር ግብጻዊ ናቸው:: እዚህ አላረፉም:: ተመልሰው ሄደዋል:: ሌላኛው ግን አቡነ ገብረ ማርያም እዚህ ማኅሌቱ ላይ መቃብራቸው አለ::" አባ ገብረ ኢየሱስ ወደ ውስጥ ቀደም ብለው ገቡ:: ተከተልናቸው::

12. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ:: የኢትዮጵያ ታሪክ:: ገጽ 113

የዋሻው በራፍ ላይ መነኮሳት እህል ያበጥራሉ፡፡ በርከት ያሉ ጭቃ የተለሰኑ ጋኖችና ማድጋዎች ተኮልኩለዋል፡፡ አባ ወደ መነኮሳቱ ሄደው ጧፍና ክብሪት ይዘው መጡ፡፡ ጧፉን አደሉን፡፡ ለአንድ ሰው ከአምስት በላይ ነው የደረሰን፡፡ በዚያ ላይ በጣም ትልቁ ጧፍ ነው፡፡ አባ ለራሳቸው ቀጭንና ጧፉ አንድ ላይ ታስራበት የነበረች ጧፍ እጃቸው ላይ ቀረች፡፡ በቻርጅ የሚሰራ ባትሪ ግን ይዘዋል፡፡

ቀደም አሉና መሩን፤ ሰልፍ ሰርተን ተከተልናቸው፡፡ ወደ ምድሩ ሆድ እየገባን ነበር፡፡ የዋሻው በራፍ ሲርቅ ብርሃኑ ቀነሰ፡፡ ጧፉን ለኮሱልን፡፡ እሳቸው እስከ አሁን ብርሃን አላስፈለጋቸውም፡፡ አሁንም መምራታቸውን ቀጠሉ፡፡

ርቀን ገብተናል፡፡ የዕጣን ሽታ ይሸታል፡፡ ያስፈራል፡፡ ብዙ ሳንጓዝ ስልና የሚቋረጥ ባልጩት ድንጋይ የተጎዘጎዘበት ጎዳና ጠበቀን፡፡ ገና ሳንጀምረው እግሬ ተቆረጠ፡፡ እያነከስኩ የምረግጥበትን ለመምረጥ ሞከርኩ፤ ሁሉም ያው ነው፡፡ እንደ ቢላ የሚሸረክት፡፡

አባ ባትሪያቸውን አበሩና ዙሪያ ገባውን አሳዩን፡፡ በተፈለፈለ ዐለት ላይ አንድ ቆጥ አየሁ፡፡ ጨርቅ ለብሷል፡፡

"ድምጻችሁን ቀንሱ፤ ይኼ የአባቶች ቦታ ነው፡፡ ሱባዔ የገቡ አባቶች አሉ፡፡"

ፈራሁ፡፡ ዋሻው ውስጥ ብዙ ደቂቃዎች ተጉዘን የደርስንበት ቦታ በእጃችን ያለው ብርሃን ቢጠፋ ወደየትም የማይኬድበት ድቅድቅ ነው፡፡

መነኮሳት እዚህም እዚያም ሊያውም ባለ ደርብ የዐለት ፍልፍል ላይ ተሸሽገዋል፡፡ ከዓለም ብቻ ሳይኾን ከምድርም የራቁ፤ ምድር ሆድ ውስጥ ያሉ መናኞች፡፡

አባ ገብረ ኢየሱስ የሚተርኩል ደግሞ እዚህ ውስጥ ተኮኖ የሚሰማ አይደለም፡፡ የገዳሙ አባቶች ዋሻው ውስጥ ቤተ ክርስቲያናትን ለመስራትና መቅደስ ለመገንባት በታውን ሲያጸዱ በርካታ የአርኪዎሎጂ ቅሪቶችን አግኝተዋል፡፡ የሽከላ ውጤቶችን አይቻቸዋለሁ፡፡

"በዚህ ዋሻ ብዙ ሰዓት መጓዝ ይቻላል፡፡ ወደ ሌላ ስፍራ የሚያወጣም መንገድ አለው፡፡ ደግሞ የጥልቅ በርም አለው፡፡ አንድ ጊዜ እኔ ወደ ውሃው ገብቼ ትንሽ አይቼዋለሁ፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ልዩ ታይቶ የማይታወቅ አውሬ ወጣ፡፡ ተቆጥቶ፡፡ በዋሻው ያለ አውሬ በሙሉ እየጮኸ ከዋሻው ወጣ፡፡ ዋሻው በአራዊት ድምጽ ተናወጠ፡፡ አባቶች እዚሁ ሱባዔ ላይ ነበሩ፤ ተመልሶ ወደ ጥልቁ ነው የገባው ግን መልኩም ምኑም ታይቶ የማይታወቅ አውሬ ነው፡፡"

ፈራሁ፡፡ በአለሁበት ቆምኩ፡፡ ሁሉም ቆሙ፡፡ ከዚህ በኋላ አልሄድም አልኩ፡፡ ከእኔ የበለጠ መፍራታቸውን ያወቅሁት እንመለስ ሲሉ በአንድ ድምጽ ነበር፡፡ ፊታችንን አዞርን፡፡ የዋሻው በር ወዴት እንደሆነ አንዳችም ምልክት አይታይም፡፡ አባ ቀደም ብለው ዳግም መምራት ጀመሩ፡፡ ኋላዬንም ፊቴንም ፈራሁት፡፡ ከምድር ሆድ ውስጥ እስከወጣ የተባለው አውሬና አውሬውን የማይፈሩት የጨለማ ውስጥ መናኒያንን እያሰብኩ ነበር፡፡

# የዱር ሕይወት ዓለም፤

"እንደግ እንደ ዛፍ
ጥቁር አፈር ዐቅፎን
ጥቁር ብርሃን ውጦን
ሥራ ሥር አንቁለን
        አዝምተን እንደ ሐረግ፤
ውስጡን ዕመቃቁን
        ጉራንጉሩን ጠገግ፤
ጭረንና አሽተን
        እንደ ፋኖ ሶለግ፤
እንንቀስ አልሚውን
እንልቀም መልካሙን
        እንደ ልባም ሰው ወግ፡፡
ከፍ ብለን እንድናኝ
        አየሩን ልንመላ
ወደ ፊት ለመሮጥ እንሂድ ወደኋላ
እንደግ እንደ ዛፍ ዋርካ እንሁን ሾላ፡፡"
ደበበ ሰይፉ፡፡ የብርሃን ፍቅር

ወይና ደጋማ አየር ንብረት ያላት ከተማ ጠዋት ደጋ ትሆናለች፡፡ ተራሮችን እንደ ኩታ አጣፍቼም በርዶኛል፡፡ እንሰት ተክል ጉያ የተወሸቁ ጎጆዎች ከሩቅ ይታዩኛል፡፡

ደመና ድንኳን መስሎ ከተማዋ አናት ላይ የተጣለ መስሏል:: የድሮ ልቦለድ ጸሐፍት ሰማይ ምድሩን እንዲህ ይመስላል የሚሉለት አካባቢ የመጣሁ መሰለኝ:: ሁሌም እስኪረፍድ ከተማዋ እንዲህ ናት::

ከአዲስ አበባ በጅማ 465 ኪሎ ሜትር ተጉዤ እዚህ ደርሻለሁ:: አመያ ነኝ:: አመያ የኮንታዎች መዲና ናት:: አረንጓዴ ቀሚስ የለበሰች ከተማ፤ አቀማመጧ ትንግርት ኾኖብኛል:: ለቅንጡ ሎጂዎች ምቹ በሆነ መልከዓ ምድር ላይ፤ ደሳሳ የገበሬ ቤቶች ዘብ እንደቆመ ዋርድያ ተገትረዋል:: በጠዋት የተነሳሁት ወደ ጨበራ ልሄድ ነው:: ጨበራ የአንድ ቀበሌ ስም ነው:: ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ የሚባለው ድንቅ ምድር የሚገኝባት አንድ ክፍል::

የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ ዋና ጽ/ቤት መገኛም እዚሁ ጨበራ ቀበሌ ነው:: ጉዞዬ ከዚያ ይጀምራል:: ወደ ጥቅጥቁ ደን ለመግባት::

አዳነ ሰዓቱን አክብሮ በቀጠሯችን መሰረት መጣ:: በመኪናችን ተሳፍረን ከአመያ ወደ ጨበራ ቀበሌ ጉዞ ጀመርን:: ጨበራ መድረሱ ምን ፍለጋ? የሚያስብል ድንቅ መልከዓ ምድር እያየሁ ነው:: ኮንታ ድንቅ ምድር::

ኮንታ ከኢትዮጵያ ቀደምት የታሪክ አውዶች አንዱ ስፍራ ነው:: ኮንታዎች ከኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ታሪክ ተነጥለው የማይታዩ ህዝቦች ናቸው:: በርካታ አሳሾች ምድራቸውን ረግጠዋል:: ብዙ ጸሐፍት ስለ ኮንታ ጽፈዋል::

የማዕከላዊው መንግሥት አካል የነበረበትን ታሪክ በተመለከተ የንጉሡ ነገሥቱ ወዳጅ አሌክሳንደር ቡላቶቪች ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ደጃዝማች በነበሩበት ሰዓት ምኒልክን አስፈቅደው ስለመዝመታቸው ይነግረናል፡፡

ደጋግሜ ኮንታ መጥቻለሁ፤ አንድም ጊዜ ኮንታዎችን የማማርርበት አጋጣሚ ተፈጥሮብኝ አያውቅም፡፡ ኮንታዎች ለሰው ቅርብ ናቸው፡፡ ለተፈጥሮ ወዳጅ ናቸው፡፡ አገሩ ስስት አያውቅም፤ አፈሩ ቸር ነው፡፡ ለአዳም የተሰጠው የመጀመሪያ ምድር ምናልባትም ይሄን የሚመስል ድንግል ምድር ሳይሆን አይቀርም፡፡ ኮንታዎች ቸር ምድር ብቻ ሳይኾን ቸር መዳፍ አላቸው፡፡

ለግቤ አራት ግድብ ፕሮጀክት የተሰራው መንገድ የጨበራን ጉዞ ቀላል አድርጎታል፡፡ ግማሽ ሰዓት ሳይፈጅብን አስደናቂው የተፈጥሮ መስህብ በራፍ ላይ የምትገኘዋ ቀበሌ ደረስን፡፡ ይቺቺ ትንሽ ቀበሌ ከካፋ ጫፍ እስከ መሎ ከጨርጨራ እስከ ባርቦ ለተሰገሰገው ድንቅ የተፈጥሮ ሀብት ወደብ ናት፡፡
እኔ አየር ንብረቷን ወድጄዋለሁ፤ ቀላል እና ደስ የሚል ነው፡፡ ይከብዳል የሚሉም አሉ፡፡ የሚከብዳቸው ሙቀቱ መሰለኝ፡፡ ጨበራ የምትሞቅ ግና ሙቀቱ ሰውን የማይፈታተንባት ገነት ናት፡፡ በፍራፍሬዎቿ ልግስና የደከመውን የምትታደግ፣ በሙዝ ጣዕሟ ከትዝታ ጋር የምትኖር፣ በማንጎዎቿ ፍሬዎች የረገጠ የማይረሳት፡፡ አቡካዶ እንደ ወጥ የሚበላባት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በህዝብ ጥያቄ የተከለለውን ብሔራዊ ፓርክ ለቀናት ልቆይበት መጥቻለሁ፡፡ የዱር ሕይወት ደስ ይላል፡፡

የዳውሮ እና የኮንታ ህዝብ ስካውት ሆኖ ተፈጥሮን ለመታደግ ዘብ የቆመበት የተፈጥሮ ሀብት ውስጡ መግባት ሳያስፈልግ ከበራፉ የሚናገረው አንዳች ነገር አለ፡፡ ወደ ጫካው ሆድ ከመግባታችን በፊት ቁርስ ቀምሰን ቡና ጠጣን፡፡

አዳኒ ጸጋዬ የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ ዋርደን ነው፡፡ እነ ኡቴ እና እነ ጌታሁን፣ እነ በቀለ፣ እነ ደምሴ፣ ዱር ውለው ዱር የሚያድሩ የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ ስካውቶች ናቸው፡፡
እኛ ዱር ሕይወት ጠባቂዎችን ስካውት እንላቸዋለን፤ ብዙው ዓለም ሬንጀርስ በሚለው ይጠራቸዋል፡፡ የሬንጀሮቹ አለቃ በቀለ ስምሪቱ ሰጠ፡፡ ወደ ዝሆኖቹ ምድር ጉዞአችንን ጀመርን፡፡

ዳሩ መሃል የመሰለ ፓርክ ነው፡፡ ዝንጀሮ የሚያወዛውዘው ዛፍ ካልሆነ በስተቀር ድምጹ ሁሉ የወፍ ነው፡፡ የብዙ ዓይነት ወፍ፡፡ ተፈጥሮን መመልከት ብቻ እግር ያንቀራፍፋል፡፡ ሩቅ መንገድ ከፊታችን እየጠበቀን በየመንገዱ ያገኘን ይጠልፈናል፡፡ ፍል ውሃ ጠለፈን፡፡
የፍል ውሃው አካባቢው የተለየ ገጽታ አለው፡፡ ዙሪያው ገላጣ ነው፡፡ ዱር እንስሳቱ ሲመሽ መጥተው ሲነጋ የሚሄዱበት ቀን ብዙ ነው፡፡ በለስ የቀናው ጫካ ሳይገባ ዳርቻው ላይ ይሄንን ተአምር ይመለከታል፡፡ እዚህ ጫካ ከመግባት የበለጠ ተአምር እንደሌለ ስለማምን መጥፎ እድል እንደገጠመኝ አልወሰድኩትም፡፡ ይልቁንም የጎሽ መንገኛያው፣ የዝሆን መራጫው ፍል ውሃ ላይ ፊቴን ታጥቤ ተፈወስሁ፡፡

ከሩቅ የሚታየው ጥቅጥቅ ደን ነው:: የእድሜ ጠገብ ሀገር በቀል እጽዋት ቅርንጫፎች ምድርን ሸሽገዋል:: ሰማይ ከዛፍ ቅርንጫፍ የተሰራ ይመስላል:: እዚህ ብዙ ዓይነት ምድር አለ:: አንድ ፓርክ ነው፤ ከረዣዥሞቹ ሳሮች ስወጣ ግዙፍ ዘንባባዎች ይቀበሉኛል:: መንገድ አልሰለቸኝም:: የዝሆኖቹን ግዛት ተዳፍረናል::

እኩለ ቀን ኾኗል:: ብዙ መጥተናል:: ብዙ ዓይተናል:: እግሬ ይዝልና፤ ቀና ብዬ በዓይኔ ድንቅ ነገር ሳይበት መልሶ ይታዘዘኛል:: የእግር አለቃው ዓይን የሚኾንበት ዱር ውስጥ ነኝ::
አብረውኝ ያሉትን አላስተዋወቅኳችሁም:: የሚመራው ኡቴ ነው:: ለዱር የተፈጠረ ጀግና:: ጆሮውን ቀስሮ ያደምጣል:: ሰላም መሆኑን ሲያረጋግጥ ጉዞውን ያስቀጥላል:: አንዳንዴ ምድሩ ላይ ለጥ ብሎ ከርሱን በጆሮው ያደምጣል:: በሚሰማው ድምጽ መሬት እንደ ፊደል በሚያነበረው ጆሮው የዝሆኖቹ አቅጣጫ ወዴት እንደኾነ ይገምታል:: እግሩን ሰድዶ ይረግጣል:: ምድሩ ቻይ መኾኑን ሲያምን ረግጠን እንድንከተለው ያዛል:: እሱን እዚህ ዱር ውስጥ አለማድመጥ የሞት ጥሪን አቤት ማለት ነው:: ኡቴ አቴቦ የዱር ሕይወት ጀግናው::

ሌላው በቀለ ነው:: በቀለ የፓርኩ አንጋፋ ስካውት ነው:: እነ ኡቴን አሰልጥኖ ለዚህ ያበቃ የሙያ አባት ነው:: ዱርን እንደ እልፍኙ ያውቃታል:: ያለሁበት ዱር ብሔራዊ ፓርክ፣ ፓርክ ሆኖ የተከለለው በ1997 ዓ.ም. ነበር:: ያኔም ህዝቡ ጠይቆ ነው:: ዛሬም ህዝቡ ታድጎት ይኖራል::

1400 ካሬ ኪሎ ሜትር የሚሰፋውን ፓርከ ዱር ውሎ ዱር አድሮ ለማሰስ ውስጡ ገብቻለሁ:: ታላቁ የአሞ ሥነ ምህዳር ውስጥ ነኝ:: በመካከለኛው አሞ ሸለቆ፤

የሰው ልጅና ተፈጥሮ ዛሬ ጠበኞች ናቸው:: አስቀድሞ በሰውና በዱር እንስሳት የመነሻ ምዕራፍ በቋንቋ መግባባት ጭምር ነበር:: የዘፍጥረት መጽሐፍ የአባብና የሄዋንን ንግግር የሚነግረን በቋንቋ መግባባታቸውን ነው:: ዩቫል ኖኅ ሀራሪ ሰው ግብርና ከመጀመሩ በፊት ከዱር እንስሳቱ ጋር በቋንቋ ይነጋገር እንደነበር ጽፏል::[1]

ዛሬ እንዲኽ ያለው ቋንቋ የለም:: የተረት ያኽል ለምናብ የሚርቅ ሀሳብ ነው:: እንኳን ሰው ከዱር እንስሳ ጋር ይቅርና ሰው ከሰው ጋር ስለ ተፈጥሮ በአንድ ሀሳብ ማውራት አልቻለም:: እኛ ተፈጥሯችንን ያጠፋነው በቁጥር ስለበዛን ብቻ አይደለም:: ብልጥ መኾን ትልቁን ስፍራ ይይዛል:: ሰው እሳትን ካገኘ በኋላ ከእኔ በላይ ጀግና ማለቱን ብዙ ለተፈጥሮ ያደሉ ሊቃውንት ጽፈውታል:: እሳቱ የስልጣኔው መነሻ የመኾኑን ያኽል የመጨረሻው ምክንያትም እየኾነ መጣ:: ዛሬ ዓለም በአየር ንብረት ለውጥ ችግር ብዙ ስቃይ ውስጥ ገብታለች:: የመከራው አረንቋ ውጧትም ብልጡ ሰው ጣቱን ወደ ተፈጥሮ ቀስሮ ስለማውደም ያውጠነጥናል:: ኢትዮጵያ ቀደምት ህገረሰባዊ እውቀቷ ለተፈጥሮ ቤተሰብ ነው:: ነባር የህገ ልቦና እውቀቶች በእጅጉ ከተፈጥሮ ይቆራኛሉ::

1. Yuval Noah Harari,Homo Deus, page 77

ቅድመ ብሉይ ነበር የሚባለው የቅማንት ህገ ልቦና እምነት ድግና ለሚላቸው ደኖችና ጫካዎች ልዩ ስፍራ ይሰጣል፡፡[2] የኦሪት እምነት በብዙ መልኩ ከተፈጥሮ የታረቀ ነው፡፡ ለተፈጥሮ የሚሰጠው ስፍራም ይልቃል፡፡ ቅን ፈራጅ አንበሶች በጉድጓዳቸው የተጣለውን ጻዲቅ ተርበው እንኳን እንደማይበሉት የምናነብበት ታሪኮችን ይዘዋል፡፡

በኢትዮጵያ የክርስትና ትውፊት በገድላት ትረካዎችም ውስጥ በዓለም የአካባቢ ጥበቃ ታሪክ ለተፈጥሮ ቸር የመኾን መንፈስ የማይወዳደራቸው ሀሳቦች አሉ፡፡ ብዙ የዓለም የተፈጥሮ ተሟጋቾችና ለፍጥረት ይገደናል የሚሉ አዋቂዎች ከዓይን እንባን ለወፍ በማጠጣትና ዓይን የምትዘነቁልን ወፍ ባለመግደል የታየን ብቃት አይመሰክሩለትም፡፡ እኛ ግን አቡዬ ጣዲቁን ባሰብን ቁጥር እንዲህ ያሉ ታሪኮችን እናስታውሳለን፡፡

የቤተክርስቲያናት ግድግዳዎች በሰውና በዱር እንስሳት መካከል ጠብን ሳይኾን ህብረትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አባ ሳሙኤል በአንበሳ ታጅበው ሲጓዙ ማየት፣ አንበሳና ነብር ይጠብቋቸዋል የሚባሉ ቅዱሳንን ጸሎትና በረከት መለመን ሰው ከተፈጥሮ ተግባብቶ መኖር የሚችልበትን እሴት የሚያስተምር ነበር፡፡ ግን አልተማርንም፡፡

ጨበራ ጩርጩራ ዱር ውስጥ ነኝ፡፡ ከፊት ሁለት ሰው ቀድሞ ከኋላ አራት ሰው እያስከተልኩ እጓዛለሁ፡፡ ሲደክመን እናርፋለን፡፡ እንደ ሀገሬ ፓርኮች እዚህ ከብት አላይም፤ እስከአሁን የገጠመኝ አረኛም የለም፡፡

2. ባዮ በጋለ ላቀው፡፡ ቅማንት፡፡ አረማዊ-ኦሪታዊ ኢትዮጵያዊ ገበሬ፡፡ ገጽ 46

ከእኛ ውጪ ያለው የዱሩ ባለቤት ነው፡፡ የሚዘሉት ጦጣዎች፣ የሚዘምሩት ወፎች፣ የሚያተረማምሰው ጎሽ፣ የሚያጋሳው ጉማሬና አለሁ ብሎ ድምጹን የሚያሰማው ዝሆን፡፡

የካሜራ ባለሙያዬ እንረፍ አለ፡፡ አንድ ግዙፍ የዋንዛ ዛፍ ስር አረፍ አልን፡፡ ሰባት ሰዓት ያክል ተጉዘናል፡፡ እጆቻችን በሳር ስለት ተቆራርጠዋል፡፡ የሳሩ ጤዛ በጭቃ የታጠበ ልብስ የለበስን እስኪመስል ዳሌያችን ድረስ አርሶናል፡፡

የኢትዮጵያ ምድር እንዲኽ ነበር፡፡ ዛሬ እንዲኽ ያለው ድንቅ ስፍራ ይኼን መሳይ ጥቂት ቦታዎች የሚገኝ ተአምር ኾኗል፡፡ መጥረቢያ የኾነ ትውልድ ተተክቷል፡፡ አያቶቻችን ደጋ ይሉት የነበረው ምድር በአባቶች ወይና ደጋ የሚል ስም ወጥቶለታል፡፡ ድፍን ኢትዮጵያ ቆለኛ ሊኾን ነው፡፡ ሊያውም በሥነ ምህዳር መዛባት የተፈጠረ ጤናማ ያልኾነ ቆላ፡፡
ዱር እንስሳቱን ጨርሰናቸዋል፡፡ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል "የአውሬ አደን በኢትዮጵያ የጨዋ ልጆች ዋና ሙያ ኾኖ ከብርም ደረጃም ያስገኝ እንደነበር እኔም ከደረስኩ ተመልክቼዋለሁ፡፡" ይሉናል፤ በዝክረ ነገር ማስታወሻቸው፡፡ ዛሬ የሚታደን የለም፡፡ ማደኛው ተመንጥሯል፡፡ ትናንት ከነበረን ዛሬ የቀረን ስማችን ብቻ ነው፡፡
ዩቫል ኖኅ ሀራሪ ብልጡ ሳፒያንስ ይኽቺን ምድር እንደምን አድርጎ እጁ እንዳስገባት በመተረክ ወደር የሌለው ሰው ነው፡፡ በሆሞዲየስ መጽሐፉ የሰው ልጅ የሥነ-ምኅዳር ግንዛቤው እያነሰ የዱር እንስሳት ቁጥር በጣም እየቀነሰ ነው ይለናል፡፡[3]

3. *Yuval Noah Harari,Homo Deus, page 73*

አርኖ ሚሼል ዲባዲ የዚህ እውነት ማሳያ የእኛው ጉድ አንድ እማኝ ነው:: ሰውዬው ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ላይ አደረግሁት ብሎ በጻፈው የጉዞ ማስታወሻ በኢትዮጵያ ሙቀት በሚበዛባቸው አካባቢዎች ጎሽ አውራሪስ፣ ጉማሬና ዝሆን ማየት ብርቅ እንዳልነበረ ጽፏል::[4]

የሳፒያንስን ጥፋት በታዘበበት እይታው እንዲህ ያለውን ጉዞ ዩቫል ኖኅ ሀራሪ አነጻጽሮ አስፍሮታል:: በጀርመን አምስት ሚሊዮን ገደማ የቤት ውሾች አሉ:: ከሰው እጅ ምንም አንጠብቅም የሚሉት የዱር ውሾች ቁጥር ግን ሁለት መቶ ሺህ ብቻ ነው:: አርባ ሺህ አንበሶች በሚኖሩባት ምድር የቤት ድመቱ ቁጥር ስድስት መቶ ሚሊዮን ይኾናል:: የአፍሪቃ ጎሾች አንድ ሚሊዮን መሙላት አቅቷቸው 1.5 ቢሊዮን በሬዎች ከብልጣ ብልጡ ሳፒያንስ ጋር አብረው ይኖራሉ:: ለሃያ ቢሊዮን ዶሮዎች ያልጠበበችው ዓለም ለሃምሳ ሚሊዮን ፔንጉዌኖች ግን ፈተና ኾነች::[5]

መኖሪያቸውን ስናወድም እነሱ መጥፋታቸውን ብቻ መዝግበናል:: ከመጥፋታቸው ቀጥሎ መጥፋት ስለመቻላችን ግን አንድም ቀን አስበነው አናውቅም:: ብዙ የኢትዮጵያ አካባቢ አሁን ያለሁበትን ይመስል ነበር:: ዛሬ እንዲኽ ያለውን ተፈጥሮ መንጥረንዋል:: ዝናብ የለንም:: አፈር የለንም:: ምግብ ብርቋ የኾነች ሀገር ልናስረክብ ነው:: ምድራችን የኬሚካል ማዳበሪያ ሱስ ይዞታል::

4. አርኖ ሚሼል ዳባዲ:: በገነት አየለ አንበሴ:: የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ:: ገጽ 70
5. Yuval Noah Harari, Homo Deus, page 73

ተፈጥሮን መጠበቅ ቅንጦት የሚመስላቸው መንግሥታት ተፈራርቀውብናል:: ተፈጥሮን መጠበቅ ጠልቶ ከተፈጥሮ በሚገኝ ውሃ ግድብ እሞላለሁ ብሎ ገንዘቡን የሚያፈስ እብድ ትውልድ አባል ነኝ::
"ያዝ" ታምሩ እጁን ዘረጋ:: ከገባሁበት ሀሳብ አወጣኝ:: ጥሬ ሊያዘግነኝ ነው:: እጄን ሰድጄ ከእጁ መዳፍ ጥሬ ዘገንሁ:: እዚህ ቢደከምም አይከብድም:: ለዓይን ከሚርቁ ረግረጎችም የዘንባባ ደኖች ጥላ ስር የልብ ምታችን ከድካም በደስታ እስኪደልቅ ማረፍ ይቻላል::
አጠገባችን ካለች ምንጭ ውሃ ጠጣን:: የትም ጥም የሚቆርጡ ምንጮች ዳርቻ ማረፍ የሚቻልበት ገነት ውስጥ ነኝ:: እንደ ቧንቧ የሚጠጡ እንደ ከተማ ውሃ አተት በማይሰጋባቸው ወንዞች ገብቼ እጠጣለሁ፤ እታጠባለሁ:: ያለኹት ገነት ውስጥ ነው:: ዱር ገነት ነው::

ተነስተን ጉዞ ቀጠልን:: እንደ አጀማመራችን እየቀረጽን አይደለም:: ምኑ ተቀርጾ ምኑ ይተዋል? ስግብግብ ሆኛለሁ:: የሚያልቅ እየመሰለኝ አየሩን እምገዋለሁ:: ተፈጥሮው ንጹህ ነው:: እውነተኛ አየር የሚሳብበት ደን:: እጽዋቱ የመኪና ጢስ አያውቁም:: እዚህ በእግር መጓዝ የገነት ውስጥ ስደት ነው::
አዳነ አብሮኝ አለ፤ የፓርኩን ዋርደን ይዞ ዱር መግባት በዘመድ ቄስ የመፈታት ያህል ነው:: እኔ ሀገር የፓርክ ኃላፊ መሆን አበሳ ነው:: አዳነ ኮንታዎች ቅጥሩ ባይገቡበት ዳውሮዎች ፓርኩን ባይዘምቱበት ዝኖኖች የሚገድሉት፣ ጎሽ የሚያሳድደው ገበሬ ጉዳይ እንቅልፍ ይነሳዋል:: እንቅልፍ ስለማይተኙ የፓርክ ኃላፊዎች አሰብሁ::

"ኑ በዚህ" ኡቴ መራን፡፡ ተከተልነው፡፡ አንዲት ምንጭ ዳር በዓይናቸው አንዳች ነገር የሚፈልጉ ይመስል እስካውቶቹ ወዲህ ወዲያ ተቅበዘበዙ፤ ኡቴ በያዘው ቆንጨራ ምድሩን መታ መታ አደረገው፡፡ አዳነ ቀድሞ አረፍ አለ፡፡ ማረፊያችን እዚህ ነው፡፡ ምሳ የምንበላውም ትንሽ አረፍ የምንለውም እዚህ ነው፡፡ እኔ እንቅልፍ አልባ ስለኾኑ ዋርደኖች እያሰብሁ ስለነበር ያሰብሁትን በሞባይል ማስታወሻዬ አሰፈርሁት፡፡

"ሄኒ?"

"ወዬ"

"ምነው.."

"አዶ ቆይ አንድ ነገር እየጻፍኩ ነው" የጻፍኩትን አነበብኩት፡፡

"የሀገሬ ኑሮ መራራ ነው፡፡ ለመረረው አንዳች መፍትሔ የሌላት ሀገር ናት፡፡ መራራውን ሥራ ለሚሰሩ ጣፋጭ ፍቅር የሌላት፡፡ ከፓርኩ ኃላፊዎቿ ፊት ፈገግታ መፈለግ ከምድሯ ነዳጅ ማውጣት እስኪቀል መራር ኾናለች፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድም ቀን ሳትስቅ መሞት ከፈልግህ የፓርኩ ኃላፊ ሁን፡፡ ያኔ ሳቅ የለም፤ ጥርስህን ሳትገልጠው የባልደረባህን ሞት ትሰማለህ፤ በነጋታው ደግሞ ባልደረባህ የሞተለት ተፈጥሮ በቆሎ ለሚያለማ ከሀገሬ ገበሬ ለሚያንስ ባለሃብት ኢንቨስትመንት ተብሎ መመራቱ ዜና ይኾናል፡፡ የሀገርህ ከተሞች በተንቆጠቆጠ መኪና ማለፊያ አጥተው አንተ ጎማ መቀየሪያ ባጀት አጥሮህ መኪናህ ቆሞ በፈረስ ሶስት ቀን ስትሄድ ያኔ ሳቅ የገነት በር ያኽል ይርቅሃል፡፡ አዋሽ ሂድ፡፡ ሽፈራሁ የሚባል ሰውዬ ሳላ መዋያ ላይ ቆሞ፤ ከከብት ተፋጦ፤ ዓይኑ እንባ አቅርሮ ታገኘዋለህ፡፡ ሀላይደጌ አሰቦት ስትደርስ መቆያ እንባ አቅርሮ ይስቅልሃል፡፡ ነጭ ሳር ግባ ሽመልስ እንኳን ሳቅ ሊያምረው በወጉም ተኝቶ አድሮ አያውቅም፡፡

ባንኪ አብያታን በእንባ አልሸኝም ብሎ እያለቀሰ ነው:: እስቻለው ባሌ ዳደኛውን ቀብሮ ዛሬም እሳት ከመታገል በእሳት ጢስ ከማንባት አላረፈም:: ኤፍሬም አልጣሽን ከፈላታ ለማስጣል ሀገር አብሮት አልቆም ቢል ስለሚያለቅሰው እንባ መጻፍ ይቻል ይሆን?

ቃፍታ ሲነድ አብረው ስለነደዱት ገሬና ዘነበ ወይስ አሞ ስኳር ታሞበት አብሮ ስለታመመው ሄኖክ እኔ አይደለሁም:: ወይስ ዛሬም ከሞት ጋር ስለተፋጠጠው ኑሩ፤ እንደ ወላጅ በእንባው ዝ·ኖን የሚቀብረው የባቢሌው አደም፤ ማን ነው ስቆ የሚያውቅ? አንዱም የፓርክ ኃላፊ ስቆ አያውቅም:: ሳሚ አንዱን ሲለው አንዱ አልሞላ እያለው ገራሌ ሲኖር እንደምን ሳቅ ሊያምረው፤ ደስታስ በዱር እንስሳቱ ውሃ ጥም ደስታ የራቀው ሰው አይደል? እዚህ ሀገር የክልል ፓርክም ብትመራ ያው ነው:: እንባውን በቀልድ የሚሸፍነው ጋናቡል ብቻውን ለዚህ በቂ ነው:: እንዲህ ናት የኔ ሀገር፤ ዝናቧን ከሰማይዋ ለማባረር ደፋ ቀና ማለት ከጀመረች ዓመታት ያስቆጠረች::"

/ይኼን ጽሁፍ ከጻፍኩ ከዓመት በኋላ ዱር እንስሳት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተሩ ቢሮ ተቀምጬ አንድ ሰው መሰሰ ብሎ ገባ:: የማውቀው መስሎኛል:: የጠፋኝ የማውቀው ሰው ነው:: አበባው ይባላል፤ የስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ኃላፊ ነው:: ጠቁሯል:: ከል ለብሶ ሲገባ የማውቀው ሰው ጠፋኝ፤ ስሜን ተቃጥሎበት እንቅፍል አጥቶ ነው የከረመው:: እንዲህ ናት የኔ ሀገር፤ እንቅልፍ ስለማይተኙት ዋርደኖች ጨበራ ደን ውስጥ ኾኜ የጻፍኩትን አስታወሰኝ፤ ጽሑፍን በማኅበራዊ ሚዲያ ስለማጋራት አሰብሁ::/

# ዋርደንነት በምድር ያልተረገመው ብቸኛ ሥራ፤

ይኸ ዱር ስሙ በዝኆን ይግነን እንጂ 57 የሚሆኑ አጥቢ የዱር እንስሳት መኖሪያ ነው። ከእነዚህ 39 የሚደርሱት እንደ ዝኆንና ጎሽ ያሉ ትላልቅና መካከለኛ አጥቢ እንስሳት ናቸው። አስራ ስምንቱ ደግሞ ትናንሽ፤ ሳሩ ሲያልቅ ደን ይኾናል፤ ደኑ ሲያልቅ ቁጥቋጦ።

"እዴ የገረመኝ የዛፉ ዓይነት ነው።"

"ቀላል መሰለህ እንዴ 106 የሚደርስ የእጽዋት ዝርያ አለ። እይ እንግዲህ ስድስቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ናቸው።"

"ይገርማል" አልኩት፤

"ሌላውን ተወው ዘሩ ያልተቀላቀለ የዝንጅብል፣ የቡና፣ የኮረሪማ፣ የእንሰት፣ የእጣን፣ የጌሾ ዝርያ እኮ ቁጥር የለውም። የዘር ባንክ ነው።"

በአዳነ ቀናሁበት:: ዋርደንነት ያልተረገመ ሥራ ነው:: በምድር ያለው ሥራ ሁሉ የተረገመ ነው:: እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደአሰባቸው የሚኖሩት እውነተኛ አገልጋዮችና ዋርደኖች ይመስሉኛል:: እንዳወቅ የተባለ ዱር እንስሳት ባለሙያ የመጀመሪያው ዋርደን አዳም ነበር እንደሚል ከነገሩኝ በኋላ ስለ ተፈጥሮ ጥበቃ ስራ ማሰብ ጀምሬአለሁ:: ታላቁ መጽሐፍ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 19 "እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ኹሉ ደግሞ ከምድር ፈጠረ፤ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው" ሲል በዘፍጥረት መጽሐፍ የሚገልጸው አዳም አስቀድሞ ከተፈጥሮው የተስማማ ከፍጥረት የሚቀራረብ፣ የማደን ጠባይን ያልተማረ መኾኑን ነው::

ዩቫል ኖኅ ሀራሪ እንዲህ ያለውን ሀሳብ የሚጋር የዓለም ሊቅ ነው:: ሰውዬው አዳም በገነት አጽድ ውስጥ ሳለ ከአካባቢው ተስማምቶ የሚኖር ነበር ከዚያ ሲባረር ከተፈጥሮ ተጋጨ ይለናል::[6]

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በኦሪት ዘፍጥረት ትምህርቱ "አስቀድሞ ክብሩን ሰጠን፤ ከዚያም መልሶ ወሰደውና የምድር አራዊቶችን እንድንፈራቸው አደረገን::" ይላል፤[7]

ከቀናት በፊት በጨበራ ጩርጩራ የሦስተኛ ዲግሪውን ጥናት ሊሰራ ከመጣው ተመስጌን ጋር ስለዚሁ ጉዳይ አውግተን ነበር:: ሀሳቤን ሳስረዳው ያመነበት መሰሎኛል::

6. *Yuval Noah Harari,Homo Deus, page 73*

7. *ገብረ እግዚአብሔር ኪደ:: ዮሐንስ አፈወርቅ:: የኦሪት ዘፍጥረት ትርጓሜ:: ገጽ 165*

በምድር የእርግማን ውጤት ያልኾነ ሥራ የቱ ነው? ሰው ለምን ገበሬ ሆነ? ተረግሞ። ለምንስ ሐኪም መሆን አስፈለገው በሐጢአቱ ምክንያት ለበሽታ ተዳርጎ። ደግሞ ሰው ልብስ መስራት ውስጥ የገባው በሐጢአት ጸጋው ተገፎ ራቁቱን ቀርቶ ነው፤ ብዬ አምናለሁ፤ ውትድርናና፣ ሹፍርናና፣ ምህንድስና ስንቱን ዘርዝሮ መግለጽ ይቻላል? ሰው መጀመሪያ ሲፈጠር ፈጣሪውን እያመሰገነ ገነትን እየተንከባከበ እንዲኖር ታስቦ ነው። ከእርግማኑ በፊት የነበሩት የሰው ልጅ ተግባራት ፈጣሪን ማመስገንና የገነትን ተፈጥሮ መንከባከብ የአራዊቱ አለቃ መሆን ነበር። እንዲህ ያለው ሥራ ከእርግማን በኋላ የቀረው ዋርደን ጋር ነው። ስካውት ጋር ነው።

"ታድለሃል፤" አልኩት አዳነን። ያልተረገመ ስራ መስራት መታደል ነው። አዳም ጸጋው ባይገፈፍ መች ጋዜጠኝነትስ ስራ ይኾን ነበር? ድብልቅ ያለ የአእዋፍ ድምጽ ተሰማ፤ በምለው የተስማሙ መሰለኝ።
እዚህ ዱር 137 የሚደርሱ የአእዋፍ ዝርያዎች አሉ፤ ከእነዚህ ስድስቱ ሌላው ዓለም የሉም። ሌላው ዓለም ከሌሉ ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ጸጋዎቻችን ናቸው።

"ምን የኛን ኑሮ ታውቀው የለ? ያ አንተ የጻፍከው ደብዳቤ እኮ ነው። የፍቅሩ ደብዳቤ፤ አመጣህልኝ?" ዞሮ ተመለከተኝ። እራሴን ነቅንቄ አዎ አልኩት። ሞባይሉን አወጣ።
"ቆይ አንዱ ዛፍ ስር አረፍ እንበልና ላንብብልህ" አልኩት፤ ከመስጠቴ በፊት ላነብለት ፈልጌ ነው። በዚያው ማረፊያ ምክንያት ይኾነናል።

እንደ ቸኮለ የገባኝ ወዲያ በዓይኑ መርጦ እንዷ ዛፍ ጥላ ስር አረፍ ሲል ነው። ሞባይሌን እየበረበርሁ ተከተልኩት። ሌሎቹ ምን ፈልገን እንደኾነ አልገባቸውም። ማንበብ ጀመርሁ።

"የስካውቱ የፍቅር ደብዳቤ
እጅግ ለምትናፍቂኝ
ለጤናሽ እንደምን አለሽ? እኔ ካንቺ ሀሳብና ናፍቆት፣ ከምኖርበት ሜካ ውብት በስተቀር ደህና ነኝ።
አንቺስ ለጤናሽ እንዴት ነሽ?
እዚህ ሆኜ ሳስበው ናፍቆት ብቻ ሳይሆን ስጋትም ሊገድለኝ ነው። የህገ ወጦች ዓይን ዳሌሽ ላይ የሰፈረ ይመስለኛል። አንቺ የኔ ጥብቅ ስፍራ ነሽ። በናፍቆትሽ ምክንያት ፓትሮል ወጥቶን እንደ አረጀ ዋሊያ ተገንጥዬ እተከዛለሁ። ምነው? ብለው ጓደኞቼ ሲስቁ እንደ ቆሰለ ጎሽ ያዙኝ ልቀቁኝ በል ያሰኙኛል። እንዲህ የሚያደርገኝ ናፍቆትሽ ነው።
እንዲህ እየናፈቅሁሽ ግን አንቺ ግድ የለሽም። ዋናው መስሪያ ቤት ሆነሽብኛል። የምጽፈው ደብዳቤ እንኳን ቶሎ ምላሽ አያገኝም። እኔን ተይኝ እጣ ፈንታዬ ነው። አድርግ ያልሺኝን አደርጋለሁ። እንደ ዝሆን መንጋ በሴት የምመራ የሆንኩት ያየሁሽ ቀን ነው።
የኔ ናፍቆት፣ ትናፍቂኛለሽ። እንደ ደመወዝ፣ እንደ ደረጃ እድገት ትናፍቂኛለሽ።
አብረን ያሳለፍነውን ሳስብ ልቤ እንደ ሳላ ትቦርቃለች። አብረን ያደመጥናቸውን ሙዚቃዎች የምረሳቸው የአእዋፍ ዜማ ልቤን ቢያጠፋው ነውና አትፍረጂብኝ። እንደ ኢንሾ ብቻዬን እስከሞት እኖራለሁ እንጂ ካንቺ ተለየሁ ብዬ ሌላ አልጠጋም።

አየሽ አንቺ ለኔ ከሁሉ ነገር ነጻ እንደኾነ ፓርክ ነሽ፡፡ ከሰል አከሳይ እንደሌለበት፣ ህገ ወጥ እንደማያድንበት፣ ሰፈራ እንዳልገባበት ፓርክ ነሽ፡፡ የኔ ብቻ፡፡
ሳልነግርሽ፡፡ ባለፈው የላከሽልኝ ደብዳቤ እንደ አምባራይሌ ሜዳ እስኪጠበኝ አስሮጠኝ አስፈነደቀኝ፡፡ ያን ቀን እንደ ቆርኪ ቀንድ አወጣሁ ብልሽስ፤ አቤት ደስታ!!
ደብዳቤሽን ከፍቼ ሳነበው የተሰማኝ ደስታ እስከአሁን አልለቀቀኝም፡፡ ቀዩን ፖስታ እቅፍ አድርጌ ሳምኩት፡፡ ደረቴ ላይ ለጥፌው ላየኝ ሰው መቼም ጭላዳ ነው የምመስለው፡፡ ደስታዬ እንዲህ ቀላል መስሎሽ ነው? እዚህ ያሉት በሙሉ ተገረሙ፡፡ ግማሹ ላጤ አይደል? ምን የዚህ ሀገር እናት እኮ እንደ ቀይ ቀበሮ መጥና ነው የምትወልደው፡፡ ምነው? ብትያት ምን አበላችኋለሁ ብዬ ትላለች፡፡ እንዲህ ኾኖ ታዲያ እንኳን ለእኛ ለሀገሬው የሚተርፍ ሚስት ይኖራል ብለሽ?
የላጤነት ህይወት ከባድ ነው፡፡ እኔስ አንድያውን ተስፋ ኖሮኝ ነው፡፡ ተስፋ ለሌለው ሰው እንደ አብያታ ሐይቅ ከቀን ቀን መድረቅ ነው፡፡ ቀን ሲዞሩ ውሎ ማታ ጥሩ ምግብ ያላገኘ ሰው እድሜውን ተስፋ ሲያጣ ምን ይሰማው?
ባገኘሽው የደረጃ እድገት ደስ ብሎኛል፡፡ ገና ጥሳ ሁለት ትደርሻለሽ፡፡ እድልሽ ሰፊ ነው፡፡ የኔም ጸሎት አለ፡፡ አንድ ፊቱን ጉሬዛ ሆኜልሻለሁ፡፡ አርብ እሮብ ያለ ዘጠኝ መች እህል ቀምሼ፡፡
ዛሬ ደክሞኛል፡፡ ሩቅ ተጉዘን ነው የመጣነው፡፡ በዚያ ላይ እንደ መሣሪያዬ ትዝታሽን በትከሻዬ ይዤ ነው የተጓዝኩት፡፡ ነገ ፋታ ካገኘሁ ሌላ ደብዳቤ ጽፌ እሰድልሻለሁ፡፡ እስከዚያው በጣም ነው የናፈቅሽኝ በጣም፡፡ ቻው የኔ ውድ፤"
አዳነ ረዥም ሳቅ ሳቀ፡፡

"ላከው ላከው በዜንደር ላከው" አለኝ::
"ከፈት" አልኩት:: ተቀባበልነው::
ከአረፍንበት ሥፍራ ተነሳን:: ኡቴ ከጀርባችን ካለች ምንጭ ውሃ በኩዳው ይዞ መጣ:: ሕይወት ያለው እዚህ ነው:: ጥምን ለቀናት የሚቆርጡ ንጹህ አፍላጋት የሚገማሸሩበት፣ በድምጻቸው የሚያንበረክኩ የፏፏቴ ድምጾች ትዝታ ሆነው የሚቀሩበት፤ 1400 ካሬ ኪሎ ሜትር የሚሰፋው ይህ ፓርክ የሐይቅ ሀብታም ነው:: ሾሺማ ወንዝን ይመስል ይህን ድንቅ ፓርክ እየተሽከረከርነው ነው:: ሾሺማ ጨበራ ጨርጨራን የሚርመሰመስ፣ የፓርኩ ህይወት ለመሆን የበቃ ዋናው ወንዝ ነው:: ከ49 በላይ ከፓርኩ የሚፈሱ ወንዞች አሞ ገብተው መብራት የሚሆኑበት ድንቅ ምድር ነው::

16 ኪሎ ሜትር ያክል በእግር ተጉዘን ቡሎ ሃይቅ ደረስን:: የጨበራ ውበት ከሚባሉት አንዱ ቡሎ ነው:: ትናንሽ ኮረብታዎችን አልፈናል:: ረግኸርም የሳር ደኖችን ጥሰን መጥተናል:: ከአምስቱ የጨበራ ሐይቆች አንዱ አፋፍ ላይ አረፍ ብለን አዳነን እያደመጥን ነው::
"ይሄ ቡሎ ይባላል:: ባሂ የሚባል አለ፤ ትልቅ ነው:: ሺታ ደግሞ ብታየው የሚገርም ሐይቅ ነው::"
"ሁሉም እንዲህ አድካሚ ናቸው?" እዚህ መድረስ ጉልበት ይፈልጋል::
"ከረቤላ መንገድ ላይ ነው:: በእግር አስር ደቂቃ ብትሄድ ነው፤" አስር ደቂቃው በአዳነ እና በእኔ ምንዛሪው ይለያያል::
"ዓሳ የለውም?"
"ዓሳ ብርቅዬ ሁሉ አለ:: እዚህ የተገኘው የዓሳ ዝርያ ጥናት ተደርጎ ብርቅዬ መኾኑ ተረጋግጧል::"

"በሳይንስ ተረጋግጧል:: ማለቴ ያለቀለት መረጃ ነው?"
"ታዲያስ ስም ሁሉ ተሰይሟል:: ሳይንሳዊ ስሙ ጋራ ጨበራ (Gara chebra) ነው::"

ሐይቁ ላይ የሚዋኙት ጉማሬዎች ውሃውን ሽቅብ ሲተፉት የሚያሰማው ድምጽና የጉማሬዎቹ የዋና ትዕይንት ጥቂት ደቂቃ ዝምታ ውስጥ ከተተን:: ዓይኖቻችንን ወደ ሐይቁ ሰደን በየግላችን ከቡሎ ሐይቅ ጋር አወጋን:: ዮናታን የሚመለከተውን ምስል በካሜራ ለማስቀረት ደፋ ቀና እያለ ነው::
አዳነ እጁ ላይ የያዛትን እንጨት ሀሳብ ውስጥ ገብቶ ሰባበራት:: የመጨረሻዋን እየወረወረ "እዚህ ጉማሬ ነው:: ባሂ ደግሞ ብትሄድ ወፍ ታያለህ፤" የለበሰውን ሬንጀር ኮት ቁልፍ መፍታት ጀመረ፤
"ተወው እንጂ፤ ገና እኮ ኢንተርቪው አለን፤" ልብሱን እንዳያወልቀው ፈልጌአለሁ::
"አሁን ደግሞ በሌላ ልብስ እንቅረጽ፤ አባቴ ሲመለከተው እኮ ልጄ ሳይነግረኝ ወታደር ሆነ ይላል:: ስለ ስካውት ስለ ዋርደን ልብስ ማን ያውቅልሃል?"
እውነቱን ነው:: እንዲኽ ለኢትዮጵያ ተፈጥሮ ዱር ውሎ ዱር የሚያድረው ባለውለታ በዚህች ሀገር ስሙ አይነሳም:: ክብሩ አይወራም:: ስራው ገና አልተነገረም:: የአፈ ቀላጤዎች ሀገር ናት:: የሚያወሩት የሚቀድሙባት ሀገር ናት:: ዝናብ ጠብቃ የምታርሰው ሀገር የተፈጥሮ ዘቧን ገና አልተዋወቀችውም::
ከቡሎ ሐይቅ የሚመጣው ነፋስ በረታ:: ገና ጎጆ ቀልሰን አዳሪዎች ስለኾነን እዚህ የሚኖረንን ቆይታ አሳጥረን ወደ ማረፊያችን ስፍራ ለመሄድ ተስማማን::

ኡቴ በርቱ ብሎ ተነሳ። ታምሩ ኮተታችንን ሸከፈ። ወደ ባርበ እናት ጉዞው ጀመረ። ከቡሉ ሐይቅ ስንመለስ የነበረው መንገድ የሚጻፍ አይደለም። ሁለት ጊዜ ማለፊያውን ስተንዋል። ሩቅ ማየት አንችልም። አጠገባችን ከሚጓዘው ሳይቀር ረዥሙ ሳር አለያይቶናል። በተቻለ መጠን ላለመራራቅ እየሞከርን ነው። አንዱ ስንጥቆት ያለፈውን ሳር ሲለቀው ሌላውን ስለሚመታ ብዙ መጠጋጋቱ አልመረጥነውም።

ጸሐይ ገብታለች። የብርሃኗ እንጥፍጣፊ ሰማዩን ገና አስመስሎታል። ማደሪያችን ጋር ሳንደርስ እንዳይጨልም ሰግቻለሁ። ኪሴን ዳበስሁ፤ ባትሪዬ አለች። አወጣሁና ሞከርኳት። በባትሪ ብርሃን ማንጋት የማይችሉበት ስፍራ ለማደር አለመሞከር ብቻ ነው መፍትሄው። ጠደፍ ጠደፍ እያልን ነው። ድምጽ ተሰማኝ። የፈራሁት ስፍራ እየደረስን ነው። አስራ አራት ኪሎ ሜትር በእግር ተጉዘናል።

ኡቴ ቆም አለና ጆሮውን ቀሰረ። እግራችንን ባለንበት እንድናሳርፍ በምልክት አዘዘን ታዘዝን።

"ትሰማላችሁ?" አለ ኡቴ። ስለጎሽ እያሰብሁ ነው። መልስ የሰጠው የለም። "ባርበ ፏፏቴ እኮ ነው። ደርሰናል።" አለን። እውነትም፤ የባርበ ፏፏቴ ዜማ መድረሳችንን አበሰረን። ድምጹ መቅረብ ጀመረ።

ባርበ ደረስን። የሰው ድምጽ ይሰማል። ስንጠጋ ሰካውቶች ናቸው። የምናድርበትን ቦታ እያዘጋጁ ነበር።

ከሰማይ ተወርውሮ ምድር የሚያርፈው የውሃ ድምጽ መንገድ ለጠፋው እየመራ ባርቦ ያመጣል:: እንዲህ ነው የመጣነው፤ ስንደርስ የጨበራ ጨርጨሬ ሌላ ውበት ፍንትው አለ:: ድምጹን ሰብሮ የሚያሸንፍ ውበት፤ ወደ ፏፏቴው ስር ቀስ ብለን ወረድን:: እኔ ነግቶ በብርሃን አይቼው ብዬ ተመኘሁ::

አሁን ረዥሙ ፏፏቴ ስር ነን:: ጨበራ ጨርጨሬን አንድ ፓርክ ማለት፤ በአንድ ስም መጥራት፣ እንደ ቻሉት መግለጽ ከባድ መኾኑን አምኜአለሁ:: ውሃ በውበቱም በድምጹም የሚያንበረከክበት ፏፏቴ አናት ማደሪያችንን የሚያዘጋጁ ሁለት ስካውቶች ቁጥቋጦውን በቆንጨራ እየጠረጉ ነው:: ከአለንበት እስከ ብሔራዊ ፓርኩ መውጫ ቢያንስ ሃያ ኪሎ ሜትር በእግር መጓዝ ይፈልጋል:: መሽቷል:: የተሻለው ለማደሪያ የተመረጠ ስፍራ ይህ የፏፏቴ ዳርቻ ነው:: መንገድ አድክሞናል ያላሉት እነ ኡቴም ወዲያው ጓዶቻቸውን ተቀላቀሉ::

ኡቴ ባላ እንጨት ይዞ መጣ:: ታምሩ ሳር ታቅፏል:: ጌታሁን ዛፉ ስር ጎጆውን መቀለስ ጀምሯል:: አስቀድመው ከደረሱት ስካውቶች አንዱ አሁንም ምድሩን በቆንጨራ መጥረጉን ቀጥሏል:: አንዱ የማገዶ እንጨት እየለቀመ ይቆልላል:: በአጭር ጊዜ የዱር ጎጆ ሰራን:: ለማመን አቃተኝ:: ታምሩ የታቀፈው ሳር ለፍራሽነት የተፈለገ መሆኑ የገባኝ ሲደለደል ነው:: ድንኳን ስላልያዝን ደጋግሜ ስጋቴን ስገልጽ "ግድ የለም" በሚል፤ ሀሳብ እንዳይኾንብኝ ሲነግሩኝ ቆይተዋል:: እውነትም ዱር ውስጥ እንዲህ ማደር ይቻል ኖሯል::

ጣሪያው ቅጠል ነው፡፡ አልጋው መሬት፤ ፍራሹ ደግሞ ሳር፡፡ የጎጆአችን ግድግዳ በሦስት አቅጣጫ ጫካው ነው፡፡ ጀርባችንን ለፏፏቴው ገደል ሰጥተናል፡፡ የቆሰለ ጎሽ ዓይነት ቁጣ ያሳበጠው እንሰሳ ከመጣ ወደ ገደሉ ለመሸሽ ምቹ ቦታ መርጠናል፡፡ የሚያሰጋው እባብና ዘንዶ ነው፡፡

እሳቱ ተለኮሰ፡፡ ከበን ተቀመጥንና የቋጠርናትን ቂጣ በጎመን ተቃመስን፡፡ የዱር እራት ይጣፍጣል፡፡ እኔና ካሜራ ባለሙያው ዮናታንን አምስት ስካውቶችና የፓርኩ ኃላፊ አጅበውናል፡፡ አጠቃላይ ስምንት ነን፡፡ ሁላችንም ደክሞናል፡፡ እሳቱንም ኾነ ምሽቱን አላጣጣምነውም፡፡ የፏፏቴው ድምጽ እሹሩሩ ብላ ልጇን እንደምታስተኛ እናት አስተኛን፡፡
እንዲህ ያለውን አዳር የደገምኩት፤ ጉድሙ ነው፡፡ ጮፎረ ዳርቻ፡፡

# ጮፎሬ- በጬርጬራ ሰማይ

ወደ ናፈቀኝ ውበት እየሄድሁ ነው፡፡ የማያውቁት ሀገር ሲናፍቅ ያየሁ እንግዳ ነኝ፡፡ እዚህ የማላውቀውን ውበት ጉንጭ ልስም የመጣሁ የተፈጥሮ ዘመድ ነኝ፡፡ ተራራና ሰማይ የሚሰራቸውን ሲያሳጣቸው እየሁ፡፡ እየሁን መጻፍ ዋዛ እንዳልሆነ የደረስሁበት ምድር ምስክር ነው፡፡

ዳውሮ ነኝ፡፡ ንጉሥ ሀላላ ምድር፡፡ ስለ ሀላላ ሳስብ የገዳቸው ማማር፤ የስማቸው መግነን፤ ጎልቶ ይሰማኛል፡፡ ዳውሮ የኮንታ ወንድም ነው፡፡ ኮንታ እንዳየሁት ያለ ከተፈጥሮ ታርቆ የመኖርን ባህል እዚህም አያለሁ፡፡ ሁለት ስም፤ ሁለት ህዝብ፤ አንድ ጠባይ፡፡ ተፈጥሮን እንደ ራስ መውደድ፡፡

ከአመታት በፊት ደጋግሜ መጥቻለሁ፡፡ የሀላላ ግንብን ዜና ሳበስር ይኼንን ያክል ረዥም ግንብ ለረዥም አመት ተደብቆ መኖሩ ካስገረማቸው ሰዎች ይልቅ ውሸታምነቴን የተቀበሉት ብዙ ነበሩ፡፡ ጥርጣሬው ሲደጋገም ደጋግሜ ስላየሁት የግንብ ቅጥር ራሴም ተጠራጠርኩ፡፡

እርግጥ እንዲህ ያለ ግዙፍ ታሪክ አደባባይ አፍጥጦ ከታሪክ ጸሐፊዎችና ከኢትዮጵያን ገላጮች "ለምን ተደብቆ ኖረ?" ለሚል ጠያቂ አሁን ላምን አልችልም ከማለት ውጪ አማራጭ የለውም::

ሀላላ ኬላ እንደ ዐፄ ፋሲል ቅጥሩ በስመ ጥሩ ንጉሥ ይጠራ እንጂ ታሪኩ እሳቸውን ከቀደመ ዘመን የሚጀምር ነው:: የዳውሮዎች ታሪክ በሀላላ ስም የሚጠራው ረዥም ካብ በጥንት የዳውሮ ነገሥታት የተወጠነ እና የተጀመረ እንደሆነ ይገልጻሉ:: ዋናዎቹ ካዎ ማሆ፣ ካዎ ኡባኖ፣ ካዎ ዲኖና ጋዎ ጃኖ ግንባታውን እንዳስጀመረ ይናገራሉ::

የጽሑፍ ሰነዶች ደግሞ ከ1582 እስከ 1607 ዓ.ም. ባለው ዘመን የተሰራ እንደሆነ አስፍረዋል::[8] ይህ ከኾነ ይህ ዘመን የአፍሪካ ካሚሎት የተባልንበትና አንድ ቅጥር በርከት ያሉ አብያተ መንግስታትን ለመረከብ የመጀመሪያው የተሰራበት የጎንደር ኪነ ህንጻ ዘመን ነው:: በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ሌላ ክፍል ሌላ የግንባታ ታሪክ እውን ሆነ::

175 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የሐላላ ካብ ከሦስት እስከ ሰባት ዙር በረድፍ የተገነባ በግቤና በጎጀብ የተከበበውን ህዝብና ምድር ከጥቃት ለመታደግ የተቀጠረ ግንብ ነው:: አማካይ ቁመቱ ዝቅ ሲል 2.5 ሜትር ሲረዝም ደግሞ እስከ 3.8 ሜትር ይደርሳል:: ሰባት የሚደርሱ የጦር በር ማማዎች ያሉት ሲሆን የመጨረሻውና ለመጨረሻ ጊዜ አጠናቀው የሰሩት ካቲ ሐላላ 25 ዓመታትን ጊዜ ወስደው በመገንባት ያጠናቀቁት፤ የዳውሮ ነገሥታት ተቀባብለው የየራሳቸውን አሻራ አኑረው የሰሩት ቅርስ ነው::

8. ወንድሙ ለማ እና ሙሉጌታ በዛብህ:: የዳውሮ ሕዝብ ታሪክ:: ገጽ 118

እየሄድሁ ያለሁት ወደ ተፈጥሮው ሀይቅ ነው፡፡ የተነሳነው ከኢሠራ ነው፡፡ ኢሠራ ከዳውሮ ዞን ወረዳዎች አንዱ ሲሆን የጩርጩራ ቀበሌ መገኛ ነው፡፡ ጨበራ ጩርጩራን ለማየት በዚህ መግባት ጨርሼ አይቼዋለሁ ለማለት ወደሚያስደፍር ጉልበት ያደርሳል፡፡ ስመለስ ከቻልኩ የኢሰራ ባሌ ሚካኤልን እጎበኛለሁ፡፡ በዐፄ ናኦድ ዘመን የተመሰረተ ጥንታዊ ደብር መሆኑን እንብቤያለሁ፡፡[9]

አንድ ቀን ዳውሮን በስፋት አስሰው ይሆናል፡፡ ዳውሮ እንደ የም ከጎንደር የሚዛመድ ህዝብ ነው፡፡ የሞች የቀደመ ሥርወ መንግሥታቸውን አስመልክቶ ሲገልጹ የሞዋ ሥርወ መንግሥት ምንም እንኳን መነሻውን የመን ደቡብ አረቢያ ቢያደርግም፤ ከጎንደር ተዛምዶ ግቤን በመሻገር ወደ የም መምጣቱን ያስረዳሉ፡፡[10]

ከኢሰራ በመኪና መጣን፤ ከጉድሙ ፓርኩ ድረስ በሞተር ሳይክል ጀርባ ጋልበን እዚህ ደረስን፡፡ አሁን በዱር ውስጥ መሄድ ከጀመርን አንድ ሰዓት ተቆጠረ፡፡ የምናድረው ጮፎረ ዳርቻ ነው፡፡

ዳውሮ ነኝ፡፡ ከዳውሮ ጎሳዎች አንዱ ካውካ መነሻው ጎንደር ሊቦ ከምከም ነው፤ ዳፒቃራ የሚባለው ደግሞ ፎገራ፤ እርግጥ የብዝኃነት ምድር ነው፡፡ የዳውሮ አመጣጥን የሚተርኩ የብሔረሰቡ መረጃዎች ህዝቡ ከብዝኃ-ጎሳ መገኘቱን ያሳያሉ፡፡

9. ወንድሙ ለማ እና ሙሉጌታ በዛብህ፡፡ የዳውሮ ሕዝብ ታሪክ፡፡ ገጽ 11

10.የየም ወረዳ ባህል ቱሪዝምና መንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፡፡ የየም ብሔረሰብ ታሪክ፡፡ ገጽ 16

ደከሞናል፡፡ እርምጃችን ተገድቧል፡፡ ዱሩ ዝኆን እንዳተራመሰው ምልክት ትቷል፡፡ ጨለማው ሰማዩን ሊረከብ ነው፡፡ ጎሽ ያተረማመሰው ረግረግ ለመሻገር አስቸጋሪ እየሆነ መጣ፡፡ ደጀኔ ጉዞአችንን የሚመራው ስካውት ነው፡፡ ቁሙ ሲለን እንቆማለን፤ ተከተሉኝ የሚል ምልክት ሲያሳይ ምድርን ለመርገጥ እንደተጠየፈ ሰው በፍርሃት ቀስ እያልን እንረግጣለን፡፡ ወደ ፊት፡፡ እንዲህ ሆነን ደረስን፤ ጮፎረ ዳርቻ፡፡

# ጮፎረ- ጉማሬና ውበት፡፡

*"አንቺ ጨረቃ ታምሪያለሽ በጣም*
*ምን ብትናፍቂኝ ቤትሽ አልመጣ፡፡"*
*የጃኖ ሙዚቃ*

ቤትሽ መጥቻለሁ፡፡ ሽቅብ አንጋጥጬ እንደ እራፊ ጨረቃን ለብሻለሁ፡፡ የምታምረው ጨረቃ ቤቷ ይሄ ነው፡፡ በጣም ያስፈራል፤ ደግሞም በጣም ደስ ይላል፡፡ ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ ነኝ፡፡ ጩርጩራ ብዝኃ-ሕይወት የሚገኝበት ጉድሙ ቀበሌ፡፡

የጉማሬው ግርግር ራሴን እንደ ምርኮኛ እንድቆጥር አስገድዶኛል፡፡ አብረውኝ ያሉት ራቅ ብለው ለፓርክ ጠባቂዎች ማረፊያ በተሰራች የሳር ጎጆ ደጃፍ እሳት ይሞቃሉ፡፡ የእሳቱን ወገግታ ጨለማው ውጦታል፡፡ ጨረቃ ከሰማይ ቁልቁል ስታይ ጮፎረን ለተመለከተ አፈንድዳ ከሃይቁ ውሃ የምትጠጣ ይመስለዋል፡፡

ድንገት ጫጫታ ኾነ:: ያ ለብርሃንና ለሙቀት የተለኮሰ እሳት የጎጆዋን የጣሪያ ሳር ደርሶበት ነበር:: እሳቱ የደረቀ ሳር ቢያገኝም በርብርባችን መንቦግቦግ አልቻለም:: አጠፋነው:: ግን አስደንግጦናል:: የዱር ውበት ሞገሱን ድንጋጤያችን አጠፋው:: ብዙ መቆየት አልፈለግንም:: እራት እንዲሆነን ከተጠበሰው በቆሎ ግማሹ አልተበላም:: ወደ መኝታችን ገባን:: ደከሞን ነበር::

እዚህ ሲነጋ ሁሉ ብርቅ ነው:: የተኛሁበትን ምድር እንደ ሰማይ አየሁት:: ሀገር ካጠራቀመችው ጥሪት ይኼ ምትክ አልባ የለውም:: እንዲህ ያለው ጸጋዋ በምን ዋጋ ይተመናል? እዚህ ነው ያደርኩት? እራሴን ጠየቅሁት:: ከሥር በጨለማ ያየሁት ጮፎረ ሐይቅ በብርሃን፣ ሰማይን ደረቱ ላይ አጋድሞ ታየኝ:: ካሜራ ከሚናፍቅ፣ የጎብኚ እግር ከተራበ የተፈጥሮ መስህብ ውስጥ ከተሸሸገ የተፈጥሮ ሐይቅ አፋፍ ላይ ቆሜያለሁ::

ጮፎረ በውብ የምድር ገበቴ ውስጥ ተሸሽጓል:: የውሃው ቀለም ጥልቀቱን ይናገራል:: ጀልባ አይደለም ዐይን እንደ ልብ ያልቀዘፈው ለምናብ ጭምር ባዕድ ሆኖ የኖረ ሀብት ነው:: ጉማሬዎቹ አልገቡም:: ዱሩን ሲያተራምሱት እያየሁም እየሰማሁም ነው:: ጉማሬ ቀን ውሃ ውስጥ ውሎ ሌቱን የብሱ ላይ የሚዝናና ግዙፍ እንስሳ ነው:: ጉማሬን የብስ ላይ ከሚኖር እንስሳ በግዝፈት የሚበልጠው ዝኆን ብቻ ነው:: በእኛ ሀገር ሰነዶች እራሱ የአንድ ጉማሬ ክብደት 26 ኩንታል እንደሚደርስ ተጽፏል::[11]

11. ዶ/ር ፍስሃ ሃይለ መስቀል:: ታላላቅ የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ:: ገጽ 125

የ A HIPPO LOVE STORY ደራሲና እውቋ የጉማሬ ጥናት ባለሙያ እንግሊዛዊቷ ካረን በአንድ ምሽት አንድ ጉማሬ አርባ አምስት ኪሎ ግራም ሳር ይመገባል ትላለች::[12] እንዲህ ላለው ውሃ ላይ ተኝቶ የብስን የሚያተራምስ እንሰሳ በርከት ብሎ በሚቦርቅበት ዳርቻ ሲነጋብኝ ፍርሐቴ ጨመረ::

ከአለንበት ስፍራ መንቀሳቀስ የምንችለው ጉማሬው ወደ ጮፎረ ገብቶ ሲያልቅ ነው:: እስከዚያ እንኳን መንቀሳቀስ በአለንበት ሆነን በጮፎረ ሐይቅ ውበት መደመም፣ ልብ ይጠይቃል::

ለቀረጻ የወረዱት ባልደረቦቼ እያለከለኩ ሲመለሱ የሆኑትን መገመት አልከበደኝም:: ከጉማሬ ለትንሽ ተርፈዋል:: ሊያውም ጉማሬ ከጎሽ ጋር እየተሯሯጠ በደረመሰው ጎዳና:: ሬፈደ:: አሁን ሁሉም ጉማሬ ገብቷል ብለን ጮፎረን ለመሰናበት ጓዛችንን ሰበሰብን:: ይህ ውበት ብቻ አይደለም:: ገና ያልተነካ ዳቦ ነው:: የብዙ ዜጋ የዕለት ጉርስ መሆን ይችላል:: የኮይሻ የገበታ ፕሮጀክት ከአቀፋቸው አንደ የመዳረሻ ስፍራዎች አንዱ ይሄንን ይመስላል:: እንደ እኔ ሀገር መጥቶ እስኪመለከተው ጓጉቻለሁ:: ይህ ስሜቱ ባርቦ ፏፏቴ ዳርቻ በጨበራ ሥነ-ምህዳር ሳድር የተሰማኝ ስሜት ነበር::

---

12. Karen Paolillo በሀገረ እንግሊዝ የተወለደች የዱር እንስሳት ባለሙያና የጉማሬ ትረስት መሥራች ናት:: ዓለም አሁን በጉማሬ ጉዳይ ተጠያቂ ሊቅ ያደረጋት ባለሙያ ስትሆን በቢቢሲ ዋይልድ ላይፍ መጽሔትና በናሽናል ጂኦግራፊክ የጉማሬን ርዕሰ ጉዳዮች በማብራራት ትታወቃለች:: ካረን A HIPPO LOVE STORY የተባለ በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያተረኮረ መጽሐፍ አላት::

# ትልቁ ፍጡር ሥር

*"...በዋተተች ቀልቡ ከፀጥታ ጀርባ*
*በተፋፋመ ምጥ በተዳፈነ ዕንባ*
*በተፋጠጠ ሀሳብ በጭንቀት ጥቀርሻ*
*በሚያሥፈራ ፅልመት በፍርሀት መድረሻ*
*ብርሃን አሥጠግቶ ካረገዘው ፅዳል*
*ካርምም አፀመ-ወዝ ጥበብ ያመነጫል::"*

*ገዛኸኝ ጤራ:: ቀለበት*

እስከአሁን የሚገርመኝ ያደርኩበት ቦታ ነው:: ባርቦ የወፍ ድምጽ ውጦ ብቻውን ይሰማል:: ሲነጋጋ ቀድሜ ነቃሁ:: ተረኛው ስካውት ዓይኑን ገልጾ ጨለማውን እየሸኘ ብርሃኑን እየተቀበለ እስከንነቃ እየጠበቀን ነበር:: እንዲህ ያለው ስፍራ እንዲህ ያለውን እንቅልፍ መተኛት እንኳን ለሰሚ ለራስ ይገርማል:: አሁንም ከዚህ የአዳር ስሜት አልወጣሁም:: ያረፍንበት ኾኜ የማስበው ስለዚኽ ነው:: ለምሳ ነው ያረፍነው:: ነጭ ውሃ በምትባለው ምንጭ ዳርቻ ጥሩ ምሳ በላን:: በየበላነው ጎመን ቢኾንም ይበተን ብለን ፈርደን ጥሩ የማዕድን ውሃ ጠጣንበት:: ጥላ ስር ያረፍናት እረፍት ከማስደሰቷ የተነሳ አጥራብኛለች:: ምሳ አርፍደን ነው የበላነው::

እንዲኽ ያለውን የፈጣሪ ስጦታ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ምንኛ መልካም መኾኑን ጥሩ አድርጎ ገልጾታል::[13] ሊቁ በማቴዎስ ወንጌል ድርሳን ሁለት መጽሐፍ "ዓይነ ሥጋስ እንኳን ጭስ ባለበት ቦታ በኾነ ጊዜ እንደሚያነባ፣ ንጹህ አየር ባለበት በአረንጓዴ ቦታም፣ በፏፏቴም፣ በአትክልት አፅድም ሲኾን ግን አጥርቶ እንደሚያይና እጅግ ጤናማ እንደኾነ አትመለከትምን?"[14]

ከነጭ ውሃ ተነሳን:: ምንጭ እንደ ጨጨጌን የሚርመሰመስበት ፓርክ ነው:: ጥም የሌለበት የእረፍት ውሃ መስክ:: ነጭ ውሃ በጨበራ ከሚገኙ ምንጮች አንዷ ናት:: እድሷ ሆኖ ስሟ ገኖ እንጂ እንዲህ ያሉ ምንጮች እዚህ ቁጥርም ከብርም የላቸውም:: እዚህም እዚያም ምንጭ ነው:: ጣዕሙ እንደ ስፍራው የሚለያይ ምንጭ፤ እዚህ እንደ አምቦ ዓይነት የማዕድን ውሃ በየጥሻው አለ:: እዚህ ቀዝቃዛ ሆኖ የሚንተከተክ ምንጭ እንደ ልብ ነው::

ደኑ በጣም ድምጽ ማሰማት ጀመረ፤ ኡቴ እንደ ልማዱ በቆመበት ኾኖ ጆሮውን ሰደደው:: እንዲኽ ያለ ጥበብ አይቼም ሰምቼም አላውቅም:: ጆሮን ሩቅ ልኮ አጠገብ ያለ ሰው ያልሰማውን ለብቻ መስማት የዱር ጸጋ ብቻ ነው::

13. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በ347 ዓ.ም. የወቅቱ የሶርያ ዋና ከተማ በነበረችው አንጾኪያ የተወለደ ታላቅ የቤተክርስቲያን አባት ነው:: ሊቁ ከሥነ መለኮትና ምንፍስና እውቀቶች ባሻገር በዘመኑ የህግ፣ የፍልስፍና፣ የህክምናና መሰል በርካታ እውቀቶችን ያጠና በርካታ በጻሕፍትን የደረሰ ጠቢብ ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ:: ሕይወቱና ትምህርቱ:: በዲያቆን ያረጋል አበጋዝ::

14. በኀብረ እግዚአብሔር ኪ.ደ:: የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ:: የማቴዎስ ወንጌል:: 1-24

በዓለም ግዙፉ እንሰሳ አለሁበት አቅራቢያ ነው፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ዝሆን በቁሙ የታላቅ አውሬ ስም ነው ይላሉ፡፡[15] የዝክረ እንስሳት ደራሲ አህመድ በጀህት መቼም በምድር ካሉ እንስሳት መካከል ከዝሆን የተለቀ የለም ይላል፡፡[16]

ለነገሩ ዝሆን ግዙፍ ያልተባለ ማን ሊባል ኖሯል? ዝሆን አምስት ቤተሰቦች ያሉት ፍጡር ነው፡፡ አራቱ ሞሪተሪዴ፣ ጎምፎተሪዴ፣ ማስቶዶንቴዴና ዳይኖተሪዴ ይባላሉ፡፡ አምስተኛው ኤለፋንቴዴ የሚባለው የዝሆን ቤተሰብ ነው፡፡[17]

አንድ ወቅት የአሜሪካ ሳይንቲስቶች ዳንግ ወንዝ ዳርቻ ጭልጋ ወረዳ ግዙፍ የዱር እንስሳ ቅሪተ አካል አግኝተው ነበር፡፡ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የነበረ ነው፡፡ የተወሰነ ገጽታው ከዝሆን ጋር ይቀራረባል፡፡ ምናልባት ከአራቱ አንዱ ሊኾን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ዛሬ በዓለም ላይ ስለማናውቀው ብሄሞት ስለሚባል እንስሳ ሲነግሩን ከባህር ተፈጥሮ በየብስ የሚኖር ግሩማን አራዊት የሚፈሩት ይሉናል፡፡ አለቃ ብሄሞት ከአራዊት ሁሉ የሚበልጥ የመጨረሻ ግዙፍ የአራዊት ንጉሥ ሲሉት ከዝሆን ጋርም አገናኝተው የሚገልጹት እንዳሉ ጠቁመውናል፡፡[18]

15. ኪዳነወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ፡፡ ገጽ 416
16. አህመድ በሀጀት፡፡ ትርጉም በኢደም መሐመድ አባምቹ፡፡ ዝክረ እንስሳት፡፡ ገጽ 220
17. ዝሆን፡፡ ዶክተር ይርመድ፡፡ ገጽ
18. ኪዳነወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ፡፡ ገጽ 250

መጋቢ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ መጽሐፈ ፊስአልጎስን በተረጎሙበት መጽሐፍ መግቢያ ምንጭ ጠቅሰው ከጥፋት ውሃ ጋርም ኾነ ከዚያ በኋላ ባለው ሂደት ሊጠፉ ስለቻሉ ግዙፍ እንስሳት የዓለም ሊቃውንት ሲነጋገሩ እንደኖሩ ይገልጻሉ፡፡[19]

አራቱ ጠፍተዋል፡፡ ዛሬ በምድራችን ያለው ግዙፍ እንሰሳ ዝኆን ነው፡፡ የብስ ላይ ከሚኖረው እንሰሳ ዝኆን ላይ የሚደርስ ግዙፍ ፍጡር የለም፡፡ የሚገርመው አሁን በምድር ያለውን የዝኆን ቤተሰብ የአፍሪካና የኤስያ ብለው በሁለት ወገን ይከፍሉታል፡፡ ከእነዚህ አንዱ የአፍሪካው ዝኆን ነው፡፡ የአፍሪካውን ደግሞ በሁለት ንዑስ ዝርያዎች ይመድቡታል፡፡ እኔ ያለሁት ከዚህ ግዙፍ ዝኆን አቅራቢያ ነው፡፡ ምድር ሲያተራምስ ተሰማኝ፡፡ ሀገር ሲነቃነቅ አደመጥሁ፤ ዱር ሲመሰቃቀል አየሁ፡፡ ጨበራ ጨርጨራ ብሔራዊ ፓርክ ዱር ውስጥ ነኝ፡፡

ከነጭ ውሃ ስንንቀሳቀስ ስፍራዋ የገነነችበት ምክንያት ገባኝ፡፡ የዝኆኖቹ መዋያ ከሆነው አካባቢ አቅራቢያ መገኘቷ ነው፡፡ ይኸቺን ምንጭ ያገነናት ከዝንባባዎቿ ጥላ ስር መንጭታ ነፍስ የሚያሳርፍ ቅዝቃዜን መታደሏ ነው፡፡
ከሩቅ የሚመጣውን የሚያስፈራ ድምጽ ተከትለን ወደ ኤርፓ ጉዞአችንን ቀጠልን፡፡ ኤርፓ ብዙ ዝኆኖች አንድ ላይ የሚውሉበት አንዱ ቦታ ነው፡፡ በሳር ውስጥም መንገድ አለ የሚለውን ለመቀበል ሳሩ ሳይቃጠል ጨበራ ጨርጨራ መምጣት ነው፡፡

19. መጋቢ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ፡፡ ፊስአልጎስ፡፡ ገጽ 21

ሰው ከረዣዥርሞቹ የሳር ዛፎች ስር እንደ ደብረ ሲና ዋሻ ተሸሽጎ የሚሄድበት የተለየ ምድር፡፡ እዚህ ቶሎ ቶሎ አቅጣጫ ቢጠፋ አይገርምም፤ ምሥራቅና ሰሜኑን እንዳንለየው ያደረጉን የሳር ደኖች ዋጋ እያስከፈሉን ነው፡፡
ይኸ ደን የዝኖኖች ምድር ነው፡፡ ዛሬ ዝኖን እንኳን ከኢትዮጵያ ምድር ከዓለምም ሊጠፋ ነው፡፡ የዝኖን አደን ይቁም ብለው መንግሥታት ቃል ተገባብተዋል፡፡ በኢትዮጵያ ዝኖን ጥቂት ቦታዎች የሚገኝ ብርቅዬ እንሰሳ ኾኗል፡፡ ዛሬ ጎንደር ከተማ ላይ ዐፄ ፋሲል ዝኖን ያድኑ እንደነበር እንዴት ማመን ይቻላል? አለቃ ተከለ ኢየሱስ ዋቅጅራ ግን ይኼን ይነግሩናል፡፡[20]
ዝኖን የተፈጥሮን ጫና ተቋቁሞ የአየር ንብረት ለውጡን የተጋፈጠ እንሰሳ ነው፡፡ የዝኖን ባህሪ አጥኚዎች ሩህሩህ እንሰሳ ነው ብለው ቢመሰክሩለትም የሰው ልጅ ግን አልራራለትም፡፡ POACHING FACTS የተባለ ተቋም ያቀረበው ሪፖርት የዝኖን ጥርስን በጥሬ ዕቃነት የሚልጉ ውድ ጌጣጌጦች የአፍሪቃን ዝኖን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ምክንያት ኾኗል ይላል፡፡ ናሽናል ጂኦግራፊክ ደግሞ አፍሪቃ በአስር አመታት ብቻ 64 ከመቶ የዝኖን ሀብቷን እንዳጣች ያረዳናል፡፡[21] ለምሳሌ ከ2009-2012 የፈረንጆቹ ዘመን በሦስት አመታት ብቻ 100 ሺህ የአፍሪቃ ዝኖኖች በህገ ወጥ ታድነዋል፡፡ ይኼ መኖሪያው ከሚደርስበት ጫና ጋር ተዳምሮ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ ለጥርሱ የሚከፍለውን መስዋዕትነት ያሰበ ዛሬ ደርሶ ልናየው መብቃታችን አስማተኛ ፍጡር ይኾን? ሳያስብለን አይቀርም፡፡

20. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ፡፡ ገጽ 160
21. National Geogeraphic Sep.15/2015

ኢትዮጵያ የዝሆን ምድር ነበረች:: ዛሬ ዝሆን ብርቅና ጥቂት አካባቢዎች የሚገኝ እንስሳ ኾኗል:: ትናንት ዝሆን የነበረባቸው አካባቢዎች ዛሬ የሩቅ ተረት ይመስል የማያምኑት እውነት ኾኖባቸዋል:: ስቲጋንድ የተባለ አሳሽ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በተጓዘ ጊዜ ከጎፋ ወደ ዎላይታ ሲመጣ ማዜ ሸለቆ ውስጥ ዝሆን ማየቱን ጽፎልናል::[22] ዛሬ ማዜ ብሔራዊ ፓርክ ብዙ ነገር አለ:: ዝሆን ግን ምኞት ነው:: በሌላ በኩል በጎጃም ምድር አነደድ በሚባለው ወረዳ አድያም ሰገድ ኢያሱ ዝሆን ማደናቸውን የኢትዮጵያ ታሪክ ይነግረናል::[23]

በዶክተር ዘለዓለም ተፈራ የዶክትሬት ጥናት መጽሐፍ እንደተገለጸው 531 AD አንድ የባዛንታይን ተጓዥ በየሃ አቅራቢያ አክሱም ዙሪያ 5000 ገደማ ዝሆን ማየቱን ጽፉል::[24]

አሁን ፍርሃት እየተሰማኝ ነው:: የዱሩ ጠረን ተቀይሯል:: የጎሽ መንጋ በሄደበት እየሄድን ነው:: እንዲህ ባለው የሳር ደን ውስጥ ጎሽ ባበጀው መንገድ መሄድ የተሟላ መሠረተ ልማት ያለበት ጎዳና ላይ እንደመንሸራሸር ይቆጠራል:: እዚህ ዱር ብዙ ጎሽ አለ:: እንደ ዝሆን ሁሉ ጎሽም በኢትዮጵያ ምድር ብርቅ እየኾነ ነው:: እንደ ጋምቤላ፣ ኦሞና ዳቲ ወለል ያሉ ጥቂት ስፍራዎች ብቻ የሚገኝ እንስሳ ኾኗል::

22. CAPHTAIN C.H STIGAND,TO ABYSSINIA THROUGH AN UNKNOWN LAND page 228

23. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ:: የኢትዮጵያ ታሪክ:: ገጽ 166

24. Zelealem Tefera Ashenafi/PHD/, Common Property Resource Management of an Afro-alpine Ecosystem.page 16

ዛሬ ሳላ ብርቅ የኾነበት የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ የዛሬ መቶ ዓመት ጎሽ እንዳሻው የሚኾንበት ውብ ስፍራ እንደነበር ለአደን ስፖርት የመጣው አሳሽ ያየውን ባሰፈረበት የታሪክ ድርሳኑ እንረዳለን::[25]

ሩቅ የነበረው አስፈሪ ድምጽ በጣም ቀርበናል:: አዳኑ ስለ ዝሆን የነገረኝን መላልሼ ማሰብ ጀምሬአለሁ:: አምስት ሺ ኪሎ ስለሚመዝን ጉልበተኛ እንስሳ እያሰቡ ወደ እንስሳው መሄድ ያስፈራል:: ዮናታን ካሜራውን ደቅኖ ከኋላዬ ይከተለኛል:: ዝሆኑ መግደል ከጀመረ የኔ ተራ ስንተኛው እንደሚኾን ማሰብ ጀምሬአለሁ::

ዝሆን በሀገሩ ምድር ማየት የሚችለው ጥቂት የታደለ ሰው ነው:: አባቶቼ ያዩትን እኔ የማላይባት ሀገር ተፈጥሬአለሁ:: አስገራሚው ነገር አንዳንዱ የሀገሬ ስፍራ ዝሆን አደኑ ላይ የሹማምንቱ መንፈሳቸውም እጃቸውም አለበት:: የሚችን መውደቂያ የሚያፋልገን ጉዳይ ነው::
ዛሬ በሀገሬ ምድር አውራሪስ የለም:: ትናንት አውራሪስ ብርቅ አልነበረም:: አውራሪስ አነስተኛና መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር የሚል ስቲከር የተለጠፈባቸውን መኪኖች አሰብኳቸው:: አውራሪስ በምድራችን ስለመኖሩ ልጆቻችንን የምናስረዳበት አንዳች እድል የሌለን ኾነናል:: ዐፄ ምኒልክ አዛዥ ገደል ሃያ ስምንት አውራሪስ ገድሎ የላከላቸው መኾኑን ከጻፋለት ደብዳቤ መረዳት ይቻላል::[26]

25. *Powell-Cotton, A SPORTING TRIP THROUGH ABYSSINIA, page 46*
26. *ጳውሎስ ኞኞ:: አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች:: ገጽ 247*

"አውራሪስ መታጠቅ እየገደሉ ነው
ገዝቶማ መታጠቅ ነጋዴ መሆን ነው።"[27] ብለን የጨፈርንባቸው ዘመናት ዛሬ አውራሪስ ብርቁ ትውልድ እንዲፈጠር አድርገውናል። አውራሪስ ከኢትዮጵያ ምድር መጥፋቱ ባለሙያዎች ደፍረው መናገር ጀምረዋል። በዚህ ግን አያበቃም፤ ገና ወደፊት ይጠፋል ያሉትን በቅደም ተከተል እየነገሩን ነው። የKilling for profit ጸሀፊ ጁሊያን ራድማየር በአውራሪስ ላይ የደረሰውን ቀውስ ዛሬ ለደረስንበት አውራሪስ ብርቁ ዓለም እንዴት እንዳደረሰን በስፋት ገልጾታል። ወንጀሉና የጥፋቱ መሻት ምን ድረስ እንደደረሰም ጭምር።[28]

በ1980ዎቹ የፈረንጆች ዘመን በአውሮጳ ሁለት ቢሊዮን የዱር ወፎች ነበሩ ይህ ቁጥር በሰላሳ አመት ውስጥ በ2009 መቶ ሚሊዮን ቀንሶ 1.9 ቢሊዮን ደረሰ ይለናል፤[29]

የመጨረሻዎቹን ቀጭኔዎች ፍለጋ ወደ ሱማሌ ተጉዤ ነበር፤ ወደ ሀገሬ አንድ ጠረፍ ፓርክ፤ ገራሌ ወደሚባለው የገሬዎች ምድር።

27. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል። ዝክረ ነገር። ገጽ 344

28. Julian Rademeyer በምርመራ ጋዜጠኝነት የተዋጣለትና ተሸላሚ ነው። ለበርካታ የደቡብ አፍሪቃ ጋዜጠኞች በመጻፍ የሚታወቀው ይህ ሰው ዝነኛ ካደረጉት ስራዎች አንዱ ሀገ ወጡ የአውራሪስ አደንና የቀንዱ የጥቁር ገበያ ሽያጭ ላይ የሰራው የምርመራ ሪፖርት ሲሆን Killing for profit በዚህ ዘገባው ላይ የተመሰረተ መጽሐፉ ነው።

29. Yuval Noah Harari, Homo Deus, page 73

# ፋይዳ የለውም።

"ከምንሻው ስንደርስ፣ ጊዜ ይህ ጅል ነጂ
መቼ ልጓም ያውቃል፣ መከነፍ መብረር እንጂ፤
በዚያች ቅድስት እለት
ሰዓት ያቺ ቅጽበት
ስፍራም እዚያች መሬት፣
ሆነው ለዘለዓለም፤ ቀርተው በነበረ
ውበት ህያው ሆኖ፣ ተውበ በኖረ።"

ተሻገር ሽፈራሁ። የነፍስ ርችቶች

ኡደት ቀን ትሞቃለች። አየሯም ንግዷም ደመቅ ይላል። እስከ ማታ እንዲኸ የምትቆይ መስሎኝ ነበር። ሲመሽ ሌላ መልከ ያዘች። ምሽት አየሯ ደስ ይላል። እንቅስቃሴዋም ሙቀቱም ይቀንሳል።

አንዳንዱ አፉ ላይ ሲጠራት ሁደት ይላታል። የጠረፍ ዳሯ ከተማ። ሱማሌ ክልል ነኝ። ዳዋ ዞን ይባላል። የዞኑ ዋና ከተማ ናት ኡደት፤ ኡደት የሚለው ቃል ድምጻ ቀድ ነው ይላሉ። ከወፍ ዜማ ነው የተቀዳው፤

እንደገመትኩት አንዳችም ስጋት አልተሰማኝም:: ገሪዎች ረጋ ያሉ፣ እንግዳ ተቀባይና ሰላማዊ ከመሀል ሀገሩ የተሻለ ብቻ ሳይኾን የምመኘው ዓይነት ሰላም አየሁ:: አንድም ሰው መሳሪያ አንግቶ አላየሁም:: የኡደት ሰው ኑሮ ላይ ስጋት የለም:: ይኽ ስፍራ ከጥቂት አመታት በፊት "በወንድማማቾች መካከል እንዴት እንዲህ ያለ ጦርነት ይደረጋል?" የተባለበት ከባድ የግጭት ቦታ ነበር::

ገራሌ ብሔራዊ ፓርክ በብዙ ምክንያት ተደብቆ የኖረ ፓርክ ነው:: ስጋት ከሀገር ልጅ እንዲሸሸግ አድርጎታል:: መምጣት ለብዙ ሰው የሞት ያህል መርግ ነው:: እኔ ግን መጣሁ:: ቀጭኔዎቹ ታዩ ሲሉኝ በርሬ መጣሁ:: ስመጣ መምጣት የሚፈራበት ቦታ ኾኖ አላገኘሁትም::

የከተማዋ ነፍስ ጎዳናዋን ይዞ የሚያጣጥር ነው:: ከዋናው መንገዱ ጀርባ ሰፊ መንደር የላትም:: ገሪዎች አደን አይወዱም:: ደጃፋቸው ላይ የሚታዩት እንስሳት ምስክሮች ናቸው::

ከብሔራዊ ፓርኩ ሰራተኞች ጋር ተገናኘተናል:: ሰለሞን፣ ጌች፣ ገብረመስቀልና ብስራት እንደኔው እንግዶች ናቸው:: ከእኔው ጋር የመጡ የዱር እንስሳት ዋና መሥሪያ ቤት ሰዎች:: ብስራት ጎበዝ ሹፌር ብቻ አይደለም፤ የወደቀ መኪና የሚያነሳ፣ የቆመ መኪና የሚያሮጥ ምስጉን መካኒክም ነው:: እንዲህ ያለ ሹፌር ይዞ ፓርክ መግባት የስኬት ግማሽ ነው:: ገራሌ መድረስ ብሔረ ጽጌን የመጎብኘት ያክል ፍጹም ሰላም እና ስጋት አልባ ነው:: እንደ ገባን ምግብ ፍለጋ ጎራ ያልንበት ቤት ተከትሎን የገባው ሰው ሊተናኮለን ነው ብዬ አሰብኩ::

ሰውዬውን ጠረጠርኩት:: ከሳሚ ጋር ድምጹን ከፍ አድርጎ እየተከራከረ ነው:: ሳሚ የብሔራዊ ፓርኩ ኃላፊ ነው:: እዚህ ድረስ መጥቶ የሚነታረከው ሰው የፓርክ እንግዶች የእኔ እንግዶች ናቸው ብሎ ካልጋበዝሁ ሊል ነው:: የሀገር እንግዳ ልዩ ስፍራ አለው:: ሰውና ፓርክ መግባባታቸው ገባኝ:: አልተሳካለትም እንጂ የኡደት ሰው ፓርኩን ትልቅ ቦታ ማድረስ እንደሚፈልግ አየሁ::

ጎላ ያለ ድምጽ ሁሉ የጠብ ምልክት እንዳልኾነ ተረዳሁ::

የብሔራዊ ፓርኩ ሠራተኞች መሳሪያ አይዙም:: ሬንጀራቸውን ይለብሳሉ፤ ቀለባችንን እንጭናለን:: ኢትዮጵያ ከኬኒያ እስከምትለይበት የድንበር ጥግ ድረስ እንጓዛለን:: እዚህ ከከባድ መሳሪያ በላይ የጎሳ መሪዎች ቃል ኒውክለር ነው::

መብራት በሌላት ከተማ ምሽት ጎዳናዎቿ ላይ ስጓዝ አንዳችም ልቤ አልፈራም:: እዚህ በብርሃን ካልከፈልኩ ብሎ ልቡን የሰጠኝ ነዋሪ ምሽት እንደ መንፈስ ይጠብቀኛል ብዬ አምኛለሁ::

ብስራት በጠዋት ቀሰቀሰን፤ አንዳችንም አልተዝረከረክንም:: ዕቃዎቻችንን ወደ መኪናችን ጫንን:: ወፍ እየዘመረ ከኡደት ወጣን:: ጉዞ ወደ ሙባረክ፤

ልቤ ቀድሞ ደርሷል:: የመጨረሻዎቹን ቀጭኔዎች ፎቶ ሳነሳቸው ይታየኛል:: ሀገር ካልደረሰላት ቀጭኔ ጋር ዓይን ለዓይን ስተያይ በምናቤ አያለሁ:: መጥፋቷ የመብራት መጥፋት ያኽል ትውልድ ከማያስጮኸው ቀጭኔ ጋር በማንባር እየተያየሁ የትውልዱን ሀጢአት እናዘዛለሁ::

እኔ የምላልኝ ኾኜ ይኾናል፡፡ የሰው ልጅ ቀይ ባህር እየሰጠመ መሸሻ አግኝተው ጎረቤት ሀገር ስለሚገቡ ቀጭኔዎች የምጨነቀው፤ እኔ የሚሰራኝን አሳጥቶኝ ይኾናል፤ አብዮት፣ ቀይ ሽብር፣ ነጭ ሽብር፣ አሲምባ፣ አፋቤት፣ ባድመ፣ ቅንጅት እያለ በሚጫረስ ትውልድ መካከል ኾኜ አውራሪስን ጨርሰን አጠፋነው የምለው፡፡

ግን ልቤ ቀድሞ ደርሷል፡፡

ከሄድኩበት የምናብ ዓለም ተመለስኩ፡፡ ዞር ብዬ በመስታወቱ ውጪውን አየሁት፡፡ ገራሌ እንኳን ፓርኩ መንገዱ ፓርክ ነው፡፡ በሀገሬ በቅጡ ከተያዙት ፓርኮች ይልቅ የገራሌ መንገድና ዙሪያ የተሻለ ጥብቅ ቦታ ነው፡፡
"ፋይዳ የለውም፡፡"
መቤ ነው፡፡ አልፎ አልፎ የልቡን የሚገልጽ ቋንቋ ሲያጣ አልያም ያሰበው መውደቂያ የሌለው ጉዳይ እንደኾነ ሲገባው ፋይዳ የለውም ይላል፡፡ የስካውት ኃላፊ ነው፡፡ ከጎሳው ዝቅተኛ ገቢ ያለው እሱ ነው፡፡ የሚያውቃቸው ሁሉ ኮንትሮባንድ ነጋዴዎች ናቸው፡፡ ከኬኒያ ጥቂት እቃ አምጥቶ አመት መኖር የሚቻልበትን ኑሮ ገፍቶ እንስሳ እየጠበቀ ኑሮውን ይገፋል፡፡
አንገጫገጨን፡፡ የብስራት የማሽከርከር ጥበብ የሚታማ ባይኾንም መንገዱ ግን እንዳሻው ያነጥረን ይዟል፡፡
"ተመልከት፤ አሁን በዚህ መንገድ መኪና ምን ያደርጋል? አንድ ሞተር ግን ቢኖር ሽው ብለህ ትመጣና...."
አልጨረሰውም፡፡ እንደለመደው እንዲህ ብሎ ካቆመ መዝጊያው ይታወቃል፡፡ አለው፤

"ፋይዳ የለውም።"

ፓርኩ ቅጥር ሳንገባ መንገዱ ከርከሮ ብቻ ነው። ከርከሮ ብቅ ብሎ መኪናችንን ሲመለከት ዘሎ ጥሻው ውስጥ ይከተታል። መልከ ጥፉ ነው ከሚሉት ወገን ነኝ። መጀመሪያ ጉንጭ ላይ ጥርስ አስገራሚ ነው። ሲያውም ቀንድ የሚመስል ጥርስ። ሳይንሱም ትውፊቱም የአሳማ ቤተሰብ ያደርገዋል። እርግጥ ነው ጠፍጣፋው የፊት ገጻቸው ከአሳማ ጋር ወንድማማች ስለመኾናቸው ለመገመት ያስደፍራል። ጠቢብቱ ግን ከግምት ባለፈ የአሳማ አስተኔ ብቸኛ ዝርያ ነው ይላሉ።[30]

ከርከሮ ብዙ የሀገራችን አካባቢ የሚታይ እንስሳ ነው። በቁጥር እንዲህ ጥሻውን ሲሞላው ያየሁበትን ግን አላስታውስም። ከሦስት ሺ ሜትር በላይ ካልኾነበት የትም ለመኖር የሚመቸው እንስሳ ነው። ሰብል አቅራቢያ ኑሮውን ከመሰረተ የገበሬ ሁነኛ ጠላት በመኾን ከእርግማን ሳያርፍ ይሞታል። ምክንያቱም ከርከሮ በቀላሉ ብቅ ብሎ የጎበኛት ማሳ እንዳች አትተርፍምና፤

የከርከሮ እናት ልጇን አትለየኝ ባይ ናት። በልጅ ታጅባ ትኖራለች። ከዚህ ነው አጥቢዋን ከርከሮ ከግልገሏ በተጨማሪ ከፍ ያለች ሌላ ከርከሮ ስታ ስትርመሰመስ ማየት ብርቅ ያልኾነው። ከአምስት እስከ ስድስት ወራት ባሉት ጊዜ የሚወልዱት ከርከሮዎች ሲመከኑ ሁለት አልያም ሶስት መንታ ወላዶች ናቸው። እንኳን ደህና መጣችሁ ከሚለው ታፔላ ይልቅ ተፈጥሮ የት መድረሳችንን መናገር ጀመረች። ተፈጥሮን ማየት እንደማድመጥ ነው። የት እንዳለሁ እና ምን እንዳለ ሰማሁ። በማየት።

30. ዶክተር ሰለሞን ይርጋ። አጥቢዎች። ገጽ 97

እዚህም እዚያም ጉጉፍቱዎች ታዩ:: ሜዳ ፍየሎች ብቅ ብለው ጥልቅ ማለት ጀመሩ:: የኩይሳ ክምሮች ከለምለሙ ሳር መካከል ተንጠራርተው የሚመለከቱ መሰሉ:: ይኼ ገራሌ ነው::
"ተመልከት እይ ተፈጥሮ...አሁን ይኼ.... ፋይዳ የለውም:: ወላሂ፤ ገሬ እንስሳ አይገድልም:: እኛ ሞተር፤ ሞተር ብናገኝ እየመጣህ ታያስህ:: እይ...እይ እዛጋ...ፋይዳ የለውም::" እውነት ነው:: እንዲኼ ያለውን ተፈጥሮ መጠቀም ያልቻለ ሀገር የሚመኘው ሁሉ ከንቱ ነው:: ፋይዳ የለውም::

የዶዶ ኮረብታ ታየን:: ዶዶ ውቡ የገራሌ ብሔራዊ ፓርክ ስፍራ ነው:: ድንጋዮቹ ቁጥቋጦውን አልፈው አፍጥጠው ይታያሉ:: ቀለማቸው ይለያል:: ከሰማይ የፈሰሱ የቸኮላት ዐለት መሰሉኝ::

ሰለሞን በየደረስንበት ያስቆመናል:: ወፍ ሲያይ ያዘው ያዘው ይላል:: ብስራት ይቆማል:: በዚያ ሩቅ አምጪ ካሜራው ከዛፍ ላይ ኾነው ዓይኑ ስር ያደርሳቸዋል:: እንዴት የሚያምር ምስል እያስቀረ ነበር፤
ወፍ አይገባኝም:: ወፍ ሁሉ አንድ ነው:: የወፍ ሀገሯ የትም ነው የሚለው ብሂል የትም ያለች ወፍ አንድ አድረጌ ይሆናል:: በቁጥር አምስት ዝርያ አይሞላም የለየሁት:: ከዚያ በኋላ የወፍ ስምና መልክ አንድ ኾኖ ውስጤ ቀረ:: እንዲህ ብዬ ስነግራቸው ቆይ እስክትለከፍ እኮ ነው የሚሉኝ ብዙ ናቸው:: አላዛር ዳቃ ስለ ኢትዮጵያዊው የወፍ ሊቅና ሳይንቲስት ይልማ ደለለኝ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረኝ አድርጓል:: ይኼንን ሰው ያወቀ ደግሞ ከወፍ ይዛመዳል::

አልአዛር ዳቃ የወፍ ተመራማሪ ነው:: እንደ ሰው በምድር ቆሞ ይሂድ እንጂ ልቡ በየዛፉ ጎጆ ከወፍ ጋር የምታድር፣ ቀልቡ አሞራ በበረረ ቁጥር አብሮ የሚበር፤ "አልበር እንዳሞራ ሰው አድርጎ ፈጥሮኛል" የሚለው ሙዚቃ የሚገርመው የሚመስለኝ እንደ አሞራ በምናቡ የሚበር ዶክተር ነው::

አላዛር አንድ ቀን አንድ ድግስ ጠራኝ፤ ያ ድግስ የዓለም የጥንብ አንሳ ቀን ነበር:: ቀኑ በአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ሲከበር እኔም የጥንብ አንሳ እንግዳ ኾኜ ተገኘሁ:: የዚያን ቀን የሰማሁት ጉድ ዛሬ ድረስ አብሮኝ አለ:: ዓለም ለካ እኛ ከተጧደንበት የብሔር ስምና ማንነት በላይ የጥንብ አንሳ ጉዳይ አሳስቦት ይመከር ይዘከር ጀምሯል::

ያለ ጥንብ አንሳ መኖር፤ ጥንብ አይጠፋም:: ጥንብ የማይጠፋባት ዓለም ለሰው አትኾንም:: ለሰው ረብ ከሌላቸው ብዙ ሰዎች ጥንብ አንሳ ብዙ ትርጉም ያለው አስፈላጊ ፍጥረት መኾኑን አምኜ ተመለስኩ::
አልአዛር አንድ ቀን የኢትዮጵያን ወፎች ይታደግ ይኾናል:: ሳውቀው ጀምሮ ልበ ስሱ ወፍ አፍቃሪ ነው:: እሱ የተፈጠረባት ሀገር ሀይቋን አድርቃ ለወፍ አልመች ማለት ጀምራለች:: አንድ ቀን አላዛር እንዲህ አለኝ::
"ወፍ ከሌለ ምንም የለም:: ለዚህ ነው የኛ ሰው ምንም አለመኖርን፣ ባዶ መኾንን ሲገልጽ 'ወፍ የለም' የሚለው:: አየህ ወፍ ካለ ሙሉ ነው ሁሉ ነገር አለ ማለት ነው::"
እውነቱን ነው አልአዛር፤ ገራሌ ወፍ አለ:: ሁሉም ነገር አለ:: ሀገሬን ወፍ የለም የማይባልባት አድርግልኝ፤

የወፉ ድምጽ ተአምር ነው። ዓይነቱም እንዲሁ፤ ዥግራው መሬት ወርዶ መንገድ ዘግቷል። ላባዋ የሚማርከው ወፍ ዓይነቷ ብዙ ነው። 250 የሚሆን የወፍ ዝርያ መኖሪያ ነው። ቄንጠኛ ወፎች በየዛፉ ተንጠልጥለው ትርኢት ያሳዩናል። ይህ ገራሌ ብሔራዊ ፓርክ ነው።

የዶዶ ኮረብታ ሲቀርቡት ድንቅ ነው። እንዴት አለት ቁልቁል እየወረደ ደርሶ ይቆማል? እንደዚያ የቆሙ ይመስላሉ። ድንገት እንደ ከርከሮዎች ከጥሻው ብቅ ብሎ የወጣ እስኪመስለኝ አውት ፖስት ቤቱ ብቅ አለ። ስካውቶቹ ተቀበሉን።

ቡና ተፈላልን። በንኬል ኩባያ የዶዶ ኮረብታን እያየሁ በረንዳ ላይ ቸኜ የቀረበልኝን ቡና ጠጣሁ። ዓይኔን ስልከ ተአምር ይታያል። ሰጎኖች ይሮጣሉ፤ ሳላዎች አሻግረው ያዩናል። ይኸ የኢትዮጵያ ጠረፍ ተአምረኛው ገራሌ ብሔራዊ ፓርክ ነው።

# የቀጭኔዎቹ ዳና

ለምሳ ቆምን፡፡ ከዶዶ ከተነሳን ሁለት ሰዓት ተጉዘናል፡፡ አሁን ሙባረክ ደርሰናል፡፡ ሙባረክ ኢትዮጵያ ውስጥ ናት፤ ግን ደግሞ የኬኒያ ሽልንግ እንደ ሞያሌ ነፍስ ዘርቶ ይገዛባታል፡፡ ኑሮ ውድ ነው፡፡ ያም ኾኖ እንጀራ አለ፡፡ እንጀራ ተአምሩ ብዙ ነው፤ የሀገር ገንዘብ በሀገር መሬት እንዲህ መሳ ለመሳ ከሌላ ገንዘብ ጋር አንድ ገበያ በሚውልበት ጠረፍ እንጀራ ግን ቀዳሚው ምርጫ ኾኖ ይቀርባል፡፡ ሩዝ በስፋት የሚበላው የሙባረክ ዋና ምግብ ሲሆን በብዛት በስጋ ይበላል፡፡ ስለምትሞቅ ቀዝቃዛ መጠጦች ሰፊ ገበያ አላቸው፡፡ በተለይም ውሃና ለስላሳ፤

የከተማዋ ቤቶች ትንሽ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ግንብ ኾነው ጎዳናዋን ተከትለው ተሰርተዋል፡፡ ሱቆቹ የድንበር ማዶ ተጽእኖ አለባቸው፡፡ የኬኒያ መኪኖች አየሁ፡፡ የኬኒያ ታርጋ የለጠፉ ሞተሮች ይሯሯጣሉ፡፡ ገሬዎች ረዣዥም ውብ ሲኾኑ ዒማናና ሞገስ አላቸው፡፡

የገረመኝ ሙባረክ ላይ የመጨረሻውን የከተማ ምሳ የበላንባት ቤት መጥበሷ:: ትኩስ እንጀራ አይመቸኝም ማለት አይቻልም:: ምግቡን ሰናዝ እንጀራው ሊጋገር ምጣዱ ሰማ:: የሚታዘዘውን መጠን አይቶ መጋገር የከተማዋ ባህል መኾኑን ያየሁት ስመለስ በገጠመኝ ተመሳሳይ ነገር ነበር:: እዚህ በየዓይነቱ ተብሎ የሚቀርበው አንድ ወጥ ነው:: በየዓይነቱ ለእንጀራው የሚሰጥ ስያሜ መስሎኛል:: ከባለ ምግብ ቤቷ ጋር በሂሳቡ አልተግባባንም:: ሳሚ ተጠራ፤ ለካንስ ዋጋ የነገረችን በሽልንግ ነበር::

ወደ ዱሩ ልንገባ ነው:: ሰው ሁሉ የየራሱን አመል ከሚፈልግበት ገዛ:: መሐመድ ማሌዲን እኛ መኪና ውስጥ አስገባነው:: ከዚህ በኋላ እሱ መንገድ ይመራናል:: ቀጭኔዎቹ ጋር ያደርሰናል:: ከገራሌ ዱር ጋር ያግባባናል:: የጉዞአችን መድረሻ የጠረፏ ቀበሌ ትሆናለች::

መሐመድ ማሌዲ የወረዳው ሚኒሺያ ጽ/ቤት ኃላፊ ነው:: ቀጭኔ ለማሳየት ከእሱ የተሻለ የለም ተብሎ አብሮን እንዲመጣ ተመረጠ:: ዱሩን እንደ ቤቱ የሚያውቅ ነውና ለብዙ ነገር አስፈላጊው ሰው መሆኑን እያመንን መጣን::
የመቤ ጨዋታዎች አሁንም ቀጥለዋል:: ግን ሄዶ ሄዶ "ፋይዳ የለውም" የሚለው ብሶት ዝም ያስበለዋል:: ዝም ብሎ አይቆይም ዳግም ሌላ አጀንዳ ያነሳል:: ፋይዳ ያጡ ጉዳዮችን አንስቶ ይጥላል:: ጨዋታዎቹ አይጠገቡም:: የብሔራዊ ፓርኩ ስካውቶች የቀጠና አስተባባሪ ነው::
አሎ ብርቲ ቀበሌ ደረሰን:: የመጨረሻዋ የብሔራዊ ፓርኩ ወደብ ቀበሌ::

ተጨማሪ ሚሊሺያዎች ለመያዝ ጥቂት ቆምን፡፡ ጽ/ቤት ኃላፊው ወደ ተሰበሰቡ ሰዎች ሄዶ የተመደቡትን ሚኒሺያዎች ይዞ ተመለሰ፡፡

አሎ ብርቲ ልብ ታሳርፋለች፡፡ የወደድኳት መንደር፤ ሚሊሺያውን በአስተርጓሚ አዋራሁት፡፡

"ቀጭኔ አይተህ ታውቃለህ?"

መቤ በሱማሊኛ ጠየቀው፤ መልሶ መቤ መልሱን ነገረኝ፡፡

"ሰሞኑን ዱር ውስጥ ነበርን እስከ ትናንት ወዲያ ነበሩ"

"ስንት ናቸው?"

ሀገር እንኳን ባያያቸው ቢያንስ እኔ ልሰናበታቸው፡፡ እዚህ ሀገር የኖርንበት ነገር ሁሉ የምንሰናበተው እውነት ኾኗል፤ አብሮነት፣ አንድነት፣ መተዛዘን፣ ዱሩ እንስሳው፣ ሁሉ ነበር የሚባልበት ሀገር፤

"እኛ ያየነው ስድስት ነው፡፡ እዚህ ኮንሶዎች ጋር፤"

"የምን ኮንሶ?" ግራ ገባኝ፡፡

መቤ ራሱ አብራራ፤

"እዚህ ውሃ ማቆሪያ የሚቆፍሩት ከኮንሶ የሚመጡ ሰዎች ናቸው፡፡ እነሱ ናቸው በርሃውን የሚቋቋሙት፤ እዚያው እያደሩ ቆፍረው አስረክበው ይሄዳሉ፤ ተቀጥረው ነው፡፡"

አይ ኮንሶ...እውነትም የታታሪነት ተምሳሌት፡፡

"እዚህ አውራሪስ የለም?" የቀጭኔዎቹ ነገር ሰመረ ብዬ ሌላ መመኘት ጀምርኩ፡፡

መቤ በሱማሊኛ አስተረጎመ፡፡ ብዙ አወሩ፤ ሞቅ ያለ ውይይት ነበር፡፡

"አይቻለሁ ግን ሩቅ ነው፡፡ ሸለቆ ውስጥ ነው፡፡ ግማሽ ቀን ያስኬዳል፡፡ እኔ ራሴ በዓይኔ አይቻለሁ ነው የሚለው" አለ መቤ፡፡

የሚሊሺያ ጽ/ቤት ኃላፊውም ተናገረ፡፡
"እሱም አይቻለሁ እያለ ነው" አለ መቤ፡፡ ቀና ብዬ መሐመድን አየሁት፡፡ አማርኛ በደንብ ማውራት ባይችልም በትንሹ ይሰማል፡፡ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ፡፡ ከሞባይሌ ላይ የአውራሪስ ምስል አውጥቼ አሳየኋቸው፤ ሁለቱም እኩል በሱማሊኛ ተናገሩ፡፡ ራሱን ነው ዓይነት ነገር ነበር፡፡

ገራሌ ተደብቆ የኖረ ፓርክ ነው፡፡ ስሙ በአካባቢው ከሚኖረው ገሪ የተባለ ግዙፍ የሱማሌ ጎሳ የመጣ እንደሆነ መቤ አጫውቶኛል፡፡ እንዲህ እንስሳ እንደልብ የሚታይበት ብሔራዊ ፓርክ በእኔ ሀገር ጥቂት ነው፡፡ አንዱጋ መጥቻለሁ፡፡

የሜዳ ፍየሉ ብዙ ነው፡፡ ገረኖው ቁጥር የለውም፡፡ አጋዘኑ ግራና ቀኝ ይሮጣል፡፡ ሳላዎቹ ያልደረቀው ሳር ሸሸጓቸውም ይታያሉ፡፡ ሰጎኖች ሜዳው ተመችቷቸዋል፡፡ ሳልቆም የማየውን ሳልፍ፤ ልቤ ወደ ቀጭኔዎቹ ለመድረስ በምናቡ ደጋግሞ ከመኪና እየወረደ ነበር፡፡

ገራሌ የወፍ ሀገር ነው፡፡ የሚሰማው ሁሉ የወፍ ድምጽ ነው፡፡ እዚህም እዚያም ዓይነተ ብዙ ወፍ ይታያል፡፡ ደግሞም ይሰማል፡፡ የሚታየው የሚደመጥበት ልዩ ፓርክ፡፡

ፓርኩን የወረረ የመሬት ቀበኛ አላየሁም፡፡ ከብቶች ዝር ያላሉበት የሀገሬ የተፈጥሮ ሀብት ውስጥ መግባቴን አመንኩ፡፡ ወዲህ አርብቶ አደር ምድር ብኾንም የጎሳው ጠንካራ ህግ ገራሌን ታድጎታል፡፡

ኢንሹ ብቅ ጥልቅ ትላለች:: ኢንሹን እንዲህ ከጥንድነት ወደ ቤተሳባዊ ጉድኝት አድጋ ያየሁበትን ስፍራ አሞ ነው:: ኢንሹ ትንሽና ጥንድ ኾና የምትኖር ባለ ትዳር እንሰሳ ናት:: እዚህ ቁጥሯ ቁጥር የለውም::

ውሃ ኩሬ ጋር ደረስን:: ውሃ ኩሬውን ለማየት መኪናችንን አቁመን ወርደን ወደ ዳርቻው ተጠጋን:: መንገድ መሪው መሬቱን ዕቃ እንደ ጣለ ሰው አቀርቅሮ አሰሰው፤ ወደ ውሃው ስንጠጋ ኮቴ አየን:: የቀጭኔዎች ነበር::

አሁን እርግጠኛ ኾንኩ፤ ልቤ በደስታ ቀጥ አለች:: ቀጭኔ ከማየት አይደለም ጉዳዬ፤ ጉዳዬ የሀገሬን ቀጭኔ ከማየት ነው:: በኬኒያ ቅንጡ ሎጂዎች ቀጭኔ መስኮቴ ስር ስትውረገረግ አይቻለሁ፤ ያየሁት እስከጠግብ ነው:: ያቺን ትርኢት አቅራቢ የኬኒያ ቀጭኔ ስጠግባት ወዲያም "የኔ ሀገር ቀጭኔዎችስ?" ብዬ ስለ ሀገሬ ቀጭኔዎች ተርቤ ነበር፤ ረሃብተኛው በዳናቸው ደስታዬ ወሰን አጣ::

የሄዱበትን ዳና ተከተልን:: ፀሐይ ገብታለች:: እየመሸ ቢኾንም ጉጉት ብዙ መንገድ በእግር ተጉዘን እንድናስስ አደረገን:: አልተሳካም:: ሲነጋ አለ መሐመድ፤ እንዴት እንደሚነጋልኝ ባላውቅም እሺ አልኩ::

አንዱ ጥላ ስር ድንኳኖቻችን መጣል ጀመርን:: የጀንበርን የጥልቀት ብርሃን ተሻማናት፤

# የእሳት ዳር ጂኒዎች

"የሚያየው ሰው ባየው፤ ባይኑ እስከማለ
ዓይን ያላየውን፣ ደግሞም የሚያይ አለ።
የነጋ መሰለኝ.....
ፅልመት እንደሞራ፣ ብርሃን ጋረደ
ጨለማውን ደፍሮ፣ ማን ማየት ለመደ?!"

ኄኖክ ስጦታው። መንገድ የግጥም መድብል።

እሳት ዳር ነን። ጌታቸው የምሽቱ ንጉሥ ኾኗል። የገራሌ ዱር ጸጥ ባለበት ሰዓት የጌታቸው ወግ ዱር የሚያተራምስ እስኪመስለኝ ገዝፏል። ጨዋታ ይችላል፤ እንዲኽ አህዱ ሲባል እንደ ቆመ ቀራቢ ዓይኔን አፍጥጬ ያደምጥሁት ሰው በዘመኔ ትንሽ ነው። አንዱ ጌታቸው ታደሰ።
የሀረር ሰው ነው። በዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ውስጥ የፕላኒግ ባለሙያ ኾኖ ይሰራል። ሲጫወት እጁን ያወናጭፋል። መቀበል ሲከብደው "አቦ ተዋ!" ይላል።
"ስማ በአኘዋ ፈስ ነውር ነው። አይፈሳም፤ የፈሳ አይረሳለትም።" ጌች ምሽቱን ነግሶበታል። ጆሮ ሰጥተናል። ልባችን በምናብ አኘዋ ሄዷል። ጋምቤላ ባሮ ዳር ነን። ምዕራብ ኢትዮጵያ ገስግሰናል። ኡጁሉን በምናባችን ሳልነው።

ኡጁሉ ፈሳ፡፡ ልጃገረዶች ሁሉ መዝፈን ጀመሩ፡፡ ዜማው ኡጁሉ ሲፈሳ ኾነ፡፡ አልተቋቋመውም፡፡ እዚህ መኖር ከባድ ነው፡፡ ጌች ቀጠለ፤

"እንካ፤ ዘፈኑ ሁሉ ኡጁሉ መፍሳቱን የሚያሳጣ ሆነ፤ ትቀልዳለህ፤ ሚስት ሁሉ አያገኝም እኮ፡፡ ከዛ ኡጁሉ ሀገር ጥሎ ጠፋ፡፡ ሩቅ ሀገር ሄደ" ውሃ የያዘችውን የፕላስቲክ ጠርሙስ ፉት አላት፡፡ ሁላችንም የየራሳችንን እንደሱ ፉት አልናት፡፡ ስካውቶቹ ሜዳው ላይ አንጥፈው ጋደም ብለው እያደመጡ ነው፡፡ እኔ፣ ገብረመስቀል፣ ሰለሞንና ብስራት ጌችን ከበነዋል፡፡

ፉት ብለን ፊታችንን ስንጨመድድ ለተመለከተ ሃይላንዱ ምን እንደያዘች ይገምታል፡፡ ዳሩ ጨለማ ነው፡፡ ማንም ፊትና ግንባርን አይቶ አይገምትም፡፡

"ብዙ ቆይቶ መጣ፡፡ ኡጁሉ፤ ሰፈሩ ተራራ ላይ ኾኖ መረሳት አለመረሳቱን ለማወቅ ኡ...ጁ...ሉ... ብሎ ተጣራ፡፡ የሰሙት ሰዎች፤ ኡጁሉማ እኮ ፈሱን ፈስቶ ሀገር ጥሎ ከጠፋ ስንት አመቱ አሉት፡፡ ደንግጦ ወደ መጣበት ተመሰለ...."

ከአውራሪስ ኮቴ በላይ የሳቅ ድምጽ ዱር ሲያተራምስ አየሁ፤ ከዝኆን ኮቴ በሚብስ ጉልበት የሳቅ እንባ ጥሻ ሲያተራምስ ሰማሁ፡፡ ጌች የምሽቱ ኮኮብ፤ ጌች የእሳት ዳሩ ንጉሥ፡፡ የተኙት ልባቸው እኛ ጋር ነው፡፡ እንጨቱ ይጨመራል፡፡ እሳቱ ይነዳል፡፡ ወጉ ደርቷል፡፡

የጂኒ ጨዋታ ደራ፡፡

ጌታቸው እሳት እፍ ብላ ስላነደደችው ጂኒ መተረክ ቀጥሏል፡፡

"በዓይንህ አይተሃላ?" ሰለሞን ጠየቀው፤
"ምን ኾነሃል፤ እንዲህ ቁጭ ብዬ እኮ ነው፤"
ስለ ጂኒ ብዙ ተወራ፡፡ አንዳንዱ በጣም ፈራ፡፡
"ኺረ የእነሱ ሰዓት ነው" ራቅ ብለው ከተኙት አንዱ ነበር፡፡
"ይኹና እኔ አልፈራም፤" ጌች አልፈራምን ደጋግሚታል፡፡ ዙሪያውን ደግሞ አያምነውም፡፡ ባትሪውን ያበራል፡፡ ስሟን ከጠራ በኋላ በባትሪው ብርሃን አጠገቡ ያለውን ይፈትሻል፡፡ ጂኒ ስላገባው አንድ ወዳጃችን የጀመርኩት ጨዋታ የምሽቱን ድባብ ፍርሃት አስተኛበት፡፡

"ያውቃታል?" ጌች ከሳቅ ወደ ምሳጤ፤ ከምሳጤ ወደ ፍርሃት ገባ፤

አንድ ወዳጃችን መናፍስት አፍቅራው ነበር፡፡ አብሮን ኾኖ ብቻውን ያያታል፡፡ ምንም በሌለበት ፈገግ ይላል፡፡ ግባ ስትለው ራሱን ነቅንቆ ምልክት አሳይቶ ወደ ክፍሉ መሰስ ብሎ ይገባል፡፡ ጠዋት ሲወጣ ተደብድቦ ተፈነካክቶ እናገኘዋለን፡፡ ፍቅረኛው ቀናተኛ ነበረች፡፡ በዚያ ላይ ጉልቤ፡፡
ታደሰ ጸጋ የመናፍሱትን መንደር በገለጠበት መጽሐፍ የጂኒዎችን ሁኔታ በስፋት አብራርቶታል፡፡[31] ይኼንን በጨለማ ማውራት፤ ይኼንን ዱር ውስጥ ኾኖ መጫወት ዝም ለማስባል ጉልበቱ ኃያል መኾኑን የተረዳሁት ስጨርስ የካምፕ ሳይታችን ድባብ ሲቀየር ነበር፡፡

31. ታደሰ ጸጋ ጋዜጠኛ ነው፡፡ በሀገረሰባዊ ዕውቀቶችና ምስጢራት ጉዳይ ሰፊ ጥናት ሰርቷል፡፡ በጥንቆላ፣ የመናፍስት ጉዳይና ተያያዥ መረጃዎች ዙሪያ ያተኮሩ "የመናፍስቱ መንደር" "መናፍስቱ በሸለቆ ውስጥ" እና " ግዞተኛው ጂኒ" የተባሉ ሦስት መጻሕፍትን ለንባብ አብቅቷል፡፡

ጂኒዎሎጂስት የሚባል አንድ ወዳጅ ነበረኝ፡፡ መሐመድ ነው ስሙ፡፡ የዶርማችን ልጅ ነበር፡፡ ስለጂኒ ብዙ እውቀቶችን ያጋራን ስለነበር ጥናት ያደረገ ያክል አክብረነው የመጠሪያውን ማዕረግ አጎናጸፍነው፡፡

የኔና የጂኒን ታሪክ ከልጅነት ምዕራፌ ቀነጨብሁ፡፡
አንጅሶ ሰፈራችን ያለች ትንሽ ወንዝ ናት፡፡ እኔ በተወለድሁበት ሰፈር ያደገ ሁሉ በልጅነቱ አንጅሶ ይዋኛል፡፡ የዋናውን ያኽል ድንጋይ እያነሱ የወንዙን መካከል ከዳገት ላይ ሆኖ ወርውሮ በመምታትና በሞገዱ መጫወት ልማድ ነበር፡፡ እንዲህ ሳደርግ ውዬ ቤት ገባሁ፤

ማታ አያቴ ተቆጣች፡፡ እናቴን ልጅሽን ሰብስቢ አለቻት፡፡ አመድ ላይ ሲጨፍር ውሏል፡፡ እዚህ ቆሞ እቃዬን ፈጀብኝ፤ አልለቀውም ብሎ ሄደ፤ አለቻት፡፡ በወቅቱ ስሜት ባይሰጠኝም፡፡ ዛሬ ሳስበው አያቴ መቼቱና ድርጊቱን ሳተችው እንጂ ጂኒውስ እቤት መጥቶ ከሶኝ ኖሯል፡፡
እንደ ሌባ ሁሉም ተደብቆ እየደንኳኑ ገባ፡፡ ሲነጋ ቀጭኔዎቹን ፍሊጋ ለማሰስ ቀጠሮ ይዘናል፡፡

# ቀጭኔዎቹ የት ገቡ?

በጠዋት ተነሳን:: ከምሽቱ የጂኒ ወግ ፍርሃት ያልተላቀቀም ነበር:: እንደ ወታደር ተሰልፈን በእግር ጉዞው ቀጠለ:: እኔ ከፊት ሦስተኛው ነኝ:: መንገዱን የሚመራው ከሙባረክ የያዝነው የሚኒሺያ ኃላፊ ነው:: ይፈጥናል፤ ግን ተከትለነዋል:: ቀጭን የእግረኛ መንገድ መሳይ ጎዳና ይዘን እየገሰገስን ነው::

መንገድ ተአምር ያሳየናል:: መሻታችን ግን ቀጭኔን ነው:: እዚህም እዚያም ብዙ እንስሳ ይታያል:: ዳልጋ አንበሳ ሲያቋርጠን፤ ቀጭኔ ፍለጋ የምንጣደፍ ስለነበርን አልተገረምንም:: አርባ ሁለት የሚደርስ አጥቢ የዱር እንስሳ ዝርያ በተመዘገበበት ብሔራዊ ፓርክ ነው:: ቀጭኔ ካላየሁ የሚል ልብ ይገሰግሳል::

ነብር፣ አንበሳ፣ ዝሆን፣ ተኩላ፣ የዱር ድመት መኖሩ ተነግሮናል:: አውራሪስ አየሁ ያለ ሰው አብሮን እየተጓዘ ነው:: ከሁሉም በላይ ያጓጓን ቀጭኔ ነው::

ቀጭኔ እንደ ዝኆን ለጥርሷ፣ እንደ አውራሪስ ለቀንዷ፣ የጠፋች እንስሳ አይደለችም። ለጭራዋ ሞትን እንደ ጽዋ ያጣጣመች ፍጥረት ናት።

ቀጭኔን በሀገሬ ምድር አየሁ የሚል ሰው አሞ ማኅና ገራሌ ነው ያለው። ጋምቤላ እንዳለ ይናገራሉ። ሁሉም ምስል አስቀርተው አያወሩም። የአሞው ሰካውት የመጨረሻዎቹን ዘጠኝ ቀጭኔዎች እንደቀጠሩ ነግረውኛል። ከዚህ ትረካ በኋላ በኃይሉ የሚባል የGF6 ፕሮጀክት ባልደረባ ስድስት ቀጭኔዎች ታማ ጥብቅ ሰፍራ አየ። አብረውት ሰዎች ነበሩ፤ ብርቅ የሆነባቸው ጉዳይ ሲያንጫጫቸው ቀጭኔዎቹ ሽምጥ ጋልበው ነበር።

ቀጭኔ አፍሪቃ ውስጥ ብርቅ ያልነበረች እንስሳ ናት። በድፍን አፍሪቃ ነበረች የሚለው ታሪኳ ዛሬ የማይታመን እውነት ኾኗል። ባለ አራት ጡቷ ቀጭኔ፤ አንገተ ረዥሟ ቀጭኔ፣ በሀገሬ ምድር ብርቅ የኾነችው ፍጥረት፤

መንገድ መሪው ድንገት ቆመ። አብረን ቆምን። መሬት ላይ ዓይኑን ተክሎ አንዳች ነገር ሲፈልግ ያየውን አብረን አየን። የቀጭኔ ዳና፣ ትኩስ የቀጭኔ ዳና። ፍጥነት ጨመረ፤ ተከተልነው። ዳናው ሰውዬውን፤ እኛን ሰውዬው እየመሩን ተከታተልን።

ቀጭኔ ከእንስሳት ሁሉ ረዥሟ አጥቢ እንስሳት ናት ይላል ሳይንሱ፤ አንድ ወንድ ቀጭኔ እግሩ ላይ ሜትር አድርገው አናቱ ድረስ ቢለኩት አምስት ሜትር ይደርሳል።

"giraffe" የሚለው የስሟ ትርጉም ከቀደመውና "zarafah" ከሚለው አረብኛ ቋንቋ የተቀዳ ነው:: ቀጭኔ ይኼንን ስም ያገኘችው ገሪ ከሚለው የሱማሊኛ ቃል ነው:: ያለሁት ገሪዎች ምድር ነው:: ስምን መልአክ እንደሚያወጣው አምኛለሁ:: የስሟ ትርጉም ፈጣኗ ተራማጅ ማለት ነው የሚለውን ተራምዳ የሄደችበትን ሮጠን አልደርስ ስንል በአግባቡ ተረዳሁት::

እንፈጥናለን፤ ዳናዋን እንጂ እሷን አላገኘናትም:: እርግጥ ነው ረዣዥም እግሮች አሏት:: ቀኑን ሙሉ የሄድነውን አንዴ ትራመደውም ይኾናል:: ከሁሉም የሚከፋው ግን በሰዓት እስከ 60 ኪሎ ሜትር መጓዝ የምትችለውን እንስሳ እየተከተልን በመኾኑ ነው::

ቁጥራቸው ስድስት እንደሚደርስ መንገድ መሪውና የፓርኩ ሰዎች ዳና ቆጥረው ነግረውናል:: ረዥሟ እንስሳ በጠባቡ ጆሮዋ ሩቅ ትሰማለች:: ዓይኗ ጎላ ያለ ማራኪ ናት:: እንደ አንገቷና እንደ እግሮቿ ሁሉ ቅንድበ ረዥም በሚለው ትታወቃለች::

ቀደም ባለው ጊዜ የውበትና የፍቅር ምልክት ስለኾነች ነገስታት ሥጦታ የሚሰጣጡት ቀጭኔ ግልገል እንደኾነ አንብቤአለሁ:: በሰባ ወር የምትወልደው ቀጭኔ ዛሬ ቁጥሯ እንዲህ አደጋ ውስጥ ሳይገባ በድፍን አፍሪቃ የምትኖር የአህጉራችን ጌጥ ነበረች:: እንደ ቀጭኔ ረዣዥም የነበሩት ካፍያኖች ከክ. ልደት በፊት ከ8000 እስከ 6000 ባለው ጊዜ በሰሃራ በርሃ የነበረው ጠንካራ መንግስት ባለቤቶች ናቸው::

አዳኞቹ ካፍያኖች የሰሃራን ውብና ብዙ ቀጭኔዎች ጨርሰዋቸዋል፡፡ ዛሬ እነሱ ያስቀሩት የዋሻ ውስጥ ቀደምት ስዕል ብቻ የቀጭኔና አፍሪቃውያን አብሮነት ምልክት ተደርጎ ለታሪክ ቀርቷል፡፡ አንገተ ረዥሟ ቀጭኔ በኢትዮጵያ ለምን ጠፋች ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ በዝቶ ያገኘዋል፡፡

ጠዋት ቢሆንም ይሞቃል፡፡ የብሔራዊ ፓርኩ ቆዳ ስፋት 1734 ስኩዬር ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ረዣዥም የግራር ዛፎች ከምንሄድበት መንገድ ውጪ እናይ ዘንድ የፈቀዱልን ቦታ የለም፡፡ ጥቅጥቅ ያለው እጽዋት እንዴት አድርጎ አስመለጣቸው የሚለውን የራሴ ጥያቄ አልተመለሰልኝም፡፡ በኢትዮጵያ ያሉት የቀጭኔ ዝርያዎች ሁለት ናቸው፡፡ አንዱ የኑቢያው ነው፡፡ Giraffa Camelopardalis ሌላኛው Giraffa Reticulated ይባላሉ፡፡ አሁን የምገኝበት ስፍራ የ Giraffa Reticulated የቀጭኔ ዝርያዎች መኖሪያ እንደኾነ የታደሰ አባተ factors affecting the survival of giraffe in Ethiopia በሚለው ጥናቱ አስፍሮታል፡፡

ቀጭኔ በቀደመው የአፍሪቃ ስልጣኔ ውስጥ ብዙ አሻራዎች የነበሯት እንስሳ ነበረች፡፡ የአፍሪካ ፓርክና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አንድ ጥናት የኑቢያ ቀጭኔ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የቻይና ምድርን ለመጀመሪያ ጊዜ መርገጧን ይገልጻል፡፡ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስትም ይኼንን ወቅት 1416 እንደኾነ ጽፈዋል፡፡ ገሪን የሚለው ቃል ምናልባትም ያኔ ስፊ መጠሪያዋ ነበር፡፡[32]

32. *RICHARD PANKHURST, An Interoduction to The Economic History of ETHIOPIA, page 367*

በቀን 34 ኪሎ የሚመዝን እጽዋት ትመገባለች:: ማኅበራዊ ናት፤ ከሁለት እስከ ሃምሳ ቀጭኔ አንድ ቡድን ኾኖ ማየት ብርቅ አይደለም::

ስድስት ናቸው የተባሉትን አየኋቸው ለማለት እዚህ ዱር ውስጥ ሰዶ ማሳደድ ይዘናል:: ቀጭኔዎቹ ድምጻችንን ሰሙ፤ ግምት ነው:: የሩጫቸው አቧራ ግን ታየ:: ዳናቸው ጋር ስንደርስ ምድሩን ቆፈረው በረዋል:: ያ እርምጃ ሳይደረስበት እንደገና ሩጫ ታከለበት:: ተበትነን ፈለግናቸው:: ፈጥኖ የተከተለው መንገድ መሪ ያነሳው ምስል የማይኾን ነበር:: ከቀጭኔዋ ይልቅ ያቦነነችው አቧራ ጎልቶ ይታያል::

የኔ ሀገር ቀጭኔዎች ሰው ይሸሻሉ:: እውነታቸውን ነው:: የኔ ሀገር ሰው ለጌጡ፣ ለውበቱ፣ ለሆዱ ሲያድናቸው ኖሯል:: አሳሹ ብሩስ በኢትዮጵያ ቆይታው በዐፄ ዮስጦስ ዘመን ይታደኑ ስለነበረ ቀጭኔዎችና አውራሪሶች ነግሮናል::[33]
የዐፄ ዮስጦስ ዘመን ሩቅ ነው:: በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ኢትዮጵያን የረገጠው ፖል ኮተን በወልቃይት ምድር የነበረውን ቀጭኔ ሲገልጸው የተትረፈረፈ ብሎ ነበር::[34] ዛሬ ግን እንዲህ ነጭ ላብ እስኪያልበኝ ተከትዬም ከሀገሬ ቀጭኔ መተያየት አልቻልኩም:: ቀጭኔ ጉዳይ ከፍ ብሎ ሲከበር፤ ቀጭኔ አጥፊ ሀገር ኾነን እየተዋረድን ነበር ለካ:: የእኛ የኾኑት እንስሳት ሲርቁ ጥፋታችን ጓዝ ጠቅለለው የሄዱበት ጎዳና እንደሆነ አላሰብንም::

33. James Bruce KINNAIRD, ESQ,F.R.S ,TRAVELS TO DISCOVER THE SOURCE OF THE NILE, Vol 2 page 540

34. Powell-Cotton, A SPORTING TRIP THROUGH ABYSSINIA, page 486

አሌክሳንደር ቡላቶቪች የተባለውና ከዐፄ ምኒልክ ሠራዊት ጋር ወደ ደቡብ ጠረፍ የተጓዘው ምስክር ደግሞ በአሞ ኪቢሽ ወንዝ ዳርቻ መጋቢት 23 ቀን የቀጭኔ መንጋ ተመለከትን ሲል ቁጭት ሰንዶልናል::[35]

ድካም እና ያሰብነው አለመሳካቱ ቅሬታ ውስጥ አልከተተንም:: ደስ ብሎናል፤ ምክንያቱም ቢያንስ ቀጭኔዎቹ አሉ:: የት ገብተው ይሆን? ለሚል ገራሌን ለብዙ ቀናት ማሰስ ይኖርበታል:: አሊያም ውሃ ዳርቻዎች ማድፈጥ፤ ያዩ ሰዎች ሲጠቁሙም ቁጥራቸው ስድስት መሆኑን ነግረውናል:: ከቀናት በፊት ተመለከትኩ ያለ ሰው ደግሞ ሰባት ናቸው ብሏል:: ሰባት ሆነን ገብተን አንዳችንም በካሜራችን ሳናስቀራቸው፤ ወይም በዓይናችን ሳናያቸው ተመለስን:: የጠረፉ ዳሩ ውበት ድንቅ የተፈጥሮ ቅርስ ነው:: አንድ ቀን የገራሌ ቀጭኔዎችን እያቸው ይሆናል::

የጌኖከ ስጦታውን ግጥም ደግሜ አሰብኳት::

> *"....ዓይን ፈራጅ ብቻ፣ ሲል ሰማሁ "ታወረ"::*
> *ብርሃን የገባው፣ እስኪበቃው አየ፤ ፀሐይን ደፈረ*
> *የገባው ይበቃል.....*
> *ያየ ሰው ምን ገባው?!*
> *ላላየስ ምን ቀረ?!"*

35. አሌክሳንደር ቡላቶቪች:: አምባቸው ከበደ ተርጓሚ:: ገጽ 201

# ከግዙፉ እንሰሳ ጋር፤

ከገራሌ የምናብ ጉዞዬ የመለሰኝ ድንጋጤ ነው፡፡
ያ ሁሉ ወኔ የት ጠፋ? መፍለግን ፍርሐት እንዲህ ሲያሸንፈው ሳይ ራሴን ታዘብኩት፡፡

ነገር ነበር በሚባልባት ሀገር አለ ሲባል ሰምቶ መምጣት ብልጠት መስሎ ተሰምቶኛል፡፡ ከአስፈሪው እንስሳ ጋር ተፋጠጥን፡፡ ወኔ ጠፋ፡፡ ፈራሁ፡፡ እንዲኽ ያለውን እንስሳ ዓይቶ የማይፈራ ማን ነው? በጥንቃቄ ልረግጥ ነበር፤ አንድ ሜትር ተኩል ስፋት ያለው ጆሮ የትኛው ጥንቃቄ እንዳይሰማ ያደርገዋል፡፡ የአዳነ ገለጻ በጆሮዬ አስተጋባ

'ዝሆን በአማካይ በቀን 300 ኪሎ ሊመገብ ይችላል፡፡ በቀን አስራ ስድስት ሰዓት ይመገባል፡፡ ቢያንስ 150 ኪሎ ግራም እበት ይጥላሉ፡፡' አዳነ የነገረኝን ለመርሳት ስሞክር፤ የዝሆን ሳይንቲስቱ ዶክተር ይርመድ ደመቀ የጻፉት መልሶ ወደ አእምሮዬ ይመጣል፡፡

"ዝሆን የኩንቢው ክብደት 140 ኪሎ ግራም ይመዝናል:: ኩንቢው ብቻውን እስከ ሦስት ሜትር ርቀት ላይ ያለን ነገር በቀላሉ ለመድረስ ይችላል:: ውሃ የሚጠጣውም በኩንቢው ነው:: በአንድ ጊዜ 12 ሊትር ውሃ በኩንቢው በመሳብ ወደ አፉ ይጨምራል:: በኩንቢው ያሸታል:: የሰውን በአካባቢው መኖር እስከ አንድ ኪሎ ሜትር ርቀት በሽታ ማወቅ ይችላል:: በግጥሚያ ጊዜ ኩንቢውን እንደ እጅ አጥብቆ ለመያዝ ይጠቀምበታል::"[36]

"the book of animals" ብልጥ እንስሳ ይለዋል::[37] በዚያ ላይ ደግሞ ባለ ብሩህ አእምሮ፤ ይኼ ከግዙፍ ሰውነትና ምድርና እንዳሻ ከሚያደርግ ጉልበት ጋር ሲዳመር መትረፍ ሆይ ከወዴት አለሽ? ያስብላል::

ግዙፍ ግንድ የጣለ ዝሆን በኩንቢው ያሻውን ሲያደርግ ፊት ለፊቱ ሆኜ አየሁ:: ግንዱን ቁርስ ቢጤ ቀመስ ሲያደርግ ተመለከትሁ:: ምድሩ ረግረግ ነው:: ጭቃው መንገድ መሪ ካላገኘ ውጦ ያስቀራል:: ጉልበቱን የተማመነው ዝሆን ረግረጉን ረግጦ በደለደለው ጭቃ ኡቴ ተጠንቅቆ ረግጦ ወደ መሀል ተጠጋ፤ በምልክት ጠራን:: ፍርሃት የመጨረሻው መለኪያ ላይ ናት:: ተጠጋን:: ከብዙ ዝሆኖች ጋር ተፋጠጥን:: ምድሩ ተንቀጠቀጠ:: የጨበራ ሳር ዛፍ መኾኑ የገባኝ ዝሆን መዋጥ ሲችል ነው:: መቅረጽ ቅንጦት ኾነ:: ምድሩ ሲርድ ልመናው አውጣኝ ብቻ ኾነ:: ሰማዩን ቀና ብዬ አየሁት፤ እንደ ምድሩ የሚርድ መሰለኝ::

36. ዝሆን:: ዶክተር ይርመድ:: ገጽ 2

37. John Lloyd እና John Mitchinson,the book of animals, page 66

የዝኖትን ብዛት ሳይ ዳውሮና ኮንታን አደነቅሁ፤ ሲፈልገው መንደር ገብቶ እያመሰ፤ ሲያሻው ሰው ሳይቀር እየተጋጨ፤ ታግሰውት ጨበራ ጨርጨራን እንዲህ የአፍሪካ ዝኖች መበረቂያ አድርገውታል።

ቅዱሱ ሊቅ ዮሐንስ አፈወርቅ በሰውና በእንስሳት መካከል ያለን ግጭት የገለጸበት መንገድ ትዝ አለኝ። እንዲህ ይል ነበር ያነበብሁት። "በአንድ በኩል እኛን ባዮ ጊዜ ሸሽተው ይኼዳሉ እንጂ ወደ እኛ ገስግሰው አይመጡም። በሌላ መልኩ ደግሞ ጉዳት ቢያደርሱብን እንኳን ከራባቸው ወይም ከተተናኰልናቸው ነው። ይኽ ደግሞ በእኛ ላይ ስለ ሠለጡኑ ሳይኾን ከእኛ ችግር የተነሳ ነው። ከእነዚህ የምድር አራዊት አንዱ ጥቃት የሚያደርስብን እኛ እነርሱን ለመጉዳት ብለን መሣሪያ እንደታጠቅን ሲመለከቱ ነው።"[38]
የዛሬ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት ገደማ እንዲኽ ያለ የአካባቢ ጥበቃ ፍስፍናና የሰው ልጅና የዱር እንስሳትን ግጭት በዚኽ ዕይታ የሚያስታርቅ ሀሳብ ሳይንሱ የደረሰበት ዛሬ ነው። ዛሬ የኮንታንና የዳውሮን ገበሬዎች ከዝኖን ቁጣ የሚያስጥላቸው መፍትሔ አልተገኘም። ያም ኾኖ ዝኖንን በክብር ጠብቆ ማኖር የቻለው ይኽ ህዝብ ነው።
ኢትዮጵያ ውስጥ ዝኖን አደጋ ውስጥ የገባው ዛሬ አይደለም። የቀደሙት ዓለም ሳይነግራቸው ደርሰውበታል። ደጃዝማች ገብረእግዚአብሔር ዝኖን በሀገራችን ታጥቷል ብለው ለንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ደብዳቤ የጻፉት ሚያዚያ 22 ቀን በ1899 ዓ.ም. ነበር።[39]

38. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ። ገብረ እግዚአብሔር ኪደ። አሪት ዘፍጥረት ድርሳን 1-18። ገጽ 160

39. ጳውሎስ ኞኞ። አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች። ገጽ 160

ዐፄ ምኒልክም ዝም አላሉም:: ያዳኞች ደንብ 2ኛው አዋጅ ላይ ትልቅ ጥርስ ያላወጣ ዝሆን እንዳይገደል ደንግገው ነበር:: ትንሽ ዝሆን መግደልም እንደሚያስቀጣ አስፍረዋል:: ለዚህ ደግሞ አዳኝ ለዋስትና 50 ብር ያሲይዝ እንደነበር ነው ዝክረ ነገር የሚነግረን::[40]

ዐፄ ምኒልክ በዚህ ጉዳይ የጻፏቸው ደብዳቤዎች ለአወጡት ህግ ምን ያክል ትኩረት እንደሰጡ ማሳያ ነው:: ጥር 4 ቀን 1900 ዓ.ም. ለራስ ተሰማ በጻፉት ደብዳቤ ዝሆን ልግደል ያለው የራስ ተሰማ ባለሟል የሚገድለው ዝሆን ጥርስ የሌለው ወይም ትንሽ የኾነ እንደኾነ አስረህ ስደድልኝ ብለውታል::[41]

ዛሬም ከመቶ ዓመት በፊት እንደነበረው ዝሆን ከኢትዮጵያ ምድር ይጠፋል የሚለው ስጋት አልተቀረፈም:: ዛሬም በዝሆን ጉዳይ አዋጅና ደንብ ማውጣት ደንብ ኾኖብን ቀርቷል:: ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ያኔ እንዲህ ያሉ ህጎች እየወጡ "ኢልካ ሰባሪ" የሚባሉ ስድስት ዝሆን ገዳዮች ድሪና ጉትቻ አድርገው ሲሞገሱ ማየታቸውን ነግረውናል::[42]
እንዲህ ካለው ጥፋት የተረፈው ቁጡ ዝሆን አጠገብ ነኝ:: የዝሆኑ ምድሩን ማተረማመስ ድምጹ እየጎላ ሲመጣ የበለጠ እያስፈራኝ መጣ:: ኡቴም እንደ እኛው ስጋት አደረበት:: ቀስ አድርጎ ወደ አንድ ከፍ ያለ ቦታ እየመራ ወሰደን::

40. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል:: ዝክረ ነገር:: ገጽ 344
41. ጳውሎስ ኞኞ:: አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች:: ገጽ 291
42. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል:: ዝክረ ነገር:: ገጽ 342

ድንገት ስልኬ ጠራ፡፡ አነሳሁት፤ ድምጼ ያለከልክ ስለነበር በደንብ ማውራት አልቻልኩም፡፡ ሰለሞን ወርቁ የሚባል የዱር እንስሳት የኮሙኒኬሽን ባለሙያ ነበር የደወለልኝ፡፡ ጫካ የገባ ሰው እንዴት ኾንክ ማለት ወግ ነው፡፡ ጥያቄውን የመለስኩት በቀልድ አጅቤ ነበር፡፡

"ስማ በዝሆን ተከብቤያለሁ፤ ያን የጅማውን ቤት አንተ ውሰደው፡፡ የባህር ዳሩ ቤት ለልጆቹ ይሁን፤ የአዳማው ሱቅ....መኪናው...." አልጨረስኩም፤ ኡቴ አቋረጠኝ፡፡
"ቆይ እስቲ ሀብት አታባክን፤ የመትረፍም እድል አለን፤ እንወጣለን፡፡" አለ፡፡ ደነገጥሁ፡፡ በጣም ደነገጥሁ፡፡ የመትረፍም እድል...ደጋግሞ ድምጹ አቃጨለ፡፡

አዳነ እንደ ጦር አዛዥ ያለ ስጋት እንድንወጣ ቆራጥ አመራር መስጠት ጀመረ፡፡ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ቆመን የሚተራመስ ድምጽ ሰማን፡፡ ዝሆኖቹ ቀረቡ፤ ዮናታን አጠገቡ ያለው ዛፍ ላይ ወጣ፡፡ የታየውን ለመቅረጽ ካሜራውን ወደረ፤ ግን አደጋው ባሰ፡፡

ያለንበት ከፍታ በምን ዓይነት መዓት መከበባችንን ያየንበት የጭንቀታችን ማማ ኾነ፡፡ ከሁሉም የበለጠ ያሳሰበኝ የሹሩሬ ጉዳይ ነው፡፡ ሹሩሬ ዝሆን ነው፡፡ የተቆጣ ዝሆን ከሰው የሚያስታርቀው ያጣ ዝሆን፡፡ ጆሮው ቀለበት ነው፡፡ የበሳውን ነገር ያወቀ የለም፡፡ ምናልባት ጥይት ሊኾን ይችላል፡፡ ይኼንንም ለመገመት የተሞከረው ለሰው ካለው ጥላቻ የተነሳ ነው፡፡

ብዙ ሰው ገድሏል፡፡ በኩንቢው ጥሪ ስለሞቱ ሰዎች አሰብኩ፤ ከዚያ ወደ እኔ የሚመለከተው ዝ·ሆን ሁሉ እሱ መሰለኝ፡፡ ቀለበት ውስጥ መግባታችንን ያወቀው ኡቴ ድምጽ አሰማ፡፡ ጥድፊያ ኾነ፤ እኛን ቅደሙ ብሎ በመራን መንገድ ለማለፍ ካለሁበት ስዘል የዝ·ሆን እግር የፈጠረው ረግረግ ውስጥ ገባሁ፡፡ እኔን መጎተቱ ቀጠለ፡፡ አላደከምኳቸውም ብዘገይ የሚከተለኝን አውቄ ስለነበር መንጭቄ ወጣሁ፡፡

ግማሽ አካሌ ጨቀየ፡፡ ዱር መሰልሁ፡፡ በጥንቃቄ ተሹለከለክን፡፡ አምልጫለሁ ማለት የሚቻለው የት ሲደረስ ይኾን?

# ከጎፉዎች ጋራ!!
# በምድር በር-ምድር፤

ካየኸው በላይ ማን ይነግርሃል.....?
" ካየኸው በላይ ማን ይነግርሃል.....
ከሰማኸው በላይ ማን ያሻግርሃል
ካበቀለህ በላይ ማን ይማግርሃል
ሌላ መጣ ቀረ ምን ያደርግልሃል....?
ብቻ ተመልከተው..... ማየትን አትተው....
ላንተ ቢጤ ድንጉጥ አሞት የከተተው.....
ዓይንማ ዘመድ ነው--ውበት ካልጠለፈው
ዓይንማ ወዳጅ ነው--ማድ ካልከለፈው
ሁሉንም ሁሉንም-ሁሉንም ባንድነት
ሁሉንም አዋህዶ--
አይቶ ያሳድራል- ለይቶና አዋዶ----
"

መሉጌታ ተስፋዬ አያ ሙሌ
የነብያት ጉባኤ

.....ተራራ ስር ነኝ::

ሠላም የበዛላት ከተማ ያደረ ሰው መንጋቱን እንዲያውቀው በረብሻ የሚቀሰቅሰው ድምጽ አይኖርም:: ሳልረበሽ ነቃሁ:: አየሯ ቢሞቅም የዛፍ ሀብታም ናት:: አረንጓዴ የሚለው ይገልጻታል:: ከጀርባዋ የተዘረጉት ተራሮች ፎቶ ቤት ገብታ በተወጠረ ሸራ ላይ የተሳሉ ተራሮች ስር ፎቶ የተነሳች ኮረዳ አስመስለዋታል:: ግን እውነት ናቸው:: ከደጋማው የጎፋ ምድር ጋር የለዩዋት እውነቶች::

የምድር በር ነኝ:: ከመጣሁ ቀናት ተቆጥረዋል:: ከጎፋዎች ጋር ብዙ ቀን አንድ ነው:: ጊዜው ምን ቢኼድ አይሰለችም:: ያየነውን እንመሰከራለን እንዲሉ አበው፤

ምድር በሯ እዚህ ነው:: ያወጣ ማነው? ብዬ ብጠይቅ መልስ አጣሁ እንጂ ሰሚስ መልዓክ ያወጣው ነው:: ምድር ያለው ከሳውላ ወዲያ ነው:: እዚያ ሰው አለ፣ አብሮ መኖር አለ፣ መስቀል ያገዘፋቸው ተራሮች ሞገስ አለ፣ የካዎዎች ያልተነገሩ ታሪኮች ገና አልተሰሙም::

ሳውላ የሁለት ፊደል ጥምር ነው፤ "ሳኣ" እና "ውላ" ከሚባሉ የጐፋ ቃላቶች የተገኘ፤ በጎፋ ብሔረሰብ ቋንቋ "ሳኣ" መሬት ማለት ሲሆን "ውላ" ማለት ደግሞ መግቢያ በር ማለት ነው:: "የምድር በር" የሚለው አንድ ላይ ሲነበብ ሙሉ ስሟ ይኾናል:: በምድር በር ምድር ላይ ነኝ::

ከመኝታዬ ተነሳሁ:: ከተማዋ አንብርት ላይ ከሚገኘው ፕሮቶኮል የተባለው ሆቴል ነው ያረፍሁት:: አየሯ አይረብሽም:: የጎፋዎች መዲና ናት፤ የፖለቲካ ብቻ ሳይኾን የባህል መዲናቸው፣ የማኅበራዊ መስተጋብር ማማቸው፣ የትዝታ መድረካቸው፣ ለታላላቆቹ የጎፋ ነገሥታት የታሪክ እንደበታቸው::

ወጣሁ፤
ሀገር በቀል ዛፎች ግራና ቀኝ ያጀቧቸው ጎዳናዎች አሏት፡፡ ጎዳናዎቿ እንደፈረሰ፤ ሞተር ሳይክል በሚጋልቡ ወጣቶች እንደ ደመቁ ነው፡፡ ገና ስገባ የተቀበለኝ የመንገድ ዳር ዘንባባዋ ነበር፡፡ እንደ እድሜ እኩዮቿ እንደነ ሀዋሳ፣ እንደነ ባህር ዳር የዘንባባው ዘመን ከተማ ናትና በዘንባባ አሸብርቃለች፡፡ ዘንባባ አቁማ የምሥራች ሰብካ የምትቀበል ከተማ ውስጥ መከረም ደስ ይላል፡፡

አዲስ አበባ 516 ኪሎ ሜትር ርቃኛለች፡፡ ለምድር ግን ቅርብ ነኝ፡፡ ምድር በር ኾኖ ምድራዊ መኾን ጸጋ ነው፡፡ 'ጸጋህን ቁጠር' እንዳለው ደራሲው፤ ስነሳ ጸጋዬን ቆጥሬአለሁ፡፡ በላይ መጣ፡፡
ድምጹ ከሚጋልባት ሞተር እኩል ያስገመግማል፡፡ የጎፋን ባህል ከነፍሱ ያዋደደ ጎፋ ነው፡፡ ሞተሩ ላይ ጫነኝ፤ ቁርስ ለመቅመስ ወደ ስጋ ቤት ሄድን፤

ከተማዋን ለምጄታለሁ፡፡ በዓይን ያዩኝ ሰዎች ሰላምታ አይነፍጉኝም፡፡ ቶሎ የሚግባቡ ነዋሪዎች የሞሏት ከተማ ውስጥ መቆየቴን ሳስብ የምድር በር ብቻ ሳይኾን የምድር ሆድ ውስጥ ያለኹ ይመስለኛል፡፡
ጎፋዎች ጎደሎ የኾነችዋን ምድር ሙሉ አድርጌ እንዳስባት አድርገውኛል፡፡ ስጋ ቤቱ በራፍ ብዙ ሞተር ሳይክሎች ቆመዋል፡፡ ጾም ካልሆነ የሳውላ ቀዳሚው ምግብ ስጋ ነው፡፡ ጥሬ ስጋ በአዋሽ ወይን፤ ሳውላን ይሄ ይገልጻታል፡፡ ወደ ውስጧ ሰፊ ናት፡፡ እንግዶቿ ርቀት አይገድባቸውም፡፡

ከመሎ እስከ ኡባ፣ ከቡልቂ እስከ ማዜ፣ ከገዜ እስከ ዛላ........ሁሉም ጎራ ብሎ የልቡን የሚያደርስባት መዲና፤ ጥሩ ቁርስ በላን:: መርፌ ያላለጠለጠውን በሬ ስጋ ጠገብኩ ብሎ መውጣት ሃጢአት አይኾን? የሳውላን ስጋ ቤቶች ከፍሎ ብቻ ሳይኾን አመስግኖ መውጣት፣ መርቆ መለየት በረከቱ ለራስ ነው::

ሳውላ በ1953 ዓ.ም. ስትመሰረት ከቡልቂ ቀጥሎ ሁለተኛዋ መዲና እንድትሆን ታስባ ነበር:: በሶስት ዓመት ውስጥ ግን ታሪኳ ተቀየረና የአውራጃው መናገሻ ሆነች:: ሰሊጥ፣ በቆሎና ቡና እንደልብ የሚመረትበትን ገበሬ ስለከበበች እድገቷ ፈጠነ፤ እየተበደለች ያደገች ከተማ ኾነች:: ማነቆዋን በጥሳ ዛሬ ደረሰች::

በንጉሱ ጊዜ የገበያዋንና የንግዷን እንቅስቃሴ ያጤኑ አባት 'ፈለገ ነዋይ' በሚል የቀደመው ስሟን ቀይረውት ነበር:: ከአብዮቱ በኋላ ንጉሱ ሲወርዱ ፈለገ ንዋይ የሚለው ስምም አብሮ ወረደ፤ ሳውላ ከዚያን ግዜ ጀምሮ እስከአሁን ዳግም መጠሪያዋ ሆነ::

ደገኛዋ ቡልቂ ከሳውላ አናት የቆመውን ተራራ ስንጥቀው ከወጡ ትገኛለች:: የሳውላ ሰው ቀዝቃዛ አየርና የማር ጠጅ ሲያምረው ቡልቂ ይከትማል፤ አናናሱን ከአይዳ የምትጭነው ሳውላ ጓዳዋ ሙሉ ነው::
ገበያዋ ነፍሱን እስኪያጣ በገበያተኛ ይተራመሳል:: ሳውላ ገበያዋ በሚውልባቸው ቀናት ማለትም ቅዳሜ፣ ሰኞና ሐሙስ አመት በዓሏ ነው:: የገጠሩን ወዝ ሳትለቅ ከተሜነቱን ተዋኽዳለች::

ባታመሽም ሰላማዊ ከተማ ናት:: ድብድብና ጩኸት የማያደምጡባት ከተማ:: ከኡኡታ የራቀች የተራሮች ግርጌ፤

ጎዳናዋ ላይ ቆሜ ዙሪያዋን አየኋት፤ ተራሮች ከበዋታል:: ቁልቁል በረከታቸውን ይለቃሉ፤ ያ በረከት ቆላ ውስጥ እርፋ የማይሰለች አየር ያላት አድርጓታል:: ቀና ብዬ ሳየው ያየኝ መሰለኝ፤ ሰው አይደለም ተራራ ነው:: ዱዛ ይሉታል ሳውላዎች፤ ዱዛ ተራራ የሳውላ ሞገስ ነው:: ደግሞ የታሪኳ ማኅደርም ኾኖ ኖሯል:: ጣሊያን ሀገራችንን ሲወር ጎፋና አካባቢውን ለመቆጣጠር የመሸገበት ቦታ ነበር:: በ1962 ዓ.ም. ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እንደኔ ጎፋን ለመጎብኘት ሲመጡ ዱዛ እናት አረፋና የጎፋን ምድር አድማስ እስከቻሉት ድረስ ቃኙ::

ጎፋ ስከርም ጎፋ መኾን ብቻ ሳይኾን ኢትዮጵያዊነትንም እይቻለሁ:: ጎፋዎች የአባቶቻቸው ልጆች ናቸው:: አባቶቻቸው አድዋ ነበሩ፤ አባቶቻቸው ማይጨው ዘምተዋል፣ አንቺምና መኢሶ የጎፋ ጦር ጀግንነቱን አስመስክሯል::
በጣሊያን ወረራ ለሀገሬ ያሉ የጎፋ አርበኞች ቁጥራቸው ብዙ ነው:: ለኢትዮጵያዊነት ዋጋ ከከፈሉ አባቶች የተገኙ ልጆች መሃል መኾን መባረክ ነው:: ተባርኬአለሁ::

አራት ሰዓት ሲኾን ቀጠሮ አለኝ:: ከጎፋ ካዎዎች አንዱን አገኛለሁ:: የባዮ ካዎ ቀጠሮ ይዘውልኛል:: ካዎ ስል ንጉሥ እያልሁ ነው:: ጎፋ አምስት ነገሥታት አሉት፤ አንዱ ባዮ ነው:: ጎፋ፣ ዛላ፣ ዑባና ማሎ ካዎዎችን ሲጨምር በጠቅላላ አምስት ካዎዎች ይኾናሉ::

ሰዓቴ ሲደርስ ወደ ባዮ ካዎ መኖሪያ አቀናሁ፡፡ በቀጠሮዬ እየተጠበቅሁ ነበር፡፡ የመኖሪያ ቤቱ ሞገስ አንዳች መልዕክት ሰጠኝ፡፡ ከአካላዊ ግዝፈቱ ይልቅ የቤቱ መንፈሳዊ ድባብ የጎፋን ትናንት የካዎዎቹን የቀደመ ክብር በምናብ መልሰ አሳየኝ፡፡ ሠላምታ አቅርቤ ቁጭ አልኩ፤

አንጋፋው ሰው ጋቢ ነው የለበሱት፤ አርጅተዋል፡፡

ጉጃ አሻ ይባላሉ፡፡ ሳውላ መኖር የጀመሩት የቀደመውን አሻራ ለማጥፋት ወታደራዊው መንግሥት በጎፋ ካዎዎች ላይ በዘመተበት ወቅት ነበር፡፡ ያኔ የአካባቢውን ባላባት ከፍ ያለ ሞራል ለማድቀቅ የተሰራው ስራ ሰለባ ከነበሩ መሪዎች አንዱ ናቸው፡፡ ደርግ ከተመኘው ግዛት እንጂ ከባዮ ልብ ያላወጣቸው የጎፋ መሪ ስለኾኑ ዛሬም ድረስ ከነክብራቸው አሉ፡፡

የአሳቸው የግዛት ሀገር ባዮ ነው፡፡ ባዮ ሰፊ ግዛት ነበረው፡፡ ታሪኩ ብዙ ነው፡፡ ጉጃ አሻን ማድመጥ ጀምሬአለሁ፡፡
"አሁንም የባዮ ካዎ ነዎት?"
"አዎ!" አሉኝ፡፡ በልበ ሙሉነት ነበር፡፡ "ሁሉም የጎፋ ካዎ በዘር ነው፡፡ በዘር፤ ካዎ ሲሞት የቤተሰቡ ታላቅ ወንድ ልጅ ይነግሣል፡፡"

ካዎ አሻ ጉጃ አርጅተዋል፡፡ የባዮን ካዎ አየሁ የሚለውን ታሪክ ከማስመዝገብ ያለፈ ብዙ ማውራት አልቻልንም፡፡ ያም ኾኖ የነገሩኝን ይዣለሁ፡፡ ከነገሩኝ የካዎ ዳዳ ካማ ታሪክ አብዝቶ ማረከኝ፡፡ ያ የግዛት ማስፋፋቱን ወግ ብዙ ባስሰው ብዬ ተመኝቻለሁ፡፡

የጎፋ ካዎዎችን ታሪክ ለመስማት ከሳውላ የሚቀርብ ከተማ የለም:: ሳውላ ነኝ::
ውርኪ የጎፋ ነገሥታት ታሪክ የመነሻ ወጎች ማዕከል ናት:: እንዳች ያልተነገረላት የኢትዮጵያ ሀገር በቀል የአስተዳደር ጥበብ መናገሻ ነበረች::
ሰነዶች በልዩ ሁኔታ ከጎፋ ቀደምት ማዕከልነት ጋር አስተሳስረው ስሟን ያነሱታል::[1]
ከካዎ አሻ ጉጃ ቤት ስወጣ ልቤ ወደ ውርኪ ተጉዞ ነበር::

---

1. *ENCYCLOPAEDIA AETHIOPICA vol 2 page 823*

# ጥበበኛን የሚያከብረው ንጉሥ፤

ነው ሲኖሩ
"...... ከራስ ጋር ተዋዶ፣ ከራስ ጋራ ታርቆ
"እኔ ማነኝ?" ብሎ፣ ራስን ጠይቆ
መኖር እንጂ ፍቺው፣ ማንነትን አውቆ
ጊዜማ ይሄዳል ጊዜውን ጠብቆ::"
ጌትነት እነየው፤ እውቀትን ፍለጋ

አንድ ሴት ወንዙ መካከል ቆማለች:: ልብሷን አውልቃ እየታጠበች ነው:: ጸሐይ የተራራ ካባ በተጎናጸፈችው ምድር ሾልካ መጣች:: የጸሐይዋ ጨረር በምትታጠበው ሴት ማህጸን ገባ፤ ጸነሰች:: እነሆ ይኸቺ ሴት ከጸሐይ ጸነሰች:: ዘጠኝ ወር ሞላው፤ ወንድ ነበር የወለደችው::

በጎፋ ያለ ጋብቻ ማርገዝ ነውር ነው:: 'ጎሜ' ነው ይለዋል ባህሉ፤ የጎፋዎች ባህል ዝሙት ይጠየፋል:: ዛሬም ቢኾን ከተሞቻቸው ውስጥ ልጆቻቸው ሴት አዳሪ ኾነው አይታዩም:: ያለ ትዳር ማርገዝ ዝሙት ነው:: ዝሙት ደግሞ እንደ እርኩሰት ይታይ ስለነበረ ያለ ወንድ በጸሐይ ጨረር የወለደችው ሴት ቤተሰቦች በልጃቸው ላለማፈር የተወለደውን ልጅ ወንዝ ጣሉት:: ያ ወንዝ ስሙ ወምባ ይባላል::

በሳውላ ጎዳና እንደ ጅብራ ተገትሬ ሀሳቤ ሩቅ ተጉዟል፡፡ ወምባ ወንዝ አፋፍ ላይ ቆሜአለሁ፡፡ ወምባ ከተረኩ ጋር የኖረ ወንዝ ነው፡፡ ከካርጬ ተነስቶ ያላና ሳውላን አካሎ ዜንቲ የሚገባ ወንዝ ነው፡፡ ወምባ ሲወርድ ኖሯል፤ ሲወርድ ስለ ኖረው ታሪክ መልሼ አሰብሁ፡፡ ዓይኔን ከሚወርደው ውሃ ላይ አልነቀልሁም፡፡ ወምባ ወንዝ ዳርቻ የተጣለውን ሕፃን አሰብሁት፡፡ እንደ ሙሴ ታሪክ ነው፡፡ ፈርዖን ቤት አባይ ወንዝ ዳርቻ ተጥሎ በፈርዖን ልጅ እንደተገኘው፡፡[2]

አንድ ቀን አንዲት ማና ወደ ወምባ ወረደች፡፡ ሸከላ ሰሪ ናት፤ ጀበናና ድስቱን አበጅታ ገበያ ለማውጣት ማሰሪያ የሚኾናትን ልጥ ፍለጋ ነው የመጣችው፡፡[3]

ወንዙ ዳር የበቀለውን ሀረግ ለመቁረጥ ወንዙ ስር ስትደርስ ድምጽ ሰማች፤ የፈርዖን ቤት ሴት እንደሰማችው ዓይነት ድምጽ ነበር፡፡ አንድ ሕፃን አምርሮ ያለቅሳል፡፡ እንዲወስደው የተጣለበት ወንዝ ሊሸከመው የማይችል ክብርና ሞገስን የተጎናጸፈ ሕፃን ነው፡፡ ያቺ ሴት ያየችውን ሀረግ የመሰለ እጽዋት እያየሁ፤ ዓይኔን ወምባ ወንዝ ላይ ተክዬ ቁልቁል በሰማሁት ታሪክ እኔም እንደ ወምባ በዝምታ እፈስሳለሁ፡፡ ከወንዙ በሀረግ ነው ጎትታ ያወጣችው፡፡ ጎሻና የጎፋ ካዎች ዘር ሀረግ ነው፡፡ ጎሻ ማለት የተጎተተ ማለት ነው፡፡ አጥብታ አሳደገችው፡፡ ጥበበኛዋ ቤት ያደገው ልጅ ብርቱና ሃይለኛ ኾነ፡፡ ወደ ውርኪም ወጣ፡፡

---

2. ኦሪት ዘፀአት፤ ምዕራፍ ፪

3. ጎፋ ባህልና ታሪኩ፤ በበላይነህ አስጉ፤ ገጽ 37

ውርኪ በጎፋ የተለየ ትርጉም ያለው ሥፍራ ነው፡፡ ብዙ የነገሥታት ታሪኮች ከተረካቸው ያቆራኙታል፡፡ የውርኪ ቀበሌያት የጎፋ ብሔረሰብ የመጀመሪያ መንደርም ተደርገው ይቆጠራሉ ይላል ዘለቀ ዶሣ ሞርጋሞ ባልታተመ የጥናት ጽሑፉ፤[4]

ቀድሞ ንግርት አለ፡፡ እንዲህ ያለ ወንድ ልጅ ይወለዳል፤ ወደ ውርኪም ይሄዳል፤ ከዚያም ይነገሳል የሚል ንግርት፤ ያ ይፈጸም ዘንድ ይኼ ታሪክ ኾነ፡፡[5] ዑባ ዳርቻ የሚገኘው የውርኪ ምድር ቀድሞ ምድረ በዳ ነበር፤ ጎሻ በብርታቱ ምድሩን እየበሳ፣ በጦር ውሃ አፈለቀ፤

ከወምባ ወንዝ ዳርቻ ስንቀሳቀስ ጎሻን አንድ ብሎ ስለሚጀምረው የጎፋ ካዎዎች ዘር እያሰብሁ ነበር፡፡ ጎሻ ጎባን ወለደ፤ ጎባ ኮንታን፣ ጋሬ፣ ቡራ፣ በራቃ፣ ጋሞ፣ ጎቤ፣ ዙላ፣ ካንሳ፣ ቁስቴ፣ ዳዳ፣ ካማ፣ አይካ እያለ ትናንት ድረስ ይደርሳል፡፡ የጎሻ የንግሥና ዘመን ስምንት አስርት ዓመታትን ያጠቃልላል፡፡

---

4. ዘለቀ ዶሣ ሞርጋሞ በተለያዩ ጊዜያት የጎፋ አመራር ኾነው የሰሩ፤ የደንባ ጎፋ ወረዳ አስተዳዳሪ የነበሩና በኋላ የጎፋ ዞን ሲቋቋም የሳውላ ከተማ ከንቲባ የኾኑ ናቸው፡፡ አቶ ዘለቀ በርከት ያሉ የጎፋ ነገሥታትን የተመለከቱ ያልታተሙ የጥናት ጽሑፎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህ አንዱ በዚህ መጽሐፍ ደራሲ እጅ የሚገኘውና የጎፋ ጋዜ ማስቃላ በዓል ለህትመት የተዘጋጀው የዚህ ሪፈረንስ ሰነድ ይገኝበታል፡፡

5. ጎፋ ባህልና ታሪኩ፤ በበላይነህ አስጉ፤ ገጽ 37

የጎሻ የንግሥና ዘመን ስምንት አስርት ዓመታትን ያጠቃልላል፡፡ ከ1232 ዓ.ም. እስከ 1312 ዓ.ም. በጎፋዎች ምድር ጎሻ የሚባለው የመጀመሪያ ንጉሥ በግዛቱ የተከበረ ነበር፡፡[6]

ጎሻ ጎባን ሲወልድ የታሪኩ ምዕራፍ ከልጁ የሚጀምር ኾነ፡፡ የጎፋዎች ተረክ የህዝቡ ስም ስያሜ መነሻው ጎባ ነው ይላል፡፡ ቃሉ በቋንቋቸው ጠንካራ ማለት ነው፡፡ ጎባ ጠንካራ ነበር፡፡ ግዛቱ ሰፊ ነበር፤ ተረኩ ደግሞ ስሙ ለብሔሩ መጠሪያ እስከመሆን ደርሷል ይላል፡፡ እርግጥ ቀደም ሲል በጎፋ ተራራማ አካባቢዎች ጎፋ የሚባሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ይኖሩ እንደነበር የሚያወሳ ታሪክም አለ፡፡[7]

ጥበበኞችን በማከበር የጥበበኛዋ ምግዚት ልጆች የኾኑት የጎፋ ካዎች ተከነውበታል፡፡ ያቺ ከወምባ ወንዝ ዳርቻ ጎሻን ያነሳችው ሸክላ ሰሪ ከማንም ትልቅ ነኝ ባይ በበለጠ በካዎ ቤት ከብርና ቦታ የሚሰጣት ኾናለች፡፡
በቀደመው የጎፋዎች እሳቤ ማናዎች የሚባሉት የእጅ ባለሙያዎች ማንም ሰው ቤት ገብተው አብረው መብላት አይፈቅድላቸውም፤ አንዱ ቤት የቤታቸውን ያኽል የሚቆጥሩት መብታቸው የሚከበርበት ስፍራ ነው፡፡ ይኸ ስፍራ የካዎ ቤት ነው፡፡ ከሌላው ሰው ጋርም ቢኾን ካዎ ቤት ከተገናኙ መጠየፍ የለም፡፡ እርግጥ ነው በካዎ ቤት ጉሜ የለም፡፡

6 . *ENCYCLOPAEDIA AETHIOPICA vol 2 page 823*

7. *የጋሞ ጎፋ ሕዝቦች ታሪክ፡፡ ገጽ 106*

በጎፋ ካዎዎች ታሪክ ካማ ዳዳ ዝነኛው ነው፡፡ የሸዋ ጦር ዳሞታን ከቧል፡፡ ካዎ ጦና በቀላሉ አልተፈታም፡፡ ብዙ ሰነዶች የሸዋ ጦር ጠንካራ መከላከል የገጠመው በካፋው ንጉሥና በወላይታው ንጉሥ እንደኾነ ብዙ ጽፈዋል፡፡[8]

በእርግጥም ከንጉሥ ጦና ጋር የነበረው ጦርነት ከባድ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ከአምስቱ የጎፋዎች ግዛት አንዱ የኾነውን የጎፋ አካባቢ የሚመራው ካማ ዳዳ ነው፡፡ የካዎ ዳዳ ልጅ፡፡ የጦርነቱ ወሬ ጎፋን አዳረሰ፡፡

የተረኩልኝ ካዎ አሻ ጉጃ ናቸው፡፡ ካማ ዳዳ ሽማግሌዎችን ሰብስቦ ከዳሞታ አውደ ውጊያ የመጣውን የጦር ወሬ አስደመጠ፡፡ እየመጣ ያለውን ኃይል የማይመክቱ መኾናቸውን ከጦር ስለላው መዋቅር አረጋገጠ፡፡ ከዚያም "እናግዝህ እንምጣና እንግጠም" የሚሉትን አራት ካዎዎች "የለም እኔ እመከተዋለሁ" ሲል የሚከፈለውን መስዋዕትነት ቀነሰ፡፡

---

8. ካዎ ጦና በቀላሉ እንዳልገበረ ጳውሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ በሚለው መጽሐፉ ሲገልጽ፡፡ "ንጉሥ ጦና አልገብርም ብለው አስቸገሩ ይላል፡፡" ምኒልክም በሰላም እንዲገብሩ ያቀረቡላቸውን ጥያቄ አልቀበልም እዋጋለሁ ማለታቸውን ጽፏል፡፡ በሊቀ መኳስ አባተ እና በደጃች ባልቻ የተመራውን የመጀመሪያ ጦርም ካዎ ጦና ማሸነፋቸውንና በኋላም ራሳቸው ንጉሥ ምኒልክ መዝመታቸውን አስፍሯል፡፡ አጤ ምኒልክ ገጽ 35፡፡
በሌላ በኩል ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴም የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983 በሚለው መጻሐፋቸው የጦርነቱን ከባድነትና በኋላ በአድዋ ጦርነት ስማቸው የገነነ ጦረኞች ሁሉ የታሰተፋበት እንደነበር ጽፈዋል፡፡ ገጽ 72

የጦርነቱ ስፍራ የጎፋ ነገሥታት አምባ ነው:: ጫቆ ቆጤ ይባላል:: እዚያ የጎፋዎች ሕያው ታሪክ ተጻፈ:: ካዎ ካማ ዳዳ የህዝቡን ክብር ሕያው ያደረገ ጦርነት አካሄደ:: ንጉሥ እየተዋጋ ይሞታል እንጂ አልችለውም ብሎ እጅ አይሰጥም በሚል ወኔ ከታጠቀው የሸዋ ጦር ጋር ተፋለመ:: በዚኽች የታሪካ አምባ ላይ ስለ ታሪካዊ ክብሩ ተሰዋ:: የጎፋ ልሂቃንም ኾኑ የጎፋ አባቶች ደጋግመው ሲደመጡ የሚሰሙት ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ስትሰራ ስለነበራቸው ሚና እንጂ የቂምና የቁርሾ ትርክቶችን በመደጋገም አይደለም::

ሻሹሬ የካዎ ካማ ዳዳ ሚስት ናት:: ነገሥታቱ ናቸው የተጋቡት፤ እሷ የታላቁ የዳውሮ ነገሥታት ቤተሰብ ናት:: ካማ ዳዳ ሲሞት ከሻሹሬ አንድ ልጅ ወልዶ ነበር:: ስሙ አይካ ይባላል:: እንደ ጎፋ የካዎ ንግሥና ሥርዓት የካዎ ዳዳ የልጅ ልጅ የካዎ ካማ ልጅ አይካ ካዎነቱን ይረከባል::[9]
ከጦርነቱ በኋላ ያ የነገሥታቱ ማዕከል ተፈታ:: ሻሹሬ ሜላ ወደተባለው የሴላ ካዎ ግዛት ወረደች:: የልጇ ምግዚት ኾና በባላባትነት ትንሽ ኖረች:: ስሟ ተቀየረ፤ ክርስትና ተነሳችና አቅሌሲያ ተባለች:: ያልታወቀው ምድር ድርሳን ጸሐፊ የኾነው አሳሽ ስቲጋንድ ጎፋ ሲደርስ ወይዘሮ ገኔን እንዳገኘ ጽፏል:: ያኔም ጎፋ በእሳቸው ሥር እንደነበርና በኋላም አቅሌሲያ በሚል ስም እንደተጠሩ ይገልጻል::[10] የሸዋ ጦር የካዎ ካማን ዝና ምኒልክ ቤተ መንግሥት ወስዶ አናኘው:: ካዎ ካማ ቤተሰቡንም ጎፋንም አስከበረ::

9 ጎፋ ባህልና ታሪኩ፤ በበላይነህ አስጉ፤ ገጽ 44
10. unkown land through abyssinia page 285

ዐፄ ምኒልክ ለደጃች ለማ መጋቢት 24 ቀን 1900 ዓ.ም. በጻፉት ደብዳቤ የጎፉ ገኔ ዛላ ውስጥ ያለኝ ርስት ተወሰደ በደል ደረሰብኝ ብለው ደብዳቤ መጻፋቸውን በመግለጽ ደጃች ለማን ጎፉ ገኔን አትድረስባት ብለዋቸዋል::"

ንግሥት አቅሌሲያ ከንጉሥ ሀላላ ቤተሰብ ተገኝታ ከካዎ ካማ ተጋብታ ዝናዋ የናኘ ሴት ነበረች:: በምኒልክ ቤተ መንግሥት ስሟ ከፍ ብሏል:: በንግሥት ዘውዲቱ ግብር ሦስተኛው ማዕድ ላይ ከታላላቆች ጋር በክብር የምትቀመጥ ሴት ነበረች::[12] ጎፉ የሚለው ስም ከዚያን ግዜ ጀምሮ ምኒልክ ቤተ መንግሥት የጀግንነት መለኪያ ኾነ::

ራስ ወልደጊዮርጊስ የዐፄ ምኒልክ ታላቅ ሹም ናቸው:: ከጎፉ ጦርነት በኋላ ከራሳቸው በቅሎ ይልቅ ከጎፉው ንጉሥ የተማረከውን በቅሎ ነበር የሚጠቀሙት፤ ፈረሱ በብር ዕቃዎች ያጌጠም ነበር:: አሌክሳንደር ቡላቶቪች ግንቦት 23 ቀን 1890 ዓ.ም. ይኸቹን በቅሎ ከራስ ወልደ ጊዮርጊስ በስጦታ ተበርክቶለታል::[13]

---

*11. ጳውሎስ ኞኞ:: አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች:: ገጽ 351*

*12. ደጃዝማች ከበደ ተሰማ በታሪክ ማስታወሻ መጽሐፍ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ መንግሥት ጊዜ የግብር አቀማመጥ ተራውን በተመለከተ በሥዕል አስደግፈው ያቀረቡት ገለጻ ላይ የጎፉዋ ንግስት ገኔ ወይም አቅሌሲያ የሚቀመጡበትን ስፍራ በገጽ 56 አስቀምጠዋል::*

*13. አሌክሳንደር ቡላቶቪች ከዐፄ ምኒልክ ሠራዊት ጋር ብሎ የጻፈውን መጽሐፍ ዶክተር አምባቸው ከበደ ተርጉመውት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሳትሞታል:: ይኸ ታሪክም በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 261 ላይ የሚገኝ ነው::*

የጎፋ ነገሥታት ስም ገናና ነው:: የካዎ ካማ ዳዳ ወኔ ቀሪዎቹ አራት ካዎዎች በክብር እንዲደራረደሩ ጉልበት ኾኗል:: የሸዋው ጦርም የጎፋን ብርቱ ተዋጊነት አድንቋል:: ከዚያ በኋላ ለሀገር በተከፈለ ታላቅ መስዋዕትነት ሁሉ ጎፋዎች ከባንዲራቸው ጎን አሉ::

አድዋ ላይ የጥቁር የነጻነት ችቦ ሲለኮስ ጎፋዎች ሜዳው ላይ በቀሩት መሪያቸው በደጃዝማች ባሻህ አቦዬ እየተመሩ ተዋግተዋል::[14] የአድዋ ድል ብሥራት በታላቅ ሰልፍ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት በክብር ሲበሰር የጎፋ ጦር የሰልፉ አድማቂ፣ የክብሩ ባለቤት ኾኖ ተሰይሟል::[15]
ጎፋዎች ሳጋሌ ኡላ በሚሉት የሰገሌ ጦርነትም ከማዕከላዊው መንግሥት ጎን ቆመዋል::[16] የጎፋ ህዝብ በማይጨው ጦርነት ነቅሎ ወጥቶ ለሀገሩ ተዋድቋል:: ዛሬ አዲስ አበባ "ጎፋ ሰፈር" የምትለው ትናንት የጎፋ አባቶች ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ሆ ብለው ለቀናት ተጉዘው መጥተው ያረፉበትን ሥፍራ ነው::[17] በውጋዴን ለሀገር ክብር በተደረገው ተጋድሎ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው የሚመሩት የጎፋ ጦር አብሮ ዘምቷል::

ከወምባ ወንዝ ዳርቻ ከገባሁበት ሀሳብ ያወጡኝ ሆ እያሉ የሚመጡ ጨፋሪዎች ናቸው:: ሳውላ የመስቀል ድባብ ላይ ናት:: ጋዜ መስቃላ ሁለት ቀናት ቀርተውታል::

14. ተክለጻዲቅ መኩሪያ:: ከዐጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ገጽ 117
15. ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ታሪከ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ፣ ገጽ 310
16. ጎፋ ባህልና ታሪኩ፣ በበላይነህ አስጉ፣ ገጽ 196
17 ዝኒ ከማሁ .

መስቀልን ከሚናፍቅ ህዝብ ጋ ላሳልፈው በመስከረም ጎፋ ተገኝቻለሁ:: የጎፋን መስቀል ለማድመቅ ጠጠሬን አንስቼ ጥያለሁ:: አብሬ ነበርኩኝ ማለት የሚያኮራበት ድግስ መጣሁ እያለ ነው::

የጎፋ አባ ወራ በመስቀል ሣምንት ከቤት ርቆ የትም ስለማይሄድ ውሎው ቤት ነው:: በዓሉን በጉጉት ይጠብቃል:: የበዓሉ አካል የሆነው የደመራ ምሽት አይረሴ የአንድ ዓመት አንድ ምሽት ነው:: አሁን ገበያዎች መድመቅ ጀምረዋል:: ድግሱ በየቤቱ እየተሰናዳ ነው:: የታደለ ያያት ሌላኛዋ መስቀል ዳግም ልትመጣ የቀናት እድሜ ቀርቷታል:: ሰላምታው እንደወትሮው "ሃይ መሌ... ሎ" ብሎ አያበቃም:: መስቀል በራፍ ላይ ነው:: ወዲህ ሳውላ ጎፋ ጋዜ ማስቃላን ልታስተናግድ ሽር ጉድ ትላለች:: የደምባ ጎፋ ገበሬዎች ያለ ስስት በሚያከብሩት የመስቀል ዋዜማ የባህል ፌስቲቫላቸውን ሊያደምቁ ፈረሳቸውን ሸልመዋል:: ዱዛ ተራራ ይታዘባል:: ለመስቀል አብልጦ ሽር ጉድ በሚለው የሚደሰት የሚመስል ተራራ፤

የጎፋ መንደሮች እጃቸውን ዘርግተዋል:: ከቀናት በኋላ መስቀል እቅፋቸው ውስጥ ይገባል:: ያኔ እዚህ ምድር የኾነ አብሮ ይታቀፋል:: ያኔ አንዱ ሰሞን ዘለዓለም እንዲህ ኾኖ እየተባለ የሚተረክ ነው:: አዘቦት በሚያምርበት የቀና ልብ ቀዬ አውደ አመትን አብሮ መኾን ከቃል በላይ ነው:: ጋዜ ማስቃላን ከእነሱ ጋር መኾን ይታያል እንጂ አይተረክም:: ይዳስሱታል እንጂ በእውን ሊኾን የሚችለውን በሙሉ በምናብ ጨርሰው አያዩትም፤

ከቡልቂ የሚወርደው ቀዝቃዛ አየር ከተራራው አናት ቁልቁል ሲወርድ መስቀልን የሚያበስር ይመስላል፡፡ ሰሞኑ የመስቀል ነው፡፡ ከዛንጋ እስከ ሎጤ ትናንት ትንሽ የሚመስሉት ገበያዎች በዚህ ሰሞን መስቀል አድምቋቸዋል፡፡ ከመቶ አመታት በፊት እንደ እኔ የመጣው ሀገር አሳሽ ጎፉ የምድር በር መኾኗን ገልጾዋል፡፡ በርካታ ቅፍለት ቡና ወደ አዲስ አበባ ሲሄድ አየሁ ይላል፡፡[18]

አዲስ አበቤዎች ዛሬ የምነግራችሁ እውነት ጣፍጧችሁ የምትበሉት ጥሬ ስጋ ሲጫንላችሁ ቆሜ እያየሁ መሆኔን ነው፡፡ የሰንጋው ሀገር ሳውላ ነኝ፤ ያ የሚወደደው የበግ ስጋ ከነነፍሱ በአይሱዙ ተጭኖ ሲሄድ በዓይኖቼ ሸኘሁት፡፡

18. unkown land through abyssinia page 285

# ማስቃላ ዮ! ዮ!
# ዳናው ዳና አልባ ዙማዳን ዳና፤

".......

መስኩን በቀለም አዝርእት፤ በጥበብ አጥለቀለቀ
ሸለቆው ተንቆጠቆጠ፤ ተራራው አሸበረቀ
ኢዮሃ ኢዮሃ አበባዬ! ምድር ሕይወት አፈለቀ፡፡
ነጋ፤ የአዲስ ዘመን ችቦ
ፈካ፤ ፀደይ አረብቦ
ሌሊቱ እንደ ጎሕ ቀደደ፤ ጨለማው እንደ ቀን ጠራ
እንደውቅያኖስ ዕፀዋት፤ እንደ ጠፈር ኮከብ ደራ
ምድር ስጋጃ ለበሰ፤ የጌጥ አልባሳት ተቀባ
ሰማይ በእልልታ አስተጋባ
ኢዮሃ መስከረም ጠባ፡፡"
"

ጸጋዬ ገብረመድኅን፤ እሳት ወይ አበባ

ቀኑ ይለያል፡፡ እንደሌሎች ቀኖች ጨለማው ተገፎ ብርሃን ስለተተካ ብቻ የሚዋል አይደለም፡፡ ሁለቱ የዝናብ ወራት በክብር ለመሸኘታቸው የሚበሰርበት ድግስ አውዶኛል፡፡ ሳውላን እንዲኸ ኹና ሳያት ደስታዬን መቆጣጠር አልቻልሁም፡፡ ልጇን የምትድር እናት መሰላኛለች፡፡ እዚኽም እዚያም ደስታ ነው፡፡ በደስታ መንፈስ ውስጥ ማስቃላን በሚያከብር ህዝብ መሃል ጨለማውን አልፌ ለብርሃን የበቃሁ እድለኛ ነኝ፡፡

ሁሉም ጋ "ሆሴ" የሚለው የጎፋ ሙዚቃ ይሰማል፡፡ የጎፋ ተራሮች የሚያስተጋቡት ድምጽ ከመሎ እስከ ዑባ ይጣራል፡፡ ማታ የተሰናበትኋትን ሳውላ ከእንቅልፌ ስነሳ አላገኘኋትም፡፡ ይኸቺ ሳውላ የሕይወት ዘመኔ ትዝታ ናት፡፡ ይኸቺ ሳውላ የጎፋዎች የትዝታ እምባ ኾና ትዝታ ውስጥ ልትከተኝ ማልዳ ተቀብላኛለች፡፡

"ማስቃላ ዮ! ዮ!" ይኼ ሠላምታ ብቻ አይደለም፡፡ ቡራኬም ነው፡፡ ምረቃ ያጀበውን በረከት ይዟል፡፡ ወግና ባህልም ነው፡፡ ወደ ጎዳናው ወጣሁ፡፡ በየሰው ፊት ላይ የምሥራች አነባለሁ፡፡ ደስ የሚል የምሥራች፡፡ የመስከረምን መግባት ከሰው ፊት ፈገግታ ላይ አነበብሁት፤ እዚህ ካላንደር ስሜት ነው፡፡ ሰው ፊት ላይ ወራት ይቀያየራሉ፡፡ ሰው መንፈስ ላይ ሀሴት እንደ ወዝ ይፍለቀለቃል፡፡

ጎፋዎች በዓመት አንዴ ለሚያከብሩት መስቀል አይሰስቱም፡፡ ትንሽ ትልቅ የለም፤ ሀብታም ደሃ መኾን መስቀልን ከመናፈቅ የማያግድበት ባህል ነው፡፡ ይኸው መስከረም ገባ፤ ነሐሴ ሲጋመስ ጀምሮ በየመስኩ የቆሙት ቅልብ ሰንጋዎች ዛሬን አያልፉም፡፡ መስከረም ሲገባ እንኳን ሰው፣ የቤት እንስሳትም እንዳይራቡ ጎፋዎች ይጠነቀቃሉ፡፡ እያንዳንዱ አባወራ በቤቱ ቢያንስ ለሳምንት የሚበቃ የእንስሳት መኖ እና ውሃ የማቅረብ ሥራ ይሰራል፡፡
ሳውላ ነኝ፡፡ የከተማዋ ሾጣጣ ተራራዎች አፍጠውብኛል፡፡ ምናልባት ስለመስቀል የማይገባኝ ኾኜባቸው ይሆናል፡፡ ከወላይታ እስከ ሶዶ ያለው መንገድ ምንም ቢሆን ጎፋዎች መስቀልን ሀገራቸው አይቀሩም፡፡ ብዙ ሰው መጥቷል፡፡ ብዙ ሰው ቀዬው ነው፡፡ ብዙ ሰው እያየሁ ነው፡፡

በላይ በዛብህ መጣ:: ዛሬ ሠርጉ ነው:: መስቀልን ሳይመጣ ሲጎትተው ከርሟል:: ሞተር ሳይከል ኮርቻ ላይ ኾኖ እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋና
"ማስቃላ ዮ!" አለኝ::
"ዮ! ዮ!" አልኩት::
የምለው እንደ እህል አፌ ላይ ጣፈጠኝ::
"ዳናው ዳና አልባ ዙማዳ ዳና......ከንቲ ሻላዳን ዳና! መሪናው ዳና! ሀረይ ካጪ ከሳናዳን! ገላአ ገል ውራናስ ዳና!" አከታተለብኝ::

ጎፋ ቸር የሚመኝ ሕዝብ ነው:: አሜን አልኩት፤ አሜን ካልን በኋላ ትርጉም የምንጠይቀው ሕዝብ መሃል መኾን መታደል ነው::
"ምን ማለት ነው?" አሜን ብዬ ትርጉም ጠየቅሁ፤ ምርቃት አቋርጦ ማጣራት ሞኝነት ነው::
"የጎፋ ትልቁ ተራራ አልባ ዙማ ኖሮ ያየውን መስቀል ያኽል ኖረን መስቀልን እናያለን ማለት ነው:: ሻላ የተባለውን ግዙፍ ዐለት እድሜ ኖረን መስቀልን እናያለን:: ለዘለዓለም እንኖራለን ማለት ነው:: አህያ ቀንድ እስከሚያበቅል ድረስ እንኖራለን፤ ልጃገረዶች አገብተው እስኪያልቁ ድረስ እንኖራለን:: ማለት ነው::" አለኝ::

አልባ ዙማ የጎፋ ትልቁ ተራራ ነው:: ከባህር ጠለል በላይ 2400 ሜትር ከፍታና ሻኛ ያለው ተራራ ነው:: ባለ ሻኛው ተራራ እንደማለት ነው ስያሜው:: ይኼን የሚያኽል ተራራ የኖረውን ዘመን ኑር ብሎ የሚመርቅን ሕዝብ አሜን እያሉ ካፉ ላይ ምርቃቱን መንጠቅ ነው:: እስኪበቃኝ ነጠቅሁ፤

ተጠምጥሞ አቀፈኝ፤ አቀፍኩት:: እኔም እንደ ጎፋዎቹ ተመኘሁ:: አልባ ዞማ ተራራ ያየውን መስቀል ብዛት ማየት:: ለዘለዓለም መኖር ተመኘሁ:: አህያ ቀንድ እስከታበቅል ኖሬ ከጎፋዎች ጋራ መስቃላ ዮ ማለትን ተመኘሁ:: ልጃገረዶች አግብተው እስኪያልቁ መኖር ተመኘሁ::

ሞተሩ ጀርባ ላይ ወጣሁና ሳውላን ከጫፍ ጫፍ በረርንባት:: እዚኽም እዚያም የመስቀል ሙዚቃ አናውጧታል:: ጎዳናዎቿ የጎፋን ቀለም ተቀብተዋል::

ጎፋ ቀለሙ ልዩ ነው:: አረንጓዴው ያንን ለም ምድሩን ይሰብካል:: የደጋውን ምድር መልክ እንደ መስታወት ያሳያል:: የተራሮቹን የመስከረም ውበት ወክሎ ይገልጻል:: ነጩ ሰላም ወካይ ነው:: አብሮ ለመኖር የተከፈተ ልብን የሚያረጋግጥ ቀለም ነው:: ቀይ ለጎፋዎች ብዙ ቦታ እንደምናደምጠው አይደለም:: ለህዝቡ ክብር ስለተከፈለው ዋጋ የሚናገር ቀለም ነው:: በአድዋ ስለወደቁ፣ ማይጨው ስለ ቀሩ፣ ውጋዴን ስለተዋደቁ የጎፋ አባቶች ደም ምስክርነት የተቀመጠ ነው:: እዚህ ቀይ ቀለም ውስጥ የብሔራዊ ባንዲራችን ቀይ ቀለም ውክልና አለ::

መስቀል ብዙ የሚደከምበት በዓል ነው:: ድንበሩ ደርቤ የደምባ ጎፋ ባህል ቱሪዝም ባለሙያ ነው:: ስለመስቀል ጽፎ ከሰጠኝ አንዱም ስህተት ኾኖ አላየሁትም:: አብሬአቸው ሳለሁ ለመስቀል 15 ቀናት ሲቀሩ እንስሳት በክብር ሲቀለቡ አይቻለሁ:: አባወራው ቤቱ ኾኖ ይኽንን ቀን ሲናፍቅ ከጎፋዎች ጋር ነበርሁ::

ሴቶች ለበዓሉ የሚሆኑ እህሎችን በመፍጨት ቦርዴ እና የጌሾ ጠላ በመጥመቅ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ሴቶች ለማገዶ እንዳይቸገሩ እንጨት ፈልጠዉ በማቅረብ እና ለደመራ ችቦ የሚሆኑ ግንግና /Ginggina/ የተባለውን ጭራሮ በመልቀም፣ የእርድ ቢላዋና እርዱ የሚፈፀምበትን ቦታ በመወሰን የቅድመ ዝግጅት ስራውን እንደሚሰሩ የነበብኩት ሁሉ በአካል ያየሁት እውነት ኾነ።

መስቀል ነው። ለእርድ የሚኾኑ ሰንጋዎች በየሰፈሩ ተገዝተዉ ተዘጋጅተዋል። ለገንፎ የሚኾን በቆሎ ታምሶ ተፈጭቷል፣ ቡላና ቆጮ እንዲኹም የሃረግ ቦዬ ተዘጋጅቷል፣ ጠጅና ብርዝ ተሰናድቷል። እንዲህ ባለው ቀን አይደለም፤ በአዘቦትም የጎፋዎች እንግዳ መኾን መታደል ነው።

"ሎያ ባይ ሎያ ባይ
ሎያ ማስቀላ ባይ
ማስቃል ኡፋይስ ባይ
ሙሰ ሀሹ ባይ" የሰማሁትን ዜማ በላይ ተረጎመልኝ። ወደ ልጅነቱ መልሶታል። መስቀልን የናፈቁ ልጆች ከብት እየጠበቁ የሚያዜሙት ነው። በዚህ መንፈስ ውስጥ ሆኜ ወደ ሳውላ ስታዲየም ሄድን። ከደምባ ጎፋ ቀበሌያት የመጡ የጋዜ ማስቃላ ተሳታፊዎች እየጨፈሩ ነው። በማስተባበረው ፕሮግራም እንግዳ ሆኜ አረፍኩት። ፈዘዝሁ። ሆታው ሩቅ ወሰደኝ። ፈረሰኞች እዚያ ይጋልባሉ። ሴቶች እዚኽ ደምቀዋል። ወጣቶች ባራንቼ እያሉ ነው። ባራንቼ ውስጡ ከነዜማው ቀርቷል። መስቀል ያልፋል። የማያልፍ ስሜት መሸከሜን ተረዳሁ።

ደመራው ቆሟል፡፡ ይኼ የሥነ-ሥርዓት ደመራ ነው፡፡ በዓሉን ፌስቲቫል ለማድረግ የተዘጋጀ ኩነት ደመራ ነው፡፡ የጎፋ ደመራ ሥርዓቱ ብዙ ነው፡፡ ጎፋዎች ደመራን ልዩ ትርጉም ይሰጡታል፡፡ ለችቦ መስሪያ የሚያገለግሉ ደረቅ ጭራሮዎች ከሣምንት በፊት በየአንዳንዱ ቤተሰቡ አባት ወይም ታላቅ ልጅ ይዘጋጃል፡፡ ወልጋዳ እንጨት ለደመራ አይሆንም፡፡ የደመራው እንጨት ቀጥ ያለ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ ይህ ከጅምሩ ዘመኑ መልካም ዘመን እንዲሆን፣ ከበሽታ ከመቅሰፍት እንዲጠብቅ፣ ልጆች በአስተሳሰብና በአመለካከት ቀና እንዲሆኑ ወካይ ምልክት ነው፡፡

የደመራ እንጨት አዘገጃጀቱም ከደረቅ ወደ እርጥብ እንዲሆን ተደርጎ ነው፡፡ ጎፋዎች በዚህ ውስጥ ዘመኑ የጥጋብና የሰላም እንዲሆን ሽግግርን ይወክሉበታል፤ እዚህ ያለ ትርጉም የምትኾን አንድም ነገር አላየኹም፡፡ በደመራው እንጨት ጫፍ አደይ አበባ ይታሠራል፤ አደይ ላይ ተስፋና ውበት አለ፡፡ አበባው ውስጥ ዘር አለ፡፡

የደመራው ሥነ ሥርዓት ለቀጣዩ ትውልድ የማስተላለፍ ሥርዓትን ያመላክታል፡፡ ዘራችን ይብዛ፣ ይስፋም ለማለት ነው፡፡ ምስጢር በአንድ ምሽት የሚገለጽበት የተለየ አጋጣሚ ላይ ታድሜአለሁ፡፡ እንዲኽ ዓይነት ቀን በእንዲኽ ዓይነት ሥፍራ ነበርኩ ተብሎ የሚታለፍ የሕይወት አጋጣሚ አይደለም፡፡ ይልቁንስ ከነፍስ የሚቀራኝ፤ መኖሪያውን ደም ውስጥ ያደረገ ትዝታ ነው፡፡ ዓመት በመጣ ቁጥር ወደ ኋላ የሚመልስ ትዝታ፡፡ ቀናቱ እያጠሩ ይኾን? ጊዜን ቂም ያዝሁበት፡፡

የችቦ አስተሳሰርና የደመራው አቆራረጥ በቤተሰብ ቁጥር በዕድሜያቸው መሠረትና መጠን ይወሰናል:: ይኸም በመካከላቸው መደማመጥና መከባበር እንዲሰፍን ያደረጋል::

ችቦ የሚለኮሰው በመጀመሪያ ቀኑ ደንገዝገዝ ወይም ለዓይን ያዝ ሲል አባወራው በወንድ ቁጥር የታሰረውን ችቦ አጠቃላይ በመያዝ ምሰሶ ካለበት ጎጆ ቤት ውስጥ ለገንፎ ከተጣደው ድስት ስር ከሚነድ እሳት ላይ የሁሉንም ችቦ ከለኮሰ በኋላ በቀኝ በመታጠፍ ምሰሶውን በመዞር፣ የከብቶች ጋጣና በበሩ ላይ በቀኝና በግራ የቆሙትን መሪ ግድግዳዎችን "ማስቃላ ዮ! ዮ!" እያለ በተለኮሰው እሳት እየነካካ ከቤት ወደ ደጅ ይወጣል::
አባት ይኸንን ሲያደርግ ወንድ የኾነ ማንኛውም የቤተሰቡ ነዋሪ በዕድሜ ቅደም ተከተል ተራ በመያዝ ተከትለውት ወደ ደጅ ይወጣሉ:: አባትም "ማስቃላ ዮ! ዮ!" እያለ ችቦውን በዕድሜ ደረጃቸው ካካፈለ በኋላ መሃል ላይ ሆኖ በወንዶች ታጅቦ "ማስቃላ ዮ! ዮ! ዳናው ዳና" እያሉ በዱቡሻው ስር ወደ ተተከለው ዳመራ ደርሰው ዳመራውን ዞረው አባት በመጀመሪያ ችቦውን ሲያስቀምጥ ሌሎች በዕድሜያቸው መሰረት ያስቀምጣሉ፣ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፣ ይጨፍራሉ::

ከሩቅ የሚመጣ የሕብረት ድምጽ ከገባሁበት ሀሳብ አወጣኝ:: ቡልኮ ለብሰዋል:: የተደረደሩ ሽማግሌዎች ናቸው:: የችቦውን እንጨት ይዘዋል:: ሞገሳቸው የሚያስፈራ ድምጻቸው የሚያስገመግም ነበር::

ሳውላን እንዲኽ ስትኾን ማየት የሚቻለው በዚህ ቀን ብቻ ነው:: ወደ ተተከለው ደመራ መጡ:: "ማስቃላ ዮ! ዮ!" እያሉ ዙሪያውን ከበቡት:: ድምጹ ሳውላን አልፎ መሎ የሚሰማ መሰለኝ:: ድምጹ ዑባ ኮረብታዎች ላይ የሚደመጥ መሰለኝ:: ጋልማዎች የሰሙ መሰለኝ:: ከመሰለኝ የማየው ይበልጣል:: የማየውን ለራሴ ለማሳመን ከእያንዳንዱ ኩነት በኋላ ሰኮንዶች እዘገያለሁ::

ጎፋ የደመራ ዕለት በቀዬው የሌለን ጎፋ በዝምታ አያልፍም፤ ስሙ በዚህ ደማቅ ምሽት በተግባር ይወከላል:: ደመራው ሲተከል በቤተሰቡ አባል የሌለ ሰው በስሙ ችቦ ተዘጋጅቶ ለሌሎች የሚደረገው ኹሉ ይደረግለታል:: ሲያውም በምትኩ በስሙ የታሰረውን ችቦ የሚይዘው አባት ይኾናል:: ደመራው ተለኮሰ:: ጨዋታው ቀጠለ:: ዮ! ዮ! ዮ! ሁሉም ሰው ዮ! ይላል:: ዮ አንድ ፊደል አይደለችም፤ የአንድ ዘመን ብሥራት ናት:: የአንድ ሕይወት የትዝታ ቃል ናት:: በሰፊ ገበታ የተዘጋጀው ገንፎ በሰው ተከበበ:: በደመራው እለት የሚበላ ዋና ባህላዊ ምግብ ነው::

ከበቆሎ የሚዘጋጅ ገንፎ ሲሆን ስያሜውም (Masqqala dhote) ይባላል:: የጎፋ ሴቶች ከሳምንት በፊት ወተት በማጠራቀም ምንም ውሃ ሳይጨምሩ ከበቆሎ ዱቄት የሚሰሩት ሲኾን የተነጠረ ቅቤ፣ አይብና ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት የሚዘጋጅ ገንፎ ነው:: ይህ ገንፎ ከተዘጋጀ በኋላ ቤተሰቡ ሁሉ በአንድነት በመሰባሰብ እጃቸውን ወደ መሶቡ የሚሰዱበት ሥርዓት አለ:: እዚኽ ጋር ነው መስከረም የሚጠባው፤ እዚኽ ጋር ነው አዲስ ተስፋ የሚያብበው::

ይኸ ሥርዓት ከምንም በላይ ፈጣሪያቸዉን የሚያስቡበትና የሚማፀኑበት ስለሆነ ማስቃላ ዮ! ዮ! የሚለውን በጋራ ያስተጋቡበታል፡፡ በአንድነት ይቀምሱበታል፣ በፍቅርና በህብረት ይበላሉ፡፡ እንዲኸ እየኾነ ነው፡፡

እዚያ የደመራው እቶን ሰማይ ካልፈጀሁ ብሎ ሽቅብ ይንበገበጋል፡፡ እዚህ ዮ እያሉ ያንን ጣፋጭ ገንፎ ከበው እየተቃመሱ ነው፡፡ ዘለቀ ዶሳ ሞርጋሞ ወዲያ ኾኖ ለጋዜጠኞች የገንፎ ሥርዓቱን ይገልጻል፡፡

"ማንም ምግቡ ጋ ሲሄድ እጁን አሳርፎ ዮ ዳናው ዳና አልባ ዙማዳ ዳና ይላል፡፡ አባት እጁን ገንፎው ላይ ሲያሳርፍ ሁሉም የቤተሰብ አባል ዮ ብሎ እጁን ገንፎ ላይ ያደርጋል፡፡ የአምስት አመት ልጅ ኾነ የአንድ አመት ልጅ ሆነ፤ እናትም ጡቷን የሚጠባ ልጇን እጅ ይዛ ዮ ብላ ታስነካዋለች፡፡"

የሚታይም የሚደመጥም ስፍራ ነኝ፡፡ የምሰማውን እየዋለሁ፡፡ አባቶች መርቀው፤ ህዝቡ ዮ ብሎ በሰፌ ገበታ የተዘጋጀው ገንፎ መበላት ጀመረ፡፡ ጭፈራው ቀጥሏል፡፡
ይህ ምሽት ከደመቀው የደመራ እሳት ቀለም በላይ በጎፋዎች ባህል እስከ ጥግ የሚዋብ ነው፡፡ ከደመራው እሳት ሙቀት በላይ ከልብ ሲገባና ሲቀር ጉልበት ያለው ነው፡፡
ማስቃላ ዮ....

# ወደ ሩቁ ገዳም
# ጉንዳ ጉንዶ ማርያም
# በአንድ ቀን ብዙ ቀናት መጓዝ፡፡

" ይመሻል -ይነጋል
ብራን ያባርራል....
ጨለማ ይሮጣል....

እንዲህ ሲባረሩ.....
ምድር እየዞሩ.....
ጨለማ ጓደኛ
ኢትዮጵያ ላይ ተኛ፡፡

ያው ብራ'ን አልመጣም
ጨለማም አልሄደም
ጊዜው ግን ይሄዳል
ለ'ኛ መች ይታያል
ጨለማው ሸፍኖን-
ዘግተን ተኝተናል፡፡"

አበረ አያሌው ፍርድ እና እርድ

ፈራሁ፡፡
እግሬን አላመንኩትም፤ እንኳን እግሬ ዓይኔ ደከመው፡፡
ሩቅ አየሁ...... ተራሮቹ እስቲ ሞክረኝ የሚሉ መሰለኝ፡፡ ብዙ ግዜ አቅጄ ብዙ ግዜ ፍርሐት እንዳፈገፍግ ወደ አደረገኝ ስፍራ ከመሄድ የሚያግደኝ ነገር እንደሌለ አድማስ አልፈው የተሰለፉትን ተራሮች እያየሁ መንገድ ለመጀመር ኋዜ አህያ ላይ ሲጫን መጨከኔ ገባኝ፡፡

መንገዱን የማይፈሩት አህዮች ጓዛችንን መሸከም ጀምረዋል፡፡

ለእይታ ከሚርቁት ተራሮች ጋር ፊት ለፊት ተፋጥጠናል፡፡ ገብለን የደረስነው በጠዋት ነው፡፡ ገብለን ወደ ጉንዳ ጉንዶ የሚጓዝ ሰው ሜዳ ምድርን የሚሰናበትባት የተራሮቹ ወደብ ናት፡፡ ዓጋመዎች ምድር ነኝ፡፡ ዙሪያውን ታሪክ በከበበው አንድ ስፍራ ኾኜ የተሸሸገ ዓለም ለማሰስ መጥቻለሁ፡፡

የተጓዥ ጋዜጠኞች ቁጥር ሰባት ቢደርስ ነው፡፡ በአህያ የተጫነው ጓዛችን ብዙ ነው፡፡ መተኛችን፤ የካሜራ እግሮቻችን፣ የምንደርበው ልብስ፣ ሻንጣችን፤ በእርግጥም ራስን ይዞ ይኼን የተራራ አድማስ መስንጠቅ ብቻውን ጀግንነት ነው፡፡

ዕቃው ተሸክሮ አህያ ነጂዎቹ መንገድ ጀመሩ፡፡ እኛና ጓዛችንን የያዙት አህዮች እኩል መሄድ አንችልም፡፡ መድረሻቹን ላይ ልንገናኝ ተቀጣጥረናል፡፡ አስገራሚው ነገር ግን ገና ስንነሳ ወደኋላ መቅረት መጀመራችን ነበር፡፡
ወደ ሩቁ ገዳም ጉዞው ጀመረ፡፡ ሩቅ ስላችሁ የእናንተ ሩቅ አይደለም፡፡ የእኔም የከዚኽ ቀደም ዓይነት ሩቅ አይደለም፡፡

ይሄ ጉዞ ከባድ ነው፡፡ አብረንታት አልያም አዘሎ፣ ደብረ አባይ ወይም ደብረ አሰቦ፣ ደብረ ዳሞና ዝቋላ እንደ መሄድ አይደለም፡፡ ወንድ ልጅ በእንብርክክ የሚያስኬድ ገደል ቁልቁል አፍጥጦብኛል፡፡ እንደ ገርዓልታ ተራሮች ጫፍ ምጡ ያላጠረውን ሩቅ መንገድ የውሃ ኮዳዬን አንጠልጥዬ ካሜራዬን አዝዬ ተያያዝሁት፡፡

የኢሮብ እናቶች ልጅ አዝለው ለአስተርዮ ሀገራቸው ለመግባት ቁልቁለቱን ሲጀምሩት እንደ ደጀን እናት እንደ ቅዱስ ያሬድ መንገዱ ቀላል መስሎኝ ነበር፤ እንደዘር አምባ የሰዓታት ጉዳይ አድርጌ ያሰብኩት መንገድ ይፈትነኝ ጀምሯል፡፡

ተሰብስበን የጀመርነው መንገድ ሁለት ሰዓት ሳንጓዝ ተበትነን ተያያዝነው፡፡ መንገዱ ሳይጋመስ ኸረ እንደውም ሳይጀመር እግሬን ወደ አገኘሁበት ቦታ መወርወር ጀምሬአለሁ፡፡ ድካም ሀገሯ እዚህ ነው፡፡ በጉዞ ላይ ሰዓታት አልፈዋል፤ ግን የሚታይ ገዳም የለም፡፡ ይልቁንስ ግዙፍ ተራሮች አፍጠውብኛል፡፡

አባ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ወቅት ምስራቃዊው ዞን ደርሶ ጉንዳ ጉንዶን መርገጥ አልቻነለትም፡፡ ምክንያቱን ሲያስቀምጥ እንዲህ ይላል፤ "ወደዚህ ገዳም መሄድ ፈቅጄ ነበር፤ ነገር ግን ተራራውን በእጅ በመጧጠጥ ካልኾነ በስተቀር ለመውጣት ስለማይቻልና ከገዳሙ ለመድረስ የአንድ ቀን ጉዞ ነው በማለት ለመሄድ ከለከሉኝ" ይላል፡፡[1]

1. አልቫሬዝ፡፡ በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት፡፡ በአቶ ዮና ቢጋለ ወደ አማርኛ የተተረጎመ፡፡ ገጽ 117

በዘመኔ እንዲኽ ለመንገድ ተሸንፌ አላውቅም፤ በዘመኔም ማዶ የተባለ ስፍራ እንዲኽ ልብ የሚያጠፋ አካል የሚያዝል ሩቅ ሆኖብኝ አያውቅም:: እንዲያም ኾኖ የነገሩኝ እንደአልቫሬዝ ያላስቀረኝ መንገደኛ ነኝ:: እኔ ግን ጉንዳ ጉንዶን እንደፈሩት እንደ አንዱ አልቆጠርም፤ ይልቁንም መንገዱን ከደፈሩ እንደ አንዱ ስሜን በራሴ ታሪክ የማነሳ ብርቱ ነኝ:: ይኽ ምድር የዓጋመዎች ምድር ነው:: ዓጋመ ታሪክ ብዙ ነው:: ብዙ ስለ ታታሪዎቹ ተጽፏል:: በትግራይ ምሥራቃዊ ክፍል ይገኛል::

ሬይሞንድ ጆናስ የአድዋን ጦርነት በተረከበት መጽሐፍ የዚያን ዘመን ሁናቴዋን እንኳን ሲገልጸው አዲግራት በለም ሸለቆ ውስጥ ያለች የገበያ ከተማ ነች ይላታል:: አዲግራትና የአጋመን አካባቢዎች በጣም ለም ሲል ነው የሚገልጻቸው::[2] ሄነሪ ሞርተን ስታንሊ እንደ እኔ አዲግራትን ያየ ሰው ነው::[3] ሰውዬው የመቅደላ ዘማቾችን ጉዞ በተረከበት ዘገባ የአዲግራትን ውበት የመንገዱን ጥድና ዛፎች ደስ ማሰኘት፤ የቤተስኪያኗን ማፍዘዝ መስክሯል::[4]

2. ሬይሞንድ ጆናስ:: የአድዋ ጦርነት:: ኤፍሬም እንዳለ:: ገጽ 85

3. ሄነሪ ሞርተን ስታንሊ የአሜሪካው የኒውዮርክ ሄራልድ ጋዜጣ ዘጋቢ ሲኾን የእንግሊዝ ጦር ወደ መቅደላ ሲመጣ ለዘገባ አብሮ ከጄኔራል ናፒር ሠራዊት ጋር ወደ አቢሲኒያ የመጣ ጋዜጠኛ ሲኾን ከጉዞው በኋላ የተመለከተውን በመጽሐፍ መልኩ ጽፎታል:: መጽሐፉን ከዚህ ቀደም የተደበቀው ማስታወሻን የተረጎሙት ዶክተር ገበየሁ ተፈሪ ወደ አማርኛ መልሰውት ለህትመት አብቅተውታል::

4. መቅደላ:: የቴዎድሮስ ዕጣ:: ሄነሪ ሞርተን:: ትርጉም በዶክተር ገበየሁ ተፈሪ:: ገጽ 102

ዓጋመዎች ምድር ነኝ። ዓጋመዎች ብርቱ ናቸው። ሥራ ወዳድ ግብራቸው ስማቸውን አናኝቶታል። የፍስሐ ጊዜያቸው መስቀል ነው።
የዓጋመን ምድር አውቀዋለሁ። ለመስቀል ደጋግሜ መጥቻለሁ። ዓዲግራት ዋና ከተማቸው ናት። አሁን መስቀልን በጋራ ሆ የሚሉባት የኩነት መዲና ኾናለች። አቤት ከዓጋመ ጋር መስቀልን ማሳለፍ፤

"ዓኾኺይ" የሚለውን ቃል ዛሬም ድረስ የማልረሳው ነው። ሰፊ መስከ ላይ ነበር። መስከረም ስለኾነ ለምለም ነው። ከብቶቹ ሜዳ ላይ ይርመሰመሳሉ። ሥርዓቱ ጀምሯል። አዛውንቶች እሳት ይዘው "ዓኾይ ዓኾኺይ" እያሉ ይተኩሳሉ። ድግስ አለው። ዓጋመ መስቀል ከማንነቱ ጋር የራቀ ቁርኝት እንዳለው ለማየት ይኽ በዓል በቂ ነው።
መስቀልን ከዓጋመ ጋር ያላሳለፈ ዓጋመን አውቀዋለሁ ቢል ዕውቀቱ ልክ አይመጣም። መስቀልን ከዓጋመዎች ጋር ማሳለፈ ዓጋመን በብዙ የማወቅ ያኽል ጥቅም ያለው የህይወት አጋጣሚ ነው። ዛሬም ጆሮዬ ላይ "ዓኾይ ዓኾኺይ" የሚለው ቃል ያቃጭላል።
የወንዶች በዓል ነው። ከአምስት የማይበልጡ ቤተሰቦች ወይም ጎረቤታሞች አንድ ቡድን ይመሰርታሉ። እርድ አለው። መስቀል ሳምንት ሲቀረው በሚደረግ ዝግጅት በመዋጮ የተገዛው በግ ወይም ሙከት ይታረዳል። ደሙ በዕቃ ተደቅኖ ይጠራቀማል። አዛውንቶች ደሙን በእቃ ይዘው በቅጥሩ ይረጩታል። በሁሉም አግጣጫ እየዞሩ በዝንጣፊ የሚረጩት ደም በዚህ ቀን መስቀልን ጠብቆ የሚካሄድ ሥርዓት ነው። በየእንሰሳው ግንባር ላይ ደሙን ይቀቡታል።

ቆሜ ከማየው ነገር መንፈሴ ሌላ ስፍራ ሄደብኝ:: ደሙን በጉበኑ መቃን ስለቀቡት እስራኤላውያን አሰብሁ:: እስራኤል በግብጽ እጅ ሳለ፤ እግዜአብሔር ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት ለእናንተ ይኹን ያለውን ቃል ከማየው ጋር አገናኘሁት:: በኦሪት ዘፀአት ምዕራፍ አስራ ሁለት ላይ እንደተገለጸው እስራኤል ጠቦቱን አርደው፤ ደሙን የቀቡት ጉበንና መቃን የግብጽ ሀገር በመቅሰፍት ሲመታ ለእስራኤላውያኑን ቤት ምልክት ኾነና አተረፈ::

ዓኾ኿ይ የከብቶች የበረከት ቀን ነው:: ቀንዳቸው ቅቤ የሚቀባበት፤ ቀንበር የሚያርፍበት፤ ገላ ከብር የሚቀናጅበት:: ጥጃ እስከትጠግብ የእናቷን ጡት የምትምግበት፤

በዓጋመዎች ምድር እየተጓዝሁ ነው:: የዓጋመዎችን መስቀል ሳስብ ትዝታ ጉልበቴን ያበረታዋል:: ወይኖ /ሲታገል/ በርሃ እንደ ገባ ሰው የኢያሱ በርሄ
"ዓጋመ ዓደይ ሜዳ ውልዋሎ
ዝናር ከዓጥቐ ብረት ከልዕሎ
ስረ ወለደይ 'ውን ይብለነ'ሎ" የሚለው ዘፈን ሩቅ ይወስደኛል:: ለነገሩ አሁንም ሩቅ እየኼድሁ ነው::

መንገደኛው ብዙ ነው:: አንዳንዱ ከመንገዱ የተሻረከ ይመስል በሚያስፈራ ገደል ቆሞ ቁልቁል ተንሸራቶ እንኳን አይወድቅም::
እናቶች ስዕለት ሆኖባቸው በዝማሬ ስጦታቸውን አዝለው ያለ ጭንቀት ይወርዱታል:: እኔ እዚህ እየሄድሁ፤ በምናብ መስቀልን እናፍቃለሁ:: ለደብረ ገሪዛን የሚሰጠው እልልታ ወደ መስቀል በትዝታ ወስዶኛል::

እልልታ እሰማለሁ:: ዓጋመዎች እንዲህ ያለ የደስታ ቀናቸውን በዕልልታ ያጅቡታል:: የመስቀሉ ችቦ ከቀንዳዕሮ ተራራ ላይ ሲወረድ ጨለማውን ከሚያሸንፍ የችቦ ብርሃን ጋር የሰማኹት የዕልልታ ድምጽ ተራሮች በከበቧት ከተማ ያስተጋባ ነበር:: ቀንዳዕሮ በተራሮች ከተከበበችው አዲግራት ከተማ አቅራቢያ የሚገኝ ኮረብታማ ስፍራ ነው:: አናቱ ላይ ከቆመው መስቀል ስር የሚለኮሰውን ችቦ የያዙ ሰዎች በሰልፍ ወደ ከተማዋ እንብርት ይመጣሉ::

አዲግራትን በመስቀልም ያለ መስቀል ሰሞንም አይቻታለሁ፤ ግን የመስቀል ሙሽራ ናት:: ሁሉ ነገሯ ከመስቀል የተቆራኘ ከተማ:: በዋዜማው ደመራ አታበራም:: ሲጨልም የተራራው መስቀል በራ:: ይኸ ባለ 28 ሜትር መስቀል የቆመበት ስፍራ ለብዙ ጊዜ መጠኗ አነስተኛ በአርማታ በተተከለች ስፍራ የቆመች መስቀል ነበረችበት:: አሁን ከየትም ሲታይ የሚበራው መስቀል ቀንዳዕሮ ቆሟል::

እንዲኸ ያለው ባህል ነፍሴን ዓጋመዎች ዘንድ እስረኛ አድርጎ አስቀርቷታል፤ አሁንም በታሰርሁበት ምድር ነኝ:: በፍቅር የታሰረ ሰው በጠብ አይፈታም:: እንዲህ ባለ የሀገሬ እሴት ያለ ዋስ ወህኒ ገብቼ ከተቀረቀርኩ ቆየሁ:: ከዚያ የመንፈስ እስር ቤቶች አንዱ ይኼ ድንቅ የዓጋመዎች ባህል ነው::
ከቀይ ባህር ወደ ከነዓን የሚገቡት እስራኤላውያን መሀል የገባሁ እስኪመስለኝ ድረስ ጉዞው አድካሚ ቢሆንም ሰንሰለታማዎቹን፣ ሲታዩ የሚያስፈሩትን፣ የማይደረስባቸው የሚመስሉትን የትግራይ ተራሮች እንደ ቃዴስ በርኔ እያቆራረጥሁ የበረከት ሀገር ወደ ተባለችው ደብረ ገሪዛን መጓዜን ቀጥያለሁ::

ማኅበረ እስጢፋኖሳውያን ይኸቺን ዓለም እንዴት እንደተጠየፏት ገባኝ:: ዓለምን ንቀዋታል:: የቤተ መንግሥቱ ወሬ የማይሰማበትን የምድር ጥግ መርጠዋል:: ሰማይን ጣሪያቸው አድርገው ከሰው በራቁ ሰንሰለታማ ኮረብታዎች የምንፍስና ከተማ መርጠዋል:: ተራሮች አያልቁም:: ያለፉኩት ድጋሚ ከፊት የቀደመ እስኪመስለኝ አንድ ዓይነት ተራሮች ደጋግመው ያጋጥሙኛል:: እወጣለሁ እወርዳለሁ፤ ሩቁ ገዳም ጋር ለመድረስ::

የማኅበረ እስጢፋኖሳውያን አባት አባ እስጢፋኖስ ነው:: አሁን ካለሁበት ምሥራቃዊ የትግራይ ምድር ልዩ ስሟ ስቡሐ ከምትባል ቦታ አንድ ቀን አንድ ሰው ተወለደ:: ጊዜው 1387 ዓ.ም. ነው:: እናቱ ሣራ ትባላለች:: አባቱ ብርሃነ መስቀል፤ የሙት ልጅ ነው:: እንደ ተወለደ አባቱ ሞተ:: ስሙን ኅድገ አንበሳ አሉት::

ያደገው በአባቱ ወንድም ቤት አጎቱ ዘንድ ነበር፤ ገና በልጅነቱ ጠባዩ ሸጋ እንደ እኩዮቹ ቧልት የማያምረው ብስል ኾነ:: ትምህርት ጀመረ:: እውቀቱ ወደ ምንፍስና መራው:: በወጣትነቱ ወደ ቈየጻ ገዳም ገባ፤ መነከሰ:: ስሙም እስጢፋኖስ ተባለ::

ወደ ማኅበረ እስጢፋኖስ ታሪካዊ ገዳም እየተጓዝሁ ነው:: ከአሲምባ ተራሮች ወዲህ ከተገተሩት ግዙፍ ተራሮች ስር ወደ አረፈው ገዳም ስጓዝ እግሬ መሆን እስኪቀራቸው አብረውኝ የነበሩ ኢሮቦች አይረሴ ናቸው:: የኢሮብን ደግነት ሳስብ የአሲምባ ስትራቴጂያዊ ቦታነት ይገዝፍብኛል:: እንደ ልጁ የሚያይ ማኅበረሰብን የሚያህል መሸሸጊያ ከወዴት ይገኛል::

ኢሮቦች ጓዳቸው የእንግዳ ነው፡፡ ነጩን ማር በአነባበሮ ያለ ስስት ዝቀው ለምነው ያበላሉ፡፡ ለማርያም የጠመቁት ጠላ ሳይቀመስ መንገድ ጠይቆ በዚህ ነው መባል እንደሌለ ገባኝ፡፡ ከኢህአፓ እስከ ህወሓት ወደ አሲምባ ተራሮች አናት የወጡት የቦታው ምቹነት ብቻ ማርኳቸው ሳይሆን የኢሮቦች ጓዳ ቸርነትም ታድጓቸው መሰለኝ፡፡

አብረውኝ ያሉት ማርዋ ደርሰናል አሉን፡፡ ዮናስ የትግራይ ባህል ቱሪዝም ባለሙያ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም መጥቶ ያውቃል፡፡ ድፍረቱ የገረመኝ መንገዱ አልገፋ ሲል ነው፡፡ የካሜራ ባለሙያዬ ዮናታን ድካም ተስፋ አስቆርጦታል፡፡ መሄድ እንጂ መድረስ እንደሌለ ራሱን አሳመነ፡፡

ኢሮቦች ወደ ቤታቸው አስገቡን፡፡

የኢሮብ ጎሳዎች ከምስራቃዊ የትግራይ ሰንሰለታማ ተራሮች ግርጌ እስከ ቀይ ባህር በሚዘልቀው ምድር ይኖራሉ፡፡ ከብት ያረባሉ፤ ከበርሃው ሥነ ምህዳር እጽዋት ንብ ያንባሉ፡፡ ወይናደጋማውን ክፍል የሚኖሩበት የኢሮብ ጎሳዎች ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ ሐሰበላ፣ ቡክናይታና አድጋዳ ጎሳዎች ቀናኢ ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ ቡክናይቶዎች በስፋት በአካለ ጉዛይ ሲኖሩ ሁለቱ በዓጋመ ምድር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ ጎሳዎች ናቸው፡፡[5]
አሁን ኢሮቦች መንደር ነኝ፡፡ ምድሩ ጭምር አንዳች መንፈስ አለው፡፡ እንግዳን ባለቤት የሚያደርግ፤ አዲስ መንደር፣ አዲስ ቀዬ ገብቻለሁ፡፡

5. ጊጋር ተስፋዬ፡፡ የኢትዮጵያ ዓመታዊ ታሪክ መጽሔት፡፡ 13ኛ መጽሔት ገጽ 55

አዲስ ስፍራ እንደመጣ ሰው ባይተዋርነት አልተሰማኝም፡፡ በተቃራኒው ደጋግሜ ወደመጣሁበት የቤተሰቦቼ ባድማ የደረስሁ መስሎኛል፡፡ የድንጋዮ ቤት ነፍስ በሚያሳርፍ ቅዝቃዜ ተቀበለን፡፡ ቁጭ ብለው የሚጫወቱ መንገደኞች አርፈውበታል፡፡

ኢሮብ ማለት በሳሆ ቋንቋ ኢሮባ ከሚለው የመጣ ቃል ነው ሲባል ስሰማ የኖርሁት እውነት ለመሆኑ እያየሁ ነው፡፡ ኢሮባ ማለት ወደ ቤት ግቡ ማለት ነው ይላሉ ትርጓሚውን፡፡ እዚህ ደጃፍ ለእንግዳ ተከፍቷል፡፡ ገብተናል፡፡

ቋንቋ አያስፈልግም፡፡ አቤት መስተንግዶ፤ ማር በዳቦ ተቀብቶ ቀረበ፡፡ የቅንጡ ሎጂ በረንዳ በሚመስል ደጃፍ በጥበብ ከታነጸ ቤት በረንዳ ላይ ነፋስ እየወሰድን ተጋበዝን፡፡ አደግድገው የሚያስተናግዱት የቤቱ አባወራ ልባቸውን በሚሞላ መልኩ እንደ ልብ አልበላ ብለናቸው ተቸግረዋል፡፡ በዓመት አንዴ የሚገኘውን ውድ ማር ከመጋበዝ በላይ ምን ስጦታ አለ?

ጠጅ ተቀዳ፡፡ መንገደኛ መኪናችንን ረሳነው፡፡ ኢሮብ ግብዣ ያውቃል፡፡ ስምትልህ የሚለው ኢትዮጵያዊ መንፈስ ለካ ቋንቋ አይደለም፡፡ መስቀልን ከኢሮቦች ጋር አሳልፌ አውቃለሁ፡፡ ያ መስቀል ትዝታው አብሮኝ ይኖራል፡፡

አይጋ ከፊቴ አሲምባ ከኋላዬ አጅበውኝ ያሳለፍሁት የተራሮች ስር ድግስ ነው፡፡ ደዋሃን የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ናት፤ ደምቃ ነበር፡፡ ኢሮቦች ትልቁ በዓላቸው መስቀል ነው፡፡

በኢሮብ መስቀልን ሰው ሀገሩ ካልገባ ወይ ሞቷል ወይ ታስሯል እንደሚባልበት ዘመን ሁሉ ዛሬም ኢሮቦች ተራራ የማያሸንፈው ወዳጅ ዘመድ የመናፈቅ ልብ ይዘው እየቀዩቸው ሲገቡ አብሬ ገብቼ ድንቅ ነገር አይቻለሁ፡፡

ለመስቀል ብዙ ይዘጋጃሉ፡፡ የእርዱ ፍየል እንኳን ዓይነቱ ይለያል፡፡ ደግሞ ሰውነት በልጦ ይገዝፋል፡፡ በቀይ አምባው እና በአይጋ መሃል ያረፈችው ከተማ መስቀልን በጋራ ለማክበር ድንበር የለባትም፡፡ የኢሮብ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን መስቀሉን በሀገሩ ወግ ታከብረዋለች፡፡ እንዲኽ ሲኾን የነበርሁ እና ያየሁ ነኝ፡፡ እሳት እሳት ወደ አደረገው ድንጋይ ተጥዶ የበላሁት ስጋ ጣዕም አሁን የኾነ እስኪመስለኝ አፌ ውስጥ ተላወሰ፡፡ አጣጣምሁት፤ ጠጁ ነበር ምላሴ ላይ የቀረው፡፡
ዓጋመዎች ለጠጅ ዘፍነዋል፡፡ ኪሮስ ዓለማየሁ የዓጋመ ምድር የተወለደ ኢትዮጵያዊ ዘመን አይሽሬ ድምጻዊ ነው፡፡ ንጹሁን የማር ጠጅ ፉት ስል ከጠጁ ጋር አብሮ ድንቅ ዜማው ወደ ውስጤ ገባ፤
"ሜስ ናይ ዓጋመ
እናሓደረ ጠዓመ"..... ዜማውን ጆሮዬ ብቻ ሳይኾን ምላሴም ቀመሰው፡፡ እውነትም የዓጋመ ጠጅ እያደር የሚበጅ፡፡
ውጡ ውጡ ከማይለው ቤት ወጣን፡፡ ገና ያፈጠጡ ተራሮች ሽቅብ እንወጣለን፡፡ ገና ዝንጀሮ ወዬው ጉዴ የሚልባቸው ገደሎች እንወርዳለን፡፡

---

6. ኪሮስ አለማየሁ በትግርኛ ሙዚቃ ታሪክ ከፍ ያለ ሥፍራ ያለው ተወዳጅ ድምጻዊ ነው፡፡ ተስፋዬ ለማ የኢትዮጵያን ሙዚቃ በጻፈበት መጽሐፍ በገጽ 292 ኪሮስ የራስ ቲያትር ወጣቶች የሙዚቃ ቡድን አባል እንደነበር ይገልጻል፡፡

ምስጋና አቅርበን ወጣን:: የቤቱ ሰዎች እኛን ሸኝተው የሚመጣ እንግዳ ለማስገባት ወንዟ ዳር ቆሙ:: እንደ አብረሃም በእንግዳ እስትንፋስ የሚኖር ህዝብ ኢሮብ፤
የትግሉ ስፍራ ነው ተብሎ እንደ ተረት እስኪቆጠር ስሙ በሚነሳው ማርዋ ቀበሌ አድርገን ሄይለ ወንዝን ተከትለን ጉዞአችንን ቀጠልን::

ወንዝ ወንዙን ተጉዘን፤ ዳገት አፈጠጠብን:: የመጨረሻው ዳገት እንደኾነ አምነን ሽቅብ ወጣን:: ስንደርስ ያልተጋመሰ መንገድ ነው:: ቁልቁል ሌላ ጉዞ አፍጥጧል:: የሚታይ የሌለበት ሩቅ ስፍራ:: አንድ ቀን አይመስልም:: ሰው እንዴት በአንድ ቀን ብዙ ቀን ይጓዛል?
"የመጨረሻ ቁልቁለት ነው:: በርቱ አሉ፤" አንድ ጠና ያሉ ሰው:: ጥቂት አርፈን ተነሳን::

ብዙ ተራሮች ታልፈዋል:: ጉልበቴን እየጠዘጠዘኝ መንገድ ባደከማቸው ተጓዦች ተከብቤ የመጨረሻውን ቁልቁለት እየወረድኩ ነው:: የአንድ መንገደኛ እናት ድምጽ ቁልቁለቱን አደበላለቀው:: ሸጋ ድምጽ ነበር:: ማርያም ጉንዳ ጉንዶ እያሉ በትግርኛ ያዜማሉ:: የሚሰማው እልል ይላል:: ስዕለታቸውን ይዘው ቁልቁል ሲንደረደሩ የዳገት አወራረዳችን ብልሃት ለየቅል ስለኾነ የወደድሁት ድምጽ እየራቀኝ ሲመጣ መንቀራፈፌ ገባኝ::
ከርቀት የተመለከትኩትን የብርቱካን ደን ደረስኩበት:: የጉንዳ ጉንዶ ብርቱካን የሚባለው ይኸ ነው:: ዘሩ የገነት ነው ይላሉ እናቶች:: ከዛላምበሳ እስከ መቐለ ጣፋጭ ብርቱካን ሲሸጥ የትም ቢመረት የጉንዳ ጉንዶ ነው ይባላል::

አሁን ጉዞው ረዥሙን ወንዝ ተከትሎ፤ ወደ ሰማይ በጎኑ ተራሮች መሀል ሆኗል። ተራሮቹ ድንገት የሚፈርሱ እስኪመስለኝ እሰጋለሁ። እናታቸው ላይ ያረፉ ቋጥኝ ድንጋዮች አስፈሪ ናቸው። ፍርሐት እና ድካም ድል ሊነሱ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ነኝ።

ሄይለ ወንዝን ተከትዬ ከማርዋ እዚህ እስከደርስ ግማሽ ቀን ያኽል ተጉዣለሁ። እድሜ ለኢሮቦች ድግስ ነጭ ማር በእነባበሮ እየበላሁ ስለመጣሁ ጉዞው ከአድካሚው መንገድ ውጪ እግሬን በሰበረኝ አላስባለኝም።

ተራራ ላይ ደረስን። ሌላ ቁልቁለት ገደል እንደሚወጣ ዝንጀሮ ዓይናችን ላይ ተለጠፈ። ጸሐይ ከሰማዩ ላይ ሸሸታለች፤ እንደ አቡነ አሮን ጸሐይን አቁሜ ካልኼድኩኝ አሊያም ርምጃዬን ካልጨመርኩኝ ቀሪው መንገድ አስጊ ነው። ሁላችንም ፊት ላይ በቀረው ቁልቁለት ድንጋጤ ተፈጥሯል። ቁልቁል በተዘረጋው ገደል ማዶ ያለውን ስፍራ አሻግሬ ዓይኔን ላኩ፤ የብርቱካን ዛፍ እንደ ሜዳ የተኛበት የሩቁ ገዳም አካባቢ ታየኝ። ቁልቁለቱ በዳዴ የሚወረድ ነው። የለመደው እንጣጥ እያለ መንገድ ያሳጥራል። በአበሳ አንድ ሰዓት ሊጠጋ ምንም ያልቀረው ጊዜ ፈጅተን ምድሩ ወለል ላይ ደረስን።

አሁን ደግሞ የወንዝ ውስጥ ጉዞ ቀጠለ፤ አሸዋው ወደ ኋላ እየመለሰኝ ቀላል የሚመስለው መንገድ አንድ ሰዓት ሊፈጅ ሆነ። ከረዣዥሞቹ ተራሮች ስር በድንቅ ጥበብ በድንጋይ የታነጹ የኢሮብ ቤቶች ተራራው ላይ ተለጥፈው አየሁ። ተአምር ሆነውብኛል። መምጣትም በራሱ ተአምር ነው።

ቀጥ ካለው ዓለት ስር ቆመው የኾነ ነገር የሚያወሩ ሰዎች አሉ:: ሰው ሁሉ ሲያልፍ የኾነ ድምጽ ያሰማል:: ድምጹን ሲያሰማ ዓይኑን ሽቅብ ወደ ዐለቱ አናት ልኮ ነው:: ምንድን ነው? ስል ዘንዶ አሉኝ:: ድምጹን እንዴት እንዳልሰማሁ ጠየቁኝ:: ሲነጋ እደርስበታለሁ ብዬ በድካም የመጨረሻዋን የጉዞ ምዕራፍ ታገልኳት::

ይሄ ከስዋ ይባላል:: የቀድሞ ስሙ ነው:: አባ እስጢፋኖስ መሰረቱት በአባ ዕዝራ ቀና፤ ከዚያም ደብረ ገሪዛን ተባለ:: ሙሉ ስሙ ሲጠራ ደብረ ገሪዛን ጉንዳ ጉንዶ ማርያም ገዳም:: ጨለማው እየበረታ ነው:: ብርሃን በሽሽ ቁጥር እልልታ ይቀርበን ጀመር::

# ጉንዳ ጉንዶ ማርያም፡፡

" አገሬ ቅኔ ምድር
በቅኔ ማሕሌት የዘረፉሽ
ያመሰጠሩሽ ቅኔ ነሽ፡፡
ባንድምታ መጽሐፍ እንዳለ
አንድም እንዲህ፤ አንድም እንዲያ ነሽ፡፡
አንድም፤
እንደተገሠጸ መንፈስ በአቡዬ ስም እንደወጣ
'ፃኣ መንፈስ ርኩስ' እንዳሉት እንደ ቤተ ጠበል ጣጣ፤
ጥም እንዳሰከረው በበረሓ እንደሚዳክር መድረሻ እንዳጣ ዋላ
ደራሽ እንደሚያንገላታው ከሥሩ እንደተነቀለ ጊዜ እንደጣለው
ግንዲላ፡፡
ልጆችሽን እንደ ልደታ ንፍሮ ለአገር ለወንዞ በትነሽ
የዕጣን ሽታ የናፈቀው የተዘጋ መቅደስ ነሽ፡፡"

ግርማ ተስፋው፤ የጠፋችውን ከተማ ኅሠሣ

የወደቅሁበትን ያየሁት ሲነጋ ነው፡፡ ወፍ ሲጮህ ዓይኔን ገለጽሁ፡፡ ሰማይ ታየኝ፡፡ ሜዳ ላይ ያነጠፍነውን ሙሽማ ተሸምተን ተኝተን ነጋ፡፡ ደብረ ገሪዛን ነኝ፡፡ እንዴት እንደመጣሁ ሳስብ የህልም ዓለም ጉዞ መሰሎኛል፡፡ የካሜራ ባለሙያዎቹ ሳሙኤል ኃ/ማርያምና ዩናታን ታደሰ፣ ጋዜጠኛው እስናቀ ብርሃኑና ትእግስቱ በለጠ፣ እዚህ ያደረሰን ዮናስ፣ አብሮን ተነስቶ ቀድሞን ደርሶ የተቀበለን የመቐለው ጋዜጠኛ ሁሉም አልተነሱም፡፡

የማታውን ድባብ ለማስታወስ ሞከርኩ፤ እንደደረስን አልልታ ነበር፡፡ ቀድሞ የደረሰው ብዙ ህዝብ ጧፍ እያበራ ይዘምራል፡፡ ብዙም ሳይቆይ በቡድን በቡድን የሚቀመስ ታደለ፡፡ ደክሞን ስለነበር አንዳችንም ተሻምቶ ለመብላት አቅሙ አልነበረንም፡፡ ዝማሬው አባብሎ ያስተኛን መሰለኝ፤ በተቀመጥንበት ቦታ ምንጣፋችንን ዘረጋን፡፡ ማን ቀድሞ እንደተኛ አላስታውስም፤ ቀድሜ ተነስቼ ስመለከት ዙሪያውን ሰው ብቻ ነው፡፡

ሩቁ ገዳም ውስጥ ነኝ፡፡ ደቂቀ እስጢፋኖሳውያኑ ከቁጡ ነገሥታት እና ዓለም ካጓጓቸው መነኮሳት አምልጠው የተሸሸጉበት ገዳም፡፡ የማኅበረ እስጢፋኖስ መሥራች አባ እስጢፋኖስ ነው፡፡ ዛሬም ድረስ የሚያከራክረው ታሪክ ብዙውን ሰው ሁለት ጎራ ከፍሏል፡፡ ጻረ ማርያም በሚል ስማቸው ሲነሳ ወደኖረው ደቂቀ እስጢፋኖሳውያን ገዳም ማርያምን ላነገስ መጥቻለሁ፡፡
እርግጥ ነው የደቂቀ እስጢፋኖሳውያኑ ጉዳይ ዛሬም አነጋጋሪ የሆኑ ሌላ አጀንዳ ለመሸከም የሚችል ድንቅ ጫንቃ ያለው ጉዳይ ስለሆነ ይመስለኛል፡፡ ደብተራው በአማን ነጸረ ወልታ ጽድቅ በተባለው መጽሐፍ ጉዳዩን ያየበት አግባብ ሁሉን በልኩ የሚፈታ እውነት መስሎኛል፡፡
ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ በነገሠበት ዘመን የገዳማቱን ሁሉ ትኩረት የሳበ አንደበተ ርዕቱ የብህትውናው ኑሮ አስደናቂ የሆነ መናኝ የቤተ መንግሥቱ አጀንዳ ኾነ፡፡ ደጋግሞ ንጉሡ ፊት ቀረበ፤ ደጋግሞ የቀረበለትን ጥያቄ መለሰ፡፡ የንጉሡን ስለምናዊ መኾን አልተቀበልከም ተባለ፡፡ "ከእስራኤል ዘሥጋ እስራኤል ዘነፍስ ይበልጣል፡፡" ብሎ በመለሰው መልስ ነጻ ወጣ፡፡

መነኮሳት በዓለማዊ ስልጣን መሳተፉ የለባቸው አለ፤ ደብረ ጽዮን የለችም ይላል፤ አረማዊ ቤቱ ክርስቲያን ያስገባል፤ ለሥላሴ ካልኾነ በስተቀር ለሌላ አልሰግድም ብሏል፤ ያለ ታቦት ይቀድሳል፤ ለንጉሡም አይሰግድም፤ ክሶቹ ብዙ ናቸው:: ሁሉንም ድንቅ አድርጎ ስለመመለሱ አባ ገብረ ክርስቶስ ያኖረው ትረካ ምስክራችን ነው::

የንጉሡ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ጸሐፊ "እፍንጫዎቻቸውን ፎነኗቸው፣ ምላሶቻቸውንም ቆረጧቸው፣ በድንጋይም ወገሯቸው፣ ይህ የኾነው የካቲት ፪ ቀን ነው" ይላል::[7] ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል፤

ሁሉም ሰው ከመኝታው መነሳት ጀመረ::

ድካም ዘርሯቸው ያደሩ ሰንበት ተማሪዎች አረፍቷ ብርታት ኾኗቸው መዘመር ጀምረዋል:: ከመቐለ እና ከአዲግራት የመጣው ተጓዥ ብዙ ነው:: ከጀርባችን አንዲት ከብ ቤተ ክርስቲያን አለች:: ከአናታችን ቁልቁል የሚመለከተን ዋናው ቅጥር ነው::
ጥር ሃያ አንድ ቀን የአስተርዮ ማርያም የጠዋት ድባብ በጉንዳ ጉንዶ ይኼንን ይመስላል:: ኢሮብ ከያለበት መጥቷል:: ተራሮች ሰው በሚፈትኑበት ምድር ከየትም አሳብሮ እዚህ መድረስና ጉንዳ ጉንዶ ማርያምን ማንገስ ሊድርድር የሚገባ ጉዳይ እንዳልኾነ አየሁ::

7. የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል:: ከግዕዝ ወደ አማርኛ በዓለሙ ኃይሌ የተተረጎመ:: ገጽ 36

ያለሁበት ስፍራ የቀናው በአባ አበከረዙን ነው፡፡ ደቂቀ እስጢፋኖሳውያን በዘርዕ ያዕቆብ በትር ሲመቱ፣ ሲሰደዱ፣ ሲገረፉ የመንፈስ አባታቸው አባ እስጢፋኖስ በእስር ላይ በነበረበት ጊዜ ማኅበሩን የመሩት፣ አባቶችን ያጽናኑት፣ ከሰዋን ያቀኑት አባ አበከረዙን ናቸው ይላል የቦታው ታሪክ፡፡[8] ማኅበረ እስጢፋኖሳውያን አባ አበከረዙንን እንደ ቀዳሚ የጉንዳ ጉንዶ አበምኔት ይቆጥሯቸዋል፡፡ በአክሱም አውራጃ ናዕዴር ቀበሌ ከታላላቅ ቤተሰብ የተገኙት አባ አበከረዙን ከአባ እስጢፋኖስ ጋር የተዋወቁት በቆየፃ ገዳም ሳሉ ነበር፡፡[9]

ማኅበረ እስጢፋኖስ ጠንካራ ገዳማዊ መዋቅር አላቸው፡፡ አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርትን የያዘው ቡድን ማኅደር በሚል የሚጠራ የመጀመሪያው እርከን ነው፡፡ የማኅደር ስብስቦችን የያዘው ማዕከላዊ መዋቅር ደግሞ ማኅበር ይባላል፡፡ ከፍተኛው መዋቅር ገዳሙ ነው፡፡

የገዳሙ አባት የኾኑት አባ ለምለም እንደገለጹልኝ ሽሬ ቆየጻ ገዳም የተመሰረተው አንድነት አራት ማኅበር ነበረው፡፡ አንዱ እዛው እስከመጨረሻው ሽሬ የቀረ ነው፡፡ አንደኛው ተንቤን ገባ፡፡ አንዱ ማኅበር በዛሬዋ ሀገረ ኤርትራ ሲሄድ ሌላውና በአቡነ ይስሐቅ የሚመራው ደግሞ ወደ ከሰዋ፣ ደብረ ገሪዛን ጉንዳጉንዶ መጣ፡፡

---

7. የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል፡፡ ከግዕዝ ወደ አማርኛ በዓለሙ ኃይሌ የተተረጎመ፡፡ ገጽ 36

8. የደብረ ገሪዛን ጉንዳ ጉንዶ ማርያም ታሪክ ያልታተመ ብሮሸር፡፡

9. ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ፡፡ በጉንዳ ጉንዶ ማርያም ገዳም የታተመ፡፡ ገጽ 26

ለሽንት ወጣን፤ የገዳሙ ቅጥር በለመለሙ የግራር ዛፎች የታጀበ ነው:: የጥንቱ ሕንፃ ከፍ ካለ ቦታ አርፏል:: የገዳሙ አካል ረገሮችሮቹ ተራሮች ስር የተሸሸገ ነው:: በዙሪያው የከበቡት ተራሮች ላይ የተገነቡ የድንጋይ ቤቶች በጎርፍ የሚወሰዱ፣ በየጊዜው ፈርሰው የሚሰሩ ናቸው:: ከፍታ ላይ የሆኑት እንዲኽ ኾነው በሁለት ወንዞች የተከበበው እና ለዕይታ ዝቅ ካለ ስፍራ ላይ ያረፈው የገዳሙ ቅጥር ግቢ ግን እየጋለበ ቀይ ባህር በሚገባው ወንዝ አደጋ ገጥሞት አያውቅም:: እናም አቤት ጥበብ ማለት ይህንን ምህንድስና ነው ስል አሰብኩ::

ዙሪያው በድንቅ ለዕይታ በሚማርኩ፣ ደቂቀ እስጢፋኖሳውያን ምን ሲያደርጉ አዩት በሚያስብል ምድር ላይ ያረፈ ነው:: ትንሽ ውሃ ያላት ወንዝ በበጋም አልደረቀችም:: በዐለቱ ወገብ ላይ ከድንጋይ የታነጹት ቤቶች የሰው ልጅ ጥንካሬ እንደስፍራው የሚለካ እንደኾነ ማሳያ ናቸው::

ተመልሰን መጀመሪያ የአደርንባት ስፍራ ወደ ነበረችው ቤተ ክርስቲያን ገባን:: ከብ ናት፤ ዋናው ገዳም የወንዶች በመኾኑ ለሴቶች የተሰራች ቤተ ክርስቲያን ናት:: አስቀድሞ በዘመነ መሣፍንት ነበር የተሰራችው፤ ፈርሳ ዳግም ተሰርታ ነው::
ቀስ ብዬ በቀጭንና ጉልበት በሚፈትነው መንገድ ወደ ወንዶቹ ገዳም ወደ ጥንታዊው ስፍራ አመራሁ:: የድንጋዮ ግድግዳ የውስጥ ለውስጧ መንገድ ከጀጉል አስታራቂ ጎዳና ጋር ተመሳሰለብኝ:: ከርቀት የማየውን ሕንፃ ቤተክርስቲያን ስጢጋው አሰራሩ እጅን አፍ ላይ ያስጭናል:: የሚደንቅ ነው::

የዛሬ ስድስት መቶ ዓመት የተገነባ ነው፡፡ የተጠበቡበት መናኝ አባ ዕዝራ ይባላሉ፡፡ አባ ዕዝራ ከማኅበረ እስጢፋኖስ መነኮሳት ስማቸው ጎልቶ ከሚነሳ ጥበበኞች አንዱ ናቸው፡፡ አባ ዕዝራ ሀገሩ ስቡሐ ነው፡፡ ከጽዮን ጋር ከእስራኤል ከወጡ ከሌዊ ነገዶች የተገኙ እንደኾነ ታሪኩ ያስረዳል፡፡ አባቱ ይስሐቅ እናቱ ልዑል ሰምራ ይባላሉ፡፡ እንደ አባ እስጢፋኖስ ሁሉ አባ ዕዝራም አባቱ በልጅነቱ ሞተ፡፡[10]

የመነኮሰው በአስራ ሁለት አመቱ ነበር፡፡ የሚካኤል የስልት ልጅ ስለነበረ የመጀመሪያ ስሙ ዐቀበ ሚካኤል ሲኾን ሲመለኩስ ዕዝራ ተባለ፡፡ አባ ዕዝራ የሚለው ስያሜ አንድ የማኅበረ እስጢፋኖስ አባል አባት ብቻ ሳይኾን በጥበቡ ስሙ ከዘመን ዘመን የተሻገረ መነኩሴ መጠሪያ ኾነ፡፡

አስቀድሞ የተሰራው ቤተ ክርስቲያን የሳር እንደነበር የስፍራው ታሪክ ይናገራል፡፡ ከአስራ ሦስት ዓመት በኋላ በአባ ዕዝራ ይኼ ዛሬ ድረስ የቆመው ሕንፃ ተገነባ፡፡ የማየውን ነገር የዛሬ ስድስት መቶ ዓመት አንዳች ምቹ ነገር በሌለበት በዚህ ስፍራ የተሰራ ቅርስ ስለመኾኑ ከማመን የሚበልጥ ምንፍስና የለም፡፡ አራት መዓዘን ዓይነት ቅርጽ ያለው ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ጣሪያው ቆርቆሮ ነው፡፡ ለዘመናት የኖረው እና ከዓመታት በፊት በደረሰበት አደጋ የተቀየረው የሳር ክዳን የለም፡፡ ትናንት በድንጋይ እንዲኽ የተጠበቡ አባቶች ነበሩን፡፡ ዘመን ዛሬ ለማደስ እንኳን ተቸግሮ ግራ ገብቶት የሚመለከተውን ድንቅ ቅርስ ተደምሜበታለሁ፡፡ ይሰሯል እንዲህ ነው፡፡

10 ደቂቀ እስጢፋኖስ፡፡ በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፡፡ ገጽ 28።

ደብረ ገሪዛን የነገሮች መነሻም መድረሻም ማርያም ናት:: ከቀናት ሁሉ የሚበልጠው ጥር ሃያ አንድ ነው:: ጥር ሃያ አንድ ቀን እዚኽ ደርሻሁ::

በሮች የሌሉት መሆኑ ገርሞኛል:: ወደ ውስጥ ገባሁ:: አሁን በኢትዮጵያ ከአምስት መቶ ዓመታት በላይ ኖሮ ዛሬም ግርም የሚለው ኪነ ሕንፃ ውስጥ ነኝ:: ይኸ ሌላ ገጽታችን ነው:: እንደ ላሊበላ ውቅር ዐለት ያልሆነ፤ እንደ ጎንደር፣ እንደ ሀረር እንደ ሌሎችም የማይመስል፤ የራሱ መልክ፣ የራሱ አሰራር፣ የራሱ ጥበብ የሚታይበት ሕንፃ፤ እያንዳንዱ ጥበብ ላይ የአባ ዕዝራ አሻራ ታትሟል::

አባ ዕዝራ ሲበረታ በዘመኑ የነበሩት ጳጳስ አባ ገብርኤል አርፈው ነበር:: በዚኽ ሳቢያ ከሕነት የሚሰጥ ጳጳስ አልነበረም:: ችግሩ በጣም ከፍቶ ማኅበረ እስጢፋኖሳውያንን አሳሰበ:: አባ አበከረዙን ማኅበሩን ስብሰባ ጠርቶ ሁኔታውን ለውይይት አቀረበ::
"ያለ ክህነት መኖር እንደምን ይኾንልናል?" ሲል ጥያቄም አቀረበ::
አንዳንዶች ሀሳቡ ሀሳባቸው መኾኑን ገልጸው በዚያውም ኢየሩሳሌም የጌታን መቃብር ተሳልመው፣ ለጳጳሱም በሀገር ቤት ስለገጠማቸው ፈተና ገልጸው ስለመምጣት ተናገሩ:: ሀሳቡ ተቀባይነት አገኘ:: ከዚያ ቀደም በዚህ መልኩ ለመሄድ አቅደው በስደቱና በስቃዩ ሳይሳካላቸው የቀሩ እንደነበሩ በአባ አበከረዙን ተነሳ:: በዚህ መልኩ ወደ ኢየሩሳሌም ከተጓዙት አባቶች አንዱ አባ ዕዝራ ኾነ::"

" ደቂቀ እስጢፋኖስ:: በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ:: ገጽ 283

ወደ ሕንፃው ውስጠኛ ክፍል ገባሁ፡፡ ካህናቱ እየተዘጋጁ ነው፡፡ ቃለ እግዚብሔሩ በቅኔ ማሕሌቱ ቀጥሏል፡፡ ከቅኔ ማህሌቱ ወደ መቅደሱ የሚያስገባው በር በግሩም ሁኔታ የተሰራ ነው፡፡ እንዲኽ ዓይነት ብሎ መጻፍ መቻል ራሱ የመስራትን ያኽል ሌላ ጥበብ የሚጠይቅ ነው፡፡

የመስኮቶቹ ቅርጽ እንጨት ላይ ከስድስት መቶ ዓመት በፊት እንዲኽ የተራቀቁ አባቶች ዛሬ እንዴት ይኼንን እጅ እግሩ የጠፋው ስራ የሚሰራ ትውልድ ተኩ የሚያስብል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በሮቹ ሁለት ተካፋች ሲኾኑ መካከላቸው ላይ የቆመው የማካፈያ ማዕዘን በተለየ ጥበብ ተፈልፍሎ የተቀረጸ ነው፡፡

አባ ዕዝራ ጥበበኛው አባት፡፡ መናኘም የእጅ ባለሙያም፣ መነኮሴን አናጢም፤ በብዙ መከራ ኢየሩሳሌም ደርሶ ከአባ ዩሐንስ ቅስና ተቀብሎ የአቡነ አበከረዙንን ነገር እያሰበ ወደናፈቀችው ሀገሩ ልቡ ላይ ወደሚመላለሱት የከስዋ ማኅበር አባላት ሲል ፈጥኖ መጣ፡፡ ሲደርስ በማኅበረ ከስዋ ታላቅ ደስታ ኾነ፡፡

ቆይቶ የአባ አበከረዙንን ማለፍ ሲያረዱት መሪር ሀዘን ተሰማው፡፡ ቀጣዩ የማኅበረ እስጢፋኖሳውያን መሪ የመኾን ኃላፊነት እርሱ ላይ ወደቀ፡፡ ዝናው በንጉሡ ዘንድ ናኘ፡፡ ዐፄ ናእድ ሰማ፡፡

ከአመታት በፊት የማኅበረ እስጢፋኖሳውያን ስም በቤተመንግሥቱ የተወገዘ እንዳልነበረ ሌላ ንጉሥ ሌላ ዘመን አመጣ፡፡ አባ እዝራ ወደ ዐፄ ናእድ ቤተ መንግሥት ተጠርቶ ሲመጣ መነኮሳቱ የቀደመውን ቁርሾ አልተውትም ነበር፡፡

አሁንም ክርክሩና ሙግቱ ቀጠለ፡፡ እምነት ተፈተነ፣ መንፈሳዊ ፍልስፍና በተጠየቅ ተሞገተ፡፡ በጠቢቡ አባ እዝራ አንድም ከአባቶች ያፈነገጠ አስተምህሮ አልተገኘበትም፡፡
አስቀድሞ የተጣለው ግዝት በጳጳሱ በአባ ይስሐቅ የተፈታ ኾነ፡፡[12] አባ እዝራም ቤተ መንግሥቱን ከአዳዲስ ፈጠራዎች ጋር አስተዋወቀ፡፡ በአህያ የሚሰራው ወፍጮ የዐዌ ናአድን ሹማምንት ሳይቀር አፈዘዘ፡፡ ያን የሰራው ጠቢብ እዚህ ተራሮች ሆድ ውስጥ ይኼንን ድንቅ ቅርስ ትቶልን አልፏል፡፡ አባ ዕዝራ በሀገረ ኤርትራ በቀድሞው ማይዳድ ወረዳ በስሙ ትልቅ ገዳም አለ፡፡ ኤርትራውያን ትልቅ ክብር ከሚሰጡት አባት አንዱም ነው፡፡[13]

ደውል ተደወለ፡፡ ደብረ ገሪዛንን እልልታ አናወጸው፡፡ ዝማሬው ሽቅብ ወደ አለሁበት የወንዶች ገዳም ወጣ፡፡ ካህናት በዝማሬ እያሸበሸቡ ቀደሙ፡፡ ብዙ ሰዎች ጥላ ዘርግተው በአረድፍ ቆሙ፡፡ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቆብ አድርገው ተመሳሳይ ስካርብ ወገባቸው ላይ እንደ ዝናር የታጠቁት አባት ባንዲራ የተጠመጠመባት የብረት መቋሚያቸውን ተመርኩዘው የያዙትን ጡሩምባ ወደ አፋቸው ከተቱት

...ጡ....ጡ.....ጡ.....ጡ

ቀድማ ሥዕለ ማርያም በአንድ ዲያቆን ተይዛ፣ በዲያቆናቱ ግራና ቀኝ ጥላ ተዘርግቶላት ከቤተ መቅደሱ ወጣች፡፡ እልልታው አስተጋብቷል፡፡

12 ደቂቀ እስጢፋኖስ፡፡ በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፡፡ ገጽ 297

13 መርቆሪዎስ አረጋ ታሪክህን ዕወቅ፡፡ ገጽ 123

ለዓመታት የጥይት ድምጽ ያስተጋባባቸው ተራሮች በዝማሬ ተንቀጠቀጡ:: ያ ድምጽ የጥቂቶች አይመስልም ነበር:: ያ እልልታ እነኛን ረዣዥም ተራሮች ሰንጥቆ የመጣ ድካም ያጎሳቆለው ህዝብ እንደበት ያወጣው አይመስልም ነበር::

ከዛሬ አምስት መቶ አመት በፊት ጀምሮ ማኅበረ እስጢፋኖስ በሚል የሚጠሩት አባቶች ሁሉ ይኽቺን ቀን ደብረ ገሪዛን ጉንዳ ጉንዶ ማርያም ይሰበሰባሉ::

የደቂቀ እስጢፋኖሳውያን ዋነኛ ክስ ለማርያም አይሰግዱም የሚለው ነው:: ይኼንን አባ እስጢፋኖስ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ፊት ቀርቦ ተጠይቆበታል:: አባ አበከረዙን ተፈትኖበታል:: ከብዙ ጊዜ በኋላ እንኳን አባ ዕዝራ የወደደው ዐፄ ናኦድ ዘንድ ሲቀርብ አስተምህሮቱን ለመመርመር ከቀረበው ጥያቄ አንዱ ነበር::

አሁን ያለኹበት ስፍራ ያኔ መከራው ሲበዛ፤ ያኔ የማኅበረ እስጢፋኖስ አባቶች ሲሰደዱ፤ ያኔ ግርፋት፣ ስደትና ሞት ሲበዛ፤ አባ እስጢፋኖስ በስደት ላይ ሳለ:: ከደቀመዛሙሩ ከገብረክርስቶስ ጋር በተከዜ ወንዝ ዳርቻ ሳሉ እንዲኽ አለ፤ "የእግዚአብሔርን በረከትና ሕይወት ካሁን እስከ ዘላለም እንድታገኙባት እግዚአብሔርን ስለሠራው ሁሉ ለመባረክ በሁሉም ነገር እንደዚህ ጸንታችሁ በደብረ ገረዜን ኑሩ" አላቸው:: በዚህ ስፍራ ነኝ::[14] ደብረ ገሪዛንን አቡነ ይስሐቅ መሰረቷት፣ አባ እስጢፋኖስ ባረከት፣ አባ ዕዝራ ተጠበበባት ይላሉ::

14 ደቂቀ እስጢፋኖስ:: በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ:: ገጽ 75

ጽንሐ የያዙ ካህናት ወጡ:: ሁሉም በሰልፍ ነው:: ከዚያ በግዙፍ ጥላ የተከለለች ታቦት ወጣች:: ብዙ ቦታ ያየሁትን ዓይነት ታቦት አልነበረም:: ምናልባት ካህናት ወደ ቅዳሴ ሲገቡ ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ይዘውት ከሚጓዙት የስጋ ወደሙ ማስቀመጫ ጋር የሚመሳሰል ሳይኾን አይቀርም:: ይኸንን ለማሰብ እልልታውና ዝማሬው ፋታ አይሰጥም::

አንድ የበቁ ባህታዊ መነኩሴ ኮከብ የሌለባት አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ይዘው ከመቅደሱ ወጡ:: ባንዲራ ተይዞላቸዋል::
ኮከብ ያላቸው የፌዴራል ባንዲራዎች አንድ ሁለት በሰው ተይዘው አይቻለሁ:: የትግራይ ክልል ባንዲራም እንዲሁ፤ ሁለቱም ግን ጥላ አልተዘረጋላቸውም:: የያዟቸውም ሰዎች ጋቢ የለበሱ ምዕመናን ናቸው:: በባህታዊው የተያዘችው ባንዲራ ሰልፍን መምራት ጀመረች::

የኢሮብ ባህል እንዲህ ነው:: እስራኤላውያን በታቦቱ ፊት እንደሚያደርጉት የተለየ ሥርዓት አየሁ:: ኢሮቦች በባህላዊ እንቅስቃሴያቸው መንፈሳዊ ምስጋናቸውን ቀጠሉ:: ካህናቱ በሽብሸባ እየዘመሩ ነው:: በውስቴታ ታቦት በውስቴታ እያሉ ይጓዛሉ:: ደውሉ እየተደወለ ነው:: ቀኑን አድምቆ ያበስራል::

ህዝቡ ወደሚገኝበት የታችኛው አውደ ምህረት ስንቀርብ ይጠብቁን የነበሩት ሴቶች በግንባራቸው መሬት ተደፍተው በእልልታቸው አደመቁት:: ንግሡ በኢሮብ ባህላዊ ዜማና ጭፈራ ታጀበ:: አባቶች በታቦት ፊት ምስጋናና ሰላምታ የማቅረብ ባህላዊ ሥርዓት አከናወኑ::

ይኸ ሁሉ እዚህ ከየቦታው በመጣው ሰው የደመቀ ንግሥ አይመስልም፡፡ ሕዝቡ እጅግ ብዙ ነበር፡፡ የገጠሩ የኢሮብ ቀበሌ ዛሬ ብቻውን እንደዋለ ገባኝ፡፡ "ጊዜ እረፍቷ ለማርያም" የሚለው ዜማ ዳር እስከ ዳር አስተጋባ፡፡ ተራሮች በአመት አንድ ጊዜ እንዲህ ያለ የምስጋና ዜማ ያደምጣሉ፡፡

ኢሮብ ሰው መኾን እንደሚበልጥ አየሁ፡፡ ወንድሞቻቸውን ብለው የመጡ ሙስሊሞች ጉንዳ ጉንዶ ስትነግስ አብረው ይውላሉ፡፡ ፈቅ ብለው ደስታ የሚጋሩ አብሮ የመኖር ሸማ ደራቢዎችን አየሁ፡፡ ከረገረጋማቹ ተራሮች ወዲህ ይኸ ሁሌም የሚታይ እውነት ነው፡፡

ረዥም ሰዓት አልቆየም፤ ስብከት ተሰበከ፣ ቡራኬ ተሰጠ፡፡ ኢሮቦች ለጉንዳ ጉንዶ ማርያም ያሉትን ሰጡ፡፡ እንደ አመጣጡ ሥርዓቱ በተመሳሳይ ኹኔታ ወደ መቅደሱ ጉዞ ተደረገ፡፡ ሴቶች እስከሚችሉበት ተከተሉ፤ ከዚያ ደግሞ በድምጻቸውና እና በእልልታ አብረው ወጡ፡፡ ወደ ላይ ወንዶች ብቻ ወደሚገቡበት የገዳሙ ክፍል፡፡

የንግሡ በዓል እንዳለቀ ብዙው ሰው ጉንዳ ጉንዱን ለቆ ሄደ:: እኛ ብቻ ቀረን:: የሚቀመስ ፍለጋ ወደ ኢሮቦቹ መንደር ወጥተን ነበር:: ጥህሎና ሽጋ የሆነ ጠላ አገኘን:: እርጎም ነበር፤ ከዚያ መልስ ብዙው ሰው ባልቀረበትና ትናንት ጥቅጥቅ ብሎ በነበረው ሜዳ ላይ አረፍ ለማለት ተሰብስበናል::

"አባ መጥተዋል" አለ አስተባባሪያችን ዮናስ፤ ለቃለ መጠይቅ የገዳሙን አባት ቀጥረናቸው ነበር:: ተነሳንና ከጀርባችን ወደአለችው ታችኛዋ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ገባን::
ከመቀመጫቸው ተነሱ:: ቀጭን ናቸው:: ብርቱ ገዳማዊ እንደኾኑ ያስታውቃሉ:: ማኅበረ እስጢፋኖሳውያን አካላዊ ብቃታቸውን አድንቄአለሁ:: እነኚህን ተራሮች እየሰነጠቁ ማለፉ ንቁም ብቁም ያደርጋል::
ሰላምታ አቀረብን::
በአጻፋው መስቀላቸውን አሳለሙን:: ግንኙነታችን የአባትና የልጅ እንዲኾን ፈልገዋል:: ሊያቀርቡን የሞከሩበት መንገድ የምንፈልገውን ለመጠየቅ ነጻነት ሰጠን:: ድካሙ እንዳደቀቀን አውቀዋል:: ሰውነታችን ያሳብቃል:: የመጣነውን መንገድ ስለመመለስ ማሰብ ስለጀመርን እንደ ሌባ ዓይናችን ዙሪያውን ይንቀዠቀዣል:: ቀልባችን አላረፈም::
"መንገዱ ከበዳችሁ?" ሳቅ አሉ:: መልሱን አውቀውታል::
"እንዲኽ ያለ ፈተና ገጥሞኝ አያውቅም" አልኳቸው::
የስፍራው ሁኔታ ገርሞኛል:: ቅዱሳኑ ከሰዋን ፍለጋ ምን እዚህ እንዳመጣቸው አልገባኝም:: የቀደመ ታሪክ ይኖር ይኾን ብዬም ራሴን እጠይቃለሁ:: ከደናከል አፋፍ፤ ተራሮች ስር በተሸሸገ ምድር ገዳም መትከልን አስበ ወዲኽ መምጣት ከምን መጣ?

"በፊት ይኼ ቦታ ምን ነበር?" ያብሰለሰለኝን አነሳሁት፡፡
"ምንም፤ ቀድሞ ቅዱሳን እዚህ ሳይመጡ እኮ ከሰዋ ነው፡፡ ከሰዋ ነበር የሚባለው፡፡ ምንም ያልነበረበት"
"ከሰዋ ማለት?" አልኳቸው መልሼ፤
"አዎ፤ ከሰዋ ማለት ምን መሰለህ? ሰው የሌለበት በርሃ ማለት ነው፡፡"
"ደብረ ገሪዛንስ?" ጥያቄን አስከተልኩ፤
"እሱማ ደብረ በረከት ማለት ነው፡፡" አሉኝ፡፡

በረከትን ፍለጋ እዚህ ምድር ስለመጡ ቀደምት አባቶች አሰብሁ፡፡ አባ ለምለም ወልደሥላሴ ያደጉትም የተማሩትም እዚህ ነው፡፡ የደብረ ገሪዛን ምክትል አስተዳዳሪ ናቸው፡፡ በድፍን ኢሮብ ወረዳ ደግሞ ሊቀ ካህንና የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ኾነው ያገለግላሉ፡፡

"ቅርሱም ሕንፃውም እንደነበር ነው?" አባ ለምለም ራሳቸውን ነቅንቀው አረጋገጡልኝ፡፡ ቀጠሉናም፡፡
"አዎ፤ ብዙ ጦርነት ሲደረግ አንዱም አልደረሰበትም፡፡ በግራኝ አህመድ ጦርነት አልተነካም፡፡ በከፋው በዐፄ ሱሲንዮስ ችግርም ጊዜ ሃይማኖታችንን አንቀይርም ብለው እንቢኝ ያሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን የስደት ኑሮ የኖሩበት ነው፡፡ ጉንዳ ጉንዲም ያሉት እነሱ ናቸው፡፡ በኢጣሊያም እንዲሁ አልተነካም፡፡"

ስፍራው ከዓለም ለመገለል ምቹ ነው፡፡ ዓለም ውስጥ ኾኖ ዓለምን ተደብቋል፡፡ የጠላትን ዓይኖች የሚከልሉት ተራሮቹ ብቻ አልመሰሉኝም፡፡ የሆነ መንፈሳዊ ምትሃት አለው፡፡

የቆሙበት ኾነው ጀርባው የማይታይ እዚህም እዚያም ረዣዥም ተራሮች ጭምር ከዓይን የተሸሸጉበት አካባቢ ነው። አባ የገዳሙ ሁኔታ በአንድ በኩል አሳስቧቸዋል። የሀገር ሀብት ቢኾንም መንግሥት ከሃይማኖት ተለያይቷል በሚለው መርህ ቅርሱ ብቻ ሳይኾን ወደ ቅርሱ የሚወስደው መንገድም ምቹ እንዳይኾን እንቅፋት ፈጥሯል።

"እዚህ ቦታ ያሉት መፃሕፍት በሌላ ቦታ የሉም። ብርቅና ድንቅ ናቸው። ይኼ ገዳም የኢትዮጵያ ታሪክ ጠባቂ ነው። ልማት እናለማለን፤ ከአትክልት ነው የምንጠቀመው። አሁን አትክልቱን ለገበያ ለማውጣት ሰው ማግኘት ከባድ ኾኗል። ስፍራው ለከብት አይኾንም። ለማርባት ምን ይበላል? ግጦሽ የለውም። መንገዱን አይታችሁታል እንዴት ከባድ እንደኾነ?"

መንገዱ ከባድ ነው። ከማየትም ያለፈ ትርጉም ሰጥቶናል። ገዳሙ ያረፈበት አካባቢ ብዙም ሰው ያለበት አይደለም። መነኮሳቱ በማይመች ሁኔታ የሀገር ታሪክ አቅፈው ኖረዋል። ደብረ ገሪዛን የሚደምቀው በአመት አምስት ጊዜ ነው። የጥር ማርያም የበለጠ ይደምቃል። ነሐሴና ታህሳስ ሃያ አራት የተክለሃይማኖት ንግሥ ነው። የካቲት እና ነሐሴ ኪዳነ ምህረትም እንዲሁ።

ዛሬም ድረስ የሚነገሩ የማኅበረ እስጢፋኖሳውያን አስተምህሮት ጉዳይ ደብረ ገሪዛን ሲደርሱ መልስ ያገኛል። የአባን ምላሽ ለመስማት ስለፈለግሁ የሚባለውን አልኳቸው።

"የአባ እስጢፋኖስ ትምህርት ተቀባይነት ሲያገኝ ጥቅማችን ተነካ የሚሉ መነኮሳት የዘሩት ነው:: ማርያምን የሚጠላ የማርያምን ቤተ ክርስቲያን አይሰራም:: እውነቱ ከጥንትም ዛሬ እንዳያችሁት ነው::"

በአማን ነጸረ በመፍቅሬ ዘርዓ ያዕቆብና በመፍቅሬ እስጢፋኖሳውያን የሚነሱ ጫፍና ጫፍ የቆሙ ሀሳቦችን ከእውነታው አንጻር ቃኝቷቸዋል::

ምሳ ለመጋበዝ ወደ ገዳሙ ተግባር ቤት ተያይዘን ወጣን::

ደቂቀ እስጢፋኖሳውያን በምንም ልኬት የሉተራውያን አብዮት ጀማሪዎች ሊባሉ አይችሉም:: አንዳንዶች አባ እስጢፋኖስና ማኅበረ እስጢፋኖሳውያኑን ከኦርቶዶክሳዊ ይልቅ ፕሮቴስታንታዊ ዕይታዎች ያሉት እንደኾነ ለማስረዳት ይሞክራሉ::[15]

የማኅበረ እስጢፋኖሳውያን ተግባር ግን ሌላ ነው:: አስቀድሞ ወደ ኢየሩሳሌም የመሄድና የጌታን መቃብር የመሳለም ትውፊት ተከታዮች መኾናቸው ታይቷል:: ከህነትን ፍለጋ በርሃ አቋርጠው ጳጳስ ዘንድ ሄደዋል:: በጣም የደከሙ በጸሎት የበረቱ ነበሩ:: የቀደሙትን አባቶች ገድልና ቱሩፋት ጽፈው አኑረዋል::[16]
ምሳው ቀረበ:: ሽሮ ወጥ ነው:: ስጋ አልፎ አልፎ አለው:: ምናልባት ለአስተርዮ ያልኾነ ብለው ይኾናል::

15. ወንድዬ ዓሊ:: በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን:: ገጽ 23
16. በአማን ነጸረ:: ወሊታ ጽድቅ:: ገጽ 97

በትሪ ቀረበልን፡፡ አባ ለምለም ጸሎት አድርገው ባረኩት፤ ሰብሰብ ብለን ወደ ማዕዱ ተጠጋን፡፡ ቀመስነው፡፡ ምንም ምንም አይልም፡፡ ጨው የለውም፤ ማኅበረ መነኮሳቱ ውሃ በሌለበት ምድር እንዳሻቸው ለመኖር ጨው የሌለው ውሃ ውሃ የሚል እህል ይቀምሳሉ፡፡ ሲያውም በታላቁ የንግሥ በዓል ዕለት፡፡

ከምሳ በኋላ የምነና ስሜት ተሰምቶኛል፡፡ ትንሽ አርፈን ዕቃ ቤቱን እንድንጎበኝ ተፈቀደልን፡፡ ጉንዳ ጉንዶ የቅርስ ሙዚየም ነው፡፡ ገና ሲከፈት ሙሉ ግድግዳው የመጽሐፍት መደርደሪያ የቀደሙ ቅርሶች ማኖሪያ መኾኑን አየሁ፡፡ በየዘመናቱ በስደት የመጡ ጥንታዊ የጽሑፍ ቅርሶች አድራሻቸው እዚህ ነው፡፡ ማኅበረ እስጢፋኖሳውያን ንባብ የሚወዱ መኾናቸውን ያሳዩባቸው ከየገዳማቱ የተገለበጡ ጥንታዊ ብራናዎችም አሉ፡፡ ዓለም ጉንዳ ጉንዶ ስለሚባለው ስፍራ የሚያውቀው የጽሑፍ ቅርሶች ማዕከል ስለመኾኑ ነው፡፡

አንቶኒዮ ሞርዲኒ የተባለ ጣሊያናዊ እንደ እኔ ጉንዳ ጉንዶ በመጣ ጊዜ የተመለከታቸውን መጻሕፍት ዝርዝር ጽፎ ነበር፡፡ ዛሬ ማየት እንጂ ማገላበጥ አይቻልም፡፡ የአባ ዕዝራ እጅ ያበጃቸውን ድንቅ መስቀሎች አየኋቸው፡፡ የእቃ ቤት ቆይታዬ ረዥም አልነበረም፤ በዚያ ላይ የንቁ መነኮሳት የጥንቃቄ ፍጥነት ሰዓቱ አሳጠረብኝ፡፡
ወደ ማረፊያችን ስፍራ ሄድሁ፡፡ የመልስ ጉዞውን የሚያስቡ ጓዶቼ እዝን እንደተቀመጠ ሰው ተኮራርፈው ምንጣፉ ላይ ተኝተዋል፡፡ ገና ከመቀላቀሌ አንድ ሰው በእኛ ትይዩ እንደእኛ መሬት አንጥፎ ያረፈ በምልክት ጠራኝ፡፡ ተነስቼ ሄድኩ፡፡

ስሙን በመንገር ነበር ትውውቃችንን የጀመረው:: ስሜን ነገርኩት::

"ልጆች ነግረውኝ ነው:: አልፎ አልፎ የምትጽፋቸውን አነባለሁ፤" አለኝ:: አመሰገንሁ:: ጉልበት ለመሰብሰብ በሚመስል መልኩ ሰው ሁሉ በየቦታው ምንጣፉ ላይ ተጋድሟል:: በከርኔ ደገፍ አልኩ::

"ከአሜሪካ ነው የመጣሁት:: አባ ዘወንጌል የሚባሉ አባት አሉ:: የበቁ አባት እዚህ በርሃ ውስጥ ናቸው::" ፊቱን ከገዳሙ በላይ ወደአለው አድማስ አድርጎ በአገጩ ሽቅብ አሳየኝ::

"እሳቸውን ፍለጋ ነው የመጣሁት፤ እዚህ አገኛቸዋለሁ ብዬ አስቤ ነበር:: በዚህ በበርሃው ያለ አንድ ስፍራ ናቸው አሉኝ፤ የሚወስደን ሰው አለ:: አሲምባ ላይ ነው ያሉት ብሏል:: አብረኸን ትሄዳለህ?"

አሲምባ ከጀርባችን ከነአድማሱ የተሸከምነው ተራራ ነው:: ግዙፉ የኢሮብ ተራራ:: 3248 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ ለሚረዝመው ተራራ ጉዞ ታጨሁ:: እንደ ወዳጅም እንደ ጠላትም አየሁት:: አቅሜን አውቀዋለሁ:: ከባዱ ጎዳና ነው:: ኢህአፓዎች የደም ላብ ያወጡበት:: እንደ ተረከ ስሰማው በአደግሁት ተራራ ላይ ለበረከት እንድወጣ ታጨሁ::

አባ ዘ ወንጌል መልካም ስም ያላቸው አባት ናቸው:: አድሜአቸው ብዙ ስለመኾኑ ሰምቻለሁ:: የበቁትን አባት ለማግኘት በርሃውን የሚንከራተቱ ብዙ ናቸው:: ከታላላቆቹ ገዳማት የበቁት አባቶች ጋ በመንፈስ ወይም በአካል የሚተዋወቁ ታላቅ አባት ናቸው::

አመነታሁ፤ ግን ደግሞ አቅሜ አይፈቅድም:: ተወስውሻለሁ፤ የማላገኘው እድል እንደኾነ ተነግሮኛል:: ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን በርሃ ላይ የቆሙ ተራሮችን ሰንጥቆ ለማለፍ የሚበቃ ጉልበት የለኝም::

ሌላ ግዜ ብዬ ስልክ ተለዋወጥን:: የማልረሳውን ሀሳብ ስላሸከመኝ ወደ ወንዙ ወረድሁ:: እግር ለማፍታት ብዬ ነበር የተንቀሳቀስሁት:: ራቅሁ:: ወደ ግዙፍ ዐለቱ ስር፤ ዘንዶ አለ ብለው ሲያደምጡ የነበረበት ስር ቆሜ ለማድመጥ ጆሮዬን ቀሰርሁ::

ታሪኩ እንዲህ ነው:: አባ ዕዝራ ወደ ገዳሙ ሲመጡ አንድ ዘንዶ በስፍራው ነግሦ ነበር፤ ያገኘውን ሲበላ የተቸገረው የሀገሩ ሰው ዘንዶው ራሱ ከሚበላ ሰው ፈቅዶ እንዲገብር ተስማሙ:: ልትገበር የተሰጠች ወጣት ሴት ዛፍ ላይ ኾና ስታለቅስ በስር ያልፉ የነበሩት አባት ላይ እንባዋ ጠብ አለ:: ቀና ሲሉ ሰው አለ:: ምክንያቱ ቢጠይቁ እንዲኽ ስለኾነ ብላ መለሰችላቸውና መምጫው ስለደረሰ እሳቸውን እንዳያጠቃ ይሂዱ ፍጠኑ ስትል ተማጸነች:: ቆመው ጠበቁት:: ሲመጡ ገዙቱት፤ በግዙፍ ዐለቶች መሀል ተሰንቅሮ የቀረው በዚህ ግዝት ነው:: እስከ ምጽአት እንዲህ እንዲኖር ተፈርዶበታል:: ለዚህ ሳይኾን አይቀርም ጉንዳ ጉንዶ በዘንዶ የሚጠበቀው ገዳም የሚባለው::[17]

በለሊት እንደምንነሳ ሳሰብ ፍርሐት ያዘኝ፤ ተራራውን ፈራሁት:: አልመንን ነገር ኾኖ እንጂ ከዚህ መንገድ ደብረ ገሪዛን ምን ያለች ገነት ናት::

17. መርቆሪዎስ አረጋ:: ገጽ

ጸሐይ ምስራቃዊውን የትግራይ ክፍል አናት መልቀቅ ጀምራለች:: እቃዎቻችንን የሚጭኑት አህዮች ራቅ ብለው ታስረዋል:: ለሊቱ ሲጋመስ መንገድ ለመጀመር ቀጠሮ ይዘናል:: ጋደም አልኩ:: ሰብሰብ ብለው በማኅበር ከመቐለ የመጡ ወጣቶች ከመተኛታቸው በፊት የህብረት ጸሎት ይዘዋል::

"ያድህነነ ከመዓቱ ይሰውረነ በምህረቱ በእንተ ማርያም ወላዲቱ"...የህብረት ድምጻቸው አስተጋባ፤ በተኛሁበት አሜን አልሁ:: አሜን!!

# ነገረ አንበሳ

"አንበሳ አገድላለሁ የሚለው ባልሽ
ቅጠል ሲንኮሻኮሽ ገደል ገባልሽ"
የሀገሬ ህዝብ

የረግረጉ ሽታ ይሰነፍጋል:: ከግራ ጨፌ ከቀኝ ኮረብታ መካከል ላይ እኔ አለሁ:: አብሮኝ የነበረው ከአዋሽ ሰባት እስከ ገዋኔ የጫነኝ የከባድ መኪና ሹፌር ነው:: ሳንደርስ ቆመናል:: ያስቆመን ደግሞ ግዙፍ የአፍሪቃ አንበሳ:: እንዲህ አንበሳን ማየት አጋጣሚ ብቻ አይደለም፤ የህይወት ዘመን ከስተትም ኾኖ ይቀራል:: ሰውነቱ ጎዳናውን አጥቦታል:: ሞገሱ አፍዝዞናል:: አንበሳ ምን ማለት እንደኾነ እንዲህ ያለው ስፍራ መገናኘት ያስፈልጋል:: ከዱር ንጉሥ ጋር ተፋጥጫለሁ:: በስፖኪዮው ስንመለከት ከኋላ መኪና ተደርድሯል:: ከፊት የቆሙትም እንዲሁ መብራታቸውን አጥፍተዋል:: በጨለማው የነጩ ቦቲ አካል ይታያል:: ጨረቃዋ ለአንበሳው የወጣች መሰለኝ:: መንገዱን እስኪለቅና እስክንንቀሳቀስ ወራት ያለፉ መሰለኝ:: ተንጎማሎ ወደ ፍል ውሃው ገባ:: መትካ፤ አፋር፤ ገዋኔ::

ከዚያ አጋጣሚ መልስ የኔ ዓይነት ገጠመኝ ስለነበራቸው ሰዎች ሰማሁ፡፡ ከጅቡቲ የሚመጡ ሹፌርና ረዳት አስፋልት ዘግቶ የተኛ አንበሳ ገዋኔ አዘሎ ስር አቆማቸው፡፡ በቆሙበት ወደ ፍሬንና ፍሪሲዮኑ ጉያ ውሽቅ አሉ፡፡ መሄድ አለመሄዱን ለማየት ሹፌሩ ረዳቱን ብቅ ብሎ እንዲመለከት አዘዘው፤ ረዳቱን ትዕዛዙን አልተቀበልም፡፡ ሹፌሩ ራሱ ጭንቅላቱን ብቅ አድርጎ በፊት ለመስታወት ለማየት ብቅ አለ፡፡ መሬት የቆመው አንበሳ መዳፉን መስታወቱ ላይ ድፍን ሲያደርግ እኩል ሆነ፡፡ ሹፌሩ ራሱን ሳተ፡፡ ረዳቱ የተሸሸገበት ሆኖ ስሙን ሲጠራው አልሰማውም፡፡

ከቆይታ በኋላ የመኪና ጥሩንባ ስፍራውን አተራመሰው፤ ረዳት ቀና ብሎ ሲመለከት አንበሳው የለም፤ ጎዳናውን ግን መኪና ተደርድሮበታል፡፡ ራሱን የሳተውን ሹፌር ወደ ረዳቱ ቦታ አስቀምጦ የሹፌሩን ቦታ በመያዝ መኪናውን እየነዳ ቀጣይዋ ከተማ ድረስ ተጓዘ፡፡

ከዚያ በኋላ የሹፌሩ ዕጣ ፈንታ ሲነቃ ማበድ ሆነ፡፡ ቤተሰቡን በትኖ የጫት ገረባ ጉያው ሰበሰበ፡፡ ሰው ባለበት ቦታ ሄዶ "እጁን አይተህዋል? እጁን...." እያለ መኖር ጀመረ፡፡
ስለ ኢትዮጵያ አንበሶች ብዙ ሰምቻለሁ፡፡ ብዙዎቹን እዚያው ዱር ለማየት ችያለሁ፡፡ አንበሳ የተረከ ቅራኔ መሆኑ የሚገርመኝ ሰው ነኝ፡፡ አንበሳን ማተም ያሰረ ክርስቲያን አድርገው የሚቆጥሩ ልሂቃን ገጥመውኛል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ታልሙድ አንባቢ ይሁዲ ያደርጉታል፡፡ እሱ ግን የዱር ፍጥረት ንጉሥ ነው፡፡ ከዚያ ያለፈ የሰው ልጅ የምኘ ሀሳብ ሀሳቡ አይደለም፡፡

አንበሳ በሰው ልጅ ባህል ውስጥ ብዙ ዘመን የኖረ ቤተሰባዊ አውሬ ነው:: በሥዕል፣ በቅርጽ፣ በተረት፣ በዜማ ሲገለጽ ኖሯል:: የባንዲራ ዓርማ የማሸነፍ ምልክት ተደርጎ ከፍ ካለ ስፍራ ተሰቅሏል:: በእኛ ሀገር ደግሞ የዱር ብቻ ሳይኾን የምልክትነትም ንጉሥ ነው:: አንበሳ ቤተ መንግሥትና ዘውድ ኾኖም በልዩነት በተከታታይ ትውልድ ተቀርጾአል::

ላዮን የሚለውን ስም የተጠቀመው ካርል ሊናኔስ የተባለው የሳይንስ ሊቅ ሲሆን ዘመኑም እ.ኤ.አ 1758 ነው:: ሊቃውንቱ የአንበሳን ዝርያ የ"ሰሜን አንበሳ" እና የ"ሰሜን ንዑስ" በሚለው ይከፍሉታል:: ኢትዮጵያ ሁለቱን የምታገናኝ የአንበሳ ሥነ-ተፈጥሮ ምስጢር ናት የሚሏትም ከእነዚህ ሁለት ዝርያዎች ዝምድና ያላቸው አናብስት መኖሪያ በመሆኗ ነው::

በኢትዮጵያ አንበሳ የረዥም ዘመን ታሪክ ያለው ከኢትዮጵያውያን ተረክ ጋር የተቆራኘ አውሬ ነው:: ውክልናው ያይላል:: የጦር አውድ ጀግኖች በስሙ ይጠራሉ:: የቀደምት ጋሞ አባቶች ታሪክ አንበሳን ከማንነታቸው ያቆራኘ ነው::
አንበሳ ለጋሞ በጥረት ድል የማድረግ ምሳሌ ነው:: ችግር ተቋቁሞ የመኖር ማሳያም ተደርጎ ይቆጠራል:: ለዚህ ነው ጋሞ "ቱማ ኑ ጋሞ ዶኮኒ" ያለው:: ትርጉሙ፤ እውነትም እኛ ጋሞ ነን ማለት ሲሆን:: ጋሞ ማለት አንበሳ ማለት ነው:: በጥረት ለድል የበቁ አባቶች በመጨረሻ እውነትም እኛ አንበሳ ነን አሉ::[1]

1. የደቡቧ ኮከብ ጥንታዊት ጽዮን ሰማያዊት ብርብር ማርያም ገዳም:: ገጽ 11

ጋሞዎች ለአንበሳ የሚሰጡትን ቦታ ከስማቸው መለስ በየተረቶቻቸው በክብር አስቀምጠውት ይኖራሉ፡፡ ከጋሞ ተረቶች የሚገዝፈው አንበሳን ከመብረቅ ጋር በማጋባት አንድ ጎጆ ያስወጡበት ይመስለኛል፡፡ መብረቅን የሚያኽል የሰማይ ነጎድጓድ ለአንበሳ መዳር አንበሳ በጋሞ ዘንድ ያለውን ስፍራ ይነግረናል፡፡[2]

በኢትዮጵያ የአንበሳ ክብርና ነገር ስፍራ የሚወስነው ዓይደለም፡፡ ደጋግሞ እንደሚባለው አንበሳውን ስሜናዊ የማድረጉና ይሁዲነትን የማጎናጸፉ መንፈስ ከአባቶቻችን የተቀዳ ሳይኾን የበታችነት ከተሰማው ተማርኩ ባይ የተፈበረከ ነው፡፡

ከጥንት በነበረ ልማድ አንበሳ እንደ ስፍራው የራሱ ነገር ያለው ልዩ ክብር የሚቸረው እንስሳ ነው፡፡ አንበሳ የጀግንነት መገለጫ ብቻ ሳይኾን ከፍ የማለትም ምልከት ነው፡፡ አንበሳነት ሁሉን ድል የማድረግ ወካይ ነው፡፡ "አንበሳ ሰነፍ ነው" የሚል ሰው ስሰማ አንበሳን አርሶ ይበላ ዘንድ የሚጠብቅ የዋህ ይመስለኛል፡፡ ዱር የሚኖር ኃያል አውሬ አድኖ መብላቱ ካስኮነነው የነገረ ፍጥረት እውቀት አፈር በልቷል ማለት ነው፡፡
አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አንበሳን በቁሙ ግርማ ያለው አውሬ ይሉታል፡፡ ኃይለኛና ተፈሪ መኾኑን አስቀምጠዋል፡፡ በኪዳነ ወልድ ክፍሌ ትርጉም ታላቁ መዝገበ ቃላታችን እንኳን አንበሳን ከነገረ ተፈጥሮው ያፈነገጠ ትርጉም አይሰጠውም፡፡

2. ጋሞኛ ተረቶች፡፡ ጸሐይ አሳታሚ፡፡ ገጽ 91

አንበሳ አድኖ መብላቱን ከነገረ ተፈጥሮው ነጥሎ ለሚኮንኑት "ወትሮስ ሽምቶ ሊበላ ኖሯል?" የምትለው ስላቅ ሸጋ መልስ ትመስለኛለች፡፡ በአንበሳ የተሳከረ መረዳት አውሬው ፍጡር "እርሶ ካልበላ" ዓይነት ውጣ ውረድ ከፍተቱ ወየት ጋር ነው ቢያስብልም፡፡ መነሻውን ለማግኘት መሞከር ግን ሞኝነት አይደለም፡፡

የአንበሳ አድኖ መብላት የአህያ ሰርታ የምትበላውን ያኽል ልክ የሆነ ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ መጀመሪያውኑስ ቢኾን ጥሮ ግሮ መብላት የሐጢአት እንጂ የጽድቅ ውጤት እኮ አይደለም፡፡ የተረገመው ሰው እጸ በለስ በመብላቱ ምክንያት ምድር አሜኬላ ታበቅል ዘንድ ምክንያት ሲሆን አብሮ የተረገመው እርግማን ጥሮ ግሮ በወዙ እንዲበላ ነበር፡፡ "እኔ በወዜ በልቼ አንበሳ እንዲሁ ጠገበ" የሚል መንጬርጬር ከሆነ አድኖ ከመብላት በላይ ከባድ ስራ አለመኖሩን ለመረዳት አዳኝ መኾንን አይሻም፡፡ ያም ኾኖ ደግሞ ይበልጥ ህይወቱ የተመሰረተው ጥንብ በመብላት ላይ መኾኑን የሚያምነውን ሳይንሳዊ እውቀት ደግሞ ፈጽሞ ተዘንግቷል፡፡
አንበሳ በጋራ መረዳዳትና መተጋገዝ የሚታወቅ እንስሳ ነው፡፡ አንበሳ ጡቷን እንኳን ለልጇ ብቻ የማትል ፍጡር ናት፡፡ ብዙ ደቦል በእከስቱ ጡት የሚያድግ መኾኑማን አይነገርም፡፡ የአንበሳ ማህበራዊ ሕይወት ጸሐፊ Schaller,Leyhausenን ጠቅሶ ባሰፈረው ጽሑፍ ከድመት ቤተሰቦች እንደ አንበሳ በከፍተኛ ደረጃ ለማኅበራዊ ሕይወት ጥገኛ የሆነ የለም ይላል፡፡[3]

3. *Judith A. Rudanai, Social Life of The Lion,Page 45*

ቀደምትና ነባር የኢትዮጵያ እውቀት፣ እምነትና ፍልስፍናዎች ከአንበሳ ማኅበራዊነት ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ የአባ ሳሙኤል ገድል ታላቁ ጻድቅ አንበሳን እንደ በቅሎ ገልበው ያሻቸው ጋር የሚሄዱ እንደነበሩ ይነግረናል፡፡ አንበሳና አባ ሳሙኤል ዘ ዋልድባ የጠበቀ መስተጋብር ነበራቸው፡፡ አንበሶቹ ለጻድቁ ይታዘዛሉ፡፡ እቃ ይጭናሉ፡፡

አባ ሳሙኤል ዘ ዋልድባ ሰባቱ ከዋክብት ከሚባሉት አንጋፋ የቤተክርስቲያን አባቶች አንዱና በ14ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ የዋልድባ ገዳም ዳግም ሲቀና የመሰረቱ አባት ናቸው፡፡[4] አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ በርካታ አንበሶች እንደሚከተሏቸውና መጻሕፍቶቻቸውን ሳይቀር በአንበሳ ላይ እንደሚጭኑ ገድላቸው ሲነግረን ቀደምቱ መንፈሳዊ የኢትዮጵያ እሳቤ ምን ያህል ለዱር ህይወት ያለውን የጥበቃ ፍልስፍና መራቀቅ የሚናገርና በሰውና በአንበሳ መካከል የነበረውን የአዳኝ ታዳኝ አጥፊና ጠፊነት የሚያስታርቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡[5]

እርግጥ አባ ሳሙኤል እንደ አንበሳ ሁሉ ከበርካታ ዱር እንስሳት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ታሪካቸው ይናገራል፡፡ ለምሳሌ ዘንዶ፣ ነብር፣ ጅብና ዝኆንን የመሳሰሉ እንስሳት ለጻድቁ ይታዘዛሉ፡፡ ከጻዲቁም ይቀራረባሉ፡፡ ማርኮ ፖሎ በጉዞ ሪፖርቱ የአደን ስፖርት ያደረሰው ጥፋት በገለጸበት ዘመን እኔ ሀገር ግን እንዲህ ያለ የሰውና የአንበሳ ዝምድና ነበር፡፡[6]

4. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፡፡ አራቱ ኃያላን፡፡ ገጽ 20

5. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፡፡ የቤተክርስቲያን መረጃዎች፡፡ ገጽ 486

6. wildlife-habitat Relationship,Page 6

ከአንበሳ ጋር ያላቸው ወዳጅነት ግን ልዩ ቦታ የሚሰጠው ነው:: አንበሶች እሾህ ሲወጋቸውና እግራቸው ሲመግል ወደ ጻዲቁ መጥተው በእሾህ ያወጡላቸዋል:: መንታ የወለደች አንበሳን ልጇን ታቅፎ በየተራ የእናቷን ጡት ያጠባታል::[7]

የሚገርመው ነገር ደግሞ የአባ ሳሙኤል ዘ ደብረ ዋሊ ወይም የዋልድባው አባት የቅርብ ወዳጅ ስምም አባ አንበስ መሆኑ ነው::[8]

አቡነ አንበስ ዛሬ በአንበሳ በሚታወቀው በያንጉዲራሳና ብሔራዊ ፓርክ አቅራቢያ በሚገኘው የአዘሎ ገዳም የነበሩ አባት ናቸው:: ስማቸውም አቡነ አንበስ ዘ አዘሎ ነው::[9] የትውልድ ቦታቸው ትግራይ እንትጮ ሲሆን ዛሬም ድረስ በአንበሳ በሚጠበቀውና በ16ኛው ክፍለ ዘመን የወደመው የደብረ አዘሎ መነኩሴ ነበሩ:: በአንበሳ በሚጠበቀው ገዳም ሲወጡም ሲገቡም አናብስት ያጅቧቸው እንደነበር ታሪካቸው ይናገራል:: ዛሬም በአዘሎ ተራራ የሚኖሩ መነኮሳት ከአንበሳ ጋር ጥብቅ ወዳጅነት አላቸው:: አዘሎ በገዋኔ ከተማ ጀርባ ከአዲስ አበባ 376 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ 2145 ሜትር ከባህር ወለል በላይ ርዝመት ያለው ተራራ ነው::[10] ተራራው ቀደም ባለ ጊዜ ታላቅ ገዳም እንደነበረ አንዳንድ መረጃዎች ሲገልጹ ከተራራው ግርጌ የሚኖሩ ሰዎች ዛሬም በርካታ መነኮሳት የሚኖሩበት ገዳም እንደሆነ ይናገራሉ::

7. መዝገበ ቅዱሳን:: ገጽ 160
8. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት:: የቤተክርስቲያን መረጃዎች:: ገጽ 486
9. መርቆሪዎስ አረጋ:: የቅዱሳን ታሪክ:: ገጽ 135
10. የኢትዮጵያ ፓርኮችና ተፈጥሮ ማውጫ:: ገጽ 16

አባ በኪሞስ የአባ ሳሙኤል ደቀ መዝሙር ናቸው:: አንበሳን የአባቴ ፈረስ ይሉታል:: በዐፄ ይስሐቅ ዘመን አንድ ከዱር ወጥቶ ከተማ የሚያተራምስ አንበሳ ሁሉም ሲሸሸው የደብረ አባዩ አባ በኪሞስ ይሄማ የአባቴ ፈረስ ነው ብለው ወደ ዱሩ እንዳስገቡት ታሪክ ያስረዳናል::"

እንዲህ ያሉ ነባር የራሳችን ከፍጥረት ጋር የማይጣላ አብሮነት ዓለም ልሂቃን ዘንድ አልደረሰም:: ቀደምት የተፈጥሮ ጥበቃ ታሪክ ጥናት ባለሙያዎች አርስቶትልን ቀዳሚው ሰው ሲያደርጉትና ከዚያ በኋላ በየዘመኑ የመጡትን ሊቃውንት ሲዘረዝሩ ኢትዮጵያውያኑ ቦታ አልተሰጣቸውም::

በኢትዮጵያ ሀገረሳበዊ እውቀቶች አንበሳ የትም ከፍ ያለ ቦታ ያለው አውሬ ነው:: አፋር አንበሳ ዓይነት ይላል:: ከፋ የምድሩ ክብር ከአንበሳ መቆራኘቱን ያምናል:: ቋረኛ እንደ አባት ከስሙ ቀጥሎ አንበሳ የሚለውን ቦታ ይሰጠዋል:: የቋራው አንበሳ የሚለውና ለዳግማዊ ቴዎድሮስ የተሰጠው ቅጽል ስምም መነሻ ይኼው ነው:: ከማጂ ጫፍ እስከ ቀይ ባህር ዳርቻ አንበሳ አንበሳ የወል ክብር ያለው ፍጥረት ኾኗል::

አንድ ወቅት በካፋ አንድ የገጠር ቀበሌ በጠለፋ ይዘዋት የሚሄዱትን ሴት ከጠላፊዎቹ የነጠቁት አንበሶች እጃቸው ላይ ያሳደሯትን ህጻን በማግስቱ ለቤተሰቦቿ ማስረከባቸው የአንበሳን ጠባይ ከሚያጠኑት የሳይንስ ልሂቃን ይልቅ የሀገሬ ሰው ትውፊት ትርጉም ያለው እንደሆነ ያሳየናል::

11. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት:: የቤተክርስቲያን መረጃዎች:: ገጽ 231

በርካታ ቀደምት የኢትዮጵያ ሰነዶች ከአንበሳ ጋር ያለንን ግንኙነት ከጥፋት ይልቅ ለጥበቃ በሚረዳ ፍልስፍና የሚያወድሱና ቅርበትና ኅብረትን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው በኢትዮጵያ የዛሬው ዘመን ድረስ በዘለቀ መልኩ አንበሳ ከመገበያያ ሳንቲሞቻችን ጀርባ አንዱን ገጽ በክብር የያዘው፤ እድሜ ጠገቡን የአዲስ አበባ የከተማ አውቶቢስ ጨምሮ በርካታ የንግድ ስያሜዎች መገለጫም የኾነው ከዚህ ትስስራችንየተነሳ ነው፡፡

ቀድሞ የሰለሞናዊው ሥርወ መንግስት ልዩ ዓርማ ነበር፡፡ እርግጥ አስፈራለሁ ብሎ የሚያስብ ወይም መፈራት የሚፈልግ ወይም መልኩን ከጠንካራ መንግስትነት ጋር የሚያቆራኝ ንጉሥና ሥርወ መንግስት ራሱን ከጦጣና ከዝንጀሮ ያቆራኛል ብሎ ማሰብ ቀልድ ነው፡፡

የፊስአልጎስ ጸሐፊ አንበሳን መንፈሳዊ ምስጢር እንዳለው የሚያስረዱ የሥነ-ፍጥረት ጠባያቱን ያነሳል፡፡ ለምሳሌ "በዋሻ ውስጥ በተኛ ጊዜ ዐይኖቹን እና ቅንድቦቹን ገልጦ ያልተኛን ይመስላል፡፡" ይላል፡፡[12]

አህያን ለመውደድ አንበሳን የማንቋሸሹ አባዜ ምናልባት ከአህያ ፍቅር የተነሳ ሳይሆን ከነገሥታቱ ጥላቻ ያደረ ስሜት እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ለአህያ ሽንጡን ገትሮ የሚከራከረውን ሰው "አንበሳ"ብለንእንድናደንቀው እየፈለገ "አንበሳን ብሎ ምልክት"ካለንነገረ አንበሳ አልገባውም ከማለት ውጪ ምን እንላለን?

12. መጋቢ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ፡፡ ፊስአልጎስ፡፡ ገጽ 29

አንበሳ ግዙፍ ክብር ያለው ግዛቱን የማያስደፍር እናሳዎችን የማያወድም የዱር ንጉሥ ነው:: በመላ ዓለም ያለ ልዩነት አንበሳ የጀግንነት መገለጫና ምልክት ነው:: እንደ እኛ ሀገር አንበሳ ማተም ያሰረበት አልያም የቶራህ አንባቢ ይሁዲ ተደርጎ የሚቆጠርበት የዓለም ክፍል የለም::[13]

በሲሬንጌቲ አንበሳ ላይ የተደረገ ጥናት በአናብስቱ መካከል ያሉ ግንኙነቶች በቀጥታ ከደረጃ አሰጣጥ ጋር የተያያዙ እንደሆነ ያሳያል::[14] እንዲህ ያሉ የተፈጥሮ ጠባያት አንበሳን ለቤተ መንግሥትና ለነገሥታት ስሜት ቅርብ አድርጎታል:: ወደ ራቀ ዘመን ከሄድን ከክርስቶስ ልደት በፊት 1380 በሀገረ ግብጽ የነበረው ፈርዖን ስለ ገደላቸው ከመቶ የማያንሱ አናብስት እነሱን ገድሎ ስለሚሰማው የላቀ ጀብድ በጽሑፍ የቀረው ሰነድ በፈርዖን ቤት ስለነበሩት አይሁዳውያን ስናስብ የታላቁ ነገድ ምክንያት ስለመሆኑ ተጨማሪ እውቀት እናገኛለን::

እንደ እኛ ሀገር የዛሬ ፖለቲካ ምዕራፍ አንዳንዶችን የ"ይሁዳ አንበሳ"ከሚለው ስም በመነሳት አንበሳን ለመጥላት ምክንያት ሲኾንባቸው አያለሁ:: ለመኾኑ አንበሳና ይሁዳ እንዲህ ባለው ስም ተስማምተው በጋራ ለመስራት የት ዱር ውስጥ ውል ይዘው ይኾን? ብዬ የምጠይቀው ግን አላገኘሁም::
አንበሳን የዘውዳዊ ክብር መገለጫ የማድረጉ ባህል የአይሁዳውያኑ ልማድ ብቻ አይደለም:: ብዙ የዓለም ሀገራት ባህልና ወግ ለአንበሳ ይሄንን ከፍ ያለ ሥፍራ አይነፍገውም::

13. book animals,page113

14. The Serengeti Lion,page 131

መገለጫ የማድረጉ ባህል የአይሁዳውያኑ ልማድ ብቻ ስዋህሊ አንበሳን Simba ይለዋል:: ቃሉ በቋንቋው ውስጥ ኃይለኛ፣ ንጉሥና ብርቱ የሚሉትን ሁሉ የሚሸፍን ነው:: ስዋህሊ እንዲህ ሲል ግን ራሱን ከዘአምነገ ይሁዳ መዝዞ አይደለም:: ከአንበሳ ነገረ ተፈጥሮ ተነስቶ እንጂ:: ማሊም እንዲሁ እኛ ጃንሆይ የምንለውን ያኽል ቀደምት ነገሥታቷን አንበሳ ስትል በዚህ ልዩ ፍጥረት ስም ስትጠራ ኖራለች::

ይሁዳ ነገዱን ለመግለጽ አንበሳውን እንደ ምልክት ተጠቅሞ "አንበሳ ነኝ" አለ እንጂ አንድም አንበሳ እኔ ይሁዳ ነኝ ሲል አልሰማንም:: የይሁዳ ነገድ ምድር የአይሁዳውያኑ ሀገር እስራኤል እንደ ብሔራዊ እንስሳ የምትጠቀመው ጋዜል የተባለውን ዱር እንስሳ ነው::

ቀደምት እስራኤላውያን አንበሳን በማወቅ በኩል ከፍ ያለ ግንዛቤ ያዳበሩት በግብጽ የባርነት ዘመን ቆይታቸው ሊኾን እንደሚችል ብንገምት ሞኝ አያስብለንም:: ጥንታዊ ግብፃውያንየድል ምልክትና የማሸነፍ ምክንያት አድርገው የሚቆጥሯቸው አማልክቶቻቸው ሴትአንበሳ እንደሆኑ ያምናሉ:: የስፊኒክስ ምስል አንበሳን መጠጋቱም ምስጢሩ ይኼው ነው:: ከአራት ሺህ አምስት መቶ ዓመት በላይ እድሜን የኖረው ግዙፉ የኖራ ሐውልት ዛሬ ከዓለም ቅርሶች አንዱ ለመሆን በቅቷል::

ስፊኒክስ ከሰው አካል ጋር የተጋመደበት የሥነ-ቅርጽና ሥነ-ተረክ ውጤት አስቀድሞም በግዞት በኖሩት እስራኤላውያን ላይ ተጽእኖ ይኖረው ይኾናል::

የከነዓን ናፋቂ ህዝቦች ዘንድ የቀደመ አንበሳን የታላቁ ነገድ መገለጫ እስከመሆን ያደረሰ የነገረ አንበሳ እውቀት ከተጋዙበት ያጋዙትስ ቢሆን ያስብለን ይሆናል፡፡

የእስራኤል ገዳ የሚባለው ጋዜል ጋዝላ ወይም ተራራማ በሚል ስያሜ የሚጠራ በብዛት በፍልስጤምና በእስራኤል የሚገኝ እንሰሳ ነው፡፡ ይኸ እንስሳ የእስራኤል ብሔራዊ ቅርሷም ብሔራዊ የዱር እንስሳት ምልክቷም ኾኖ እያገለገ ይገኛል፡፡ አንዳንድ የዋህ ግን እስራኤል የአንበሳ ዋስ ጠበቃ፣ አንበሳም አይሁዳዊ፣ ሀገሩም እየሩሳሌም ይመስለዋል፡፡ ምልክትን ከፍጥረት ያቆራኛል፡፡

በዘፍጥረት መጀመሪያ ይሁዳን ከአንበሳ ደቦል ጋር ሲያናጽረው ኃይሉን ሲገልጽ ነው፡፡ በሌላ ስፍራ ዳንንም የአንበሳ ደቦል ሲለው እንዲሁ እንመለከታለን፡፡ አንበሳን ደጋግሞ የብርታት የጥንካሬና የአልሸነፍ ባይነት ምልክት ማድረጉ በብዙ ቦታዎች ተደጋግሞ ይታያል፡፡
ቀደምት የኢስላም የጽሑፍ ቅርሶችም ቢኾኑ እንደ ሂብሩው ሁሉ አንበሳን በልዩ ሞገስ ቦታ የሚሰጡት ናቸው፡፡ አሰድ በሚለው ስም ጎልቶ የሚጠራው አንበሳ በአረብኛ ቋንቋ 500 ስምና መገለጫ አለው፡፡ በታላቁ ቅዱስ ቁርአንም በአል-ሙደሂር ሲታይ የሚሸሸነቱን ከሜዳ አህያ ፍርሃት ጋር ተናጽሮ ቀርቧል፡፡
ከከድር ታጁ ባገኘሁት መረጃ ደግሞ የነብዮ ባልደረባ የነበሩት አቡሁረይራ ባስተላለፉት ትውፊት እንዲህ ብለዋል፡፡ "ነብዮ መሐመድ እንዲህ አሉን፤ 'ስጋን ከደዌ አሸሽው፡፡ ልክ ከአንበሳ የምትሸሸውን ያኽል'

ዛሬ አንበሳን ከሃይማኖት ጋር አብዝቶየማቆራኘቱ ልማድ የደዌ ያህል ፈውስ ቢፈልግም፡፡ እንደ ኢራን ያሉ ኢስላማዊ መንግስታት የሀገረ መንግስታቸው ምልክትና ብሔራዊ እንስሳቸው አንበሳ ነው፡፡ ታላቋ ሀገር ኢራን አንበሳን ምልክቷ ለማድረግ ታሪኳም ክብሯም ስለሚፈቅድላት የጥንቷን ፋርስ የዛሬዋን ኢራን ከአንበሳ የነጠለ አንድም ምድራዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

አፍጋኒስታን አንበሳ ጌጧም አርማዋም ኾኖ ኖሯል፡፡ በአፍሪቃዊቷ ኢስላማዊት ሀገር በሞሮኮም ባርባራ አንበሳ የብሔራዊ ክብሯ ምልክት ሆኖ ያገለግላል፡፡ እያንዳንዱ ሞሮኳዊ "ብሔራዊ እንስሳህ?" ቢባል "ማሻ አላህ" ብሎ አንበሳ ይላል፤ ታሪክ ቅድመ ክርስቶስ ልደት 190 ሺህ ዓመት ታሪክ አለሽ ያላት ሞሮኮ ከጥንተ ታሪኳ እስከ ዛሬ አንበሳ ልዩ ስፍራ ያለው እንስሳ የኾነባት ሀገር ናት፡፡
አንበሳ በተለይም ከአፍሪቃነት ጋር ልቆ ይቆራኛል፡፡ ሴራሊዮን ለአንበሳ ተራሮች ስም ሰጥታ በአንበሳ ከመወከል ስሟን ከአንበሳ ጋር አቆራኝታ እስከመጥራት የደረሰች ሀገር እንደኾነች ቢነገረን "ከየትኛው ነገደ ይሁዳ ጋር ተዛምዳ ይኾን?" ማለታችን አይቀርም፡፡

ቡሩንዲ አንበሳ ጌጧም ክብሯም ነው፡፡ እያንዳንዱ ካሜሮናዊ የድል መንፈሱ ምልክት ከኾነለት አንበሳው ይቀዳል፡፡ የኮንጎ ሪፐብሊክ ለአንበሳ በመዛመድ "ከኔ በላይ ለአሳር" ያለች ሀገር መኾኗን ከምልክቶቿ እልፍነት መረዳት ይቻላል፡፡ በሴኔጋልና ጋምቢያ ከክብር ልብሳቸው ጋር ያከበሯቸው አንበሶች ምልክትና ጌጥ ብቻ አይደሉም፡፡

ኬኒያ አንበሳ ብሔራዊ እንስሳ ብቻ አይደለም የጦር ሠራዊቷ ጭምር ልዩ የክብር ምሳሌ ነው:: ሲንጋፖር አንበሳ ግዙፍ አፈ ታሪኳና መገለጫ የኩራት ምልክቷ ሆኖ ቀርቷል:: ሴሪላንካ ደርሶ "አንበሳ ምንህ ነው?" ለሚል ጠያቂ "ምኑ ሞኙ ነው!" የሚያስብል ግርምት ይጭራል፤ እዚያ አንበሳ ሌላ ትርጉም ያለው ክቡር ፍጥረት ነው::

በእንግሊዝ "በግዛቴ ጸሐይ አትጠልቅም" ስትል ታላቋ ከሚለው ስሟ ጋር ሁሌም ታላቁ አንበሳ በክብር ምልክትነት ታትሞ ኖሯል:: አንበሳን በክብር የምትይዘው ሉክዘምበርግ አንበሳ ብሔራዊ መገለጫዬ ነው ያለች ትንሽ ሀገር ናት:: ኖርዌይ ረዥም ዘመን ታሪኳ ከአንበሳው ሳይነጠል ዛሬም አንበሳዋ የብሔራዊ እንሰሳዋ ምልክት ኾኗል:: ቤልጂየም ያለ ወርቃማዋ አንበሳ ምን መለያ አላት? በሶፍያ ከተሞች ሞገስ ባለው ክብር የሚገለጠው አንበሳ ለቡልጋሪያ ልዩ ምልክት ነው:: ድርብ ጅራቱ አንበሳ ለቼኮች ድርብ ኩራት ኾኖ ይኖራል:: በጆርጂያ የአንበሳ ተምሳሌት የብሔራዊ ቀለሟን ያኽል ትርጉም ይሰጠዋል:: ሲውዲን፣ ኔዘርላንድ፣ ፊንላንዶች፣ ዴንማርኮች በከንዳቸው የሰቀሉት አንበሳ ክንደ ብርቱ ነን የሚሉበት ተምሳሌት ነው::

ሌላው ቢቀር ቤርሙዳ የሚሷት የሰሜን አትላንቲክ ውቅያኖስ ደሴት ከቀይ አንበሳ የተቆራኘች መኾኗ አንበሳን ልዩ ያደርገዋል::

በግሪክ የኢሊያድ ድርሰት ውስጥ አንበሳ ስሙን ያተመ እንሰሳ ነው:: ሆሜር ደጋግሞ የጠራው አንበሳ ትርጉሙ ከዓለም ዳር እስከ ዳር አንድ የመኾኑ ምልክት እልፍ ነው::

አርግጥ ዳቦ ከማይገዛ ሳንቲም ጀርባ ጎፈሬውን ገጭ አድርጎ የታተመ የአንበሳ ምስል እያየ ለሚኖር የነገረ አንበሳ እንግዳ አንበሳ ዝም ብሎ ሊመስለው ይችላል:: ዝም ብሎ አለመኾኑን ግን ዓለም ፊት ተከብሮ ያሳየ ፍጥረት በመኾን አሳይቷል::

የከፈረውም፣ የሰለመውም፤ ማተብ ያሰረውም፣ እምነት ለምኔ ያለውም፤ በወል አንድ የሚያምኑት ነገር ቢኖር አንበሳ ትልቅ የዱር ንጉሥ፣ የድል አድራጊነትና የአሸናፊነት ምልክት መኾኑን ነው:: ለአደን ተፈጥሮ ድል አድርጎ ማደን ትጉህ ሰራተኛነት ብቻ ሳይኾን ስራን በድል የመወጣት ማሳያ ነው:: ፈረንሳዮች ቴሌን እናስተዳድር ብለው ጎራ ሲሉ በሳቅ የገደላቸው የአንዲት ደሃ አፍሪቃዊት ኔት ወርክ አልባ ሀገር የቴሌ ካምፓኒ ምልክቷ አንበሳ መሆኑ መሰለኝ፤ ደባ ሰርተው ከቴሌዋ አንበሳዋን ከስራ ገበታው ኢትዮጵያዊውን ነቅለው ሄዱ:: "አንበሳ እንደ ኢትዮጵያውያን ላሉ ሀገራት ምልክትነት ሊውል አይገባም" የሚሉት አይገርሙኝም፤ "አንበሳ አይወክለኝም" የሚሉት ግን ይደንቁኛል:: በልክ የመወከል ጉዳይ ዘመን የሚያጎናጽፈን ካባ ቢኾንም አንበሳ ከድፍን ኢትዮጵያ ምድር ጋር ያለውን ስር የሰደደ መስተጋብር ሳጤን ግን አንበሳን ዘውጋዊ አድርጎ ዓለም ካከበረው ምልክት ጋር አይናቆርም::

አሁን ባለው ሁኔታ አንበሳ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምልክት ተደርጎ በህግ ስፍራን ያገኘ እንስሳ አይደለም:: ይኹን እንጂ ምትክ የለሽ እሴቶችን ወክሏል:: የሀገራችን ምትክ የለሽ የሚባለው ግዙፍ ሆስፒታል በአንበሳ ይጠራል::

ከአዲስ አበባ የማይነጠለውም የከተማ አውቶቢስ አንበሳ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የአርበኝነት ታሪክ ባህውርታዊነት የታየበት የታጋዮች ስብስብ ጥቁር አንበሳ ነኝ ብሎ ጥቁር አንበሳ መኾኑን ከነጻነት ጋር እንድንጠረንፈው አሻራ ትቶልን አልፏል፡፡ ዛሬ በህገ ወጥ የዱር እንስሳት ዝውውር ከፍተኛ ራስ ምታት የኾኑት የመካከለኛው ምስራቅ ባለ ነዳጅ ልዑላንና ከበርቴዎቻቸው ስለ አንበሳ ቢጠየቁ ነገዱ ይሁዳ መኾኑን ሳይኾን የተከፈለ ተከፍሎ ቢኖራቸው የሚመርጡት ብርቅ ውድና ድንቅ እንስሳ እንደኾነ ይመሰክራሉ፡፡

እንደ አባቶቻችን የአንበሳ ሕይወት ካደለን አንበሳ መባሉ አያሸማቅቅም፡፡ በማያሸማቅቅ ስም ስንጠራ የምንጠራበትን ስም ደጋግምን ለምን ሲል እናጤነዋለን፡፡ ያኔ ነገረ አንበሳ ሰፊ አውቀት ይሆናል፡፡ ያም እስኪሆን ግን ኢትዮጵያ የአናብስት ሀገር ከመኾን አታርፍም፡፡

# መልከዓ ምኒልክ፤

ጥቁር ነኝ፤
ለጥቁር ሁሉ ኩራት የኾኑ ንጉሠ ነገሥቴ የተወለዱበትን ቀን አከብራለሁ።

ስላስከበሩኝ መወለዳቸውን አወድሳለሁ።

ዘመነ መሣፍንት ባበቃ፣ ዓለም አንዱ ሀገር አስር ቦታ ኾና በተሳለቀበት ዘመን ማብቂያ፣ ሁለቱን ታላላቅ ነገሥታት ተከትሎ ስለ ነገሡት ንጉሣችን ልደት ደስታችን ወደር የለውም።

ምኒልክ ከእናታቸው ከኢትዮጵያ ከአባታቸው ከጥቁሮች ምድር አፈር የተወለዱ እንጂ እንዲያው በቀላሉ የእከሌና የእከሊት ልጅ የምንላቸው ተራ አፍሪቃዊ አይደሉም። ይልቁንም አፍሪቃአውሮጳ ጠረጴዛ ላይ መነጋገሪያ ትሆን ዘንድ የቀደመችዋን ገናና ሀገር ዳግም እንድትታፈር ያደረጉ ናቸው።

አንጎለላ ደስ ይበልሽ፤

አንቺ ዘንድ እትብቱ የተቀበረው ንጉሥ ዓለም ጥግ ድረስ ዝናው የናኘ ጥቁር መሪ ነውና፤

አንቺ ትንሿ መንደር ተወለደ የተባለው፤ ትልቁን የአፍሪቃ የነጻነት መንፈስ ወልደሏልና፡፡

ንጉሣችን ምኒልክ ስንል፤ ጥበብን ከሀገር ፍቅር ጋር ስለታደሉት ታላቅ መሪ እያወራን ነው፡፡ ነሐሴ ከመጋመሱ በፊት እረኞች ጅራፍ እያጮኹ፤ ሴቶች በእልልታ፤ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤተ መንግስት ግርጌ፤ ከታላላቆቹ ኢትዮጵያኖች መንደር፤ ከነ ገበየሁ የትውልድ ቀዬ የተወለዱትን ጀግና ልደት በኢትዮጵያዊ ልብ በአፍሪቃዊ መንፈስ እናከብረዋለን፡፡

በዚህ ቀን ዳግም ስሟ ከቅዱሱ ንጉስ ከዮሐንስ ተረክ ጋር የሚነሳው፣
ሆመር የተቃኘላት፣
ዓለም ሲፈልጋት የኖረው፤
የነቢላል ሀገር፣ የነጃሺን ግዛት ስሟ ዳግም እንዲናኝ ያደረጉ ንጉሥ ተወለዱ፡፡

ይኸ ቀን የንጉሡ ልደት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ለተዋረደው ጥቁር ቀለም ትምክህት ሆነዋልና የጥቁር ሁሉ ልደት ነው፡፡ በአንዲት አፍሪቃዊ መንደር አፍሪቃን ተሻግሮ ጥቁር ሁሉ የኔ የሚለው ጥበበኛ ንጉሥ የተወለደባት ቀን፡፡

በዚህ ቀን የአውሮፓን ስልጣኔ የተራበች ሀገር አብራ ተወለደች፤

በዚህ ቀን ለጥበበኞች ክብር የሰጠ ንጉሥ ወደ ምድራችን መጥቷልና የጥበበኞች ልደት ኾነ።

በዚህ ቀን ኢትዮጵያውያን እምዬ የሚሏቸው ንጉሥ ተወለዱ።

በዚህ ቀን የአድዋ ተራሮች ላይ ዘለዓለማዊ ታሪክ ያተመ፣ አንድነትን የፈጠረ ኢትዮጵያዊ መሪ ተፈጠረ።
እናም ልደቱ ልደታችን ነው ስንል በደስታ ነው።

ልደቱ ልደታችን የኾነው የታላቁ ባለዕራዕይ የአባቶቻችንን ሀገር እሰራለሁ ብሎ ስሟ የገነነ የጥቁር ህዝቦችን ምድር፣ የኩሽን ገናና ክብር የሚመልሰው የንጉሠ ነገሥታችንን መልዕክ በኢትዮጵያዊ መንፈስ ተደረሰ።

ንጉሣችን ሆይ በገብረ ሥላሴ መንፈስ፤ ከሆኑት ያነሰ፤ ግብርዎን የማይስተካከል መልክ የሚወዷትን ሀገር በተለዮ አንድ ክፍለ ዘመን፤ ዛሬም እምዬ ከሚል ቅሪት ትውልድ ይህ እውነት ተጻፈ።

ደግሞ አንቱ ከነገሥታቱ መካከል መልክ የሚገባዎት ነዎትና ሠላም እልዎታለሁ።
ሠላም ለዙፋንዎ!
ከጥቁር ልብ አልፎ በሮማ መንበር ላይ በክብር ለነገሠው።

ሠላም ለግርማ ሞገስዎ! ቀለሙ ለጠቆረ፤ የጨለማ ሳይሆን የብርሃን ምልክት ኾኗልና፡፡

ሠላም ለናኘው ዝናዎ! ስኪነር ዘንድ ለደረሰው፤ ዓለም ሩቅ ስላለች ሀገር ሰምቶ ቅርብ ስለሆነበት ክብሯ፡፡ መሪ ብቻ ሳይሆኑ የምሥራቅ አፍሪቃ ኮኮብም ሆነው ሩቅ ምሥራቅ ድረስ አብርተዋልና፡፡

ሠላም ለምኞትዎ! ሀገርን ከሌላው ሀገር ጋር ለማስተካከል፤ እንደ ታሪኳ ገናና ለማድረግ በሥልጣኔ ምዕራፍ ትጓዝ ዘንድ መዓልት ከሌት ለደከመው፡፡ ደግሞም ላደረገው፡፡

ሠላም ለልደት ቀንዎ! እሷ ዳግም ልደታችን ናትና፡፡ ዓለም የእርስዎን ልደት ችላ ቢል ምን ይጎድልበታል? ምኞቱን ያጎደሉ የነጻነት ምልዓት ነዎትና፡፡ እኛ ከእርስዎ መወለድ ደስታን ባናተርፍ ግን እንዳንጎድል የደከሙት ከንቱ ኾነ ማለት ነው፡፡
ደግሞም ጎድለናልና፤

ሠላም ለዘመንዎ! ለነበሩባቸው ቀናትና ወራት፡፡

የእርስዎ ዘመን መስከረሞች ምነኛ የታደሉ ናቸው፡፡ ከየሰው ልብ የማይረግፍ አደይ አፍክተዋልና፡፡

የእርስዎ ዘመን ሌሊቶች ምንኛ የተባረኩ ናቸው፡፡ አንድ የምትሆን ታላቅ ሀገር የፈጠረ ታላቅ ብርሃን በርቶባቸዋልና፡፡

እንኳን የእኛ ዘመን ሰው አልሆኑ፤ የእኛ ዘመን ሰው ሆነው በእኛ ዘመን ሰው ተማክረው ቢሆን ኖሮ ለባቡሩ መስመር ከጅቡቲ በአልዩ አምባ አንኮበርን በመረጡ፡፡

ለኢ-ታማዥር ሹምነት ከፈታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ይልቅ ደጃዝማች ባሻ አቦዬ ቀልብዎትን በገዙዎት ነበር፡፡

ከታላቁ ምትክ የለሽ ኢትዮጵያዊው ከራስ ጎበና ዳጬ ይልቅ በራስ ልዑል ሰገድ አጥናፍ ሰገድ ልብዎ ባረፈ ነበር፡፡

እንኳን የኔ ዘመን ሰው አብርዎት አልነበር፡፡ አዲስ ዓለም እናት ከመውጣት ለቤተ መንግሥትዎም ቢሆን አንጎለላን ያድርጉ ብሎ፤"ከራስ በላይ ነፋስ" ባለዎት ነበር፡፡

እንኳን የኔ ዘመን ሰው አልሆኑ፤ እንኳን በእርስዎ ዘመን መጡ፡፡ ያ መልካም ዘመን ለእርስዎ ቱሩፋት ነው፡፡ ለእኛ ትዝታ አይደለም፡፡ ዛሬ ኾኗል፡፡ እየኖርንበት ነው፡፡ እንኳን ተወለዱ፡፡

ደግሞም በዚህ መንፈስ ተአምርዎትን እንጽፋለን፡፡

# ተአምረ ምኒልክ፤

ክርስቶስ በተወለደ በ1836 ዓ.ም. በቀዳሚት ሰንበት መስከረም ሊጠባ 23 ቀናት ሲቀሩት፤ ነሐሴ በኾነ በአስራ ሁለተኛው ቀን። ከቀንም ሸጋ በኾነችው በቀዳሚት ሰንበት የተወለደው ንጉሣችን ጥቁሩ ጌጥ፤ በንግሥና ዘመኑ ሁሉ ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

የኃይለ መለኮት ሳህለ ሥላሴና የእጅጋየሁ ለማ አድያሞ ልጅ የሆነው ንጉሠ ነገሥታችን ምኒልክ በዘመኑ ያደረገውን ተአምር ከቁጣው በሚያጥር መጠን አሳንሼ ተአምሩን እንዲህ እጽፋለሁ።

ለሀገር ያለው ፍቅር በተገለጠለት በጻሐፊ ትእዛዙ በገብረ ሥላሴ መንፈስ ስለ ታላቋ የአባቶቹ ሀገር ስለ ኢትዮጵያ ታላቅን ነገር ያደረገው ንጉሥ ተአምር ይህ ነው።

ንጉሠ ነገሥታችን ዳግማዊ ምኒልክ ሰኔ በገባ በሃያ አራተኛው ቀን በቆቂት በር እንዲህ አደረጉ፤

ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ውጥን የነበራቸው ዳግማዊ ቴዎድሮስ በመቅደላ ካሰሯቸው እስረኞች አንዱ ንጉሣችን ምኒልክ ነበሩ፡፡ ሰኔ 24 ቀን በመቅደላ ከባድ ዝናብ ጣለ፡፡ በታላቁ አምባም የመብረቅ ድምጽና የወታደር ሆታ ተሰማ፡፡ ወታደሩስ ሆታውን ያሰማው ስለምን ነው ቢሉ፤ የአንበሳ ድምጽ ተሰምቶ ነው፡፡ የወታደሮቹን ጫጫታ የሰማው አንበሳ ወደ ዱር ቢሸሽ የበረቱ ወታደሮች እግር በእግር ተከተሉት፡፡ ነገር ግን አልተገኘም፡፡ ወዲያው ቢመለሱ የቆቂት በር ክፍት ነበር፡፡ የከፈተውም አልታወቀም ነበር፡፡ የመቅደላ እስረኞች ሲፈለጉ ግን የሸዋው ምኒልክ አልነበረም፡፡ ከሀያ ተከታዮቹ ጋር የቆቂትን በር አልፎ የመቅደላን ግዞት አምልጧልና፡፡

ደግሞም ንጉሡ ነገሥታችን ምኒልክ ያደረጉት ሌላው ነገር ይኸ ነው፡፡

ለትልቅ ሀገር ህዝብ ትንሽ ሀገር ያሳንሳል፡፡ እናም እንደ አባቶቻቸው ግዛቷ የሰፋ፣ ክብሯ የተንሰራፋ፣ ስሟ የገነነ፤ ታላቅ ሀገር ስለመፍጠር አሰቡ፡፡ እንዲህ ባለው ሀሳብ ብዙ ደከመዋል፡፡ ምኞታቸው ታላቅ ህዝብና ሀገር መፍጠር ነበር፡፡ የተመኙትን ያደረጉ ንጉሣችን ይልቁንም ለጥቁር ሁሉ ኩራት ሆኑ፡፡

ንጉሣችን ሰላምን ስለመፈለግ ያደረጉት ተአምር ይህ ነው፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ ሰላምንስ እንደ ሰማይ መንግሥት ይመኟታል፡፡ ደግሞስ ምን ይጠላሉ ቢባል የሰው ደም ሲፈስ ማየትን ነበር፡፡ የሚያሸንፉትን የሚለማመጡ ጀግና ነበሩ፡፡

ድል የሚያደርጉትን ጦርነት ይጠየፉታል፡፡ ይህ እንደምን ያለ እውነት ነው ቢሉ እንባቦስ ለዚህ ምስክር አይደለምን?

ንጉሥ ምኒልክ በእንባቦ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጦር ጋር መዋጋትን ተጠየፉት፡፡ የአንድ ወገን ሁለት ጎራ ፍልሚያን ስለመሸነፍ አስበው ብቻ ሳይሆን በወገን ላይ ማሸነፍን እንደመሸነፍ ቆጥረው ሸሹት፡፡ በሸሹት ጦርነት ድሉ የእሳቸው ሆነ፡፡

ደጉ ንጉሣችን ድል ላደረገው ፍቅር ያለው ስለመሆኑ በድል ማግስት ያደረጉት መልካም ተግባር ደግሞ ይህ ነው፡፡

የሸዋ ጦር የጎጃምን ጦር ድል አደረገ፡፡ ንጉሥ ሚኒልክ ግን የጎጃሙ ንጉሥ መትረፍ ከድላቸው የሚበልጥ ደስታቸው ሆነ፡፡ እናም "እንኳን እግዚአብሔር አተረፈዎ" ሲሉ ምስጋናን በንጉሥ ተክለሃይማኖት ፊት ለንጉሣቸው አቀረቡ፡፡ አርደው ለቆሰለው የምርኮ ገላቸው በከብካቤ አስታመሟቸው፡፡ ማነውስ ጦር ሰብቆ የመጣበትን ባላንጣ ስለመትረፉ ፈጣሪውን የሚያመሰግን? ንጉሣችን ይህንን አድርገዋል፡፡

ደግሞም ንጉሣችን ከዳሞታ ጦርነት መልስ ያደረጉት ትናንትን የመርሳት የድል ማግስት ስሜት ይህ ነው፡፡
በወላይታ ታላቅ ንጉሥ ነበር፡፡ ጉልበቱ የበረታ ጦርነትን የሚያውቅ፣ በዳሞታ የተደረገውስ ጦርነት እንደምን ያለ ነው? ቢሉ ከባድ ነበር፡፡ ሞቶሎሚን ቆጥሮ የነገሠው ብርቱ ከሳህለ ሥላሴ የሚመዘዘውን ዘውድ በጽኑ ተጋፈጠው፡፡ ድል ለንጉሥ ምኒልክ ሆነ፡፡

ከድል በኋላ ቂም የማያውቀው ንጉሥ መልሶ ካዎ ጦናን በዚያ ገናና መንግሥቱ ላይ ንጉሥ አድርጎ አስቀመጠው፡፡

ንጉሣችን ምኒልክ ለጥቁር ሁሉ ኩራት የሆነውን የነጻነት ችቦ የለኮሰበት ተአምር ይህ ነው፡፡ ይኸስ ተአምር እንጂ ሌላ ምን ይባላል፤

ጣሊያን ምድራችንን ወረረ፡፡ አስቀድሞስ በውል ስበብ ጦርነት እንዳይሆን በጽኑ ሲለምን የኖረው ንጉሣችን ለውጊያ ተገደደ፡፡ ነገር ግን ብርቱ ሰራዊት ነበረው፡፡ ጥቅምት እኩሌታ ወረኢሉ ከቶ፤ የካቲት ጊዮርጊስ የድል ጥዋን የተጎነጨው ብርቱ የጥቁር ጀግኖችን አሰለፈ፡፡ እንዲህ ሀገሩን አንድ የሚያደርግ፣ እንዲህ በሀገሩ ብርቱ ተዋጊዎች የድል ዝናን በጥቁር ህዝብ የሚጽፍ ንጉሥ ስለነበረን እንመካለን፡፡ ደግሞም ህይወቱን እንናገራለን፡፡

የንጉሠ ነገሥታችን ስራው ድንቅ ነው፡፡ ውሃን በመዘውር ሽቅብ አውጥቷል፡፡ ይህ እንደምን ነው? ቢሉ በጥበብ ነው፤፤ ይህ ጥበብ እንደምን ታመነ ቢሉ? ይህስ የሰይጣን ስራ ነው እንጂ ተባለ፡፡ ንጉሣችን ግን በምኞቱ ስንፍና የለበትም፡፡ ያለ እውቀት የሚሉትን ሳይሰማ እውቀትን በመናገሻው እውን አደረገ፡፡

በነፋስ ማውራትን ማን አደረገው? በንፋስስ ማውራትን ከሳጥናኤል እንደመነጋገር ያልቆጠረውስ ማን ነበር? ጨለማ በነበረው ምድር አባቶቹ ድንቅ ባደረጉበት ጥበብ ስለ ድንቅ ሀገር መስራት የተጨነቀው ንጉሣችን ተአምረኛ ነበር፡፡

ፈረሰስ የአባቶቻችን ወግ ነበር፡፡ በባቡር የተጫነው ግን ንጉሠ ነገሥታችን ምኒልክ ነው፡፡

ልቡ ሰፊ እጁ ለጋስ፤ ደግሞስ ከእሱ በኋላ እምዬ መባልን ማን አገኘ? ደግሞስ ከዓለም እኩል ከዓለም ጋር ስሙ የተጠራ አስቀድሞስ ናግራን በደረሰ ክብር ካሌብ በተገለጠበት ሞገስ፤ ሞገሱ የተገለጠ እንደ ምኒልክ ያለ ንጉስ ማን ነው?

እስከ ህንድ በገዛቸው በሳባ ምድር ዳግም ከህንድ ያለፈ ዝና የናኘ እንደ ምኒልክ ያለ ንጉሥ ማን ነው?

አስቀድሞስ ዓለም ሳይራቀቅ የአደንን ህግ አበጀ፡፡ ደግሞስ ፓስታ ማህበርን ፈልጎ ያገኘ ንጉሣችን ከሰራው የቱ ለሀገር የማይበጅ ሆኖ ነው?
ዘረኝነትን የሚጠየፍ፤ ሀገርን የሰራው የንጉሣችን የምኒልክ ተአምርማ ብዙ ነው፡፡

ምኒልክ ከአንኮበር ተራሮች አልፎ የሚመለከት ሰፊ ልብ ነበረው፡፡ በሰፈር ልጅስ አስቦ ባልቻን መድፍ ተኳሽ ማድረግ እንደምን ይቻል ነበር፡፡ ወንዝ የማይሻገር ሀሳብ ያለው ቢሆን ሞሮስ ግቤን የተሻገረ የአባ ጅፋር ወዳጅነት ከምን ይገኝ ነበር? ወንድሞቼን ሰብስቡልኝ የሚል ጠባብነት ቢኖረውስ እንደምን የአባ መላ ወንድም መሆን ይቻል ነበር፡፡ ልጅንስ ለመዳር ከአርአያ ዩሐንስ የቡልጋ ባላባት በቀረበ፡፡
ንጉሣችን ምኒልክ ሰው ነው፡፡ ስናከብረው ያመልክነው የሚመስላቸው ሞኞች ናቸው፡፡ እርሱስ በሃይማኖቱ የቀና ፈጣሪው ፈሪ ትሁት ነው፡፡

ንጉሣችን ግን ዛሬም ትናንትናው ሲታሰብ የማያሸማቅቅ የሀገር መሃንዲስ ነው፡፡ ሀገርንስ ድንቅ አድርጎ ሰርቷታል፡፡ በተሰራች ሀገር የምኖር እኔ ባሪያው የንጉሡ ነገሥቱን ተአምር ለመጻፍ ከምኑ እንደምጀምር አቅቶኝ ተውኩት፡፡

ስለ ፍቅሩ አንተ ስለ ክብሩ አንቱ የምንለው ንጉሣችን ምኒልክ ከአባቶቹ ሀገር የመውደድ ገድል፤ ከወንድሞቹ ለሀገር የመጋደል መንፈስ ራሱን የሰራ ነውና ሁሉን ትቼ የአበውን የሀገር ፍቅር ገድል ለመጻፍ ተነሳሁ፡፡

# ገድለ አበው ዘ አድዋ፤

ይኽ ታሪክ እውን በኾነ 123 ዓመት ነጻ በወጣችው ምድር የተፈጠርሁ እኔ ሄኖክ ስዩም የቀደሙት በዓይናቸው አይተው ከጻፉት፤ ያልጻፉት በልባቸው አኑረው ካቆዩት፤ የሰማሁትን የአባቶቼን ገድል እንዲህ ጻፍሁ።

አባቶቻችን ነፍሳቸውን እስከ መስጠት ያልሳሱላትን ኢትዮጵያ ለሚጠብቅ ለእርሱ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይኹን፤

አንድ ዘመን እንዲኽ ኾነ።

ያ ዘመን ኢትዮጵያ በመሳፍንት ምኞት ከተበተነችበት በተሰበሰበች የነገሡት 3ኛው ንጉሠ ዐፄ ምኒልክ ጥንት ከዓለም መዘመን ቀድሞ በዘመነች ሀገር እንደ ቀደሙት ነገሥታት የሀገረ ኢትዮጵያ ንጉሥ ሆነው በዙፋን ተቀመጡ።

የሀገረ ኢትዮጵያ ስምም እንደ ቀደሙት ታላላቅ ነገሥታት ዘመናት ከፍ አለ፡፡
ይኸ ከፍታዋ ጆሮው ሲደርስ፤ ደጃፏን ረግጦ ህዝቧን ማጋዝ የፈለገ የሮማ ንጉሥ በከፉ ተመኛት፡፡ ለምኞቱም ወሰን አልነበረውም፡፡ ይኸ ምኞት፤ ሀሳቡ ባህረ ኤርትራ ገብቶ እንደሰጠመው የፈርዖን ጦር ሳይጨበጥ ይሰጥም ዘንድ የአባቶቻችን አምላክ ኢትዮጵያን በደግ አሰባት፡፡ የዚህም ምልከቱ እንደምን ነው? ቢሉ በተበተነችው የመሳፍንት ሀገር ልቡ ያልተነሳሳ ሁሉን አንድ ባደረገው ፀሐይ ንጉሥ የታፈረችዋን ሀገር መውረር ፈልጓልና፡፡

አባቶቻችን በአድዋ ያደረጉት ገድል ይኸ ነው፡፡ ፈጣሪ ነፍስን እስከመስጠት የተዋደቁላትን ሀገር የምንጠብቅበት መንፈስ ይስጠን፡፡

አሜን፡፡

አንድ ቀን ንጉሥ አዋጅ አስነገረ፡፡ ይህ አዋጅ ሀገር ሊቀማ የመጣ ወራሪ እንደፍልፈል ምድራችንን እየሰረሰረ አድብ ቢባል አልሰማ ያለ ነው የሚል ነበር፡፡

የንጉሡን አዋጅ ሀገር ሁሉ ሰማ፡፡ ያኔውኑ የሸዋ ሰው ጥቅምት ሲጋመስ ወረኢሉ ገባ፡፡ ያኔ በኢትዮጵያ ምድር የሆነው የአባቶቻችን ገድል እንዲህ ነው፡፡
ከጠረፍ ሀገር ለሚነሱ አባቶቻችን የደዴሳ ወንዝ ሙላት ስጋት አልነበረም፡፡ ከበርሃ ለሚመጡ አባቶቻችን የጥምና የሀሩር ጉልበት ፈተና አልነበረም፡፡

አባቶቻችን እሾህና አሜኬላን ረግጠው፣ በባዶ እግር ሙሉ ሀገር ሊያስረክቡን መንገድ ዝመሩ፡፡
በአራቱም አቅጣጫ እንዲኽ ሆነ፡፡

የንጉሠ ነገሥታችንን ጥሪ የሰማው ሠራዊት ብዙ ነበር፡፡ ከተት ብሎ የተነሳው ሠራዊት ከጉልበቱ ይልቅ ፈጣሪውን የታመነ ኾነ፡፡ ግቤ ሸለቆን በዱአ ተከዜን በጸሎት የተሻገረው ሠራዊት ለሀገሩ ፍቅር ቁጥሩ ለአብረሃም እንደተገባለት ቃል ኪዳን ከምድር አሸዋ በዝቶ ወደ ስሜን የሚፈስ የሰው ጎርፍ ሆነ፡፡

አባቶቻችን ለንጉሣቸው ቃል ታመኑ፡፡ ብዙ ቋንቋ፤ በምልክት የሚግባባ፣ በመንፈስ የሚናበብ አንድ ህዝብ ሆነ፡፡ ጠላት እንደ ሰናዖር ሰዎች አንዱ ከሌላው ቃሉ ተደበላልቋል ብሎ ሲል በአንድ ድምጽ በአንድ ቃል ኢትዮጵያ ሲባሉ አቤት ብለው የወጡት አባቶቻችን ታላቅ ገድል ይኽ ነው፡፡

እኔ ታናሽ የሁንሁ ኢትዮጵያዊ፤ የጣሊያን ንጉሥ እስር ቤታ ሊያደርጋት ባይሳካለት መንፈሱን የወረሱ ትውልዶች በተተኩበት፤ አንድ ሀገር ለመፍጠር ሰማዕት የሆኑ አያቶች የተኳቸው የልጅ ልጆች እንዲቷን ታላቅ ሀገር ብዙ ቤታ ለመሰንጠቅ በሚባትሉበት ዘመን፤ ዓለም አምኖት ይህ ትውልድ ከዶት የሚነታረከበትን ገድል ለመጻፍ ተነሳሁ፡፡

በጸሐፊው በገብረ ሥላሴ ያደረው ለንጉሠ ነገሥቱ የመታመን መንፈስ በኔና በትውልዴ ያድር ዘንድ በየአቅጣጫው ሆ ብሎ የዘመተው የአድዋ ሠራዊት ገድል ይኽ ነው፡፡

ቀኑ የካቲት በኾነ ካያ ሦስተኛው ቀን ሆኗል። በቀደሙት ነገሥታት እንዳለው ልማድ ሁሉ በታቦቱ የታመኑት ንጉሠ ነገሥት በጊዮርጊስ ዕለት ስለሆነው ውጊያ ድሉ ከፈጣሪ ጋር የእሳቸው እንደሚኾን ዘማቹ አምኗል።

የኾነውን የመሰከረው በርክሌይ እንዲህ አለ፤ "የተተከለው ድንኳን ሲታይ ከብዛቱ የተነሳ አፍሪካ ኤሮጳን ለመጠራረግ የተነሳች ይመስላል።" ይህ የአባቶቻችን ገድል ነው። ከብዛታቸው የተነሳ ውቅያኖስን ደፍነው የሚያልፉ እስኪመስሉ የተሰለፉት፤ የማዜን ወንዝ አልፈው የመጡት፣ ጎጀብን ተሻግረው የተሰለፉት፣ ጉደርን አቋርጠው በፈረሳቸው ኮቴ ድምጻቸው እስከ ሮም የተደመጠው፣ አዋሽን አልፈው ዝማን አቋርጠው ከሰምን ሰንጥቀው የመጡት አባቶች የሀገራቸው ሰማይ ላይናገር ታዝቦ ባስቀረው እውነት ስለ ባንዲራቸውና ስለ ቀለማቸው ተዋደቁ።

ከብላቴ መለስ፣ ከቡልቡላ በላይ፣ አሞን ተሻግረው፣ ደዴሳን አቋርጠው፣ ኩልፎን ሰንጥቀው፣ በለስን አልፈው የተከተቱት እውነትም አውሮጳን ጠራርገው ሊያጠፉ የተነሱ እስኪመስሉ የሰማያትን ደመና በሚገፍ ድምጽ ሸለሉ አቅራሩ፤
የአባቶቻችን ገድል ቢያንስ እንጂ ተጋኖ ቢጻፍ የኢትዮጵያ ወንዞች ቀለም ሆነው ባልበቁ፤

በየካቲት ጊዮርጊስ ሌሊት አስራ አንድ ሰዓት የጠላት ጦር ተኩስ አሰማ። ያኔ የዘቡ ተራ የራስ መንገሻ ነበር። የትግራይ ጦር በጽኑ ተዋጋ። ይህ ጦርነት በአድዋ ተራሮች ግርጌ ነበር።

ብዙ ተጋድሎ ተደረገ:: አባቶች ለሀገር ክብር ተዋደቁ:: ከወገን ጣር ይልቅ በርታ የሚለውን አዝማሪ መሰንቆና ዜማ የሚሰማው ኢትዮጵያዊ ወታደር ብዙ ነበር:: ሞት ከአንድ ሽክና ጠላ ቀለለች:: ለሀገር መሞት ትንሳዔ ሆነ:: ከየት ነህ? ያለመባባል ከአንድ ኢትዮጵያ አንድ ኢትዮጵያን ብሎ የተሰለፈው የንጉሠ ነገሥት ጦር ከካሌብ የናግራን ጦርነት በጀመረው የቀደሙት አያቶቹ ክብር ለሀገር መፋለምን አሳየ::

ይኼ እንደ ኢዛና ጦርነት በድንጋይ የታተመ የድል ታሪክ አልነበረም:: ብራና ፀሐፊዎችም ሞላውን አላስቀሩትም:: ይልቁንስ ሰማይና ምድር ለነጻነት የተከፈለን የጥቁር ህዝብ ተጋድሎ ተመለከቱ::

የተጋድሎው እማኝ የድሉ ባለቤት ከሆኑት አንዱ አለቃ ገብረ ሥላሴ የጂ ከእንዝርት ቀሎ ተአምር መስራቱን ሲነግሩን መች ሞላውን ሆነ፤ በጌምድር ከነብር ፈጥኗል ሲሉን መች ጨርሰው ያዩትን ነገሩን፤ ሸዌ ከአሞራ ረቧልስ ሲሉ ጎጃሜ ከንብ ብሶ ጠላትን አባሮታል ብለው ሲጽፉስ ከነገሩን ያልነገሩን የአባቶቻችን ገድል እንደሚበልጥ አሰብን እንጂ መቼስ ተጋነነ ብለን ተጠራጠርን::

በአድዋ ተራሮች የኾነው፤ የእኛ ኢትዮጵያውያን ኩራት ብቻ አይደለም:: ጥቁር ሁሉ ይኮራ ዘንድ የተፈጸመ የአያቶቻችን ገድል ነው:: የአድዋ ተራሮች ከዳሞታ እስከ ጉጌ፤ ከዳቲ ወለል እስከ ካራ ማራ፤ ከበላያ እስከ ሙሳ ዓሊ፤ ተራሮቻችን ሁሉ የገድል ሰሌዳ ሆነው የአባቶቻችን ገድል አትመውታል::

አስቀድሞ በዶጋሊ፣ በጉርዓና በጉንደት እንደሆነው ያለ ለሀገር የተከፈለ መስዋዕትነት መካን ያልሆነች ምድር እንዳለችን አሳመነ፡፡

የአባቶቻችን ገድል እንዲህ ነው፡፡ ለሀገር በአንድነት ተጋድለዋል፡፡ ሞት በፊታቸው ሸሽቷል፡፡ በመሞት ህይወት ሰጥተውናል፡፡ እንደ ዛሬው ያይደለ፤ አብሮ መብላት ከባድ ሳይሆን፤ አብሮ መሞት ቀላል ሆኖ የድል ቀለም ምሳሌ አድርገውናል፡፡

የአባቶቻችን ገድል በእድል ሳይሆን በሞት የተጻፈ ነው፡፡ አባቶቻችን ድል ለቂም ሳይሆን ለነጻነት በተከፈለ መስዋዕትነት የተገኘ ነው፡፡

ከዚያ በኋላ እንዲህ ኾነ፡፡
በኢትዮጵያ ምድር አድዋን የሚያስታውስ ትውልድ ጠፋ፡፡ በዚህ ግዜ አድዋን የሚዘከሩ ወጣቶች ተነሱ፡፡ አድዋ አብረው የዘመቱ የአንድ አያት ልጆች ስለ አድዋ ሁለት ሀሳብ ኾኑ፡፡ በአንድ ሀሳብ አንድ ሀገር ያኖሩልን አባቶች ገድል ለትውልድ ፍቅር ሲባል ዳግም ኖኘ፡፡

በአድዋ የሞቱ አባቶችን ብንዘክር ከብሩ ለራስ ነው፡፡ በስራው የተዘከረ በመረሳቱ አይዋረድምና፡፡ አባቶቻችን በሰሩት ገድል ሀገር አለን የምንል ሰዎች እንደአባቶች ገድል ሰሪ ለሀገር አንድ ልብ ያለን እንሆን ዘንድ የአባቶች መንፈስ በእኛ እንዲያድር ይህ ከሰማይ ከዋከብት የበዛ ተግባራቸው አጥሮ ተጻፈ፡፡

የአባቶቻችን ሞት ቀና ብለን በሕይወት የምንሄድ ሀገር ዜጎች አደረገን:: በድህነታችንም ቢኾን ኪሳችን እንጂ ክብራችን አላቀረቀረም:: ስማችን ከአባቶቻችን የድል ታሪክ የተቀዳ ነው::

ደግሞ ጀግና የማይነጥፍባት ሀገር ዳግም የአባቶቿን ገድል ለመመስከር የኾነውን ሁሉ ባይሆን አሳጥረን እንጽፋለን:: ከአድዋ ወዲህስ ቢሆን የአበው ገድል እንደምን ነው ቢሉ እንዲህ ነው፤

# ገድለ አበው፤ ዘ ኢትዮጵያ።

ይኸ ከአድዋ በኋላ የተፈጸመ የአባቶቻች ገድል ነው። አባቶች ለነጻነት ሳይሆን ነጻነትን ላለማስደፈር ስላደረጉት ገድል ድልን ባጎናጸፋቸው ፈጣሪ ስም ገድላቸውን እንዲህ እጽፋለሁ።

እኔ የአባቶችን ገድል የምጽፈው አባቶችስ ገድላቸው ሳይጻፍ ወይም ከተጻፈው አዲስ ነገር ለመጻፍ አይደለም። ይልቁንስ ከተራሮች አናት የተሰቀለው የአባቶች ገድል በማን ተጻፈ? ከወንዝ ጋር የፈሰሰው ደማቸውን ማንስ ተከትሎ ተረከው? ገደልን እንደሜዳ የሮጡበት ጀግኖች የድል ዜናስ መች ተዘገበ? ብሎ ለሚጠይቅ ትውልድ እነሆ ከዘመን በኋላ የተፈጠርሁ፤ እኔ ሄኖክ ስዩም የምባል በአባቶቼ ገድል ድል አድርጋ በቀናች ሀገር የምኖር ስለ ውለታቸው ይሄንን ገድል ጻፍሁ።

ከአባቶቻቸው የሮምን ገናናነት ሲሰሙ የኖሩ ኢትዮጵያውያን ዳግም አባቶቻቸው በአድዋ ተጋድሎ የሮምን ታሪክ ከምድራቸው አስተሳሰሩ።

አባቶቻችን ከአድዋ በኋላ የሰሩት ገድል ይህ ነው::
በኢጣሊያ ሞሶሎኒ ተነሳና አባቶች በተጋድሎ ያቆይዋትን ኢትዮጵያ ደፈረ:: ያኔ እንኳን አባቶቻችን ተራሮቻችን ተቆጡ:: ኮረብታዎች ሸለሉ፤ ተዳፋቱ ሽቅብ ጎነ፤ ወንዙ ኩሬው አጉረመረመ::

በመሣሪያው ብዛት የታመነው ሠራዊት ወደ ምድራችን ገባ፤ አባቶቻችን በፈጣሪያቸው ታመኑ:: በጀግንነታቸውም ልባቸው ደነደነ፤ አባቶቻችን በጦር ስልት አዋቂነታቸው ድል እንደሚቀናኟ አመኑ::

በመሳሪያው ብዛታ የታመነውን ሠራዊት አባቶቻችን ተራሮችን እንደ ቀስት ወረወሩበት፤ በውሃ ሙላት ጠረጉት:: በሀገር ፍቅር ስሜት ከሰማይ አቶን እየዘነበ፤ መርዝ ጋዝ እንደ ካፊያ እየወረደ ለነጻነት የሚከፈል መስዋዕትነት ስለሆነ የደም ዘር በቀለበት::
ይህ የአባቶች ገድል በአባቶቻችን ዘመን በምድራችን የሆነ እውነት ነው:: ባሳንስ እንጂ እንደአላበዛሁ የአባቶቼ መንፈስ እውነቱን በሚገልጥ ዛሬ እንዲህ ነገረኝ::

የመስከረም ኡራኤል ዕለት በካያ ስምንት ክተት ታወጀ:: ዳር ሀገር መሀል ሆነ:: ሁሉም ከየአለበት መጣ:: የጎፋው ሠራዊት ጎፋ ሠፈር ሰፈረ:: የሃድያው ባላባት ጌጃ ሠራዊቱን አምጥቶ ጌጃ ሠፈር አሰፈራቸው::
በዚህ ሀገር እንዲህ ሆነ፤ ከሰውስ የቀረ የለም:: ፈረሶች ስለምድራችን በየሜዳው ሊቀኑ ጓዝ ይዘው ዘመቱ:: አህያና አጋሰሱ ቁጥር አልነበረውም::

ያኔ በትግራይ ያሉ ጀግኖች አባቶች ስለ ሀገራችን ነጻነት ቀድመው ተዋደቁ፡፡ ያኔ በተከዜ በርሃ የደጃች አያሌው እና የራስ እምሩ ጦር ሆ ብሎ ተመመ፡፡ በጦርና በጎራዴ ታንከን የማረኩ አባቶች ገድል ይኸ ነው፡፡

ከሁሉ በከፋ የጦር ሜዳ በሽሬ የተደረገ የአባቶቻችን ገድል ይህ ነው፡፡

ከጎጃምና ከጎንደር የዘመተው አምስት ሺ ጦር ከቆላ ወገራ እስከ ተከዜ ወርዶ ተዋደቀ፡፡ እንዳባጉና ተአምር ተሰራ፡፡ ቀኑም ታህሳስ ሰባት ነበር፡፡ ዓመቱን በዚያው ዓመት፡፡ ዘጠኝ የኢጣሊያ የወራሪ ጦር መኮንኖች በጦርነቱ ሞቱ፡፡ 392 ሠራዊት ሊወር የተመኘው ምድር ላይ ወደቀ፡፡

ዳግም እንዲህ ያለው ተጋድሎ በአምባ ደስሬና በሰለከለካ ተደረገ፡፡ አባቶች ከአባቶቻቸው ለተረከቧት ሀገር ተጋደሉ፡፡ ሞት ቀላል ነበር፡፡ እንደ ብርዝ የሚጣፍጥ፡፡ በሀገር ፍቅር ያልሰከረ አበው አልነበረም፡፡ እናም የዛሬ መሠረት ትናንት ሆነ፡፡

ደግሞ በሌላ ስፍራና በሌላ ጊዜ አባቶች ያደረጉት ገድል ይህ ነው፡፡ ይህስ ገድል እንጂ ሌላ ምን ሊባል ይችላል፡፡ ከሰማይ እሳት በሚተፉ የብረት አሞራ አለመበገር እንደምን ያለ ብርታት ነው፡፡ አባቶች ግን አድርገውታል፡፡ ካደረጉት ጥቂቱን እናወሳዋለን፡፡
ባራስ ካሳና በራስ ሙሉጌታ ከሚመራው ጦር ጋር የዘመቱት አባቶች በተምቤን ግንባር ለግንባራቸው መች ሳሱ፡፡

ገዱሉን ሜዳ አድርገው ስለ ተዋደቁ የከንባታ ጀግኖች ምን ያለ ብራና በቅቶ ተአምራቸውን መጨረስ ይቻል ይሆን? ፈረሰኞቹን የወረ ጃርሶ ጀግኖች ፈረስ እንደ አሞራ በገደል ላይ እያበረሩ ስለፈጸሙት ተጋድሎስ ምን ያለ ቀለም በቅቶ ሊጻፍ ነው?

በአምባራዶም ስለሆነው እንተርከህ ቢሉት ምን ትውልድ ጽናት ሰጥቶ አድምጦት ያልቅና ነው? አምባራዶም በሞቱ አባቶች ሀገር የድል ደጃፍን ተራምዳ ገባች። አምባራዶ ያሸነፈ የመሰለው ጠላት የብዙ ወገን ሞት፤ ብዙውን ለሀገር ዳግም ሆ የሚያስብል ጉልበት እንደሆነ የቀደሙት አባቶቻችን ገድል ሳያውቀው ቀርቷልና፤

አባቶቻችን በእረፍት ውሃ መስከ ተዋድቀው ድል አላደረጉም። በበርሃ ተጋድለዋል። አበው በበርሃ ያደረጉት ገድል ይህ ነው።

ወልወል የታየችው ጢስ ኡጋዴንን የጦርነት ምድር አደረገችው። ሐረር፣ አርሲ፣ ኢሉ አባ ቦራና ባሌ ኡጋዴን ተመመ። እነ ደጃዝማች ነሲቡ ዘ አማኑኤልን የተከተለው ሠራዊት በበርሃ የሰራውን ተአምር ከበርሃው አሸዋ እኩል የማይቆጠር ቢሆንብን ተውነው።

በኡጋዴን የገባውን ጦር ከካፋ ተነስቶ ከሲዳማ ከከተተው ጋር የተቀላቀለው የካፋ ዘማች የሰራውን እንደምን አድርገን ገልጸንስ እንጨርሰዋለን? የቀደሙት ለሀገር ለመሞት በማንም መቀደም አይፈልጉም።

አባቶቻችንስ የወንድምን ሞት ሞቶ የልጆችን ሀገር የታፈረች ማድረግ የኑሯቸው ምክንያት ነው።

በሚታወቀው ማይጨው ድል የተደረጉ የመሰሉ አበው በማይታወቀው ዱር ገደል ተናነቁ። በተፈሪ ኬላ ተናነቁ፤ በአርሲ በዶዶላ ተናነቁ። ታንቆ አንገት ያላት ሀገር ለማስረከብ። በጉራጌ ምድር እስከ ውቤ በርሃ ትንቅንቅ ሆነ። ሞትን ጀግኖች ተጋፈጧት። እነ ራስ ደስታ ዳምጠው ሞተው ብዙ ፍሬ አፈሩ።

አባቶቻችን ወድቀው ፍሬ ያላፈሩበት የት ነው?

ጋሞ ጎፋ ነው? አሉባቡር? ካፋ ነው? ጊምቢ ነው? ጊዳ? የግንደ በረትና የሜጫ ተጋድሎስ? ከሰላሌ እስከ ቡልጋ፣ ከምንጃር እስከ መራኛ አበው ያልተጋደሉበት የት ነው? አበው ዛሬ የደረሰችዋን ሀገር በአንድ ልብ ለአንድ ባንዲራ በሶማ ተጋድለው፣ በዳሞት ወድቀው፣ በደንቢያ፣ በስማዳ፣ በአምባሰል፣ በወረኢሉ፤ ደግሞስ ሀገር ቢዘረዘር የወደቁት ቢነሱ ምን ጊዜ ምን ሰዓት ይበቃልና ነው።

አባቶች እምነት ሳይለያቸው ያደረጉት ተጋድሎ ይህ ነው። በቃጥባሬ እንደ ሆነው ድንቅ አርበኝነት ደግሞ በምሁር ኢየሱስም ኾኗል። ሼህ ከቄስ ሳይለይ ዓሊም ከመነኩሴ ሳይነጣል በአንድ ልብ ስለ አንድ ሀገር ተዋድቀዋል። ለአንድ ሀገር የወደቁት አንድ ሀገር ለልጆቻቸው እንድትጠብ አይደለም። ልጆቻቸው በእነሱ ተጋድሎ ልባቸውም ሀገራቸውም እንዲሰፋቸው እንጂ።

አበው ስለሰሩት ስራ እኛ እንኮራለን፤ አበው በሞታቸው ሕይወት ያለው ታሪክ ያላት ሀገር አስረክበውናል፡፡ ሙት ታሪክ የሽንፈት ታሪክ ነው፡፡ ሙት ታሪክ ሀገር የመሸጥ ታሪክ ነው፡፡ ሙት ታሪክ የመለያየት ታሪክ ነው። ሙት ታሪክ የመከፋፈል ታሪክ ነው። ቢገባንስ አንድ እንኾን ዘንድ ሺዎች ስለ አንድነታችን መስዋዕት ኾነዋል።

አበው ሀገር በሕይወት ስለመግዛት የከፈሉት መስዋዕትነት ድንቅ ታሪካችን ሆኖ ይኖራል፡፡ እኛ ነጻ የወጣን ህዝቦች ሳንሆን ለነጻነታችን ድል ያደረግን፤ ያልተደፈርን ህዝቦች ነን፡፡

# ዋቢ ሰነዶች

1. አፋር በታሪክ ዓምድ፤ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጀ፤ አፐል ማተሚያ ቤት፤ ዓ.ም. አልተጠቀሰም፤

2.ሐቢብ ሙሐመድ፤ መስከረም 2011 ዓ.ም. የአፋር /አዳል/ ህዝብ ታሪክ፤ @ 3H ማተሚያ ቤት የታተመ::

3.ሼህ ጀማሉዲን ኢብራሂም፤ አፋር /ደናኪል ታሪክና አርኪ ምንጭ/ አልመንሀል::

4. ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ፤ ስውሩና ያልተነገረው የአይሁዳውያንና የኢትዮጵያውያን ታሪክ::

5.መጽሐፍ ቅዱስ፤ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር::

6.በበላይነህ አስጉ ሙኩሎ፤ 2009 ዓ.ም.፤ ጎፋ ባህልና ታሪኩ፤ አሌኒ ማተሚያ ቤት፤

7.ቢጋሞ ጎፋ ዞን ማስታወቂያና ባህል ዋና መምሪያ የባህል ጥናት ቡድን የተዘጋጀ፤ 2004 ዓ.ም.፤ አርባ ምንጭ፤ የጋሞ ጎፋ ህዝቦች ታሪክ ከጥንት እስከ 1974፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት፤

8.ጳውሎስ ኞኞ፤ 2006 ዓ.ም.፤ አጤ ምኒልክ፤ በማንኩሳ አታሳሚ የታተመ፤ ግራፊክስ አታሚዎች፤

9. ባሕሩ ዘውዴ፤ 2003 ዓ.ም.፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤

10. ጳውሎስ ኞኞ፤ 2003 ዓ.ም.፤ አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች፤ አስቴር ነጋ አሳታሚ፤ ሮሞቦት አታሚዎች፤

11.ደጃዝማች ከበደ ተሰማ፤ 2ኛ ዕትም ሐምሌ 2007 ዓ.ም.፤ የታሪክ ማስታወሻ፤ ማንኩሳ አሳታሚ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤

12. አሌክሳንደር ቡላቶቪች፤ 1892፤ ከዐፄ ምኒልክ ሠራዊት ጋር፤ ተርጓሚ አምባቸው ከበደ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤

13. ተክለጻዲቅ መኩሪያ፤ ሁለተኛ ዕትም 2000 ዓ.ም.፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ አዲስ አበባ

14. ጸሓፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ፤ 2008 ዓ.ም.፤ ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፤

# ዋቢ ሰነዶች

15. አልቫሬጽ፤ በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት፤ ከ1520-1527 ወደ ኢትዮጵያ የተላከ የፖርቱጋል መልዕክት፤ በአቶ ዮና ቦጋለ ወደ አማርኛ የተተረጎመ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ.የግ.ማኅበር ማተሚያ ቤት፤

16. ሬይሞንድ ጆናስ፤ የአድዋ ጦርነት፤ ነጻ ትርጉም ኤፍሬም እንዳለ፤ የመጀመሪያ ህትመት 2009 ዓ.ም.፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ.የግ.ማኅበር ማተሚያ ቤት፤

17. መቅደላ፤ የቴዎድሮስ ዕጣ፤ ሄነሪ ሞርተን፤ ትርጉምና ተጨማሪ ሥራዎች በዶክተር ገበየሁ ተፈሪ፤ 2ኛ ዕትም 2011 ዓ.ም.፤ CAESAR Print & Advert;

18. ጊጋር ተስፋዬ፤ የሦስት ኢሮብ ብሔረሰብ አጭር ታሪክ፤ 1985 ዓ.ም፤ የኢትዮጵያ ዓመታዊ ታሪክ መጽሔት፡፡ 13ኛ መጽሔት፤

19. የ፬ፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል፤ ከግዕዝ ወደ አማርኛ በዓለሙ ኃይሌ የተተረጎመ፤

20. የደብረ ገሪዛን ጉንዳ ጉንዶ ማርያም ታሪክ፤ በገዳሙ የተዘጋጀ፤ ያልታተመ ብሮሸር፤

21. ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ፤ በጉንዳ ጉንዶ ማርያም ገዳም የታተመ፤

22. ጌታቸው ኃይሌ፤ 2003 ዓ.ም፤ ደቂቀ እስጢፋኖስ "በሕግ አምላክ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤

23. መርቆሪዎስ አረጋ፤ 1991 ዓ.ምም፤ ታሪክህን ዕወቅ እንዳትሆን መናፍቅ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፤

24. ወንድዬ ዓሊ፤ በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን፤

25. በአማን ነጸረ፤ የመጀመሪያ ዕትም ታኅሳስ 2009 ዓ.ም.፤ ወልታ ጽድቅ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ.የግ.ማኅበር ማተሚያ ቤት፤

26. ፍስሐ ያዜ ካሳ፤ ሁለተኛ ዕትም 2004 ዓ.ም.፤ የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ፤ መጽሐፍ ፩፤ አልፋ አታሚዎች

27. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፤ የጎጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ፤ ግርማ ጌታኹን እንዳዘጋጀው፤ 2003 ዓ.ም.፤ አዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ ፕሬስ፤ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፤

# ዋቢ ሰነዶች

28. በሰብስቤ ንሳዬ፤ ቤዋ-የጉምዝ ህዝብ ጥንተ ታሪክ ምንጩና ባህሉ፤
29. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፤ ዝክረ ነገር፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤
30. አለቃ አጽሜ፤
31. መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት፤ 2009 ዓ.ም.፤ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም እና የክርስቲያናዊ የምናኔ ሕይወት ሥነ-ምግባር፤ ኤች ዋይ ኢንተርናሽናል ማተሚያ ቤት፤
32. ሊቀ ብርሃናት መርቆሪዎስ አረጋ፤ 5ኛ መጽሐፍ የካቲት 1998 ዓ.ም.፤ የቅዱሳን ታሪክ፤ አስግ ሉሲ ማተሚያ ድርጅት፤
33. ካህሳይ ገብረ እግዚአብሔር፤ ምንኩስና በኢትዮጵያ፤
34. አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል ቀሲስ ከፍያለው መራሒ፤ 1992 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ ትርጓሜ ቅኔ ፊለገ ሕይወት፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤
35. መርሻ አለኸኝ ዶ/ር፤ 2011 ዓ.ም.፤ በአንተ ስማ ለማርያም ጥንታዊው የኢትዮጵያ ትምህርት ይዘቱ፣ ሥርዓቱ፣ ሕይወቱ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ.የግ.ማኅበር ማተሚያ ቤት፤
36. አለማየሁ ሞገስ፤ የቅኔ ቤት ሥርዓተ ትምህርት፤ ያልታተመ
37. ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፤ ሁለተኛ ዕትም 2001 ዓ.ም.፤ ዋዜማ። በማግስቱ የኢትዮጵያን ነገሥታት የታሪክ በዓል ለማክበር፤ ጎሕ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፤
38. መሪራስ አማን በላይ፤ ሁለተኛ ዕትም ጥቅምት 2009 ዓ.ም.፤ የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ፤ Nebadan m.c plc
39. መልአከ ምክር ከፍያለው መራሒ፤ 2003 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ ዝክረ ሊቃውንት፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፤
40. አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ዝግጅት፣ ሐተታና አርትዖት በሥርግው ገላው ዶክተር፤ ሁለተኛ ተሻሽሎ የታተመ 2008 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
41. አሰግድ ተስፋየ፤ ህዳር 2007 ዓ.ም.፤ ጎንደር የአፍሪካ መናገሻ፤ ዱሮዮጋዳ ማተሚያ ቤት፤

# ዋቢ ሰነዶች

42. ፕሮፌሰር ሲ ጋምስት፤ 1993 ዓ.ም.፤ ቅማንት አረማዊ-አሪታዊ ኢትዮጵያዊ ገበሬ፤ ትርጉም ባዮ ቦጋለ ላቀው፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

43. አርኖ ሚሼል ዳባዲ፤ የመጀመሪያ ዕትም ህዳር 2009 ዓ.ም.፤ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ፤ ተርጓሚ ገነት አየለ አንበሴ፤ ግራፊክስ አታሚዎች፤

44. ገብረ እግዚአብሔር ኪዳ፤ ሁለተኛ ዕትም የካቲት 2010 ዓ.ም.፤ አሪት ዘ ፍጥረት ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ እንዳስተማረው፤ ድርሳን 1-18፤ H&F ማተሚያ ቤት፤

45. ወንድሙ ለማ እና ሙሉጌታ በዛብህ፤ የመጀመሪያ ዕትም የካቲት 2003 ዓ.ም.፤ የዳውሮ ሕዝብ ታሪክ እስከ 1983 ዓ.ም.፤ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፤

46. የየም ወረዳ ባህል ቱሪዝምና መንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፤ የመጀመሪያ ዕትም የካቲት 2004 ዓ.ም.፤ የየም ብሔረሰብ ታሪክ፤ ቼምበር ማተሚያ ቤት፤

47. ዶ/ር ፍስሃ ሃይለ መስቀል፤ ታላላቅ የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ፤

48. ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ፤ ሐምሌ 2011 ዓ.ም.፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ፤ ጃጀው አታሚዎች፤

49. ገብረ እግዚአብሔር ኪዳ፤ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የማቴዎስ ወንጌል 1-24፤

50. ኪዳነወልድ ክፍሌ፤ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም፤ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አሳታሚ ደስታ ተክለወልድ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤

51. አህመድ በሀጅት፤ የመጀመሪያ ዕትም 1998 ዓ.ም.፤ ዝክረ እንስሳት፤ ተርጓሚ በአደም መሐመድ አባምቼ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፤

52. ዶክተር ይርመድ፤ ዝኖን፤ የጥናት መጽሔት

53. መጋቢ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ፤ የመጀመሪያ ዕትም 2009 ዓ.ም.፤ መጽሐፈ ፊስአልጎስ፤ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፤

# ዋቢ ሰነዶች

54. ሰለሞን ይርጋ ዶ/ር፤ በ2000 ዓ.ም.፤ አጥቢዎች፤ ዮናይትድ አታሚዎች፤
55. ዲ/ን ኃ/ሚካኤል መቶ፣ ዲ/ን አዕምሮ ሾሎ እና ተገኝ ሾሎ፤ ሁለተኛ ዕትም ነሐሴ 2011 ዓ.ም.፤ የደቡቧ ኮከብ ጥንታዊት ጽዮን ሰማያዊት ብርብር ማርያም ገዳም፤ ሌንስ ማተሚያ ቤት፤
56. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፤ ጥቅምት 2006 ዓ.ም.፤ አራቱ ኃያላን፤ አግዮስ አሳታሚ፤ አማኑኤል ማተሚያ ቤት፤
57. ሙሐዘ ጥበባት ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)፤ ሁለተኛ ዕትም 2012 ዓ.ም.፤ የቤተክርስቲያን መረጃዎች፤ ቅጽ 1፤ አሳታሚና አከፋፋይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን፤
58. ገብረ ሥላሴ፤ ተሻሽሎ የታተመ 2009 ዓ.ም.፤ መዝገበ ቅዱሳን፤ አሳታሚና አከፋፋይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን፤ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት
59. ሀገሬ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ኃ/የተ/የግ/ማኅበር፤ የኢትዮጵያ ተፈጥሮና ፓርኮች ማውጫ፤ ማስተር ማተሚያ ቤት
60. ዶክተር አያሌው ሲሳይ፤ የአገው ህዝቦችና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ታሪክ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፤
61. የቅዱስ ላሊበላ ሰበካ ጉባኤ፤ 2ኛ ዕትም 2010 ዓ.ም.፤ ገድለ ላሊበላ፤ ፕሮግረስ ማተሚያ ቤት
62. ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፤ የካቲት 1981 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት፤ የኢትዮጵያ ብራና ጽሑፎች ማይክሮፊልም ድርጅት፤ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር፤ ያልታተመ
63. ሙሐዘ ጥበባት ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)፤ ሦስተኛ ዕትም 2013 ዓ.ም.፤ የናግራን ሰማዕታት፤ አሳታሚና አከፋፋይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን፤

# ዋቢ ሰነዶች


64. ኮ/ል ጌታቸው ዳኛው፤ 2007 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ ሠራዊት እና የጦርነቶች ታሪክ፤ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት እስከ ኢፌዲሪ፤ ብራና ማተሚያ ቤት

65. አባ፡ ጋስፓሪኒ፡ ገ-ማ፡ የአሥመራ፡ ኮምቦኒ፡ ኮሌጅ፡ ዲሬክተር፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከረኸሮሙ ባጭሩ የተውጣጣ፤

66. ጌታቸው ኃይሌ፤ 2ኛ ዕትም 2006 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ፤ ግረፊክ አታሚዎች


## English


67. RICHARD PANKHURST B.Sc (Econ.), Ph.D. An Interoduction to The Economic History of ETHIOPIA from early times to 1800, 1961 LALIBELA HOUSE.STAPLES PRINTERS LIMITED.

68. Mesfin Wolde-Mariam, 1972, AN INTROSUCTORY GEOGRAPHY OF ETHIOPIA, by,Departement of Geography H.S.I. University. Berhanena Selam H.S.I Printing press. Addis Abeba.

69. ENCYCLOPAEDIA AETHIOPICA. vol 1-5

70. CAPHTAIN C.H. STIGAND, F.R.G.S, F.Z.S 1910, TO ABYSSINIA THROUGH AN UNKOWN LAND, AN ACCOUNT OF A JOURNEY THROUGH UNEXPLORED REGIONS OF BRITISH EAST AFRICA BY LAKE RUDOLEF TO THE KINGDOM OF MENELEK, Southern Branch of the University of California Los Angeles.

71. Juan Maria Schuver's, HAKLUYT SOCIETY,SECOND SERIES, NO 184, Travels in North East Africa 1880-1883, Printed in Great Britain at the University press,cambridge.



ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም በሀገራችን የቱሪዝምና የጉዞ ጋዜጠኝነት ዘርፍ ላለፉት አስራ አምስት አመታት የተለያዩ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የሀገሬ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን መስራች ሲሆን "ቱባ" የተባለ የቱሪዝምና ባህል ዘርፍ መጽሔት በአማርኛ ቋንቋ እያዘጋጀ ያሳትማል፡፡ በተለያዩ የህትመት ውጤቶች፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የዲጅታል ሚዲያዎችና ብሎጎች ላይ ተከታታይ የጉዞ ማስታወሻዎችን በመጻፍም ይታወቃል፡፡

በአሁኑ ወቅት "ጉዞ ኢትዮጵያ" የተባለ መደበኛ የቱሪዝም የቴሌቭዥን ዘጋቢ ፊልም እያዘጋጀ በየሳምንቱ ለአየር ያበቃል፤ የጉዞ ማስታወሻዎችንም በመጻፍ ያሳትማል፡፡ ከዚህ ቀደም ከሌሎች ጋር "ደቦ" እና "አቦል" በተባሉ የጋራ መድብሎች ስራውን ያሳተመ ሲሆን በተናጥል ደግሞ "የመንገድ በረከት" እና "ጎንደርን ፍለጋ" የተባሉ ሁለት የጉዞ ማስታወሻዎችን ጽፎ ለአንባቢያን አድርሷል፡፡ "ሀገሬን" ሦስተኛው የጉዞ ማስታወሻ መጽሐፉ ነው፡፡

ባሻገር የምናያት ሀገራችን፣ ባነጸርንበት የዘመኑ መስታወት መቆሸሽ መልኳ ጠፍቷል፡፡ እግረ ቀጭኑ ሄኖክ ስዩም "ሀገሬን" ሲል የተነሳው ይሄንን ያደፈ፣ የጎደፈ ማንፀሪያ "ወዲያ" ብሎ ሌላ የጠራ አቅርቦ ማሳያ ዐይናችን ላይ ለመደቀን ነው፡፡ ተሳክቶለታል፡፡ እደግመዋለሁ ተሳክቶለታል!!

ሀገራችን እንደ ተፈጥሯዊ ኩነቷ፣ አባቶች እንደአበጃጇት ውበቷ ሆና ዓይነ ህሊናችን ሥር ትደቀናለች፡፡ "ሀገሬን" ካነበብን በኋላ አንዲት ቃል ለአቅመ መዝሙር በቅታ ግጥሙንም ዜማውንም በመንትያነት በማህጸኗ ትፀንሳለች፡፡ ያቺ ቃል "ሀገሬን" ናት፡፡ እኔ "ሀገሬን" አንብቤ "ሀገሬን" ዘምሬያለሁ፡፡ እነሆ እናንተም "ሀገሬን" አንብባችሁ "ሀገሬን" ባትዘምሩ ቀጣዩ ጉዞአችሁ በህጸጽ አራሙቻ የተጠላለፈ ተደነቃቃፊ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ "ሀገሬን" ያለ "ሀገሬን" ያንብብ!!

ሃያሲና ደራሲ ዓለማየሁ ገላጋይ

"የጉዞ ማስታወሻ" እንደሌሎች የታሪክ መዛግብት ሁሉ ከራሱ ባህርይ በሚመነጭና ከጸሐፊው ሁለንተናዊ አቋም የተነሳ እጅግ አስቸጋሪ ጠባይ እንዳለው ይነገራል፡፡ ይሄውም ጸሐፊው ተጉዞ የሚደርስባቸው ቦታዎችና ባህሎች አዲስ ስለሚተዋወቃቸው እንግድነቱ የተገለጠ ነው፡፡ በእንግዳ ዓይን የሚታይ አዲስ ዓለም ደግሞ ለመተርጎምም ሆነ ለመበየን የተመቸ አይደለም፡፡ ወይም ብያኔው ስር ከሰደደ መረዳትና ምልከታ የመነጨ ስለማይሆን ተዓማኒነቱ አጠያያቂ ይሆናል፡፡ ሌላው የተጓዡ ዓላማና ነጽሮተ ዓለም የጉዞ ማስታወሻውን ተገቢነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል፡፡ ይህን ሐሳብ ለማጉላት የምዕራቡ ዓለም አሳሾች የጻፏቸው ድርሳናት ለቅኝ ገገርዎች መስፋፋትና ለተገገርዎች ስሁት ውክልና (miss representation) ሰበብ መሆናቸውን እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይሁንና ይህ አስቸጋሪ ጠባይ ሥነ-ጽሑፋዊ ዘውጉ የሚሰጠውን ሁለንተናዊ ፋይዳ አላጎደለበትም፡፡ ዛሬም "የጉዞ ማስታዎሻ" በስፋትና በምላት ታሪክን በመዘከርና በሌሎች ሰፊ አካዳሚያዊ ልምምዶች ውስጥ ስፍራው ብዙ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር "ሀገሬን" የሚለው የሄኖክ ስዩም መጽሐፍ ለታሪክ ጥናት፣ ለባህል፣ ለማኅበራዊ ግንኙነት፣ ለኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እና ለጠንካራ ማኅበረሰባዊ ተራክቡና ለተሰናኙ የወል እሴቶች መገንባት ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ሔኖክ እንዲህ ያለ ረብ ያለው ተግባር በመፈጸሙ ምስጋና ያንስዋል፡፡ በተጨማሪም መጽሐፉን ሳነበው ከተጓዡ ተራኪ ጋር አብሬ መድከሜንና ከፍ ዝቅ ማለቴን ሳስብ "ሔኖክ ሥዩም ሆይ! ደግመህ ደጋግመህ ጻፍ" ማለቴን አልደብቅም፡፡

ሰዓሊና ገጣሚ አገኘሁ አዳነ ድልነሳሁ
የአለ ፈለገ ሰላም የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር

ISBN 978-99944-3-192-2
9 789994 431922 >

ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር ስልክ +251 111 565 352

ዋጋ 190,00

ለውጭ ሀገር $20.00